# የልማት ዕቅድ

ፍኖተ ብልፅግና

2013-2022

## የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

ጥር 2015

ቦንጋ

## መግቢያ

ይህ ክልላዊ የአሥር ዓመት (2013-2022) የልማት ዕቅድ በሃገር ደረጃ የተያዘውን ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት የማድረግ ራእይ መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን በዚህ አስር አመት ጊዜ ውስጥ ዜጎች ፍላጎቶታቸውንና መሻቶቻቸውን የሚያሟሉባቸው በየደረጃው በፍትሐዊነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያስችሉ የገቢ አቅምና ጥሪቶች እንዲሁም እነዚህን ጸጋዎች ለመፍጠር በሚያግዙ ቁሳዊ፣ ሰብዓዊና ተቋማዊ አቅሞች መፍጠር የሚቻልበት፣ ዜጎች ያላቸውን እምቅ ችሎታ በሚገባ ተጠቅመው ጸጋዎችን በፍትሐዊነት መፍጠርና መቋደስ በሚያስችሉ እንደ ትምህርት፣ ጤናና ሌሎች አገልግሎቶች ፍትሐዊ ተደራሽነትን የሚረጋግጥበት፣ ሁሉም ዜጎች የኢኮኖሚ አቅማቸው ፈቀደም አልፈቀደም ለመኖር መሰረታዊ የሆኑትን እንደ ተመጣጣኝ ምግብ፣ መጠለያ፣ ንጹህ የመጠጥ ውኃ፣ መሰረታዊ የጤናና ትምህርት አገልግሎቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበትና እና ዜጎች የተለያዩ ማህበራዊ ማንነቶች ሳይገድቧቸው በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረሰባዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያለምንም ተጽዕኖ በእኩል ተሳታፊነታቸው በጋራ የሚያረጋግጡበት አዎንታዊ ሥርዓታትን መገንባት ነው።

የልማት ዕቅዱ በክልላችን እየተተገበሩ ያሉ እና በቀጣይ ተግባራዊ የሚሆኑ ሀገራዊና ክልላዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን፣ ባለፉት ሁለት ስትራቴጂክ የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የተመዘገቡ መልካም ውጤቶችና በትግበራ ሂደት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችና ያጋጠሙ ፈተናዎችን በክልላችን ኢኮኖሚ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሊያሳድሩ የሚችሉትን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ እንደ መነሻ ተወስደዋል።

በአጠቃላይ የዕቅዱ ሰነዱ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን በክፍል አንድ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ፣ በክፍል ሁለት በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የልማት ዕቅዱ አድማስ፣ በክፍል ሦስት የቀጣይ አስር ዓመታት መሪ የልማት ዕቅድ እንዲሁም በክፍል አራት የልማት ዕቅዱ ማስፈጸሚያ ስልቶች እና የክትትልና ግምገማ ስርዓት በቅደም ተከተል ተቀምጧል።

**የክልሉ አጠቃላይ ገጽታ**

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በኢትዮጵያ ከሲዳማ ቀጥሎ 11ኛ ክልል ሆኖ 6 ዞኖችን በመያዝና 4 የክላስተር ዋና ከተሞችንና ሁለት ተደራሽ ክላስተር ከተሞችን በመያዝ ህዳር 14/2014 ዓ/ም የተመሰረተ ክልል ነው። ክልሉ በሰሜን አቅጣጫ ከኦሮሚያ ክልል፣ በምዕራብ በኩል ከጋምቤላ ክልል፣ በስተደቡብ በኩል ከደቡብ ሱዳን እና ደቡብ ኦሞ፣ በስተምስራቅ ከጎፋና ወላይታ ዞኖች፣ በስተሰሜን ምስራቅ ከምባታና ሀድያ ዞኖች ያዋስኑታል። ክልሉ በላቲትዩድ መስመር በ 50° 33’ እና 80° 31"N - በሎንግቲውድ መስመር 34° 88’ እና 38° 46’ E አቅጣጫ ላይ የሚገኝ ሲሆን አሁን ባለዉ አደረጃጀት በዉስጡ 6 ዞኖች ያሉት ሲሆን አጠቃላይ የቆዳ ስፋቱ 39,061.4 ስኩዌር ኪ/ሜ (3.91 ሚሊዮን ሄ/ር) እንደሚሆን ይገመታል።

የ1999 ዓ.ም የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤትን መሰረት በማድረግ በተደረገው ትንበያ በ2012 ዓ.ም የክልሉ ህዝብ ብዛት 3,397,005 እንደሚሆን ሲገመት ከዚህ ውስጥ ወንድ 1,695,529 (49.91%) እና ሴት 1,701,476 (50.09%) ድርሻ አላቸው። ከአጠቃላይ ሕዝብ ብዛት በገጠር 86.4% እና በከተማ 13.6% የሚኖሩ ሲሆን የህዝብ ጥግግቱ በአማካኝ በ1 ካሬ ኪ/ሜትር መሬት 87 ሰዎች እንደሚኖሩ ይገመታል። ከጠቅላላው የህዝብ ቁጥር ከ15-64 ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ብዛት 52% መሆኑ ሲታይ በምርት ተግባር ላይ ሊሠማራ የሚችል የልማት ሃይል በበቂ ሁኔታ መኖሩን ያመላክታል።

የክልሉ መልከዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ከባህር ወለል በላይ ከ348-3346 ሜትር ወሰን ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ የአየር ፀባዩ ለተለያዩ የግብርና ሥራዎች ምቹ ነው። አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠን ከ400-2200 ሚ/ሜ ሲሆን የሙቀት መጠን ከ15.1°ሴ.ግ-27.5°ሴ.ግ ይደርሳል። ክልሉ ከሥነ-ምህዳራዊ ስብጥር አንፃር በረሃ 4.09%፣ ቆላ 56.50%፣ ወይናደጋ 33.51%፣ ደጋ 5.86% እና ዉርጭ 0.03% የአየር ፀባይ አለው። የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ሕዝቦች ክልል በሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸዉ የተለያዩ ዕምቅ የተፈጥሮና ግብርና ሀብቶች ባለቤት ሲሆን ለአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ የኮንስትራክሽን ማዕድናት፣ የከበሩ ማዕድናት፣ የገጸ-ምድር ውሃ፣ ቡና፣ ቅመማ ቅመሞም ወ.ዘ.ተ. እንዲሁም የተለያዩ ዓይነት ዕፅዋእትና እንስሳት የሚገኙበት ክልል ነዉ። በአገሪቱ ከሚገኙ ብሔራዊ ፓርኮች ውስጥ የኦሞ እና የጨበራ ጨርጨራ ብሔራዊ ፓርኮች የሚገኙበት ሲሆን በተጨማሪነትም በካፋና በሸካ በተባበሩት መንግስታት የሳይንስ፣ የትምህርትና የባህል ድርጅት (በዩኔስኮ) የተመዘገቡ

ለቱሪዝም ልማት ዕምቅ አቅም ያላቸው ባዮስፌር ሪዘርቮች ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በሰዉ ሰራሽና በተፈጥሮ ያሉ በቀጣይ ተከልለዉ በፓርክነት ሊለሙ የሚችሉ በርካታ ስፍራዎች ይገኛሉ፡፡

የክልሉ የኢኮኖሚ አንቅስቃሴ ሲቃኝ 90% ያህሉ ህዝብ የሚተዳደረው በግብርና በዋነኛነት ሰብል በማምረት፣ ከብት በማርባትና ንብ በማነብ ነው፡፡

**የልማት ዕቅዱ ዓላማዎች**

የአስር አመቱ የደቡብ ምእራብ ኢትዮጲያ ህዝቦች ክልል ያሉትን የተፈጥሮ ሃብትና ስነ ምህዳራዊ ተሰጥኦ፣ የቡናና እና ቅመማ አቅም፣ በእንስሳትና አሳ ሃብት እንዲሁም በማእድን ሃብት ያለውን አቅም ያማከለ እንዲሆን ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ የእቅዱ ዋና ዋና አላማዎችም

- የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ገበያ መር የኢኮኖሚ ሥርዓት (pragmatic market-based economic system) በመከተል የግል ዘርፉን ጉልህ ሚናና ተሳትፎ በማሳደግ የበለጸገች ሀገር መገንባት፣
- የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን በመፍጠር ፈጣንና ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ምርታማነት፣ ጥራትንና ተወዳዳሪነትን በማጐልበት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ (structural economic transformation) ማረጋገጥ፣
- የማህበራዊ አካታችነትን የሚያረጋግጡና ሌሎች የመሠረተ ልማቶች ጥራትንና ተደራሽነትን በማረጋገጥ ዜጎች የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- ብቁ፣ ገለልተኛና ነጻ የሕዝብ አገልግሎት ሥርዓት በመገንባት የመንግስትን የመፈጸም ብቃት በማጎልበትና መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዜጎችን እርካታ ማሳደግ እና
- ሰላምና ፍትሕን የሚያረጋግጡ ጠንካራ ሥርዓት በመገንባት የሕግ የበላይነትንና ሰብዓዊ መብትን በማስከበር የዜጎችን ደህንነት ማረጋገጥ ናቸው፡፡

# ክፍል አንድ

## ያለፉት አሥር ዓመታት የልማት አፈጻጸም

(2003-2012)

# ምዕራፍ አንድ

# የማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም

## 1.1. የኢኮኖሚ ዕድገት እና ድህነት ቅነሳ

### 1.1.1. የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥ

በደቡብ ምእራብ ኢትዮጲያ ህዝቦች ክልል ከ2008-2012 ተከታታይነት ያለው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት የታቀደ ሲሆን የክልላችን አጠቃላይ ኢኮኖሚ ሁኔታ አፈፃፀም ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ (2008-2012 ዓ.ም) የክልሉ ጠቅላላ ምርት 2008 ዓ/ም በነበረ ቋሚ ዋጋ በ2008 በጀት ዓመት ከነበረበት 18.754 ሚሊዮን ብር በ2012 በጀት ዓመት 26.988 ሚሊዮን ብር ማድረስ የተቻለ ሲሆን በወቅቱ የገበያ ዋጋ በ2008 ከነበረበት 18.754 ሚሊዮን ብር በ2012 ወደ 35.32 ቢሊዮን ብር ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን (2008-2012) ባሉት አምስት ዓመታት ኢኮኖሚውን በከፍተኛ የዕድገት አማራጭ ግብ ተቀምጦ የነበረ ሲሆን ባለፉት ዓመታት ይመዘገባል ተብሎ ከሚጠበቀው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት አንዱ መለያ ባህሪይ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማሳየት ነው፡፡ የመዋቅራዊ ለውጥ መለኪያ ተደርጐ ከሚወሰደው አንዱ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከጠቅላላው የከተማ ምርት ያለው ድርሻ ነው፡፡ ኢኮኖሚ ዘርፎች ከክልሉ ምርት ውስጥ ያላቸው ድርሻ ሲታይ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ በ2008 በጀት ዓመት 57.3 በመቶ የነበረው በ2012 በጀት ዓመት ወደ 59.8 በመቶ በመያዝ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ሲሆን፤ የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ ተጨማሪ ዕሴት ከክልሉ ያለው ድርሻ ደግሞ በ2008 ከነበረበት ከ18.5 በመቶ በ2012 ወደ 19.6 በመቶ ከፍ ብሎ ተመዝግቧል፡፡ የአገልግሎት ዘርፍ በ2008 ከነበረበት ከ24.3 በመቶ በ2012 ወደ 22.7 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ ይህ የሚያሳየው በክልሉ ውስጥ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ አለመመዝገቡን ነው፡፡ በተጨማሪም የግብርናው ዘርፍ የኢኮኖሚውን ትልቁን ድርሻ መያዙን እና የኢንደስትሪ ድርሻ ዝቅተኛ በመሆኑን በቀጣይ አስር አመታት የሚታቀደው እቅድ ላይ የኢንደስትሪ ዘርፉን ለማሳደግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ማቀድና ማነቆዎቹን ለይቶ መፍታት ያስፈልጋል፡፡

| የኢኮኖሚ ዘርፎች | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | አማካይ (2009-2012) |
|---|---|---|---|---|---|
| የኢኮኖሚ ዘርፎች ዕድገት | | | | | |
| ግብርና፣ደንና ዓሳ | 9.61 | 7.07 | 7.94 | 7.46 | 9.03 |
| ኢንዱስትሪ | 9.56 | 17.92 | 5.23 | 5.53 | 10.87 |
| አገልግሎት | 11.06 | 11.60 | 10.42 | 9.34 | 12.41 |
| ጥቅል ተጨማሪ ዕሴት በመሠረታዊ ዋጋ | 9.98 | 10.22 | 8.08 | 7.61 | 10.24 |

**ጠቅላላ የክልሉ ምርት ዕድገት በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች(በመቶ)**




**ምንጭ:** ከተለያዩ መረጃ ምንጮች የልማት ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ቴክኒክ ኮሚቴ ሥሌት

ለተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት የግብርና ዘርፍ በአማካይ የ9.03 በመቶ አስተዋጽዖ ሲያደርግ ከዚህም ደንና አደን ንዑስ ዘርፍ 18.64 በመቶ እንዲሁም እንስሳትና አሳ ሃብት 16.92 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። የኢንዱስትሪ ዘርፉም በአማካይ የ10.87 በመቶ አስተዋጽዖ ያደረገ ሲሆን ከዚህ ድርሻ ውስጥ የኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ 13.03 በመቶ እና የመብራት ሃይልና ጋዝ አቅርቦት 14.93 በመቶ ድርሻ የነበራቸው ሲሆን ይህም ለተመዘገበው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕድገት የኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ ትልቅ ድርሻ የነበረው መሆኑን ያመላክታል። ክልላችን

ካለው የማእድን አቅም አንጻር በዘርፉ በጣም ዝቅተኛ (-6.41 በመቶ) ሚና የነበረው የማእድን ቁፋሮ ንኡስ ዘርፍ ላይ የተለየ ትኩረት ሰጥቶ የዘርፉን ማነቆዎች ለመፍታትና የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችል እቅድ ማቀድ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል በአገልግሎት ዘርፍ ለተመዘገበው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት 12.41 በመቶ አስተዋጽዖ ሲያደርግ ከዚህም ድርሻ ውስጥ ከትምህርት እና ጤና አገልግሎት በመቀጠል ትልቅ ሚና ያስመዘገቡት የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ንዑስ ዘርፍ 11.96 በመቶ ድርሻ፣ ሪልስቴት ንኡስ ዘርፍ 12.65 በመቶ ድርሻ ይዘዋል። በአጠቃላይ ከአቅርቦት አንፃር የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት በዋነኛነት በቅደም ተከተል ደንና አደን፣ እንሣትና አሳ፣ ከኮንስትራክሽን እና ከጅምላና ችርቻሮ ንግድ ንዑስ ዘርፎች የመነጨ መሆኑን የአፈጻጸም መረጃው ያሳያል።

**ጠቅላላ በክልሉ ውስጥ የተመዘገበ የምርት ዕድገት በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች (በመቶ)**

| የኢኮኖሚ ዘርፎች | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | አማካይ ዕድገት በመቶ |
|---|---|---|---|---|---|
| ግብርና፣ደንና ዓሳ | 9.61 | 7.07 | 7.94 | 7.46 | 9.03 |
| ኢንዱስትሪ | 9.56 | 17.92 | 5.23 | 5.53 | 10.87 |
| አገልግሎት | 11.06 | 11.60 | 10.42 | 9.34 | 12.41 |
| ጠቅላላ ምርት | 9.98 | 10.22 | 8.08 | 7.61 | 10.24 |

### 1.2. የኢኮኖሚ መጠንና ዕድገት በዘርፎች

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ሕዝቦች ክልል አጠቃላይ ኢኮኖሚ ሁኔታ አፈፃፀምን በተመለከተ ባለፉት አምስት ዓመታት (2008-2012 ዓ.ም) የክልሉ ጠቅላላ ምርት ቋሚ በነበረ ዋጋ

(በ2008 ዓ.ም ዋጋ) ተሰልቶ ከነበረበት 18.75 ቢሊዮን ብር በ2012 በጀት ዓመት 26.47 ቢሊዮን ብር መድረሱን አፈጻጸሙ ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 1 የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ሕዝቦች ክልል የኢኮኖሚ መጠን በ2008 ቋሚ ዋጋ (2008-2012)፡ ጠቅላላ ምርት (ቢሊዮን ብር)

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| የኦኮኖሚ ዘርፎች | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| ግብርና፣ደንና ዓሳ | 10.74 | 11.78 | 12.62 | 13.64 | 14.67 |
| ኢንዱስትሪ | 3.46 | 3.79 | 4.47 | 4.71 | 4.96 |
| አገልግሎት | 4.56 | 5.06 | 5.65 | 6.24 | 6.83 |
| ጠቅላላ ምርት | 18.75 | 20.63 | 22.75 | 24.59 | 26.47 |

ምንጭ፡ ከተለያዩ መረጃ ምንጮችና የልማት ቴክኒክ ኮሚቴ ስሌት

### 1.3. የነፍስ ወከፍ ገቢ

የነፍስ ወከፍ ገቢ ማለት የክልሉ ዓመታዊ ጥቅል የምርትና አገልግሎቶች የገበያ ዋጋ ግምት ለጠቅላላ ነዋሪዎች ተካፍሎ የሚገኝ የአንድ ሰዉ አማካይ ዓመታዊ ገቢ ሲሆን የአንድ ኢኮኖሚ ማሕበረሰብ/ክልል ነዋሪ ሕዝብ ቁጥር ከምርታማነቱ ጋር ያለውን ዝምድና በማመላከት ንፅፅራዊ የኑሮ ደረጃን ለማሳየት ቀዳሚ አመላካች መስፈርት በመሆን ያገለግላል፡፡ በዚሁ መሠረት ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተገኘው የሕዝብ ብዛት ትንበያ መሠረት ክልሉ የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2008 በጀት ዓመት ከነበረበት ብር 6,229 በ2012 ወደ ብር 10,398.14 ደርሷል፡፡ ይህም የክልሉ የነፍስ ወከፍ ገቢ በአማካይ በዓመት በ13.75 በመቶ ያደገ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይሁን እንጂ በአገር ደረጃ ካለው የነፍስ ወከፍ ገቢ /1000 ዶላር/ አማካኝ ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አመላካች ነው፡፡ ይህም ከግብርና በተጨማሪ ሌሎች የኢኮኖሚ ዕድገት ዘርፎች በተመጣጣኝ ደረጃ ባለማደጋቸው እንደሆነ ይታመናል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ የነፍስ ወከፍ ገቢ

| ዝርዝር | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|
| ጥቅል የክልሉ ምርትና አገልግሎት በገበያ ዋጋ (ቢሊዮን ብር) | 18.75 | 22.32 | 27.19 | 32.19 | 35.32 |
| አማካይ ዶላር ከብር ያለው ምንዛሬ | 22.1 | 22.4 | 26.1 | 28.1 | 31.9 |
| የህዝብ ብዛት (ሚሊዮን) | 3.01 | 3.102 | 3.197 | 3.285 | 3.397 |
| የነፍስ ወከፍ ገቢ (ብር) | 6,229.05 | 7,196.00 | 8,503.44 | 9,768.86 | 10,398.14 |
| ጥቅል የክልሉ ምርትና አገልግሎት በገበያ ዋጋ (ሚሊዮን ዶላር) | 848.61 | 996.61 | 1,041.62 | 1,145.66 | 1,107.29 |
| የነፍስ ወከፍ ገቢ (ዶላር) | 281.86 | 321.25 | 325.80 | 347.65 | 325.96 |
| የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት በብር | | 15.5 | 18.2 | 14.9 | 6.4 |

ምንጭ፡ ከተለያዩ መረጃ ምንጮችና የልማት ቴክኒክ ኮሚቴ ስሌት

### 1.4. የፊስካል ፖሊሲ አፈጻጸም

**የክልሉን ፊስካል ፖሊሲ ከማሻሻል አንጻር፡-** በአጭርና በመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ፖሊሲ በመቅረፅና አፈፃፀማቸውን በመከታተል እንዲሁም በጥናት ላይ የተመሠረተ የተጣጣመ የፊስካል ፖሊሲን ተግባራዊ በማድረግ የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ በማዘጋጀት፣ የፊስካል ጉድለት ማሚያ ዘዴዎችን በአግባቡ በመጠቀም ጤናማ የመንግሥት ዕዳ መጠን እንዲኖርና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲሰፍን ለማድረግ ተሞክሯል።

#### 1.4.1. የክልሉ የገቢ አፈፃፀም

ክልላዊ ጠቅላላ ገቢ አሰባሰባችን ሲታይ በ2003 በጀት ዓመት ብር 207.78 ሚሊዮን ከነበረበት በ2012 በጀት ዓመት 1.292 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ተችሏል። ባለፉት 10 ዓመታት በክልሉ በአማካይ ብር 718.78 ሚሊዮን ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን በ10 አመት በአማካይ

ለመሰብሰብ ከታቀደው ብር 806.37 ሚሊዮን አንፃር የ89.14 በመቶ አፈጻጸም ተመዝግቧል፡፡ ለዚህ በዋናነት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ በየደረጃው ከሚገኝ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተፈጠረው ጠንካራ ቅንጅታዊ አሠራር፣ ተግባሩ በሠራዊት ቅኝት በመፈፀሙ፣ የግብር ከፋዩ ሕብረተሰብ ስለ ግብር/ታክስ ያለው ግንዛቤ እያደገ መሆኑ እና የተቋሙ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም እያደገ መሆኑን ያመለክታል፡፡

የባለፉት አመታት አማካይ የገቢ አፈፃፀም አጥጋቢ ቢሆንም በተለይ በ2009፣ በ2010 እና በ2011 ዓ.ም በቅደም ተከተል ለመሰብሰብ ከታቀደው ብር 1.09 ቢሊዮን፣ 1.18 ቢሊዮን እና 1.30 ቢሊዮን አንፃር ሲታይ የተሰበሰበው መጠን ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ለዚህም ከሚጠቀሱ ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ በወቅቱ በሀገር ደረጃና በክልላችን በነበረው ከፍተኛ የሆነ የለውጥ እንቅስቃሴ ህዝቡ በሚያነሳቸው የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች አንጻር ግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ግዴታውን ለመወጣት የነበረው ፍልጎት የተቀዛቀዘ በመሆኑ ነበር፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አምስት ዓመታት የክልሉ የገቢ አሰባሰብ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕድገት እያሳየ የመጣ ቢሆንም እ.ት.ዕ ላይ በክልሉ መንግሥት ከታቀዱ በርካታ የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶች፣ በሕዝቡ ውስጥ ከተፈጠረው አዳጊ የመልማት ፍላጎት እና ክልሉ ካለው አጠቃላይ ገቢ የማመንጨት አቅም አንፃር ሲታይ ተጨማሪ ጥረትና ቁርጠኝነት ከገቢ መ/ቤትና ከባለድርሻ አካላት ይጠበቃል፡፡

| ከ2003 እስከ 2012 ድረስ ጠቅላላ በበክልሉ የታቀደ የተሰበሰበ ገቢና ያልተሰበሰበ ገቢ በሚሊዮን ብር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የበጀት ዓመት | ጠቅላላ የታቀደ ገቢ | የተሰበሰበ ገቢ | | | | | |
| | | ጤና | ትምህርት | የሰራተኛ ስራ ግብር(1101) | በክልሉ በጥረት የተሰበሰበ ገቢ | ጠቅላላ የተሰበሰበ ገቢ | ያልተሰበሰበ ገቢ |
| 2003 | 169.18 | 14.71 | 5.00 | 99.77 | 88.30 | 207.78 | (38.59) |
| 2004 | 260.94 | 19.12 | 6.00 | 128.40 | 162.54 | 316.07 | (55.13) |
| 2005 | 415.86 | 24.33 | 9.33 | 159.61 | 219.15 | 412.42 | 3.44 |
| 2006 | 638.39 | 34.71 | 11.09 | 176.48 | 298.42 | 520.70 | 117.69 |
| 2007 | 719.62 | 38.48 | 11.74 | 295.38 | 352.42 | 698.02 | 21.59 |
| 2008 | 884.75 | 35.82 | 12.04 | 327.05 | 377.10 | 752.01 | 132.74 |
| 2009 | 1,093.05 | 36.91 | 14.79 | 341.29 | 483.38 | 876.37 | 216.68 |
| 2010 | 1,182.37 | 42.53 | 18.21 | 455.65 | 526.22 | 1,042.61 | 139.76 |
| 2011 | 1,301.50 | 46.00 | 18.34 | 512.30 | 492.85 | 1,069.49 | 232.01 |
| 2012 | 1,398.07 | 61.90 | 24.03 | 595.17 | 611.23 | 1,292.33 | 105.74 |
| **አማካይ ገቢ** | **806.37** | **70.96** | **27.17** | **957.05** | **1,018.39** | **718.78** | **87.59** |

### 1.4.2. የክልሉ የወጪ አፈፃፀም

የበጀት አፈጻጸም በ2003 በጀት ዓመት በክልሉ ምክር ቤት የፀደቀዉ ጠቅላላ በጀት ብር 722,129,924.00 ሲሆን በተጨማሪነት የታወጀ 118,329,256.88 ብር ሲጨመር የተስተካከለ በጀት ብር 840,459,180.88 ይሆናል። በ2012 በጀት አመት የፀደቀ ጠቅላላ በጀት ብር 4,740,888,312.00 ሲሆን በ2003 የፀደቀዉ በጀት ከ2012 የፀደቀ በጀት ጋር ሲነጻጸር የተከታታይ ዓመታት ዕድገት በአማካይ 23 በመቶ መሆኑን ያሳያል። ዝርዝሩን ቀጥሎ በተመለከተዉ ሥዕል ማየት ይቻላል።

ተከታታይ ዓመታት የክልሉ በጀት




**የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነት ማሻሻል፡-** ከ2003-2012 ባሉት ተከታታይ ዓመታት ለክልሉ የተመደበዉን ሀብት የአሰራር ሥርዓቶችን ተከትሎ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል እየተደረገም ነዉ።

ከተስተካከለ በጀት አኳያ የፌደራል ድጎማ፣ የክልሉ ገቢ እና ጠቅላላ ያልተሰበሰበ ገቢ ድርሻ ስናይ በ2003 በጀት ዓመት የፌደራል ድጎማ፣ የክልሉ ገቢና ያተሰበሰበ ገቢ በቅደም ተከተል 76.89%፣ 24.72% እና -1.61% ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት የፌደራል ድጎማ 68.98%፣ የክልሉ ገቢ 24.59% እንዲሁም ያለተሰበሰበ ገቢ 6.48% ድርሻ አላቸው። ባለፍት 10 ዓመታት አማካኝ ድርሻው ስንመለከት የፌደራል ድጎማ 67.07%፣ ከክልሉ የተሰበሰበ ገቢ 27.46% እና ያልተሰበሰበ ገቢ 5.48% ድርሻ አላቸው። ባጠቃላይ በ10 ዓመታት ውስጥ

የፌደራል ድጎማ በጀት እየቀነሰ የመጣ ሲሆን በክልሉ ውስጥ የሚሰበሰበው ገቢ ድርሻ እያደገ የመጣ መሆኑን ያሳያል። ነገር ግን ከጠቅላላ በጀት ከክልሉ የሚገኘው ገቢ ድርሻ በፈጣን ሁኔታ እያደገ ያልመጣና ክልሉ ያለውን የገቢ መሰብሰብ አቅም ያገናዘበ ዕድገት ያልመጣ መሆኑን አመላካች ነው።

በክልሉ ባላፉት ተከታታይ ዓመታት የገቢ ዕቅድና አፈጻጸም ድርሻ በፋይናንስ ምንጭ ተለይተዉ እና ታቅዶ ያልተሰበሰበዉ ገቢ ድርሻ በመቶኛ ቀጥሎ ባለዉ ሥዕል ማየት ይቻላል።

ተከታታይ ዓመታት ከፌደራል ድጎማ፣ የክልሉ ገቢ እና ጠቅላላ ያልተሰበሰበ ገቢ ድርሻ በመቶኛ




የመደበኛና ካፒታል በጀት ድርሻን በሚመለከት በቅደም ተከተል በ2003 በጀት ዓመት ብር 716,757,277.71 (85 በመቶ) እና 123,201,212.81 (15 በመቶ) ከነበረበት በ2012 ብር 4,401,013,617.97 (89 በመቶ) እና 564,032,407.86 (11 በመቶ) ሲሆን አማካይ ዕድገቱ ለመደበኛ በጀት 86% እና ለካፒታል በጀት 14% ነው። ይህ የበጀት ድርሻ በወቅቱ ክልሉ ገና

ያልተቋቋመ ስለሆን ለታችኛዉ የአስተዳደር እርከን ብቻ (የዞኖች፣ የወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች ብቻ ነዉ)፡፡

ተከታታይ ዓመታት የመደበኛና ካፒታል በጀት ድርሻ በመቶኛ




የዕድገት ተኮር ተቋማት በ2003 በጀት ዓመት የተመደበ በጀት ብር 482,972,920.85 ከነበረበት በ2012 በጀት ዓመት ብር 2,804,203,793.00 ሲሆን በ2003 እና በ2012 በጀት አመት የወጪ አፈጻጸማቸው ከተፈቀደዉ በጀት በላይ መሆኑን መረጃ ያሳያል፡፡ ባለፉት አስር ዓመታት አማካኝ የወጪ አፈጻጸም ድርሻ 98 በመቶ ነው፡፡

የተከታታይ ዓመታት ለመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተፈቀደ በጀትና ወጪ አፈጻጸም (በብር) ና ድርሻ (በመቶኛ)

| የተከታታይ አመታት ለመሰረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተፈቀደ በጀትና ወጪ አፈጻጸም | | | |
|---|---|---|---|
| **በጀት ዓመት** | **የተፈቀደ በጀት** | **የወጪ አፈጻጸም** | **የወጪ አፈጻጸም በመቶኛ** |
| 2003 | 482,972,920.85 | 507,202,451.18 | 105.02 |
| 2004 | 630,953,105.51 | 630,413,064.51 | 99.91 |
| 2005 | 770,297,074.31 | 725,377,805.55 | 94.17 |
| 2006 | 853,648,741.68 | 801,125,080.29 | 93.85 |
| 2007 | 1,081,042,457.42 | 1,045,835,294.52 | 96.74 |
| 2008 | 1,409,622,966.66 | 1,334,483,519.60 | 94.67 |
| 2009 | 1,928,958,427.74 | 1,858,684,446.39 | 96.36 |
| 2010 | 2,223,915,893.64 | 2,166,361,575.25 | 97.41 |
| 2011 | 2,506,168,048.48 | 2,526,348,515.89 | 100.81 |
| 2012 | 2,804,203,793.00 | 2,918,030,495.78 | 104.06 |
| **አማካይ** | **1,469,178,342.93** | **1,451,386,224.90** | **98.30** |

ከፍ ሲል ባለው ሠንጠረዥ እና ቀጥሎ ባለው ሥዕል በተመለከተው መረጃ መሠረት የዕድገት ተኮር ሴክተሮች ከተፈቀደው በጀት አንፃር በስራ ላይ ያልዋለ በጀት አፈጻጸም አማካይ 2 በመቶ በመሆኑ ወደፊት በተፈቀደው በጀት መሠረት በወቅቱ ሥራዎችን በማከናወን አፈጻጸሙን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

**የተከታታይ ዓመታት ለዕድገት ለመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተፈቀደ በጀትና የወጪ አፈጻጸም ድርሻ በመቶኛ**



# ምዕራፍ ሁለት

# 2. የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት አፈጻጸም

## 2.1. የግብርና አፈጻጸም

ዘርፉ ለጠቅላላ የክልሉ ኢኮኖሚ ዕድገትና ለድህነት ቅነሳ የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ከማሳደግ አኳያ በዘርፉ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ዕድገት በማምጣት የግብርና (የሰብል፣ እንስሳትና ዓሳ) ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦትን ማቀላጠፍ፣ በዘርፉ የገበያ ትስስርን ማሳደግ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ የግብርና ልማትን ማረጋገጥ፣ የህዝቡን ተጠቃሚነት በየደረጃው ማረጋገጥ እና በዘርፉ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ ማስቻል የዘርፉ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ነበሩ።

የግብርና ዘርፍ ከአጠቃላይ የክልሉ ኢኮኖሚ ዕድገት ባለፉት አምስት ዓመታት በአማካይ በየዓመቱ የ57.6 በመቶ ድርሻ የነበረው ሲሆን በግብርና ውስጥ ከሚጠቃለሉት ዋና ዋና ንዑስ ዘርፎች መካከል ዋና ዋና የሰብል ምርት 43.6 በመቶ፣ የእንስሳትና ሀብት 8.5 በመቶ፣ በደን እና አደን 5.0፣ እና አሳ 0.5 በመቶ በአማካይ አድገዋል።

### የግብርናው ዘርፍ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ በመቶ (2008-2012)

እስከ 2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ ድረስ በመሰረታዊ የገ/ቁ/ብ/ኅ/ሥ/ማ እና በዩኒየኖች ውስጥ በድምሩ ብር 145,000,000 ብድር፣ 86,672,000 ብር ቁጠባ ማስቆጠብ የተቻለ ሲሆን ከክልሉ እምቅ ሀብት አንጻር የተመዘገበው አፈጻጸም ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል። በዚህ መሠረት የኦዲት አገልግሎት ለመሰረታዊ ማህበራትና ለዩኒየኖች 1,199 ህብረት ሥራ ማህበራትን የኦዲት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ 728 የህብረት ሥራ ማህበራት የኦዲት አገልግሎት ተሰጥቷል። የክልል ኅብረት ሥራ ልማት ኤጀንሲ የ2ኛ ዕትዕ የ5 ዓመት የአፈጻጸም መረጃ እንደሚያሳየው በክልል አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ በአማካይ ከሚሰራጨዉ የአፈር መዳበሪያ ውስጥ የኅብረት ሥራ ማህበራት ድርሻ 96 ከመቶ ደርሷል።

### ሀ/ የሰብል ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል

የሰብል ምርትና ምርታማነትን ከማሻሻል አንጻር በ2007 ምርት ዘመን ከ216,434 ሄ/ር የተገኘዉን 5.7 ሚሊዮን ኩ/ል የአዝርዕት ሰብሎች ምርት በ2012 ምርት ዘመን የማሳ ሽፋኑን ወደ 371,255 ሄ/ር በማሳደግና ምርታማነቱን በማሻሻል 12.6 ሚሊዮን ኩ/ል ለማድረስ ተችሏል። ከአዝርዕት ሰብሎች መካከል በአገዳ ሰብል አጠቃላይ ምርት በ2007 ከነበረበት 3.3

ሚሊዮን ኩ/ል በ2012 ወደ 8.8፣ በብርዕ ሰብል ከ1.03 ሚሊዮን ኩ/ል ወደ 1.9፣ በጥራጥሬ ሰብል ከ1.4 ሚሊዮን ኩ/ል ወደ 1.6፣ በቅባት ሰብል ከ0.009 ሚሊዮን ኩ/ል ወደ 0.1 ሚሊዮን ኩ/ል እድገት አሳይተዋል፡፡

የሆርቲካልቸር ሰብሎችን (አትክልትና ፍራፍሬ) ልማት በተመለከተ በ2007 ምርት ዘመን በ43,738 ሄ/ር የተመረተውን 7.5 ሚሊዮን ኩ/ል በ2012 ምርት ዘመን በ161,844 ሄ/ር 10.7 ኩ/ል ማምረት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በ2007 ምርት ዘመን ከ21,169 ሄ/ር የተገኘዉን 4.6 ሚሊዮን ኩ/ል የእንሰት ምርት በ2012 ምርት ዘመን ከ75,842 ሄ/ር ወደ 13.9 ሚሊዮን ኩ/ል ማድረስ ተችሏል፡፡

የግብርና ኤክስቴንሽን አፈጻጸምን በተመለከተ ለአርሶ አደሩ በብቃት አሃድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና ለመስጠት እንዲችሉ በብቃት መመዘኛ ስርዓት ዉስጥ አልፈዉ አርሶ አደሮችን እንዲያበቁ በተቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት በአምስት ዓመታት ዉስጥ 66,536 አርሶ አደሮች በብቃት አሃድ (COC) ተመዝነዉ ብቃታቸዉን እንዲያሻሽሉ ተደርጓል፡፡ በተመሣሣይም 629 የልማት ጣቢያ ሠራተኞች በደረጃ 3 እና 4 ተመዝነው ሙሉ በሙሉ የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ ዓመታት 232,682 ወንድ እና 35,032 ሴት በድምሩ 267,714 አርሶ አደሮች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትና ተደራሽነትን ከማፋጠን አንጻር በደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልል የሚገኙ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት (አማማ) በአገልግሎት አሠጣጥ ደረጃቸው እንዲለዩ ተደርገዋል፡፡ በዚሁ መሰረት “ወደ ኋላ የቀሩ” (Pre-basic) 136፣ በመሠረታዊ ደረጃ (Basic) 443፣ በመካከለኛ ደረጃ (Intermediate) 98 እና በከፍተኛ ደረጃ (Advanced) 59 ማድረስ ተችሏል፡፡ የአማማ የተደራጁበትን አላማ ከማሳካት አኳያ ሲታይ ከላይ ከተሰጣቸዉ ደረጃ ማየት እንደሚቻለዉ የአርሶ/አርብቶ አደሩን አመለካከት እና ግንዛቤ በመቀየር የቴክኖሎጂ ሰርፀት በማስፋፋት የሚጠበቀዉን ምርትና ምርታማነት ከማሳደግ አንፃር ተገቢዉን ሚና አለመጫወታቸዉን ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 124 ግንባታዉ የፈረሰባቸዉ እና 108 አማማ የሌላቸዉ የገጠር ቀበሌዎች በክልሉ መኖራቸዉን መረጃዉ የሚያሳይ ስለሆነ በአጠቃላይ በክልሉ ያለዉን የአማማ ሁኔታ በቀጣይ ፈትሾ በማጠናከርና ጉድለቶችን በማሟላት፣ በተለይም የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸዉን በማሳደግ የአገልግሎቱንም ተደራሽነት ከፍ ማድረግ ትኩረት የሚሻዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

**ለ/ ቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት**

የቡና ልማት ስራዎች አፈጻጸም በተመለከተ የቡና ማሳ ሽፋንን በ2007 ምርት ዘመን ከነበረበት ከ387,051 በ2012 ወደ 423,723 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 422,349 ሄ/ር ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከዚህም 200,057 ቶን ቡና ለማምረት ታቅዶ 275,694 ቶን ምርት ማምረት ተችሏል። ይህም የክልሉ አማካይ የቡና ምርታማነት 6.5 ኩ/ል በሄ/ር መድረሱን ያሳያል።

የሻይ ልማትን በተመለከተ አርሶአደር አዉትግሮወርስ የማሳ ስፋትን በ2007 ምርት ዘመን ከነበረበት ከ757.9 ሄ/ር በ2012 ወደ 1,042.4 ሄ/ር በማድረስ 7,090.2 ቶን ለማምረት ታቅዶ በ942.5 ሄ/ር 6,165.4 ቶን የሻይ ምርት የተገኘ ሲሆን ምርታማነቱም በአማካይ 65 ኩ/ል በሄ/ር ሆኗል።

በቅመማ ቅመም (ኮረሪማ፣ ዝንጅብል፣ ጥምዝ፣ እርድ፣ በርበሬ) ሰብሎች ልማት በ2007 የነበረውን 23,475.2 ሄ/ር የመሬት ሽፋንን በ2012 ወደ 61,760.9 በማሳደግ 323,773.8 ቶን ምርት ለማምረት ታቅዶ በ53,380.1 ሄ/ር 305,578.3 ቶን ማምረት የተቻለ ሲሆን ምርታማነቱንም በአማካይ ወደ 57.2 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ተችሏል።

በደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልል የቡና ምርታማነት እያደገ እንደመጣና አንዳንድ ሞዴል አርሶ አደሮች አስፈላጊዉን የምርት ማሻሻያ ፓኬጅ በመጠቀምና ተገቢዉን እንብካቤ በማድረግ በሄ/ር እስከ 22 ኩ/ል የቡና ምርት ማግኘት እንደቻሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ስለሆነም ክልሉ ለቡና ልማት ካለዉ ተጨባጭ ተስማሚነት አኳያ የምርታማነት ማሻሻያ ሙሉ ፓኬጆችን በቀጣይ ተግባራዊ በማድረግና አስፈላጊዉን የኤክስቴንሽን አገልግሎት በማጠናከር ክልላዊ አማካይ የቡና ምርትን በ2ኛዉ የዕ.ት.ዕ. ዘመን ከተመረተዉ 6.5 ኩ/ል በሄ/ር በተሻለ በማምረት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በክልሉ በ2012 የምርት ዘመን ከጫካ እና ከከፊል ጫካ ቡና እንደቅደም ተከተላቸዉ 1.27 ኩ/ል በሄ/ር እና 2.1 ኩ/ል በሄ/ር ቡና ማምረት የተቻለ ቢሆንም ምርታማነቱ ዝቅተኛ ነዉ። የቡና ምርታማት ከማሳደግ አኳያ በዘርፉ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማነቆዎች የራሳቸዉ አሉታዊ ሚና ሲጫወት ቆይቷል። ለምሳሌ የተሻሻሉ የቡና ዝሪያዎችን ያለመጠቀም፤ ተገቢዉን እንክብካቤ ያለማድረግ፤ቅድመ ምርትና ድህረ-ምርት አያያዝ (የቡና ምርት ዝግጅት) ስራዎች በዘርፉ ተግባራዊ አለመደረጉ ለምርታማነት ማነስና ለምርት ጥራት መጓደል አስተዋጽኦ አበርክቷል። ስለሆነም የቡናን እንክብካቤ በማሻሻልና በልዩ ትኩረት የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት ጥቅል የቡና ዘርፍ ምርትና ምርታማነቱ የሚጨምርበትን አሰራር መከተል አስፈላጊ ነዉ።

የደቡብ ምዕራብ ክልል ለሻይና ቅመማ ቅመም ልማት እጅግ አመቺ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በሻይ ልማት ኢንቨስትመንት ድርጅቶች አቅራቢያ ያሉትን አርሶ አደሮች በአውት ግሮወር ዘዴ ከሻይ ልማት ድርጅቶቹ ጋር አስካሁን ያላቸዉን ትስስር በማጠናከር፣ የትስስር አድማሱን በማስፋትና የምርታማነት ማሻሻያ ፓኬጅ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ አርሶ አደሮችንም ሆነ አልሚ ድርጅቶችን የሁለትዮሽ ተጠቃሚነትን በሚያረጋገጥ መልኩ የሻይ ምርት ኤክስፖርት መጠንን በመጨመር ዘርፉ በአገራችን ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ጉልህ ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የአልሚ ባለሀብቶችን ሻይ ልማት መሰረታዊ መረጃ በመያዝ እንደአስፈላጊነቱ ተገቢዉን ድጋፍ ማድረግና ከሻይ ምርቱ ከሚገኝ ገቢ መነሻ የግብር ክፍያ በአግባቡ ማስፈጸም ተገቢ ይሆናል፡፡

በተመሳሳይም በቅመማ ቅመም ልማት ዘርፍ ክልሉ ያለዉን እምቅ አቅም በአግባቡ መጠቀም ባለመቻሉ የምርትም ሆነ የምርታማነት እድገት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ከመገኘቱም ባለፈ ለአምራቹና ለሀገር ኢኮኖሚ ማበርከት ያለበትን አስተዋጽኦ አላደረገም፡፡ የክልሉን ምቹነትና የማልማት አቅም በተገቢዉ በመጠቀም አምራች አካላትንና አገሪቱን ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል በቀጣይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እጅግ ጠቃሚ ነዉ፡፡ የኮረሪማና ጥምዝ ምርታማነት እንዲሻሻል ተገቢዉን እንክብካቤ ማድረግ፣ ቁንዶ በርበሬ በአርሶ አደር ማሳ እንዲመረት በማድረግ አስፈላጊዉን ድጋፍ መስጠት እንዲሁም በቀጣይ የቡናና የቅመማ ቅመም ምርት ተቀነባብሮ ለገበያ የሚቀርብበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ነዉ፡፡

### ሐ/ የተፈጥሮ ሀብት ልማት

ከተፋሰስ ልማት ሥራዎች አንጻር ትላልቅ ተፋሰሶችን ወደ ንዑስ የማህበረሰብ ተፋሰሶች በመከፋፈል ያሉባቸውን የጉዳት ደረጃ በመለየት በጥናት ላይ የተመሠረተ የልማት እቅድ ተዘጋጅቶላቸው እንዲፈፀሙ በማድረግ በቁጥር 1,158 የማህበረሰብ ንዑስ ተፋሰሶችን በ240,337 ሄ/ር ላይ ለማልማት ታቅዶ 395 ንዑስ ተፋሰስ ለማድረስ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት 610,358.5 ሄ/ር የማህበረሰብ ተፋሰሶችን በተለያዩ ስነ አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ለመሸፈን የተቻለ ሲሆን ከዚህም ዉስጥ 36,479 ሄ/ር ያህሉ ከእንስሳትና ከሰዉ ንክኪ ነፃ ሆኖ እንዲበለጽግ ተደርጓል፡፡

ከስነ-ህይወታዊ ሥራዎች አፈጻጸም አንጻር በዕቅድ ዘመን 102 ኩ/ል ፈርጀ-ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን የእፅዋእት ዘሮች ለመሰብሰብ ታቅዶ 325 ኩ/ል መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በዚሁ መነሻ

116 ሚሊዮን ችግኞችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 329 ሚሊዮን ችግኞችን በማዘጋጀት 37,858 ሄ/ር መሬት በስነ ሕይወታዊ ዘዴ መሸፈን ተችሏል፡፡

የመስኖ ልማትን በተመለከተ በክልላችን የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ አቅምን የመጠቀም ሥራ በህዝብ ንቅናቄ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት በሰፊው በመሰራቱ የተለያዩ የመስኖ ውሃ አማራጮች እንዲሰፉ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በቁጥር 6,457 አነስተኛ ወንዝ ለመጥለፍ ታቅዶ 3,052፣ የእጅ ጉድጓድ በቁጥር 3,561 ለማስቆፈር ታቅዶ 2,675፣ ምንጭ ማጎልበት በቁጥር 4,080 ታቅዶ 5,587፣ ቤተሰብ ገንዳ ቁፋሮ በቁጥር 240 ታቅዶ 28፣ ማህበረሰብ ኩሬ በቁጥር 50 ታቅዶ 5 እንዲሁም የዉሃ መሳቢያ ፓምፕ በቁጥር 115 ታቅዶ 745 ለመፈጸም ተችሏል፡፡ በዚህም እያንዳንዱ አርሶ አደር ቢያንስ የአንድ ውሃ ባንክ ባለቤት እንዲሆን ጥረት በመደረጉ በ2012 ምርት ዘመን 147,669 ወንድ እና 53,343 ሴት በድምሩ 201,012 አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ በመቻሉ በጠቅላላዉ 46,291.3 ሄ/ር መሬት በባህላዊና በዘመናዊ መስኖ በማልማት 13.5 ሚሊዮን ኩ/ል የተለያዩ ሰብሎችን ማምረት ተችሏል፡፡ ሆኖም ክልሉ ዝናብን ጨምሮ ካሉት በርካታ የዉሃ አማራጮች አንጻር የዉሃ አጠቃቀም ደረጃን በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግና የምግብ ዋስትናን በዘላቂነት ማረጋገጥና ወደ ትርፍ አምራችነት እንዲሸጋገር ማድረግ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በተጨማሪም በቀጣይ በጥናት ላይ የተመሰረተ የአነስተኛ፣ የመለስተኛና ከፍተኛ የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክቶችን በየደረጃዉ ተግባራዊ በማድረግና የገበያ ምርቶችን በስፋት በማምረት ዘርፉ ለክልሉና ለአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከአፈር ለምነት ማሻሻያ አኳያ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በሀገራችን የአፈር አሲዳማነት ሽፋን እያደገ መጥቶ እስከ 43% የደረሰ ሲሆን በክልላችም ከ45% በላይ መሬት በከፍተኛ አሲዳማነት የተጠቃ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም ከ2008 እስከ 2012 ዓ.ም ድረስ የአፈር ምርመራ ውጤት መሰረት በማድረግ 23,054 ሄ/ር መሬት በኖራ ለማከም ታቅዶ 7,451.5 ኩ/ል ኖራ በማቅረብ 1,194 ሄ/ር መሬት ለማከም ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በህያው ማዳበሪያ 248 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 1,560 ሳቼት ህያው ማዳበሪያ በማቅረብ 495 ሄ/ር መሬት በተለያዩ የጥራጥሬ ሰብሎች እንዲለማ ተደርጓል፡፡ የደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልል ለአፈር አሲዳማነት ካለዉ ተጋላጭነት አኳያ ልዩ ትኩረት በመስጠትና የላቦራቶሪ ምርመራን መሰረት በማድረግ በኖራ አፈርን ከማከም ጎን ለጎን በጥናት ላይ

ተመስርቶ የኖራ ማምረቻ ማዕከል በክልሉ በመገንባት እስካሁን በአገር ደረጃ ያለዉን የአቅርቦት ችግር በተወሰነ መልኩ መቀነስ ተገቢ ይሆናል፡፡

የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን ከማሻሻል አንጻር የገጠር መሬት ባለይዞታዎችን የመጠቀም መብት ለማረጋገጥ የተጀመረውን የአንደኛ ደረጃ የመሬት ልኬት በማሳ ቁጥር 510,217 ለማድረስ ታቅዶ 461,758፣ የሁለተኛ ደረጃ የመሬት ልኬትን በማሳ ቁጥር 115,843 (93,211 ሄ/ር) ማድረስ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ባለፉት አምስት ዓመታት በአንደኛ ደረጃ ልኬት የ124,275 እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ልኬት የ49,076 አርሶ አደሮችን ማሳ ለመለካት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ተግባር በአጥጋቢ ሁኔታ ያልተፈፀመና ከተገቢዉ ጊዜ በላይ የዘገየ በመሆኑ በቀጣይ ይህን አፈጻጸም በመፈተሽና ቀሪ ሥራዎችን በመለየት ሥራዉ በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቅበትን አሰራር መከተል ያስፈልጋል፡፡

**መ/ የግብርና ግብዓት አቅርቦት**

በክልሉ ባለፉት አምስት ዓመታት 21,142.5 ኩ/ል የሰብል ምርጥ ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 7,390.5 ኩ/ል፣ 13,700.5 ኩ/ል የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ ታቅዶ 59,001 ኩ/ል እንዲሁም 10,469 ሊትር የፀረ-አረም፣ ፀረ-በሽታና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በማቅረብ የክልሉን አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ ሆኖም ከክልሉ የመልማት አቅምና ከአርሶ አደሩ ቁጥር አንጻር አፈጻጸሙ እጅግ አነስተኛ ነዉ፡፡ የግብዓት አቅርቦቱም ቢሆን የክልሉን ስነምህዳራዊ ተስማሚነትን ያለገናዘበና የአርሶአደሩን ፍላጎት መሰረት ያላደረገ መሆኑ ሌላዉ የዘርፉ ተግዳሮት ነዉ፡፡ ስለሆነም በቀጣይ በአርሶ አደሮች ማሳ እና በአማማ ላይ በግብርና ምርምር የታገዘ የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅና ሥርፀት ሥራዎችን በስፋት በመስራት፣ የእርሻ መሬቶችን የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት በጥናት በመለየት የሰብል ምርጥ ዘርና የአፈር ማዳበሪያ አጠቃቀም ሽፋንን በማሳደግና የክልሉን ምርትና ምርታማነት በማሻሻል የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ከፍ የማድረግ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡

**ሠ/ የግብርና ምርምር**

በግብርናው ዘርፍ የሚታዩ ዘርፈ-ብዙ የግብርና ማነቆዎችን ለመቅረፍ ቴክኖሎጂዎችንና አሠራሮችን ለተጠቃሚው ከማቅረብ አንጻር በሰብል ምርምር በ28 ፕሮጀክቶች ሥር 42 ተግባራት ታቅደዉ 38፣ በእንስሳት ምርምር በ9 ፕሮጀክቶች ሥር 16 ታቅደዉ 16፣ በተፈጥሮ ሀብት ምርምር በ8 ፕሮጀክቶች ሥር 11 ታቅደዉ 11 ማከናወን የተቻለ ሲሆን ዉጤታማ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች ፓኬጅ ተዘጋጅቶላቸዉ ለተጠቃሚዎች በመቅረብ ላይ

ይገኛሉ፡፡ የቅድመ ኤክስቴንሽን ሠርቶ ማሳያ ሥራዎችን ለአርሶ አደሩ ከማቅረብ አኳያ ቴክኖሎጂዎችን በ20 አርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት (አማማ) እና በ200 አርሶ አደር ማሳ ለማካሄድ ታቅዶ በ12 አማማ እና በ255 አርሶ አደር ማሳዎች ላይ የተከናወነ ሲሆን 16,500 ወንድ እና 8,500 ሴት በድምሩ 25,000 አርሶ አደሮችን በሥራዉ ማሳተፍ ተችሏል፡፡

በደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልል እስካሁን ያለዉ የግብርና ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ሥርፀት እንዲሁም አጠቃቀም ሁኔታ ሲታይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የዚህም ዋነኛዉ ማሳያ ለክልሉ አርሶ/አርብቶ አደር በሰብል፣ በእንስሳትና ዓሣ እና በተፈጥሮ ሀብት ዘርፎች እስካሁን ሲቀርብ የነበረዉ ቴክኖሎጂ እጅግ ዉስን በመሆኑ የክልሉ ምርትና ምርታማነት በሚጠበቀዉ ደረጃ ማደግና በዚያዉ ልክ ጎብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ አለመቻሉ ነዉ፡፡ ስለሆነም በምርምር ተፈትሽዉ ዉጤታማነታቸዉ የተረጋገጡ የሰብል፣ የእንስሳትና ዓሣ፣ የእንስሳት መኖ እና የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂዎችን ለክልሉ አርሶ/አርብቶ አደሮች በስፋት በማስተዋወቅና አቅርቦቱንም ተደራሽ ከማድረግ ባሻገር አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በማፍለቅ በሚጠበቀዉ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ለማድረግም በቀጣይ በጥናት ላይ ተመስርቶ የግብርና ምርምር ዘርፉን የዉስጥ አቅም መገንባትና የተደራሽነት አድማሱንም ማስፋት ተገቢ ይሆናል፡፡

### 2.1.2 የህብረት ስራ ልማት

የሕብረት ስራ ማህበራት ለአባላቱ የተለያዩ ግብዓቶችን በማቅረብ፣ የምርት ግብይት በማካሄድና የብድርና ቁጠባ አገልግሎት በመስጠት አጠቃላይ የአባላቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የመፍታት አላማ ለማሳካት የተፈጠረ ተቋም ነዉ፡፡ የሕብረት ስራ ማህበራት በዋናነት ተልዕኳቸዉ በደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልል በ 5 ዘርፎች የተደራጁ 2235 መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራትና 18 ዩኒየኖች የሚገኙ ሲሆን የካፒታል አቅማቸዉ በመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት 348,679,623 ብር እና በዩኒየን 157,061,018 ብር ደርሷል፡፡ ጠቅላላ የአባላት ቁጥር 184,038 የደረሱ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ 54,038 ሴቶች ናቸዉ፡፡ የመሰረታዊ የገ/ቁ/ብ/ኅ/ሥ/ማህበራት እና የዩኒየኖችን ቁጠባና ብድር በተመለከተ 916.9 ሚሊዮን ብር ለማስቆጠብ ታቅዶ ብር 837.9 ሚሊዮን ማስቆጠብ የተቻለ ሲሆን ብር 53,396,343.00 በብድር ለማሰራጨት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ማሰራጨት ተችሏል፡፡ ለጎብረት ሥራ ማሕበራት የምርት ግብይት ፋይናንስ ከማመቻቸት አንጻር ባለፉት 5 ዓመታት 306.20 ሚሊዮን ብር ብድር ለማመቻቸት ታቅዶ 353.00 ሚሊዮን ብር ብድር የማመቻቸት ስራ

ተከናውኗል። እንዲሁም ለግብዓት ብድር አቅርቦት 399.6 ሚሊዮን ብር ለማመቻቸት ታቅዶ ብር 135.70 ሚሊዮን ለማመቻቸት ተችሏል።

የኅብረት ሥራ ማህበራት በዕቅድ ዘመኑ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ወደ ውጭ አገር በመላክና ለአገር ዉስጥ ገበያ አቅርበዋል ። በዚሁ መሠረት 7,749 ቶን ያልታጠበና 3,261 ቶን የታጠበ ቡና በድምሩ 11009 ቶን ወደ ለማዕከላዊ ገቢያ የቀረበ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ 4,723.5 ቶን ሻይ እና 546.ቶን ማር ለማዕከላዊ ገበያ በማቅረብ 98,038,278 ብር እንዲሁም 2,003 አዉራ በጎችን ለተለያዩ ተቋማትና አካባቢዎች በማቅረብ ብር 7,228,013.00 ገቢ ማግኘት ተችሏል። የግብርና ግብዓት ከማቅረብ አንጻር 21821 ቶን የአፈር ማዳበሪያ በማቅረብ ለተጠቃሚዎች የማሰራጨት ስራ ተከናውኗል። ከምርት ግብይት፣ ከአባላት የቁጠባ ወለድና ከተለያዩ ሥራዎች ከሚገኘዉ ትርፍ ብር 36.5 ሚሊዮን ለአባላት ለማከፋፈል ታቅዶ 31.1 ሚሊዮን ብር ለአባላት የማከፋፈል ስራ ተሰርቷል።ቢሆንም በዩኒየኖች በኩል የሚገኝ ትርፍ ገቢ በህገ ደንባቸዉ መሰረት ለመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራትና ለአባላቶቻቸዉ በአግባቡ የማይከፋፈል ከመሆኑም በላይ አባላት ላቀረቡት ምርት በወቅቱና ተመጣጣኝ ክፊያ የማያገኙ በመሆናቸዉ ከተቋቋሙበት አላማ አንፃር ተልዕኳቸዉን እየተወጡ ነዉ ማለት አይቻልም። ከዚህ በተጨማሪ መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራትም ሆነ ዩኒየኖች ግልፀኝነት ተጓደለ አሰራር በመከተል በትርፍ፣ ኪሳራና ተቀማጭ ካፒታል ላይ አባላቱ የተሟላ መረጃ እንዲኖር ባለማድረግ የሀብትና ንብረት ብክነት በማስከተል በአባላቱ ዘንድ ለተለያየ ቅሬታዎችና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ምንጭ ሆኖ ቆይቷል። ከአገልግሎት አሰጣጥ አንፃር የምርት ግብዓትና የፍጆታ ምርት አቅርቦት ከማቅረብ አንፃር ዉስንነትና አቅም ማነስ፣የካፒታል እጥረት እንዲሁም የማህበራት የእርስበርስ ተደጋጋፊ ግንኙነቶች አለመጠናከር ቁልፍ ማነቆዎች ናቸዉ። በአዳራጅ መስሪያ ቤቱም በኩል ጠንካራ የክትትልና የቁጥጥር እንዲሁም የድጋፍ ስራዎችን የማከናወን ቁመናዉ ደካማ በመሆኑ ማህበራቱንና ዩኒየኖችን ካሉበት ችግር በማዉጣት ሂደት የሚጠበቅበትን ሚና እየተጫወቱ አይደለም።

ስለሆነም የአዳራጅ መሥሪያ ቤቱን የዉስጥ አቅም በማጠናከር በሁሉም የኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጀ የኦዲቲንግና ኢንስፔክሽን ሥራዎችን በየወቅቱ በማካሄድ የአባላቱን ገንዘብ/ፋይናንስና ንብረት ከጥፋትና ብክነት መከላከል ያስፈልጋል። በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራት ከግብይትና ከገንዘብ ቁጠባ የሚያገኙትን ትርፍ ወቅቱን ጠብቀዉ ለአባላቱ በማከፋፈል በተለይም በአርሶ አደር አባላት በኩል ከትርፉ መጠንና ከወቅታዊነት አንጻር

በየጊዜው የሚነሱ ቅሬታዎች የሚወገዱበትን የተሟላ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ትልቅ ትኩረት የሚያስፈልገው ጉዳይ ስለሆነ በዚህ ረገድ የተጠናከረና በህግ ማዕቀፍ የተደገፈ የማምረትና የንግድ ሂደቶች ያለገደብ ተዋኒያን መሆን የሚያስችላቸው ተነፃፃሪ ነፃነት ያላቸው የህብረት ስራ ማህበራት አደረጃጀትና አሰራር የሚሰፍንበት ስርዓት ሊበጅ ይገባል፡፡

### 2.1.3 እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት

#### ሀ/ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት

በክልሉ 2,073,368 የዳልጋ ከብቶች፣ 1,042,422 በጎች፣ 459,917 ፍየሎች፣ 1,811,742 ዶሮዎች፣ 340,933 የጋማ ከብቶች እንደሚገኝ ከማዕከላዊ ስታቲስትክስ የተገኘ መረጃ ያመላክታል፡፡ ባለፉት የዕቅድ ዓመታት የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍን ምርታማነት ለማሳደግ በርካታ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ በዚህ መሰረት የሥጋ ምርትን ወደ 63,759.2 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 49,405.6 ቶን፤ 211,462 ቶን ወተት ለማምረት ታቅዶ 116,973.1፣ 5,330 ቶን እንቁላል ለማምረት ታቅዶ 4,339.6፣ በቁጥር 1,096,782 ቆዳና ሌጦ ለማምረት ታቅዶ 1,032,671፣ 49,568 ቶን ማር ለማምረት ታቅዶ 43,315.6፣ 1,612.1 ቶን ዓሣ ለማምረት ታቅዶ 1045 ቶን ማምረት ተችሏል፡፡ ከእንስሳት ግብኣት አቅርቦት በኩል በተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች አቅርቦት በቁጥር 1,137,996 የ40 ቀን ቂብና ኮክኔ እና 1,123,083 የአንድ ቀን ጫጩት እንዲሁም 134,661ለም እንቁላል እና 32,240 የዓሣ ጫጩት ለተጠቃሚ አርሶ አደሮች እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ከማር ምርት ግብዓት አቅርቦትን በተመለከተ ባህላዊ ቀፎ 51, 693 ዘመናዊ ቀፎ 3,738 በድምሩ 55,431 ቀፎ በአቅድ ዘመኑ ተሰራጭቷል፡፡

የወተት ምርታማነትን በተመለከተ ከአንድ የሀገር በቀል የወተት ላም የሚገኝ አማካይ የቀን የወተት ምርት ከ1.5 ሊትር ወደ 1.7 በማሳደግ 13.3%፣ ከአንድ ዲቃላ የወተት ላም የሚገኝ አማካይ የቀን የወተት ምርትን ከ9.4 ሊትር ወደ 10.5 ሊትር በማድረስ 11.7% ዕድገት አሳይቷል፡፡ በተመሳሳይም ከአንድ ዳልጋ ከብት የሚገኝ አማካይ የሥጋ ክብደት (carcas weight) ከ99.3 ወደ 103.3 ኪሎ ግራም በማድረስ 4%፣ ከአንድ በግ የሚገኝ አማካይ የሥጋ ክብደት ከ12.3 ወደ 13.6 ኪሎ ግራም በማድረስ 10.6% እንዲሁም ከአንድ ፍየል የሚገኝ አማካይ የሥጋ ክብደት ከ11.8 ወደ 12.6 ኪሎ ግራም በማሳደግ 6.8% የምርት ጭማሪ አሳይቷል፡፡ በሁሉም የእንስሳት ዘርፎች ካለዉ የእንስሳት ሀብት አቅም አንፃር የተገኘዉ ምርት በእቅድም ሆነ በአፈፃፀም ሲታይ አነስተኛ መሆኑን የእቅድ አፈፃፀሙ መረጃ ያሳያል፡፡ የእንስሳት ዘርፍ ምርት ማነስ ዋና ዋና ምክንያቶቹ የተሻሻሉ የዝርያና የምርታማነት ማሻሻያ

ፓኬጆችን አሟልተው ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ያለው ውስንነትና ከዚህ ጋር በተያያዘ የእንስሳት ዝሪያ ማሻሻያ ስራዎች በሰፊ አለመተግበራቸው እንደሆኑ አመላካች ነዉ፡፡ የዶሮ እርባታ ማእከላት አለመስፋፋትና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አለመኖር እንደ ዋነኛ ተግዳሮት ሲሆን ያለው አንድ መንግስት የዶሮ እርባታ ማእከል ካለው ሰፊ ፍላጎት አንፃር የተደራሽነት ችግር ያለበት መሆኑና ከሌሎች አካባቢዎች የዶሮ ምርት ለማቅረብ የሚደረጉ ጥረቶችም ቢሆኑ ችግር ፈቺ አለሆን ይጠቀሳሉ፡፡

በመሆኑም በክልሉ የሥጋ፣ የወተት፣ የእንቁላልና የማር ምርታማነት መጨመር እንዲችል አስፈላጊ የቴክኖሎጂ ፓኬጆችን አሟልቶ በማቅረብ፣ ተገቢዉን ድጋፍ በመስጠትና የተሻለ የምርት ጭማሪ በማምጣትና ህጋዊ የገበያ ሥርዓት እንዲሰፍን በማድረግ በፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለዉን ክፍተት ከማጥበብ በተጨማሪ ዘርፉን ወሳኝ የገቢ ማመንጫ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በቀጣይ የእንስሳት ሀብት ምርቶችን በተለይም የሥጋ፣ የወተትና የማር ምርቶች ማቀነባበሪያ ተቋማት በክልሉ የሚገነቡበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ምርቶቹን በተገቢዉ በማስተዋወቅ ለአገር ዉስጥና ለዉጭ ገበያ በስፋት ቀርበዉ ከፍተኛ ገቢ የሚያመነጩበትን አሰራር በመከተል ዘርፉ ለክልሉም ሆነ በአጠቃላይ በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያበረክተዉን አስተዋጽዖ ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ለ/ የእንስሳት መኖ ልማትና አጠቃቀም**

በተሻሻለ የእንስሳት መኖ ልማት ዘርፍ 11,398.4 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 11,386 ሄ/ር በተሻሻለ መኖ ለምቷል፡፡ የተሻሻለ የመኖ ዘር ሥርጭትን በሚመለከት 323 ኩ/ል ዘር ለማቅረብ ታቅዶ 470፣ 227 ሚሊዮን ቁርጥራጭ/ግንጣይ ሰንባች የመኖ ዘር (ደሾ እና ዝሆኔ ሳር) ለማቅረብ ታቅዶ 221.5 ሚሊዮን፣ 50.9 ሚሊዮን የመኖ ችግኝ ለማቅረብ ታቅዶ 22.1 ሚሊዮን ችግኝ ለተጠቃሚ አርሶ አደሮችና በእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ ለተሰማሩ አካላት ቀርቧል፡፡

በሰብል ተረፈ ምርት አያያዝና አጠቃቀም ረገድ የንጥረ መኖ ይዘትና ተበይነትን ማሻሻል የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችና የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠትና በአግባቡ በመሰብሰብ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በዚህም በዕቅድ ዘመኑ 792,950 ቶን የሰብል ተረፈ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ 463,345.7 ቶን ተሰብስቦ አገልግሎት ላይ ዉሏል፡፡ የተቀነባበረ መኖ እና አግሮ-ኢንዱስትሪ ተረፈ ምርት አቅርቦትን በ2012 አመት ወደ 3,422 ቶን ለማሳደግ ታቅዶ

3,239.7 ቶን የተመጣጠነ መኖ በወተት ሀብት፣ በማድለብ፣ በማሞከት እና በዶሮ የተሰማሩ አርሶ አደሮች ገዝተው እንዲጠቀሙ ማድረግ ተችሏል፡፡

ሆኖም እስካሁን ያለዉ የመኖ አቅርቦት በክልሉ ካለዉ ፍላጎት አንጻር የማይጣጣም ከመሆኑም ባለፈ አብዛኛዉ የመኖ አቅርቦት በተፈጥሮ ላይ የተመሰረተ መሆን፣ የተመጣጠነ የመኖ አቅርቦት አለመኖር/በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆን እንዲሁም ማቀነባበሪያ ተቋማት በክልሉ አለመኖር ይጠቀሳሉ፡፡ስለሆነም አቅርቦቱን ከማሻሻል በተጨማሪ በቀጣይ ለሥራ ዕድል ፈጠራ መስኮችም ሆነ ለአልሚ ባለሀብቶች ሁኔታዎችን በማመቻቸት የመኖ ማቀነባበሪያ ተቋማት የሚገነቡበትን ድጋፍ ማድረግ እጅግ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

**ሐ/ የእንስሳት ጤና አጠባበቅ**

በክልሉ በአጠቃላይ 252 የእንስሳት ጤና ማዕከላት ያሉ ሲሆን ባለፉት አምስት ዓመታት የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋንን ለማሳደግ ድንበር ዘለልና መደበኛ የእንስሳት በሽታዎችን ከመከላከል አንጻር 9,978,688 ዶዝ የክትባት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ እስከ 2012 በጀት አመት 8,242,843(82.6%) ዶዝ ለተለያዩ እንስሳት 4,219,024 የታመሙ እንስሳትን ለማከም ታቅዶ 3,477,346(82.4%) የተለያዩ እንስሳት የህክምና አገልግሎት፣ እንዲያገኙ የተረገ ሲሆን የቆላ ዝንብ በሽታን ከመከላከል አንጻር 1,180,599 የኬሚካል ርጭት ለማድረግ ታቅዶ 806,580(68.3%) ማከናወን እንዲሁም የበጎችና ፍየሎች የውጭ ጥገኛ ቁጥጥር ሥራን በተመለከተ ለ500,110 አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 47,500(9.5%) በጎችና ፍየሎች አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የክትባቱን ዉጤታማነት በተመለከተ እስካሁን በተደረገዉ እንቅስቃሴ እንስሳቱ ከተከተቡ በኋላ የሚሞቱበት ሁኔታ እየተስተዋለ ስለሆነ ክትባቱ ዉጤታማ እንዲሆን በማጓጓዝ፣ በአያያዝና ክምችት በኩል ያሉትን ችግሮች፣ የህክምና መድሃኒት፣ መገልገያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች እጥረት፣ የህክምና ተቋማት ያለመስፋፋት እንዲሁም የእስሳት ጤና ባለሙያ እጥረት ዋነኛ ችግሮች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንዳንድ በሽታዎች (ለምሳሌ በግንቦት ወር አካባቢ የሚከሰት የአፍሪካ የፈረስ በሽታ) በወረርሽን መልክ የሚከሰቱበትሁኔታዎችም ስላሉ ካለፉት ጊዜያት ተሞክሮ በመነሳት በቅድሚያ የበሽታዎችን ሁኔታ ቅኝትና አሰሳ በማድረግ በሽታዎቹ እንደተከሰቱ ጉዳት ከማድረሱ በፊት ክትባቱ ወዲያዉኑ በበቂ መጠን ቀርቦ አገልግሎት ላይ የሚዉልበትን አሰራር መከተል እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡ የእንስሳት ህክምና መድኃኒት አቅርቦትን በተመለከተም ከፍተኛ ክፍተት ያለበትና ብልሹ አሰራር የሚስተዋልበት

ስለሆነ ይህንን ማስተካከልና በቀጣይ በክልሉ የመድኃኒት ማከማቻና ማከፋፈያ ማዕከል በማቋቋም ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን ሊደረግ ይገባል፡፡

**የአደጋ ስጋትና ቅድመ ማስጠንቀቂያ አፈጻጸምን በተመለከተ**

ክልሉ ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግርን ከመሰረቱ ለመፍታት በሁሉም አካባቢዎች በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፣ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ላይ ተመስርቶ መስኖና ደጋፊ መስኖ ማስፋፋት አጠቃላይና ዋናው የርብርብ ማእከል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለድርቅ ተጋላጭ አካባቢዎችንና ለከፋ የምግብ ዋስትና ችግር የተዳረጉ የህብረተሰብ ክፍሎችን የተለየ ድጋፍ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት ከተሰሩ ስራዎች ውስጥ አንዱ በልማታዊ ሴፍትኔት ታቅፈው ተጠቃሚ ከነበሩ 23,669 የሕብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ጉልበት ያላቸው ቤተሰቦች በማህበረሰብ ስራዎች ተሳትፈው የሚጠቀሙ 17000 (72%) እንዲሁም የቋሚ ቀጥታ ተጠቃሚዎች 3,256 (38%) ናቸው፡፡ ለነዚህ ተጠቃሚዎችም የተከሰተባቸውን የምግብ ክፍተት ለመሙላት ባለፉት መርሀ ግብር አመታት ብር ከ30,0000,000.00 በላይ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ከልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ ውጭ ለሚደርሱ ድንገተኛ ጉዳቶች በ5% በመደበኛ ሴፍትኔት ወይም በእለት እርዳታ መሸፈን ሲገባቸው በልየታ ስህተት ሳይካተቱ የቀሩና ለምግብ እጥረት የተጋለጡትን በአደጋ ስጋት ተጋላጭነት ለተለዩ አርሶ/አርብቶ አደሮች ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በነባር ሰፈራ ጣቢያዎች በሰፋሪው ላይ ያሉ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በማጥናት የመለየት ስራ የተሰራ ሲሆን በነባሩ ክልል አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ከክልሉ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን ጋር በመቀናጀት ለሰፈራ ፕሮግራም መልሶ ማቋቋም ከተያዘው ብር 5,000,000.00 በዴቻ ወረዳ ከሻሎ ቀበሌ እስከ ተሜ ሻሎ ቀበሌ 30 ኪ/ሜትር የገጠር መንገድ ጠረጋ ስራ ተከናውኗል፡፡

በአፍጻጸም ወቅት በልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም - 4 ተጠቃሚ ከነበሩት ተጠቃሚዎች መካከልም የምግብ ዋስትናቸውን በቤተሰብ ደረጃ ማረጋገጣቸው የታመነባቸው ሁሉንም የማህበረሰብ ስራ ተጠቃሚዎችን ከማስመረቅ አንጻር ያለዉ ጉድለት መረጃን መሰረት ያደረገ እና ተጠያቂነት ያለው የምረቃ ስርዓት አለመኖር ችግር ታይቷል፡፡

## 2.2. የአርብቶ አደር ልማት ሥራዎች አፈፃፀም

### ኢኮኖሚያዊ ስራዎች አፈፃፀም በተመለከተ

የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የመኖ ዘር ማባዣ ጣቢያዎችና የመኖ ባንኮች ማቋቋም የተቻለ ሲሆን በእስከ አሁኑ የእንስሳት የመኖ ምርት በመኖ ባንኮች ከመከማቸቱም በተጨማሪ 120 ሄ/ር የተፈጥሮ ግጦሽ በመከለልና 541 ሄ/ር የተጎዳ መሬት እንዲያገግም የተለያዩ እስትራክቸሮችን በመስራት ማልማት ተችሏል፡፡ 58 የጤና ኬላዎችና ኪሊኒኮችን በመገንባት 1,302,905 የተለያዩ እንስሳቶችን ክትባት መስጠት ተችሏል፤ 89 የእንስሳት ጤና ቴክኒሺያኖች፣ 100 የማህበረሰብ እንስሳት ጤና ተጠሪዎችን በማሰልጠን ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ከዝሪያ ማሻሻል አኳያም በኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ የእርባታ ቡድኖች በማቋቋምና በማሰልጠን 254 የተሻሻሉ የፍየል ዝሪያዎች ቀርቧል ፡፡

በዋና ዋና ሰብሎች የምርታማነት ሁኔታ ስንመለከት የአርብቶ አደር ወረዳዎች የምርታማነት ሁኔታው ዝቅተኛ ማለትም በአማካይ 20 ኩንታል በሄክታር ተገኝቷል፡፡ በአገዳ ሰብሎችም ሲታይ የአርብቶ አደር ወረዳዎች አማካይ ምርታማነት 16 ኩንታል በሄክታር የተገኘ ሲሆን የቅባት እህል ምርታማነት የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደር 10 ኩንታል በሄክታር ተገኝቷል፡፡

### የመጠጥ ውሃ

አቅርቦትን በተመለከተ 14 ጥልቅ የዉሀ ጉድጓድ፣ 15 መለስተኛ ጥልቅ የዉሀ ጉድጓድ፣ 59 የእጅ ዉሀ ጉድጓድ፣ 81 የማህበረሰብ የዉሀ ማቆሪያ፣ 9 የማህበረሰብ ኩሬ፣ 5 ባለ 20,000 ሜ/ኪዩብ ዉሀ የሚይዝ የዉሀ ፖንድ፣ 2 የእጅ ዉሀ ፓምፕ እና 64 ምንጭ ማጎልበት (በቦታዉና ማሰራጫ ያለዉ) ባጠቃላይ 242 የተለያዩ የመጠጥ ውሀ ተቋማት ግንባታ ተጠናቅቀዉ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በዚህ የተነሳ በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን GTP-1 ከነበረበት 32% ወደ 47.88% ማሳደግ ተችሏል፡፡

### የመንገድ ልማትን

በተመለከተ በ2ኛው ዕትዕ በፌዴራልና በክልሉ መንግስት 25 ኪ.ሜ አስፓልት፣ 254 ኪ.ሜ በዩራፕ የተሰራ ጠጠር መንገድ፣ እንድሁም በማህበረሰብ ተሳትፎ 133 ኪ.ሜ ጠረጋ ተከናውኗል፡፡ ይህም ከአጠቃላይ የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ የመሬት ቆዳ ስፋት ጋር

ተነጻጽሮ ሲታይ በ1000 ካሬ ኪሎ ሜትር ውስጥ 53.5 ኪ.ሜትር መንገድ መሰራቱን የሚያመላክት ነው፡፡

**ማህበራዊ ስራዎች አፈፃፀም**

በትምህርት ዘርፍ በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በመጀመሪያ ደረጃ 1ኛ እና 2ኛ ሳይክል የተማሪዎች ንጥር ተሳትፎ የትምህርት ሽፋንን 70.3% እና በከፍተኛ 2ኛ ደረጃ እና በመሰናዶ ትምህርት 11.5% ሲሆን ጠቅላላ አፈፃፀሙ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በ2ኛው ዕትዕ 2,059 ተማሪዎች ተመዝግበዉ የሆስቴል አገልግሎት በማግኘት ትምህርታቸዉን መከታተል ችለዋል፡፡

የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ መከላከልን መሰረት ባደረገው የጤና ፖሊስ ተጠቃሚ ለማድረግ በ2ኛው ዕትዕ 28 የጤና ኬላዎች የተገነቡ ሲሆን በጤናው ሴክተርም በተደረገው ልዩ ርብርብ ቀደም ሰል ከተገነቡት 165 ጤና ኬላዎች በተጨማሪ በተጠናቀቁትና በግንባታ ሂደት ላይ ባሉት 25 ጤና ጣቢያዎችና 2 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ተጠናቀው በህክምና መሳሪያዎች፣ በቁሳቁስ፣ በመድሓኒት እና በሰው ኃይል የማሟላት ስራዎች በቀሪ ጊዜያት በተገቢው መስራት ከተቻለ የጤና ሽፋኑን ከተቀመጠው ስታንዳርድ አኳያ 100% ማድረስ ይቻላል፡፡

በ2ኛው ዕትዕ በአጠቃላይ በየወረዳው በተደረገ የማኅበረሰብ ውይይት 45 ጦጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የተለዩ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 32 (71%) በከፊልና በሙሉ እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡

**የመንደር ማሰባሰብ ስራዎች አፈጻጸም**

አንዱ የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ፈቃደኛ ሆኖ በመንደር እንዲሰባሰብ በማህበረሰብ ዉይይት ግንዛቤ ማስጨበጥ ሲሆን ሁለተኛዉ የተሻለ ተሞክሮና አፈፃፀም ካላቸዉ አካባቢዎች ልምድና ትምህርት እንዲወስድ መስራት ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ ሲሰራ ቆይቶ እስከአሁን 10,695 የቤተሰብ ሀላፊዎች ከነቤተሰቦቻቸው 53,475 ህዝብ በፈቃደኝነት ተሰባስበዉ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡

## 2.3. ኢንተርፕራዝና ኢንዱስትሪ ልማት አፈጻጸም

በሁለተኛው የዕ.ት.ዕ ትኩረት ከተሰጣቸው መስኮች አንዱና ዋነኛው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ሲሆን ይህም ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን መዋቅራዊ ሽግግር ማፋጠን ነው። የዕ.ት.ዕ አፈጻጸም ክልላዊ ግምገማው የሚያሳየው ባለፉት ዓመታት የኢንዱስትሪ ዘርፍ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት 10.87 በመቶ መሆኑን ያሳያል።

በክልሉ በአጠቃላይ 2,047 ጥቃቅን ፣ 377 አነስተኛ፣ 190 መካከለኛ እንዲሁም 4 ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ይገኛሉ። በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች ልማት ዘርፍ ሰፊ የስራ ዕድል ከመፍጠር አንጻር በገጠር ለ12,227 እና በከተማ ለ50,157 በድምሩ ለ62,384 ተጠቃሚዎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ ዕድል ለመፍጠር ተችሏል። የኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት አፈፃፀም በተመለከተ በገጠር ቋሚ ፓኬጅ የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው ውስጥ በሰብል ልማት 2,213 (4.2%)፣ በእንስሳት 50,087 (95.6%)፣ በማኑፋክቸሪንግ 43 (0.08%) እና በንግድና በአገልግሎት ዘርፍ 57 (0.1%) ኢንተርፕራይዞችን በማደራጀት አባላትን ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል። በከተማ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን አባላት በተመለከተ በአገልግሎት 2,458 (24.2%)፣ በኮንስትራክሽን 2,942 (29.0%)፣ በማኑፋክቸሪንግ 1,963 (19.4%)፣ በንግድ 1,534 (15.1%) እና በከተማ ግብርና ዘርፍ 1,242 (12.3%) ኢንተርፕራይዞች በማቋቋም ወደ ስራ እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከ377 ኢንተርፕራይዞች ዉስጥ 75 ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት፣ ከ190 መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ዉስጥ 48ቱ ደግሞ ወደ መካከለኛና ከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የተሸጋገሩ ናቸው።

የማምረቻ/መስሪያና መሸጫ ቦታ አቅርቦት እና የሼድ ግንባታን በተመለከተ በገጠር 13,028 ሄ/ር መሬት ለማቅረብ ታቅዶ 10,900 (80.5%) እንዲሁም በከተማ 1,398 ሄ/ር መሬት ለማቅረብ ታቅዶ 267 (19.1%) በማዘጋጀት ለወጣቶች ተለይቶ እንዲተላለፍ ተደርጓል። በከተማ የኢንተርፕራይዞችን የመስሪያና መሸጫ ቦታ ችግር ለመቅረፍ ለሼድ ግንባታ የሚውል የለማ መሬት በማዘጋጀትና 421 ሼዶችን በመገንባት ለኢንተርፕራይዞች ማስተላለፍ ተችሏል።

ከፋይናንስ አቅርቦት አፈፃፀም አንጻር ለወጣቶች ስምሪት የሚያስፈልገው የብድር አቅርቦት በፌደራል ፈንድ፣ በክልል መንግስት፣ በዞን፣ ወረዳ ደረጃ ከሚመደበው እንዲሁም ከብድር ተመላሽ 457,224,625 ብር ብድር ለወጣቶች ለማሰራጨት ታቅዶ 269,457,997 ብር

ተሰራጭቷል። በተለያዩ ጊዜያት ለወጣቶች የተሰራጨዉ ብድር በሞዳሊቲው መሰረት ውዝፍና መመለሻ ጊዜው ደርሶ መሰብሰብ ከነበረበት የብድር መጠን 209,234,709 ብር ውስጥ 124,849,735 ብር ተመላሽ ሆኗል። ከቁጠባ አንጻር በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተደራጅተው ከሚሰማሩ ወጣቶች 629,623,893 ብር ለማስቆጠብ ታቅዶ 635,295,510 ብር ቅድመ-ቁጠባ እና ድህረ-ቁጠባ እንዲቆጥቡ ተደርጓል።

በተለያዩ ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተዉ ወደ ሥራ የተሰማሩ አባላትን አቅም ከመገንባት አንጻር ለ18,980 አንቀሳቃሾች አጫጭር የገበያ ተኮር ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 10,809 አባላት ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። በተጨማሪም ለ26,966 አባላት የክህሎት ክፍተት ማሟያ ስልጠና ለመስጠት ዕቅድ ተይዞ 8,995 አባላትን ማሰልጠን ተችሏል።

### 2.4. የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አፈጻጸም

በየዘርፉ በሁለተኛው ዙር (2008-2012 ዓ.ም) የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የተጣሉ ግቦች አፈፃፀም

**የኮንስትራክሽን ባለስልጣን ስራዎች አፈጻጸምን በተመለከተ፤** በክልል የዲዛይን ዝግጅትና ኮንትራት አስተዳደር ስራዎችን በሚመለከት በአማካሪ የማይሸፈኑ 1732 መካከለኛና አነስተኛ ግንባታዎች የተሟላ ዲዛ ይን ለማዘጋጀት ታቅዶ የ1896 (100%) ግንባታዎች የተሟላ ዲዛይን የተዘጋጀ ሲሆን ከፍተኛ ደረጃ ላላቸው 58 ግንባታዎች ለአማካሪ ግዥ የሚሆን ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ 22 (38%) ማዘጋጀት ተችሏል። የ1732 ፕሮጀክቶች መነሻ ዋጋ ጥናት (Engineering Estimate) በማድረግ የተቋራጮች ደረጃ በመወሰን የተቋራጭ ግዥ ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ የ1896 (100%) ተከናውኗል። ከግንባታ ጥራት ክትትልና ቁጥጥር ጋር በተያያዘ ለ1932 ፕሮጀክቶች የግንባታ መርሐ ግብር /work schedule/ በማዘጋጀት የጥራት ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ በ2031 (100%) ግንባታዎች ወቅቱን የጠበቀ የግንባታ ጥራት ቁጥጥር ማድረግ የተቻለ ሲሆን ለግንባታዎች ለተሰሩ ሥራዎች በአካል በመገኘት ስፍር በመውሰድ (Standard take off sheet) 1932 ለማዘጋጀት ታቅዶ 2031 (100%) ተዘጋጅቷል። ከፍተኛ ደረጃ ላላቸውና በአማካሪዎች ክትትል ለሚደረግባቸው 34 ግንባታዎች ዙሪያ የአማካሪዎችን የሥራ አፈፃፀም ላይ በየወሩ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ ለ22 (38%) አማካሪዎች ላይ በየወሩ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጓል። በዕቅድ ዘመኑ ለሚጠናቀቁ 1550 ፕሮጀክቶች ጊዜያዊ ርክክብ እና ለ836 ፕሮጀክቶች የመጨረሻ ርክክብ ለማድረግ ታቅዶ

የ1145 (74%) ግንባታዎች ጊዜያዊ ርክክብ እና የ546 (65%) ግንባታዎች የመጨረሻ ርክክብ ተከናውኗል፡፡

ከሰው ሃይልና ከሬጉላቶሪ ዘርፍ በአምስት ዓመት የ5000 አነስተኛ እና መለስተኛ ባለሙያዎች የቅድመ-ምዘና ምዝገባ በማከናወን የሙያ ብቃታቸውን በምዘና ለማረጋገጥ ታቅዶ የ4103 (80%) ባለሙያዎች TVET እና COC ጋር በመተባበር ብቃታቸው በምዘና ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም 10ተጨማሪ መሪ መዛኞችን ለማፍራት ታቅዶ 16 (100%) TVET እና COC ጋር በመቀናጀት መሪ መዛኞችን ማፍራት ተችሏል፡፡

የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ክፍተቶችን ለመለየት የሚረዳ 5 የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ ታቅዶ 3 (60%) ተከናውኗል፡፡ ደረጃ በወጠላቸዉ 20 የግንባታ ዕቃዎች ላይ የጥራትና ደረጃ ቁጥጥር እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ20 (100%) ማከናወን ተችሏል፡፡ የህንጻ አዋጁ ተፈጸሚ በሚሆንባቸው ከተሞች የሚገነቡ 3800 ለንግድ፣ ለኢንቨስትመንት፣ ለመንግስታዊ ተቋማት መኖሪያ አገልግሎት የሚውሉ ህንጻዎች በሙሉ የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ እና የሚጠናቀቁ 242 የምድብ “ሐ” ህንጻዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ ለ135 (95%) የግንባታ ፈቃድ እና ለ53 (40%) የመጠቀሚያ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ ለ1807 ባለሙያዎች አዲስ፣ ለ1070 የስራ ተቋራጮች የእድሳት የምዝገባ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ800 (74%) ባለሙያ አዲስ ፍቃድ እና ለ1020 ባለሙያዎች የእድሳት የምዝገባ አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የተቋሙ የልማት ግቦች አፈፃፀም ሲታይ በአጥጋቢ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም ወቅቱ ከሚጠይቀው ፍላጎት ጋር ሲነፃፀም በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል፡፡

**የከተሞች ፕላን ጥናትና ምርምር አፈፃፀም በተመለከተ፤** በእቅድ ዘመኑ የከተማ ፕላን ሽፋን 100% ለማድረስ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ማከናወን ተችሏል፡፡ የተለያየ ደረጃ ያላቸውን 150 ፕላኖችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 155 (100%) ተዘጋጅቷል፡፡ የህዝብ ብዛታቸው ከ20 ሽህ እስከ 100 ሽህ ለሆኑ 6 ከተሞች ስትራቴጂክ ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ6 ከተሞች (100%) ተዘጋጅቷል፡፡ የሕዝብ ብዛታቸው ከ20 ሽህ በታች ለሆኑ 75 ከተሞች መሰረታዊ ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ85 ከተሞች (100%) ተዘጋጅቷል፡፡ ለ6 ከተሞች የማስፋፊያ ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ6 ከተሞች (100%) ተዘጋጅቷል፡፡ ለ200 የገጠር አገልግሎት ማዕከላት ስኬች ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ 210 (100%) ተዘጋጅቷል፡፡ የመሬት አጠቃቀም ምቹ ለማድረግ 65 የሠፈር ልማት ፕላን ለማዘጋጀት ታቅዶ 33 (51%) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ለ64

ከተሞች የቦታ ደረጃ ፕላን ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ የ76 (100%) ተዘጋጅቶላቸው ወደ ትግበራ ገብተዋል፡፡

የከተማ ፕላን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥራዎችን በተመለከተ ለ40 ከተሞች የፕላን አፈፃፀም ግምገማ ለማድረግ ታቅዶ ለ32 ከተሞች (81%) ተከናውኗል፡፡ ለ130 የገጠር አገልግሎት ማዕከላት የስኬች ፕላን አፈፃፀም ግምገማ ለማከናወን ታቅዶ 110 (83%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በ65 ከተሞች የፕላን ጥሰቶችን በመለየት የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ በ48 ከተሞች (79%) ማከናወን ተችሏል፡፡ በ86 ከተሞች መሠረታዊ ፕላን የቅየሳ ነጥቦችን ለማናበብ ታቅዶ 101 ከተሞች መሠረታዊ ፕላን ቅየሳ ነጥቦችን (100%) ማናበብ ተችሏል፡፡ ስትራቴጅክ ፕላን ለተዘጋጀላቸው 8 ከተሞች የቅየሳ ነጥቦችን ለማናበብ ታቅዶ 5 ከተሞች (62%) ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

ከከተሞች አደረጃጀት አኳያ ክልላዊ የከተሜነት ደረጃ ቀደም ሲል ከነበረበት 17.5 ከመቶ ወደ 25 በመቶ ለማድረስ ታቀዶ የከተሜነት ደረጃውን 25.6 በመቶ (100%) ማድረስ ተችሏል፡፡ የገጠር አገልግሎት ማዕከላትን ከክልላዊ መስፈርት አንፃር በመፈተሽ 45 የከተማነት ዕውቅና ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 35 (77%) እውቅና ተሰጧል፡፡ እንዲሁም ለ60 ከተሞች የፈርጅ ለውጥ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ ለ45 (100%) የፈርጅ ለውጥ ተደርጓል፡፡ለ99 ከተሞች ወሠን ለማካለል ታቅዶ ለ99 (100%) ከተሞች ወሠን የማካለል ሥራ ተሰርቷል፡፡ በ2 ዙር በኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ላይ 6 የክልሉ ከተሞች ተሳታፊ በመሆን ከሌሎች አቻ ከተሞች ተሞክሮ እንዲቀስሙ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የተቋሙ አፈፃፀም ሲገመገም ከእቅዱ አንፃር የተሻለ ሊባል የሚችል ቢሆንም ከከተሞቻችን ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ሲታይ የፕላን ዝግጅት ጥራቱን ያልጠበቀ፣ በተያዘለት መርሃ ግብር መሰረት የማይጠናቀቅ እንዲሁም በየደረጃው በባለድርሻ አካላት እና በነዋሪው እየተገመገመ የማይሄድ በመሆኑ በትግበራ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳደረ በመሆኑ በቀጣይ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል፡፡ የከተሞች ፈርጅ ለውጥ መስፈርት ውስጥ በጥረት ተደራሽ በሆኑ ዝርዝር መስፈርት የተደገፈ ባለመሆኑ ለፈርጅ የሚመጥኑ ከተሞች ማደራጀት ያልተቻለ እንዲሁም ዝቅተኛ አፈፃፀም ያላቸውን ከተሞች አብቅቶ ያለመሄድ በቀጣይ በልዩ ሁኔታ መሰራት ያለበት ነው፡፡

**የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ስራዎች አፈጻጸምን በተመለከተ** ከመሬት ልማትና ማኔጅመንት አንፃር በከተሞች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 7115 ሄ/ር የለማ መሬት አዘጋጅቶ ለማቅረብ ታቅዶ 5116.248 ሄ/ር (72%) ተዘጋጅቷል፣ መሬት ከማስተላለፍ አንጻር ለተለያዩ

አገልግሎቶች የሚውል የለማ መሬት 4681 ሄ/ር ለማስተላለፍ ታቅዶ 3550.442 ሄ/ር (76%) ለማስተላለፍ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያና ውጤታቸውን በዌብ ሳይት ፖርታል ላይ እንዲጫን በማድረግ ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን በ 10 ከተሞች ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ በ12 ከተሞች(100%) ተከናውኗል፡፡ ወደ ሊዝ ያልገቡ ከተሞችንና አዲስ የከተማ እዉቅና የሚሰጣቸዉ ከተሞች ወደ ሊዝ ሥርዓት እንዲገቡ በ22 ከተሞች ታቅዶ ሁሉም ከተሞች ወደ ሊዝ ሥርዓት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ የመሬት ሀብት ቆጠራ ሥራን በ51 ከተሞች ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ በ64 ከተሞች (100%) ተከናውኗል፡፡ በመሆኑም በመሬት ዝግጅት አኳያ ከእቅድ ጋር ሲነፃፀር የተሻለ አፈፃፀም የሚታይ ቢሆንም ከማስተላለፍ ጋር ተያይዞ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ስለሆነ በዘርፉ የሚታየው የአገልግሎት አሠጣጥ ከቅሬታ ያልተላቀቀ በመሆኑ በቀጣይ በልዩ ትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡

**የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ሥራዎች አፈጻጸምን በተመለከተ፤** ከመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ አንፃር በ5 ከተሞች ከሀገራዊ የጂኦዴቲክ መረብ በመነሳት 750 የመሬት መቆጣጠሪያ ነጥቦችን መረብ ለመዘርጋት ታቅዶ በ12 ከተሞች 900 (100%) የቅየሳ መነሻ መረጃ የሚያመነጩ ነጥቦችን በማቋቋም ከሀገራዊ ግሪድ ጋር በማስተሳሰር ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጂል፡፡ ለ6 መካከለኛ እና አነስተኛ ደረጃ ከተሞች ካዳስተራል መሠረታዊ ካርታ እና ኦርቶፎቶ፣ የሳታላይት ስቴሪዮ ምስል እና የምድር ቅየሳ ዘዴ በመጠቀም ለማዘጋጀት ታቅዶ 6 ከተሞች (100%) ለማከናወን ተችሏል፡፡ ለ3 መካከለኛ እና አነስተኛ ደረጃ ከተሞች የአድራሻ ካርታ ዲዛይን በማዘጋጀት ዘመናዊ የአድራሻ ሥርዓት ለመዘርጋት ታቅዶ በ3 ከተሞች (100%)፣ ለአድራሻ ሥርዓት ዝርጋታ መነሻ መረጃዎችን በማሰባሰብ የአድራሻ ሥርዓት መነሻ ካርታ የማዘጋጀት ሥራ ተሰርቷል፡፡ በ10 ከተማ አስተዳደር ከተሞች የመሬት ይዞታ ለማረጋገጥ /Adjudication/ ሥራ ለመስራት ታቅዶ በ 7 ከተሞች (75%) የከተማ መሬት ይዞታ የማረጋገጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡ በከተማ አስተዳደር ከተሞች የ11,000 የከተማ መሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ለማካሄድ ታቅዶ 6601 ይዞታዎች (58%) መብት ምዝገባ ተካሂዷል፡፡ በ10 ከተማ አስተዳደር ከተሞች የቀጠና፣ የሠፈር እና የጣቢያ ሽንሻኖ በማከናወን ካዳስተር ካርታ ለማጋጀት ታቅዶ በ10 ከተሞች (100%) የቀጠና፣ የሠፈር እና የጣቢያ ሽንሻኖ በማከናወን ካዳስተር ካርታ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ በ10 ከተሞች የእያንዳንዱ የይዞታ ማህደር ከህጋዊ ካዳስተር መረጃ እና ከካዳስተር መሠረታዊ ካርታ ጋር ለማስተሳሰር ታቅዶ በ10 ከተሞች (100%) የይዞታ ማህደር ከህጋዊ ካዳስተር መረጃ እና ከካዳስተር መሠረታዊ ካርታ ጋር ለማስተሳሰር ተችሏል፡፡

አፈጻጸሙ ሲገመገም የጂአይኤስ መረብ ዝርጋታ፣ የካርታ ዝግጅት፣ ለመሬት መረጃ ማህደራት ልዩ መለያ ኮድ በመስጠት ከኦርቶ ፎቶና ከካዳስተራል መሠረታዊ ካርታ የተሻለ አፈጻጸም የታየበት ሆኖ በማረጋገጥ፣ በምዝገባና በአገልግሎት አሰጣጥ የተመዘገበው ውጤት ዝቅተኛ መሆኑ እቅዱ ሲዘጋጅ ነባራዊ ሁኔታን ያላገናዘበ በመሆኑ በቀጣይ እቅዱ ሲዘጋጁ የከተሞችን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ መሆን ይገባዋል፡፡

**የቤቶች ልማትና አስተዳደር ሥራዎች አፈጻጸምን በተመለከተ፤** በቤቶች ልማትና አስተዳደር በተለያዩ አማረጮች 18,665 ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 15,448 (82%) ተከናውኗል፡፡ ይህም በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ፕሮግራም በከተሞች 5000 እና በገጠር ማዕከላት ከአከባቢው ባህል ጋር የተቀናጀ 3448 በድምሩ 8500 ቤቶች ተገንብተዋል፡፡ በከተሞች ለልማት ተነሺዎች 1473 ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 1533 (100%) ማከናወን ተችሏል፡፡ ለመምህራን እና ለነዋሪዎች 550 ወጪ ቆጣቢ ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ 211 (41%) ማከናወን ተችሏል፡፡ ለድሀ ድሀ የህብረተሰብ ክፍሎች 200 ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 103 ቤቶች (52 ) ተገንበተው ተላልፏል፡፡ በተቋማት ፍላጎትና ፋይናንስ 202 ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ 137 ቤቶች ተገንብተው ለተቋማቱ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በሁሉም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ለ15,000 ዜጎች አዲስ የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 12,668 (84%) የተከናወነ ሲሆን ብር 5,000,000.00 የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 3,950,458.00 (67%) ተከናውኗል፡፡

በከተሞችና በገጠር ማእከላት ለሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች እንደ የአከባቢው ነባራዊ ሁኔታ 5 አዳዲስ ስታንዳርድ ዲዛይኖች ለማዘጋጀት ታቅዶ 5(100%) ተዘጋጅቷል፡፡ በከተሞች 25 ሄ/ር ውርስ ቤቶች ያረፉባቸውን ይዞታዎች ነፃ ለማድረግ ታቅዶ 16.33 ሄ/ር (63%) ቦታ ለኢንቨስትመንትና ለልዩ ልዩ የልማት አገልግሎት ነፃ ተደርጓል፡፡

ከቤት አስተዳደር አንጻር በከተሞች 2194 የመንግስት ቤቶች መረጃ ለመሰብሰብና ለማደራጀት ታቅዶ የ2194 (100%) ቤቶች መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በመሆኑም ጊዜያዊ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተዘጋጀ በመሆኑና በኮምፒውተር መዝግቦ በዘመናዊ መልክ ማደራጀት ተችሏል፡፡ በዚህም ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ የመንግስት ቤቶችና ይዞታዎች በሕገ ወጥነት፣ ባለቤት እንደሌላቸው ተቆጥሮ ከሚፈጸም የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር መታደግ ተችሏል፡፡ ይህ ውጤት ሊገኝ የቻለው ክልሉ ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ከሰርቬይንግ እና ድሮዊንግ ትምህርት ክፍል ተመራቂ ተማሪዎችን በመጠቀም፣ በየከተሞች ነዋሪዎችንና

ባለሞያዎችን በማሳተፍ በተቀናጀና በተደራጀ ሁኔታ በመከናወኑ የተሻለ ውጤት የተመዘገበ ሲሆን በቀጣይም የመንግሥት ቤቶች ይዞታ ማረጋገጫ ዝግጅትና የቤቶች ጥገና ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

**የከተሞች ማስፈጸም አቅም ግንባታና አካባቢ ልማት ስራዎች አፈጻጸምን በተመለከተ፤** ከማስፈጸም አቅም ግንባታ ዘርፍ አንፃር በከተሞች የተቀናጀ የመሰረተ ልማት አቅርቦትና አስተዳደር አንፃር 16.5 ኪ.ሜ የኮብል እስቶን መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 11.85 ኪ.ሜ (83%)፣ የ5000 ኪ.ሜ የአዲስ መንገድ ጠረጋና ከፊታ ለማከናወን ታቅዶ 3906.11 ኪ/ሜ (76%)፣ የ2000ኪ.ሜ የአዲስ ጠጠር መንገድ ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ 1504 ኪ/ሜ (76%)፣ የ2001 ኪ.ሜ የነባር ጠጠር መንገድ ጥገናና ደረጃ ለማሻሻል ታቅዶ 1505.27 ኪ/ሜ (72%) ለማከናወን ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የመንገድ መሰረተ ልማት ሽፋን ከነበረበት 35% ወደ 80% ለመድረስ ታቅዶ 43.35% ማድረስ ተችሏል፡፡ ከከተማ ንጹህ ውሃ አቅርቦት አንጻር የውሀ መስመር ዝርጋታ ሽፋኑን ከነበረበት 46% ወደ 100% ለማድረስ ታቅዶ 44% ማድረስ ተችሏል፡፡ የ3167 ኪ.ሜ የውሃ መስመር ለመዘርጋት ታቅዶ 2662 ኪ/ሜ (66%) መዘርጋት ተችሏል፡፡
የመንገድ መብራት ዝርጋታ ሽፋን ከነበረበት 13% ወደ 60 ከመቶ ለማሳደግ ታቅዶ ወደ 37.67 ከመቶ ላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ 1633 ኪ.ሜ የመንገድ መብራት ለመዘርጋት ታቅዶ 1002.13 ኪ/ሜ (62%) ተከናውኗል፡፡ ይሁን እንጂ ከመብራት መሠረተ-ልማት አቅርቦት አንጻር በሁሉም ከተሞችእሮሮና ቅሬታ ያለበት ነው፡፡ ከከተማ መሰረተልማት አቅርቦትና አስተዳደር አንጻር ዘርፉ ለኪራይ ተጋላጭ እንደመሆኑ መጠን በስራተቋራጮች፣ በማህበራትና በባለሙዎች ጭምር በአስተሳሰብም በተግባርም የሚገለጽ ብልሹ አሰራርና ሌብነቶች የሚታይባቸው በመሆኑ ከጥራትና ፍትሀዊ ስርጭት አንጻር ጉድለት የነበረበት መሆኑ ተገምግሟል፡፡
አጠቃላይ የከተማ መሰረተ ልማት በቅንጅት ካልተመራ ችግሩን መፍታት ስለማይቻል ነባራዊ ሁኔታ በደንብ ተገምግሞ ዘለቂ ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በየአካባቢ ከሚነሳው የፍላጎትና ጥያቄ አኳያ በተጨባጭ መሬት ላይ ያለው ተጠንቶ ታዓማኒነቱን የማረጋገጥና ለቀጣይ አስተማማኝ መነሻ እንዲሆን የኢንቨነተሪ ስራ በልዩ ትኩረት መሰራት ይኖርበታል፡፡

የከተሞች አካባቢ ልማትና የህብረተሰብ ተሳትፎ ማጠናከር ስራዎች አንጸር ፈጣን ልማትን ለማምጣት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ሥርዓትን ለመገንባትና ለማጠናከር የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ዜጎች በልማት፣ በዲሞክራሲና በመልካም

አስተዳደር የሚኖራቸውን ምትክ የማይገኝለት ተሳትፎ ለማሳደግና ለማጠናከር መንግስት የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዷል። ባለፉት ዓመታት ህብተሰብ በአካባቢው ልማት ላይ የሚሳተፍበትና በለቤት የሚሆንበት የልማት ተሳትፎ አደረጃጀ የመፍጠርና የማጎልበት ተግባር በትኩረት የተሰራ ነው። ከህብረተሰብ ተሳትፎ አንፃር የተፈጠሩ አደረጃቶችን 11,520 የ1ለ5፣1,650 የብሎክ እና 444 የሰፈር አደረጃጀቶች ተፈጥረዋል። እነዚህ አደረጃጀቶች የከተማ ልማትና የመልካም አስተዳደር አጀንዳዎችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኙ ሲሆን 17 አጀንዳዎች ተቀርጸ ተግባራዊ ያደረጉ መንደሮች የሚመረቁበት ሥርዓት ተፈጥሯል። በዚህም መሰረት እስከአሁን ባለው አፈጻጸም 85 በመቶ ለማስመረቅ ታቅዶከ 700 ሰፈሮች መካከል321 ተመርቀዋል። ህብረተሰቡ በመሰረተልማት ግንባታዎች በገንዘብ 42,661,065 ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ 45,114,669 (100%) ብር ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን 2,334,586 የሰው ኃይል በልማቱ ላይ በጉልበቱ እንዲሳተፍ ለማድረግ ታቅዶ 3,550,265 (100%) የሰው ኃይል ማሳተፍ ተችሏል።

ይሁን እንጂ በሁሉም ከተሞች ህብረተሰቡ በገንዘብ፣ በጉልበትና በቁሳቁስ ያደረገው ተሳትፎ ከመረጃው ጥራትና ተዓማኒነት አንጻር ሲገመገም ከፍተኛ ጉድለት ያለበት በመሆኑ በቀጣይ የጠራ መረጃ ሊያገዝ ይገባል። ህብረተሰቡ በአካባቢው ልማት ላይ የሚያደርገው ተሳትፎ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር አጀንዳዎቹን አሟልተዋል ተብለው የተመረቁ መንደሮች ዘላቂነት ባለው መልኩ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ ያለመሆናቸው በግልጽ የሚታይ በመሆኑ አደረጃጀቱ በቀጣይ ሊፈተሽ ይገባል።

ከከተሞች ጽዳት አስተዳደርና አረንጓዴ ልማት አንጻር ከተሞች የአየር ንብረት ለውጥ የሚቋቋሙና ምቹ እንዲሆኑ ለማስቻል በከተማ ውስጥና ዙሪያ በተራቆቱና በተፋሰስ ቦታዎች እንዲሁም የመንገድ ዳር የአረንጓዴ አሻራ ቀን አፈፃፀም ቁጥር ጨምሮ የዛፍ ተከላ 12,000,000 ተከላና እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ 21,109,442 (100%) ማከናወን ተችሏል። የተከላ እቅዶች በአጥጋቢ ደረጃ የተፈጸሙ መሆናቸው በጥንካሬ የሚገመገም ሲሆን የተተከሉ የዛፍ ችግኞች እንዲጸድቁ ባለቤት ከመፍጠርና እንክብካቤ ከማድረግ አኳያ ብዙ ጉድለት ያለበት ነው። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚወሰደው ከተከላ በፊት የእንክብካቤ ሂደት ላይ መግባባት ሳይፈጠርና ባለቤት ሳይበጅለት የሚከናወን መሆኑ ነው። በ2011 ሀምሌ 22 ሀገራዊ የአረንጓዴ አሻራ ቀን እንደሀገር በሁሉም ከተሞች ተከላ ስራው የተመራበት ግለትና ትኩረት ከተከላ በኋላ መቀጠል ይኖርበታል። የከተማ ችግኝ ልማት ጣቢዎች በስታንዳርድ በቁጥር 9 እንዲለሙ ታቅዶ 27

(100%) የከተማ ችግኝ የሚፈላባቸው ጣቢዎች ተዘጋጅቷል። የተጎዱ የከተማ ውስጥ 125 ሄ/ር ተፋሰስ በማልማት የአካባቢ ስነምህዳርና መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ ታቀዶ 401.223ሄ/ር (100%)፣ አረንጓዴ ቦታዎችን፣ የትራፊክ ደሴቶች፣የህዝብ አደባባይ ቦታዎች፣ መንገድ አካፋዮች እና ውሃማ አካላት ዳርቻዎች / Buffer zone/ በድምሩ 173 ሄ/ር ዲዛይን ተዘጋጅቶለት እንዲለማ ለማድረግ ታቅዶ 225.67 ሄ/ር ማልማት ተችሏል። በአጠቃላይ የከተሞች የአረንጓዴ እጽዋት ሽፋን ከነበረበት 0.5% ወደ 20% ለማሳደግ ታቅዶ 15.5% ላይ ማድረስ ተችሏል። በዚህም ከተሞቻችን የሙቀት አማቂ ጋዞች ተጽዕኖ የመቋቋም አቅማቸው እንዲጨምር አዎንታዊ ሚና አበርክቷል። ከቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አንጻር በከተሞች የሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሽፋን ከነበረበት 30% ወደ 80% ለማሳደግ ታቅዶ 41% ላይ ማድረስ ተችሏል። ከሚመነጨው ኦርጋኒክ ቆሻሻ ከነበረበት ወደ40% ለመቀየርና ጥቅም ላይ ለማዋል ታቅዶ 21.5% የሚሆነውን መልሶ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ተችሏል። 175 የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ ቤቶች ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ 198 (100%) ማከናወን ችሏል። በከተማ ጽዳት፣ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም ላይ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ እንዲራጁ በማድረግ ለ 350 ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ 378፣ በአረንጓዴ ልማት ለ350 ዜጎች ታቅዶ 378 ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል። በዚህም የከተማ አረንጓዴ ልማት እና የቆሻሻ አሰባሰብና አወገገድ ሽፋን ማሳደግ የተቻለ ሲሆን 50 ከመቶው ተጠቃሚዎች ሴቶች ናቸው።

ከማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት የሰው ኃይል ልማትና ስታንዳርዳይዜሽን አንጻር ኮዲፋይድ በሆኑ 6 የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት የሙያ መስኮች ከዞኖች ጋር በመተባበር 30 መሪ መዛኞች ለማዘጋጀት ታቅዶ 22(73%) መሪ መዛኞችን ማዘጋት ተችሏል። 12 የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት የሙያ መስኮች የምዘና ጣቢያዎች ለማዘጋጀት በቁጥር 15 ታቅዶ 16 (100%) ማከናወን ተችሏል።በ6 ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች የሙያ መስኮች በዘርፉ ውስጥ የተሰማሩ 300 ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲኖራቸው ለማድረግ ታቅዶ 337(100%) ማከናወን ችሏል። 32 ቁራዎች ደረጃ ወጥቶላቸው የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍና እንዲሻሻል ለማድረግ ታቅዶ 36(100%+) ቁራዎች ደረጃ ወጥቶላቸዋል። 3 የቁራ አገልግሎት መስጫ ተሸከርካሪ ለማሟላት ታቅዶ 4(100%) የስጋ ማንጓጠ ተሸከርካር ማቅረብ ተችሏል። በ2 ከተሞች ከቁራ ተረፈ ምርት በማደራጀት ለገበያ እንዲቀርብ በማድረግ የገቢ አቅም እንዲጎለብት ለማደረግ ታቅዶ በ1 (50%) ከተሞች ማከናወን ተችሏል፡ በ5 ከተሞች የበግና ፍየል እርድ አገልግሎት እንዲሰጥ ታቅዶ በ3 (67%) ከተሞች አገልግሎቱን እንዲቀርብ ተደርጓል። በ28

በከተሞች ህገወጥ ሥጋ አቅርቦትና ንግድ የሚቆጣጠርና የሚከታተል ግብረ-ኃይል ለማቋቋም ታቅዶ በ48 (100%) ከተሞች ማቋቋም የተቻለ ሲሆን በዚህም ህገወጥ የስጋ እርድና ንግድ መከላከል ህጋዊ አሰራር የማስፈን ጥረቶች ተደርጓል፡፡ የቁራ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዝቅተኛ መስፈርት ላሟሉ 13 ከተሞች እውቅና ለመስጠት ታቅዶ ለ16(100%) ከተሞች መስጠት ተችሏል፡፡ በ3 ከተሞች እሳት አደጋ ብርጌድ ለማደራጀት ታቅዶ ማሟላት አልተቻለም፡፡ በ8 ከተማ የፋየር ሀይድራንት በማዕከላዊ ቦታዎች ለመግጠም ታቅዶ አልተከናወነም፡፡ ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ አሁንም ድረስ ከቅሬታ ያልተላቀቀና የተገልጋዮችን እርካታን ያላረጋገጠ መሆኑ ተገምግሟል፡፡ በቀጣይ በስታንዳርድና በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት አሰጣጥ ሊኖር ይገባል፡፡

## 2.5. ንግድ እና ኢንቨስትመንት አፈጻጸም

ህጋዊ የንግድ ስርዓት የማስፈን ሥራዎች፡- ህጋዊ የንግድ አሠራር ሥርዓት በመዘርጋትና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት የንግድ ሥርዓት ከማዘመን አንጻር በክልሉ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ለማዘመን በተደረገው ጥረት 7 የኦን ላይን አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ለማቋቋም ተችሏል፡፡ በመሆኑም በተዘረጋው አሰራር መሰረት ለ280,000 ነጋዴዎች አዲስ የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ221,031፣ ለ12393 ነጋዴዎች አዲስ የንግድ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ8,264፣ ለ123,890 ነጋዴዎች የንግድ ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት ለ123,890 ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ለ94 በግብርና ምርቶች አቅራቢነት ለተሰማሩ የንግድ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለመስጠት ታቀዶ ለ94 መስጠት የተቻለ ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎን ለ132,431 ነጋዴዎች የንግድ ምክርና መረጃ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም የንግድ ደረጃ ለዉጥ ከማድረግ አንጻር ከሐ ወደ ለ 2577፣ ከለ ወደ ሀ 202 ነጋዴዎች የንግድ ደረጃ ለዉጥ አድርገዋል፡፡

መሠረታዊ የፍጆታ ምርቶችን አቅርቦትና ስርጭት ከማጠናከር አኳያ መሠረታዊ የፍጆታ ምርቶች ላይ የሚታየውን የዋጋ ንረት ለመቀነስ በተዘረጋው ፕሮግራም መሠረት መንግስት በከፍተኛ ድጎማ ከሚያቀርባቸው ምርቶች 497,040 ኩ/ል ስኳር፣ 521,597 ኩ/ል የስንዴ ዱቄት እና 77,579,305 ሊትር የዘይት ምርት በየአካባቢው እንዲያሰራጩ በተመረጡ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራትና ቸርቻሪ ነጋዴዎች በኩል እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡ ነግር ግን ለህ/ሰቡ መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶች ለማቅረብ የተሞከረበት አግባብ መሰረታዊ የነፃ ገበያ መርህን

ያልተከተለ፣ የምርት አቅርቦት እጥረትና የተደራሽነት ችግር፣ ስርጭቱ በብልሹ አሰራር የታጀበ ሆኖ የታሰበውን ዓላማ ማሳካት ያልቻለ ነው።

ምቹ የንግድ ስርዓት በመፍጠር ጤናማ የገበያ ውድድርን ከማሳደግ አንጻር በዕቅድ ዘመኑ በ127,394 የንግድ ድርጅቶች ላይ የኢንስፔክሽን ስራ በማከናወን ህጋዊ የንግድ አሰራር ስርዓት የማጠናከር ተግባር ተፈጽሟል። በተጨማሪም 19 የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤትና 20 የነጋዴ ሴቶች ማህበራት ማቋቋም የተቻለ ሲሆን ነባሮቹን በአባላት የማጠናከር ተግባርም በተያዘው ዕቅድ መሰረት ተፈጽሟል።

**ዘመናዊ የምርት ግብይት ስርዓት የመዘርጋት ሥራዎች**

ዘመናዊ የንግድና ግብይት መሰረተ-ልማት በማስፋፋት የገበያ ትስስር ከማሳደግ አንጻር በዕቅድ ዘመኑ 127 ነባር እና አዳዲስ የሰብልና እንስሳት የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላትን እና 2 የሁለተኛ ደረጃ የግብርና ምርት ግብይት ማዕከላት ማቋቋም ተችሏል። በመሆኑም የግብይት ማዕከላት በመቋቋማቸው የሰብልና የእንስሳት ምርቶች ጥራታቸውና ደህንነታቸው ተጠብቆ ለሀገር ውስጥ እና ለኤክስፖርት ገበያ አቅርቦት በአይነትም ሆነ በመጠን ጭማሪ አሳይቷል። በዚህም አምራቹና አርሶ አደሩ በተሻለ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

ይሁን እንጂ የመጀመሪያ ደረጃ የግብርና ምርቶች የግብይት ማዕከላት ጥራት፣ ተደራሽነትና ቀጣይነት ላይ ሰፊ ክፍተት ይታያል። በተመሳሳይ መልኩ የሁለተኛ ደረጃ የግብይት ማዕከላት አምራች አካባቢዎች ተደራሽ በማድረግና በማቋቋም ብሎም የተቋቋሙትም ማዕከላት በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት እንዲሰጡ ከመምራትና ከማስተዳደር ረገድ ከጅምር ስራዎች የዘለሉ ተግባራት አልተፈፀሙም። በከተሞች የሚቋቋሙ ዘመናዊ የግብይት ማዕለካትም ሆነ በየአካባቢው የሚገኙ የዘልማድ ገበያ ማዕከላት ደረጃቸውን ያልጠበቁና መሠረተ ልማት የሌላቸው ብሎም በህግ ማዕቀፍ የሚመሩበት ስርዓት አለመኖር በዋናነት የሚጠቀስ ችግር ነው። ለነዚህ ችግሮች መነሻ የሚሆኑ ምክንያቶች ከቦታ መረጣ ጀምሮ እስከ ማዕከል ግንባታና አስተዳደር ድረስ የአምራች፣ የባለሀብቱና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ቅንጅት አናሳ መሆን ናቸዉ። ስለዚህ የግብይት ስርዓቱን ከማዘመን ረገድ ቀጣይ ከፍተኛ ጥረት ሊደረግ ይገባል።

የገጠርና የከተማ ንግድ ትስስር ከማጠናከር አንጻር በዕቅድ ዘመኑ የግብርና ምርት ግብይት ትስስር ለመፍጠር 1 ኤግዚቢሽንና ባዛር የተካሄደ ሲሆን ለ2,742 አርሶ አደሮች ምርቶቻቸውን በማስተዋወቅ እና የገበያ ትስስር ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል።

ከደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልል ከተመረጡ የግብርና ምርቶች ለገበያ የቀረቡ ምርቶችን በተመለከተ ብና የታጠበ 22,571.3 ቶን፣ ያልታጠበ 66,834.1 ቶን፣ ጀንፊል 205,181.6 ቶን ፣ቅሽር 17205.6 ቶን፣ በአጠቃላይ 331,792.67 ቶን ቡና ለግብይት ቀርቧል። የሻይና ሌሎች ቅመማ ቅመም ምርት ግብይትን በተመለከተ 29,898.9 ቶን ሻይ፣ 1,045,154.7 ቶን ቅመማ ቅመም ሲቀርብ ሌሎች የግብርና ምርቶችን በተመለከተ13,970,277 ቶን የአገዳና ብርዕ፣ 1,497,665 ቶን ጥራጥሬ፣ 38,356 ቶን የቅባት እህል፣ 2,070,334 ቶን አትክልትና ፍራፍሬ፣ 47,711 ቶን ማርና ሰም፣ በቁጥር 3,241,008 የቁም እንስሳት፣ በቁጥር 5,434,289 እንቁላል ማቅረብ ተችሏል። የግብርና ምርቶችን ለኤክስፖርት ገበያ ከማስቀረብ አንጻር በሁለተኛ ዕ.ት.ዕ. ዘመን 16,849 ቶን የሰሊጥ፣ 1,310,600 ቶን የጥራጥሬ፣ 234,739 የቁም እንስሳት፣ 1,176,623 ቶን የቆዳና ሌጦ እና 29,276 ቶን የማርና ሰም ምርት ለማዕከላዊ ገበያ እንዲቀርብ ተደርጓል። የግብርና ምርቶችን በተለይ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እንደ ቡና፣ ሰሊጥ ቅመማቅመም ከማምረት ሂደት ጀምሮ እስከ ምርት ዝግጅት ድረስ ባሉት ሂደቶች ከፍተኛ የጥራት ችግር የሚስተዋልባቸው ናቸው። ስለሆነም ክልሉ ካለው አቅም አንፃር በብዛት ጥራት ያላቸው የግብርና ገበያ ምርቶችን አቀርቦት አስፋፍቶ ለመቀጠል የሚያስችሉ ተግባራት ተጠናክረው ይቀጥላሉ።

## 2.6. የባህልና ቱሪዝምና ስፖርት አፈጻጸም

### ባህል ዘርፍ አፈፃፀም-

በክልሉ የሚገኙ ህዝቦች ቋንቋዎቻቸዉ ተጠንቶ፣ ለምቶና ከመጥፋት አደጋ ተጠብቆ የሥራ፣ የትምህርትና የብዙሃን መገናኛ ሆኖ መቀጠልና ማበብ እንዲችል ልዩ ልዩ ሥራዎች ተሰርተዋል። በዕቅድ አመታቱ ዘመን አነስተኛ ቁጥር ተናጋሪ ያላቸውና በመጥፋት አደጋ ላይ ላሉ ቋንቋዎች 4 መዝገበ ቃላት በማዘጋጀትና በማሳተም ተደራሽ ማድረግ ተችሏል። የብሔር ብሄረሰቦችን ተረቶችን፣ ቃላዊ ተረኮችን፣ ስነቃልና ወጎችን የያዘ 10 ማከናወን ተችሏል። 7 የቋንቋ ሰዋሰዉ ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ እንዲዉል ለማድረግ ተችሏል።

የባህልና ታሪክ ልማትና አጠቃቀም በማሳደግ የክልሉ ህዝቦች የማንነት መገለጫ የሆኑ የጋራ እሴቶችን በማጉላት ተቻችሎና ተከባብሮ አብሮ የመኖር ባህልን ለማዳበርና ሀገር በቀል ዕውቀቶችን በማሳደግ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማስቻል 98 የሀገር በቀል ዕዉቀቶች አጠቃቀም ለማሳደግ ታቅዶ 86፣ 672 የባህል ተምሳሌቶች የመለየት የመመዝገብና የመሰነድ ሥራ ለመስራት ታቅዶ 679 ማከናወን ተችሏል። እንዲሁም ለቱሪስት መስህብነት

እየዋሉ ያሉና የለሙ ክብረ በዓላት በቁጥር 4 ታቅዶ 3 ክብረ በዓላት እሴታቸዉን የማጎልበት ስራ ተሰርቷል፡፡

የባህላዊ ቅርሶች ጥበቃና ልማትን በተመለከተ 4 ቅርሶችን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ የማስመዝገቢያ/ መምረጫ ሰነዶች (Nomination Dossier) ለማዘጋጀት ታቅዶ 1 የተከናወነ ሲሆን ከእቅድ ዘመኑ በፊት 2 ጥብቅ የደን ቦታ በዩኔስኮ የሰው ልጅ ወካይ ቅርስ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙ ባህላዊ ቅርሶችን መካከል 897 ተንቀሳቃሽና ቋሚ ቅርሶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 810፣ 1460 ለመጠበቅ ታቅዶ 2,658፣ 53 ለማልማት ታቅዶ 16 ተከናውኗል፡፡ የባህል ዘርፉን በሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ስራዎች ከማሳደግ አኳያ የክልሉን ህዝቦች ባህልና ታሪክ፣ የባህል እሴቶችን፣ ባህላዊ ቅርሶችንና ሌሎችንም ተያያዥ ስራዎችን ለማሳተምና ጥቅም ላይ ለማዋል በዕቅድ ዘመኑ 4 የጥናትና ምርምር ስራዎች ለማከናወን ታቅዶ 3 የተከናወነ ሲሆን 6 የጥናት ዉጤቶች ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ሆኗል፡፡

**የቱሪዝም ልማት አፈጻጸም-**

ክልሉ እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶችና የቱባ ባህል መገኛ በመሆኑ የበርካታ ሀገር ጎብኚዎችን ቀልብ እየሳበ ያለ ሲሆን ክልሉን የሚጎበኙ የሀገር ውስጥ እና የውጪ ሀገር ጎብኚዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እና በገቢም ረገድ ተመሳሳይ እድገት እየተመዘገበ ቢሆንም ክልሉ ካለው እምቅ የታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ መስህብ ሀብቶች/ቅርሶች አንጻር ሲታይ የጎብኚ ቁጥርም ሆነ ገቢው እጅግ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡

የተፈጥሮ መስህቦች ጥበቃና ልማት አጠቃቀምን በተመለከተ 100 አዳዲስ የተፈጥሮ መስህቦችን ለመመዝገብ ታቅዶ 93 ማከናወን ተችሏል፡፡ በክልሉ 4 የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ለማካለል ታቅዶ 2 ማከናወን ተችሏል፡፡ በብሄራዊ ፓርኮችና አነስተኛ የተፈጥሮ ደን ጥበቃ ቦታዎች 100 ኪ.ሜ ነባርና አዳዲስ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ጥገናና ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ 69 ኪ.ሜ የተከናወነ ሲሆን በጨበራ ጨርጨራ ብ/ፓርክ የጨበራን ሳይት ከኮንታና ከዳውሮ ዞን ጋር የሚያገናኝ ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ያለው የ42 ኪ.ሜትር የመንገድ ዲዛይንና ቅየሳ ስራ የተከናወነ ሲሆን የመንገድ ጠረጋ ስራው በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

የክልሉን ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶች በማስተዋወቅና የፕሮሞሽን ስራዎች በመስራት 15,230 የውጭ ሀገር እና 420,000 የሀገር ውስጥ በድምሩ 435,230 ቱሪስቶች

ክልሉን ይጎበኛሉ ተብሎ ታቅዶ 2,075 የውጭ አገር እና 371,990 የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች በድምሩ 374,065 ቱሪስቶች ክልሉን ጎበኝተዋል፡፡ ከቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘርፍ ብር 185,000,000 ለማግኘት ታቅዶ 9,182,400 ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በባህልና ቱሪዝም መስክ ለ 1,324 ዜጎች ጊዜያዊና ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

የቱሪዝም ልማት ለአካባቢም ሆነ ለሀገር የሚያበረክተዉን አስተዋፅኦ በመረዳት ሀብቶችን በዘመናዊ የመረጃ መረብ አደራጅቶ በተለያዩ የማስተዋወቂያ ዜዴዎች (በዘፈን፣ በፊልም፣ በፎቶ፣ የጉብኝት ፕሮግም በማዘጋጀት) ከማስተዋወቅ አንፃር ያልተካ መስክ ነዉ፡፡ በየአካባቢዉ የሚገኙ የቱሪዝም ሀብቶችን በተገቢዉና በትክክለኛዉ ገፅታ በማስተዋወቅና በማስጎብኘት የገቢ ምንጭ፣ የስራ እድል ፈጠራ አማራጭ፤ የገጽታ ግንባታና የጥናትና ምርምር ቦታዎች በማድረግ ረገድ አስጎብኚ ድርጅቶች በየአካባቢዉ አለመቋቋምና ከሌሎች ጋር ትስስር አለመፈጠር ከመሰረተ ልማት አለመስፋፋት ጋር ተዳምሮ ዘርፉ የተቀዛቀዘ እንዲሆን አስችሏል፡፡

**የስፖርት ልማት አፈጻጸም-**

በክልሉ መንግስት የበጀት ድጋፍ የስፖርት ውድድር መድረኮች ማዘጋጀትና ሀገር አቀፍ መድረኮች በመሳተፍ የክልላችንን ብሔር ብሔረሰቦች ባህላዊ ስፖርቶችና በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች የክልሉን መልካም ገጽታ የመገንባትና የማስተዋወቅ ተግባራት እያከናወነ የሚገኝ ቢሆንም የሥራው ስፋትና ጥልቀት ሲገመገም የተገኘው ውጤት ውስን ከመሆኑ ባሻገር ወደ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ዘልቆ ሕብረተሰቡን ሙሉ በሙሉ ያላሳተፈ ሆኖ ይገኛል፡፡

በየደረጃዉ የተቋቋሙ የስፖርት ኮሚቴዎችና ማህበራት አደረጃጀትን በተመለከተ 309 ስፖርት ም/ቤቶችን ለማደራጀት ታቅዶ 252 የስፖርት ም/ቤት ተቋቁሟል፡፡ 2,993 የማህበረሰብ ስፖርት ኮሚቴዎችን ለማደራጀት ታቅዶ 3,922 የማህበረሰብ ስፖርት ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡ 23 ስፖርት ፌዴሬሽኖችን ለማደራጀት ታቅዶ 13 ፌዴሬሽኖች ተቋቁሟል፡፡ 6 የተደራጁና የተጠናከሩ ክለቦች ለማደራጀት ታቅዶ 2 ክለቦችን ለማደራጀት የተቻለ ሲሆን በቁጥር1973 የተደራጁና የተጠናከሩ ቡድኖች ለማደራጀት ታቅዶ 611 ቡድኖችን ማደራጀት ተችሏል፡፡

የስፖርት ልማትና እንቅስቃሴ ከመንግስት ድጎማ ደረጃ በደረጃ በማላቀቅ ሕዝቡ ስፖርትን የመምራትና የማስተዳደር ሃላፊነት እንዲረከብ የስፖርት ፌዴሬሽኖችን፣ ማህበራትንና ምክር ቤቶች የማደራጀት ጥረቶች እየተከናወነ ይገኛል፡፡

የስፖርት ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋትን በተመለከተ 2 የስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከላትን ለመገንባት ታቅዶ 1 ማከናወን የተቻለ ሲሆን በቁጥር 2 የስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከላትን አገልግሎት ለማስጀመር ታቅዶ አገልግሎት ማስጀመር አልተቻለም፡፡

በየደረጃው የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች መገንባትን በተመለከተ 85 በገጠር የይዞታ ማረጋገጫ ያላቸዉ ማዘዉተሪያ ስፍራ ለማዘጋጀት ታቅዶ 42 እና 21 ካርታና ፕላን ያላቸዉ የከተማ ማዘዉተሪያ ስፍራዎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 20 ማዘጋጀት ተችሏል፡፡ እንዲሁም 23 አንደኛ ደረጃ የማዘዉተሪያ ስፍራዎችን ለመገንባት ታቅዶ 18፣ 21 2ኛ ደረጃ የማዘዉተሪያ ስፍራዎችን ለመገንባት ታቅዶ 4 እና 28 የይዞታ ማረጋገጫ ያላቸዉ ጥርጊያ ሜዳዎች ለማዘጋጀት ታቅዶ 18 ማከናወን ተችሏል፡፡

የስፖርት ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን ማስፋፋትን በተመለከተ በተለያዩ የስፖርት አይነቶች ለ74 ዳኞች የዳኝነት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ37፤ በተለያዩ የስፖርት አይነቶች ለ 81 ሰዎች የአሰልጣኝነት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ 41 አሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የታዳጊ ወጣቶች ፕሮግራም ስልጠናን በተመለከተ በሁሉም ዞኖች ደረጃ 412 ታዳጊዎችን ማሰልጠን ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በታዳጊ ወጣቶች ስልጠና ፕሮግራም ስልጠና የሚሰጡ 20 ለማሳተፍ ታቅዶ 19 አሰልጣኞች ስልጠናውን እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# 3. የመሠረተ ልማት አፈጻጸም

## 3.1. የትራንስፖርትና መንገድ ልማት አፈጻጸም

### የአሽከሪካሪ ተሸከርካር ብቃት ማረጋገጥ

ባለፉት የዕቅድ ዘመን የአሽከርካሪዎችን ክህሎት፣እውቀትና ስነምግባር ከማሳደግ አንጻር 8 አዲስ ብቃታቸው የተረጋገጠ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማትን ለማቋቋም ታቅዶ 11 (137%) የተቋቋመ ሲሆን 2,860 አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 2,760 (72.3%) መስጠት ተችሏል፡፡

የተሸከርካሪ ቴክኒክ ብቃት ከማሳደግ አንጻር 1,574 ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ 1,570 (99%) ምርመራ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ድንገተኛ የተሸከርካሪ ምርመራ ለ3,048 ለማድረግ ታቅዶ 2,476 (81%) ማድረግ ተችሏል፡፡ የተሸከርካሪ ምርመራ ተቋማት 2 ለማቋቋም ታቅዶ የግል ባለሀብቶችና ድርጅቶች የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራና ምቹ ሁኔታ ቢኖርም በዘርፉ ለመሠማራት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምክንያት ሊከናወን ያልቻለ ሲሆን 21 የተሸከርካሪ ጥገና ተቋማት ለማቋቋም ታቅዶ በከተሞች ላይ ያለው የመሬት አቅርቦት ችግር ምክንያት 15 (71%) ተቋቁሟል፡፡

### የህዝብ ትራንስፖርት፡-

በክልሉ 32 መናኸሪያዎች ያሉ ሲሆን በቁጥር ደረጃም ይሁን ካላቸው የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ ደረጃቸው ያልጠበቁና ለህብረተሰብ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የማያስችሉ

ናቸው። የህዝብ ትራንስፖርት የሚሰጥባቸዉ የስምሪት መስመሮች 36 ለማከናወን ታቅዶ 32 (88.9%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን ዞኖችን ከአጎራባች ክልሎች ጋር የሚያገናኙ 4 የስምሪት መስመር ለመክፈት ታቅዶ 3 (75%) የስምሪት መስመሮችን መክፈት ተችሏል። የትራንስፖርት አገልግሎቶች አደረጃጀትና ስምሪትን ከማሳደግ አንጻር 5 አዲስ መናኸሪያ ለመገንባት ታቅዶ 3 (60%) የተገነባ ሲሆን የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራትን በማደራጀት 7 ለማድረስ ታቅዶ 10 (142%) ማደራጀት ተችሏል። የከተማ ታክሲ 5 ማህበር ለማደራጀት ታቅዶ 6 (120%) ማደራጀት ተችሏል። እንዲሁም የ3 መናኸሪያዎች ደረጃ ለማሻሻል ታቅዶ ምንም ማከናወን አልተቻለም።

**ጭነት ትራንስፖርት ፦**

የጭነት ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን ወደ ክልሉ ሰሌዳ እንዳይቀይሩ ማድረግ፤ የጭነት ተሽከርካሪዎችን መረጃ በመጫን ችሎታቸውና በአገልግሎት ዘመናቸው የማደራጀት ሥራ ሲሰራ ቆይቷል። 3 አዲስ የጭነት ትራንስፖርት ማህበራትን ለማደራጀት ታቅዶ ማከናወን አልተቻለም።

**የመንገድ ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ፦**

የመንገድ ትራፊክ አደጋ ከመቀነስ አንጻር በየዓመቱ በ10% የመንገድ ትራፊክ አደጋ በመቀነስ ከመነሻው 120 የነበረውን የአጠቃላይ አደጋ መጠን ወደ 90 ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ በርካታ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም ተሽከርካሪዎችና በመንገዶች ቁጥርና ርዝመት በጣም የጨመረ መሆኑ፣ ዘርፉ እንደ ሀገር በተሟላ ሁኔታ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አለመሆን፤ የህገ-ወጥ ሞተር ሳይክሎች በከፍተኛ ሁኔታ ሀገር ውስጥ በኮንትሮባንድ መግባት፤ የተሳፋሪ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር እና የአሽከርካሪዎች ግንዛቤ ማነስ ምክንያት ወደ 173 አደጋ ከፍ በማለትና እንዲሁም በየዓመቱ በ5% የህይወት ጉዳት /ሞት/ በመቀነስ ከመነሻው 7 የነበረውን የሞት አደጋ መጠን ወደ 3 ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ ወደ 9 በመጨመሩ በተያዘው GTP እቅድ መሠረት አለመሳካቱን ያመለክታል። በየዓመቱ 5% የንብረት ጉዳት /በገንዘብ/ ሲተመን በመቀነስ ከመነሻው 2.8 ሚሊዮን የነበረውን የንብረት ጉዳት ወደ 2.7 ሚሊዮን ዝቅ ለማድረግ

ታቅዶ 2.9 ሚሊየን መድረስ ችሏል። 182 የመንገድ ዳር ገላጭ ምልክቶች ለመስራት ታቅዶ 189 (103%) ማከናወን ተችሏል።

**የመንገድ ዘርፍ አፈፃፀም፡-**

የመንገድ ልማት ስራዎችን በተመለከተ በደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል ስር ባሉ መዋቅሮች ከ2004/2005 ዓ.ም ጀምሮ ሁለት መቶ አሥራ ስድስት /216/ፕሮጀክቶች 2,143.43 ኪ/ሜ የሚሸፍን 156 የገጠር ቀበሌ ተደራሽ መንገድ ስራ /URRAP/ ፕሮጀክቶች ታቅደዉ 1,642.12 (76%) በሙሉ አጠናቆ ለአገ/ት ክፍት ተደርጓል። በእቅድ ተይዘዉ ሳይከናወኑ የቀሩ 62 የገጠር ቀበሌ ተደራሽ መንገድ ስራ እና 26 ድልድይ ሥራ ፕሮጀክቶች /URRAP/ እስከአሁን ያልተጠናቀቁ ናቸው። ባጠቃላይ የዩራፕ መንገድ 2,143.43 ኪ/ሜ ያለ ሲሆን በክልሉ ካለው ጠቅላላ የቆዳ ሽፋን (39,062) ጋር ሲነፃፀር የመንገድ ጥግግቱ ዝቅተኛ ነው።

**የመንገድና ድልድይ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም፡-**

በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም 3,644.3 ኪ..ሜ የመንገድ ጥናትና ዲዛይን በተደራጁ የዩራፕ አማካሪዎች ለመሥራት ታቅዶ 3,863.3 /106%/ ኪ..ሜ. ለማጠናቀቅ የተቻለ ሲሆን ድልድይ ጥናትና ዲዛይን ስራዎች አኳያ የ86 ድልድዮች ጥናትና ዲዛይን ለመሥራት ታቅዶ የ74 (86%) ድልድዮች ጥናትና ዲዛይን በማጠናቀቅ ለግንባታ ዝግጁ እንዲሆኑ ተደርጓል።

**የድልድይ ግንባታ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም፡-**

በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም 30 ድልድዮችን ለመገንባት ታቅዶ 5 /17%/ ተጠናቆ ለአገ/ት ክፍት ያደረገ ሲሆን ቀሪ 25 ድልድዮች በግንባታ ሂደት ዉሥጥ ናቸዉ።

**የስራ ዕድል ፈጠራ አፈፃፀም፡-** ባለፉት አስር ዓመታት በመንገድ ጥናትና ዲዛይን፣ በመንገድ ግንባታና ጥገና እንዲሁም በድልድይ ዲዛይን ግንባታና ጥገና ስራ ላይ ለሚሰማሩ 95,000 ዜጎች ጊዜያዊና ቋሚ የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለቋሚ ወንድ 751 ሴት 455 በድምሩ 1206 እና በጊዜያዊነት ወንድ 42,771 ፤ሴት 23,800 በድምሩ 66,571 ሲሆን በጠቅላላው

ወንድ 43,522 እና ሴት 24,255 በድምሩ ለ67,777 በላይ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።

### 3.2. የውሀ ልማት አፈፃፀም

በክልሉ ለመጠጥ አገልግሎት የሚውሉ የውሃ መገኛዎችን በቅድመ ጥናት በመለየት ለጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ እንዲሁም ውሃን አሸገው ለገበያ ማቅረብ ለሚፈልጉ ባለሃብቶች መረጃውን በግብዓትነት መጠቀም እንዲቻል በዕቅድ ዘመኑ መነሻ በ350 ካሬ ኪ/ሜ ቦታ ላይ ብቻ ተጠንቶ የነበረውን የውሃ ሀብት አለኝታ ጥናት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 2014ዓ.ም 1,025 ካሬ ኪ/ሜ ለማድረስ ታቅዶ ባለፉት ዓመታት በተከናወነ ተግባር ሙሉ በሙሉ ዕቅዱን ማሳካት ተችሏል።

ከውሃ ሀብት አጠቃቀም አንጸጻር በ9 ንዑስ ተፋሰሶች የውሃ ሀብት አጠቃቀም ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ በ6 ንዑስ ተፋሰሶች ላይ የውሃ ሃብት አጠቃቀም ጥናት ማከናወን የተቻለ ሲሆን የውሃ ሃብት መረጃ አቅርቦትና ስርጭትን በሚመለከት የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ተቋማት፣ የውሃ ጥራት፣ ሳኒቴሽንና ሃይጂን እና የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ መረጃዎች ለማደራጀት በታቀደው ዕቅድ መሰረት ሰፊ ክፍተት ስላለ ለቀጣይ ብዙ መስራት እንዳለበት ያሳያል።

ለክልሉ ሕብረተሰብ የሚቀርበው የመጠጥ ውሃ ጥራቱ የተጠበቀ መሆኑን ከማረጋገጥ አንፃር በ50 ውሃ አካላት ላይ ተጓዳኝ ምርመራዎችን በማካሄድና የጥራት ደረጃቸውን በማረጋገጥ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ ታቅዶ 30፣ በ5,670 አዳዲስ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መገኛዎች ላይ የፊዚኮ ኬሚካል ምርመራ በማካሄድ የጥራት ደረጃቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ 714፣ በ1,110 ነባርና አዳዲስ የውሃ ተቋማት ላይ የባክቴሪኦሎጂካል ናሙና ምርመራ ማካሄድና የጥራት ደረጃቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ 339፣ ለከተማ ነዋሪዎች የሚቀርብ 30 የውሃ ተቋም ላይ የውሃ ጥራት ቁጥጥር ለማካሄድ ታቅዶ 18 እና በክልል ውስጥ የሚገኙ 200 ኢንዱስትሪዎች በውሃ አካላት ላይ የሚለቁትን ፍሳሽ የጥራት ደረጃ ቁጥጥር ለማካሄድ ታቅዶ 100 ኢንዱስተሪዎች ፍሳሽ የጥራት ቁጥጥር ለማካሄድ ተችሏል። በሌላ በኩል በፍሎራይድ ለተበከሉ የማኅበረሰብ የመጠጥ ውሃ ተቋማት 12 የሙከራ የፍሎራይድ ማጣሪያ ቴክኖሎጂ ለመገንባት ታቅዶ ያልተሰራ ቢሆንም በቀጣይ በትኩረት ይሰራል።

በውሃ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ በመስጠትና በውሃ ሥራዎች በግንባታ፣ በማማከርና በውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና ጠረጋ ዘርፍ የድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ከመስጠት አንፃር በማማከር፣ በግንባታ፣ እና በውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ለሚሰማሩ 60 ባለሙያዎች እና 48 ድርጅቶች የብቃት ማረጋጫ ለመስጠት ታቅዶ ለ30 ባለሙያዎች እና ለ18 ድርጅቶች የብቃት ማረጋጫ መስጠት የተቻለ ሲሆን ለ30 ባለሙያዎች እና ለ18 ድርጅቶች የብቃት ማረጋጫ ማደስ ተችሏል።

## የመጠጥ ውሃ ጥናትና ዲዛይን

ከገጠር መጠጥ ውሃ ጥናትና ዲዛይን አንጻር የባለፉትን የኢትዕ ዓመታት አፈጻጸም በተመለከተ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 5,401 የመጠጥ ውሃ ተቋማት ጥናትና ዲዛይን ለማከናወን ታቅዶ 3,565 የመጠጥ ውሀ ተቋማት ጥናትና ዲዛይን ስራ ማከናወን ተችሏል።

ከከተማ መጠጥ ውሃ ጥናትና ዲዛይን አንጻር የባለፉትን አስር ሁለት ዓመታት አፈጻጸም በተመለከተ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 52 የመጠጥ ውሃ ተቋማት ጥናትና ዲዛይን ለማከናወን ታቅዶ 29 የመጠጥ ውሀ ተቋማት ጥናትና ዲዛይን ስራ ማከናወን ተችሏል።

## የመጠጥ ውሃ ተቋማት ግንባታ

**የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት ግንባታ፡-**

በሁለተኛ የዕድገትና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን እና በሁለት ተከታታይ አመታት የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን ከ30.8% ወደ 33.3% ከፍ በማድረግ 2,237 የመጠጥ ውሃ ተቋማት በመገንባት 1,025,845 ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ በ2014 የደቡብ ክልል ውሀ ቢሮ መረጃ መሰረት የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን 33.3% ብቻ ሊሆን ተችሏል።

**የከተማ መጠጥ ውሃ ተቋማት**

የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን 30.1% ወደ 39.2% በ2014 ዓ.ም መጨረሻ ከፍ ማለት ችሏል። በአጠቃላይ በከተማና በገጠር ባለፉት ዓመታት በተከናወነ ተግባር 2,274 የመጠጥ ውሃ ተቋማት በመገንባት እና 1,234,818 ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን

የደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልል አማካይ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንም 34.2% ማድረስ ተችሏል።

## የመጠጥ  ውሃ ተቋማት አስተዳደርና መሳሪያዎች ጥገና

በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን 8,874 አገልግሎት የማይሰጡ ውሃ ተቋማትን በመጠገንና መልሶ በመገንባት በዕቅድ ዘመኑ መነሻ 2003ዓ.ም ከነበረበት 10% ወደ 5% ዝቅ ለማድረግ ታቅዶ በተከናወነ ተግባር 3,440 መጠጥ ውሃ ተቋማትን ጥገናና መልሶ ግንባታ ስራ በመስራት የተቋማት ብልሽት ምጣኔን ወደ 38.8% ከፍ በማለቱ በቀጣይ ዕቅድ አመታት ላይ ሰፊ ሥራ እንደሚጠብቅ ያሳያል።

## 3.3. ማዕድንና ኢነርጅ አፈጻጸም

### በአማራጭ ኢነርጅ ዘርፍ

ባለፉት 10 ዓመታት በተደረገ እንቅስቃሴ ሃይል ማመንጨት የሚችሉ 10 ወንዞች ላይ የአዋጪነት ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ በ5 ወንዞች ላይ ጥናት የተካሄደ ስሆን አፈጻጸሙም 50% ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ ከ5 አነስተኛ ወንዞች ሃይል በማመንጨት ሕብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ በ1 ወንዝ ላይ ብቻ ግንባታ በማካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን በአጠቃላይ የፒኮ/ ሀይድሮ ፓወር ጥናትና ግንባታ ሥራ በዝቅተኛ አፈጻጸም እንዳለ ያሳያል። የሶላር ቴክኖሎጂ ስርጭትና ተከላ በተመለከተ ባለፉት 10 ዓመታት የሶላር ማሾ ስርጭት 726,601 ታቅዶ 282,230 የተከናወነ ሲሆን 38.84%፤ 149,775 የቤተሰብ ሶላር ስርጭት ለማድረግ ታቅዶ 81,892 አፈጻጸም 54.7% ላይ ስሆን፤ በተጨማሪም 2,822 ሶላር ሲስተም በተቋም ተከላ ለማካሄድ ታቅዶ 1,430 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸም 50.7% መሆኑ ተገምግሟል። ቤተሰብ ባዮጋዞችን ለመገንባት 284 ታቅዶ 139 መገንባት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 49% መሆኑን ያሳያል። ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች በተመለከተ 96,950 የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን ለማሰራጨት ታቅዶ 41,083 ማሰራጨት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 42.3% ነው።

### በማዕድን ሀብት ጥናትና አስተዳደር

በክልሉ የሚገኘዉን የማዕድን ሀብት በማጥናት፤ በህጋዊና በፍታዊ መንገድ የሚለማበትን አስራር በመዘርጋትና አልሚ ባለሀብቶችን በሰፋት በማሳተፍ ዘርፉ ለሀገርቱ ብሎም ለክልሉ ኢኮኖሚ የሚያበረክተዉን አስተዋጽዎ ከፍ ለማድረግ ባለፉት ሁለት እትዕ ዓመታት በተደረገዉ እንቅስቃሴ በጥንካሬና በጉድለት የታዩ ጉዳዮችን ለመገምገም ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሠረት በዘርፉ የውጭ ምንዘሬ ከማሳደግ አንጻር ባለፉት ሁለት የእትዕ ዓመታት 7,000 ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ለማስገባት ታቅዶ 4,783 ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ማስገባት የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም 68.3% ያህል ሆኗል፡፡ በዚህም ከክልሉ የተገኘው የወርቅ ምርት በሀገሪቱ ያለውን የወጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት ጉልህ ሚና የተጫወተ ቢሆንም ከተቀመጠው ግብ አንጻር ግን የተመዘገበው ውጤት በቂ ነው ብሎ መውሰድ አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የክልሉን የማዕድን ሀብት በዓይነትና በመጠን በጥናት እየለዩ በዘርፉ የሚደረገዉን ኢንቨስትመንት ለማሳደግ በተደረገዉ ጥረት የማዕድን ሀብት አለኝታ ጥናት ሽፋን በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ 810 ካ.ኪ.ሜ ታቅዶ 81 ካ.ኪ.ሜ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙን 10% ብቻ ሆኗል፡፡ በኤክስፖርት ምርትነት የሚታወቁና የውጭ ምንዛሪ ሊያስገኙ የሚችሉ ከወርቅ በተጨማሪ እንደ ብረት ማዕድን እና ካዮሊን ዓይነት የጌጣጌጥ ማዕድናት በክልሉ እንዳሉ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለኢንዱስትሪ ግብዓት ሊሆን የሚችል፤ የድንጋይ ከሰል  ማዕድናት በጥናት የመለየት ሥራ እንዲከናወን በማድረግ ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች በማቅረብ ሀገሪቱ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ የማዳን ሥራ መስራት ተጀምሯል፡፡ ይሁን እንጂ በቀጣይ ለዚህ ተግባር በቂ ሀብትና ሎጂስቲክስ መድቦ ሰፊ ሥራዎችን መስራት ይጠይቃል፡፡

በማዕድኑ ዘርፍ ባለፉት አስራ ሁለት ዓመታት በተደረገው እንቅስቃሴ 26,546,304 ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 22,992,770 ብር ገቢ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ 86% ያህል እንደሆነ ተገምግሟል፡፡ በአጠቃላይ በክልላችን ካለዉ ዕምቅ የማዕድን ሃብትና የቆዳ ስፋት አንጻር ሲታይ እየተመዘገበ ያለዉ ዉጤት በቂ ነው ብሎ መውሰድ አይቻልም፡፡

### 3.4. የመስኖ ልማት አፈፃፀም

በመጀመሪያዉ እትዕ ከ2003-2007 በመስኖ ጥናት ዲዛይን፡ 1,275 ሄ/ር ማልማት አቅም ያለቸዉ 27 የመስኖ ተቋማት ጥናት ዲዛይን ለማድረግ ታቅዶ 1,047 ሄ/ር የማልማት አቅም ያላቸዉ 25 አነስተኛ የመስኖ ተቋማት ጥናት ዲዛይን ተከናዉኗል፡፡ በመስኖ ግንባታ 25

ዘመናዊ የመስኖ ተቋማት በመገንባት 1,047 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 14 ዘመናዊ መስኖ ተቋማት ግንባታ ተገንብቶ 911ሄ/ር መሬት ማልማት ተችሏል። በመሆኑም አፈፃፀሙ ዝቅተኛ መሆኑ የተገመገመ ሲሆን ይህም የሚያሳየዉ ከእትዕ2 በፊት ለመስኖ የተሰጠዉ ትከረት አናሳ መሆኑን ያሳያል።

በመስኖ ጥናትና ዲዛይን 3,239 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 94 የመስኖ ኘሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ሥራ ለማከናወን ታቅዶ 2,558 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ 65 አነስተኛና 1 መካከለኛ የመስኖ ተቋማት ጥናትና ዲዛይን ሥራ ለማከናወን ተችሏል። በመስኖ ግንባታ 2,558 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 65 የመስኖ ተቋማት ለመገንባት ታቅዶ 1,766 ሄ/ር የሚያለሙ 50 የመስኖ ተቋማት በመገንባት 1,756 አባዎራ/እማዎራ ተጠቃሚ ማድረግ ተችለዋል ።

በዚህም መሰረት በነባሩ ክልል በሁለቱም የዕቅድ ዘመን በከፍተኛ መስኖ ግንባታ ዘርፍ ምንም ወደ ተግባር ያልተገባ ሲሆን በመካከለኛ መስኖ ግንባታ ከአንድ ያልበለጠ ክንዉን የታየበትና ሁሉም በአነስተኛ ደረጃ ተጠንተዉ የተገነቡ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ።

በክልሉ 305,886.51ሄ/ር በአነስተኛ፣በመካከለኛና ከፍተኛ መስኖ ሊለማ የሚችል መሬት እንዳለ ቢታወቅም በዘመናዊ መስኖ የለማዉ መሬት መጠን 2,677 ሄ/ር ሲሆን ይህም ከክልሉ ከዘመናዊ የመስኖ ፖቴንሻል አንጻር ሲታይ 0.8% ያህል ብቻ ነዉ።

# ምዕራፍ አራት

# 4. የማህበራዊ ዘርፍ ልማት አፈጻጸም

## 4.1. የሥነ-ሕዝብና የሰው ሀብት ልማት አፈጻጸም

### 4.1.1. የሥነ ሕዝብ ልማት አፈፃፀም

የአገራችን ሥነ ሕዝብ ፖሊሲ አብይ ጉዳይ የሕዝብ ዕድገት ምጣኔን ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በማጣጣም ከረጅም ጊዜ አኳያ የዜጎች የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል ማድረግ ነው። ባለፉት አመታት የሀገራዊ ስነ-ህዝብ ፖሊሲ የሴቶችንና የህጻናትን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል "የተመጠነ ደስተኛና የበለጸገ" የቤተሰብ አባላት ይኑረን የሚለው እሳቤ እንደ ትኩረት አቅጣጫ በመያዝ የሴቶችን የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ምጣኔ (CPR) በመጨመር አጠቃላይ የውልደት ምጣኔ [TFR] ወይም አንዲት በመውለድ ዕድሜ ክልል ውስጥ /15—49 ዓመት/ የምትገኝ ሴት በዕድሜ ዘመኗ ትወልዳቸው የነበሩት ልጆች ቁጥር በጣም ከፍተኛ ከነበረበት 5.6 ልጆች ወደ 4.1 ልጆች ዝቅ ማለቱና ይህንን ተመስርቶም የሕዝብ ዕድገት ምጣኔው

በአነስተኛ ደረጃም ቢሆን በመቀነስ ወደ 2.9 በመቶ የደረሰ መሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ (ምንጭ፡ DHS 2016)

### 4.1.2. ትምህርት ልማት አፈፃፀም

**የትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት፡-**

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ2007 ዓ.ም ከነበረበት 2.62% በየዓመቱ አፈፃፀሙ ከፍና ዝቅ እያለ መጥቶ በ2012 ዓ.ም 99% ለማድረስ ታቅዶ ማሳካት የተቻለዉ 40.65% ብቻ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል በዞኖች መካከል የአፈጻጸም ልዩነት ያለ ሲሆን ከፍትሃዊነትም አንፃር የሰፋ ክፍተት አለበት፡፡

የቅድመ መደበኛ ትምህርት በተመለከተ ሕፃናትን በትክክለኛ እድሜያቸው ወደ ትምህርት ቤት እንዲላኩ በማድረግ የትምህርት እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል በየዓመቱ ጥረቶች ቢደረጉም በ2007 ዓ.ም የቅድመ መደበኛ ንጥር ተሳትፎ 2.63% የነበረውን በ2012 ዓ.ም 39.43% ማድረስ የተቻለ ቢሆንም አፈፃፀሙ ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ከ1,320 የነበረውን በመንግስት፣ በግል ድርጅቶች፣ በሕብረተሰቡና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች በተደረገው ርብርብ 1,486 ትምህርት ቤቶች በመገንባት ወደ 7,006 ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ በ2007 ዓ.ም 104.9% የነበረውን ወደ 102% ለማሻሻል ታቅዶ በየደረጃው በተደረገው ርብርብ የተሳትፎ ምጣኔውን 92.76% ማድረስ የተቻለ ሲሆን የጾታ ምጥጥኑንም ከ0.9 ወደ 0.98 ለማድረስ ታቅዶ 0.91 ማድረስ ተችሏል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ንጥር ተሳትፎ ሕፃናቱ በትክክለኛ እድሜያቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲጀምሩ በማድረግ ከ93.75% ወደ 99% ለማድረስ ታቅዶ በ2012 ዓ.ም 82.59% ላይ ሲሆን ከተጣለው ግብ አንፃር በ16.41% ልዩነት አለው፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ቁጥር ከ134 ወደ 172 ማድረስ ተችሏል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ አንጻር በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከ9-10ኛ ክፍል 42.59 በመቶ ወደ 74.0 በመቶ እንዲሁም ከ11-12ኛ ክፍል ከ6.49 በመቶ ወደ 22 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ በቅደም

ተከተል 55.85 በመቶ እና 22.42 በመቶ ማድረስ ተችሏል። እንድሁም ከ9-12 በ2007 ከነበረበት 25.21 በመቶ በ2012 ዓ.ም ወደ 39.76 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ንጥር ተሳትፎ አንጻር ከ9-10ኛ ክፍል ያለው ትምህርት ንጥር ተሳትፎ 21.53% (ሴት 21.51%) ወደ 66.5% (ሴት 60%) ለማድረስ ታቅዶ 28.88% (ሴት 28.22%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከ11-12ኛ ከ20.7% (ሴት 18.66%) ወደ 35% ለማድረስ ታቅዶ 30.79% (ሴት 28.59%) ማድረስ የተቻለ ቢሆንም ከዕቅድ አንፃር አፈፃፀሙ ዝቅተኛ እንደሆነና በአጠቃላይ በሁሉም ደረጃ ያለው ንጥር ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛና ከዓመት ዓመት የመዋዠቅ ሁኔታ እንደሚታይበት መረዳት ይቻላል።

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎ በቅድመ መደበኛ ትምህርት አንጻር ልዩ ፍላጎት ያላቸው እድሜያቸው ከ4-6 ዓመት የሆናቸው ሕፃናትን በሚኖሩባቸው ቀበሌያት ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠርና መረጃ በመሰብሰብ በቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሀ ግብር እንዲሳተፉ በተደረገው ጥረት በ2007 ዓ.ም 1 ተማሪ ብቻ የነበረ ሲሆን በ2012 ዓ.ም ወደ 272 ብቻ ለማድረስ ተችሏል።

ከልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎ አንጻር፡- በ2007 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ (1-8) 2,156 ተማሪ የነበረ ወደ 31,153 ማሳደግ የተቻለ ሲሆን ከ9-10ኛ ክፍል 105 ተማሪ ብቻ የነበረውን ወደ 2,774 ማድረስ ተችሏል። እንዲሁም ከ11-12ኛ ክፍል የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ቁጥር ከ10 ወደ 1,136 (ሴት 506) እንዲሆን ተደርጓል።ይሁን እንጂ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎ ከዕቅድ አንጻር አፈፃፀሙ ከፍተኛ ክፍተት እንዳለበት ያመለክታል::

በሁለተኛው ዕ.ት.ዕ በአርብቶ አደር አካባቢ ያሉ ሁሉም እድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ ህጻናት እንዲሁም ለሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ትምህርትን በፍትሃዊነት ለማዳረስ በቅድመ መደበኛ በ2007 ዓ.ም ምዕራብ አሞ 30.9% እና ካፋ 9.2% የነበረ ሲሆን በ2012 ዓ.ም በአርብቶ አደር አካባቢዎች የተመዘገበው አፈፃፀም 38.12% እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ።። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎን ከ84.7% ወደ 85.78% የደረሰ በመሆኑ አፈፃፀሙ መሻሻል ያሳየ ቢሆንም ዝቅተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል የሁለተኛ ደረጃ (9-10) ትምህርት ተሳትፎን ከ11.8% ወደ 55% ለማድረስ ታቅዶ 5.7% ሲሆን አፈፃፀሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ የ2012 ዓ.ም መረጃ ያመለክታል።

የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት ኘሮግራም አንጻር በ2007 ዓ.ም 217,656 ተማሪዎች የነበሩ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት 166,161 ተማሪዎች እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ተግባሩ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ መሆኑን ያመላክታል፡፡

**የትምህርት ጥራትና ተገቢነትን ከማረጋገጥ አንጻር፡-**

የትምህርት አመራሩ ትምህርት ቤቶች በብቃት በመምራት የሚፈለገዉ የሰዉ ሀይል በማምረት ረገድ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ደግሞ የ2ኛ ዲግሪ አንዲኖራቸዉ ግብ ተጥሎ ሲሰራ የቆየ ሲሆን ከ1-8ኛ ክፍል የሰለጠኑ ር/መምህራን ሽፋን ከ27.6 በመቶ ወደ 100% ለማድረስ ታቅዶ 32% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከ1-8ኛ ክፍል የሰለጠኑ ሱፐርቫይዘሮች ሽፋን ከ61.7 በመቶ ወደ 100% ለማድረስ ታቅዶ 70.2% ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከ9-12ኛ ክፍል የሰለጠኑ ር/መምህራን ሽፋን ከ11.2 በመቶ ወደ 48.6% ለማድረስ ታቅዶ 27% ማድረስ የተቻለ ሲሆን ከ9-12ኛ ክፍል የሰለጠኑ ሱፐርቫይዘሮች ሽፋን ከ33.3 በመቶ ወደ 93% ለማድረስ ታቅዶ 69.5% ማድረስ ተችሏል፡፡

በክልላችን የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ተመርቀው ማስተማር ስራ ላይ የሚገኙ ሲሆን በዚህም ለደረጃው የሰለጠኑ የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ሽፋን ከ6.35% ወደ 70% ለማሳደግ ታቅዶ 61.76% ማድረስ ተችሏል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት /ከ1-8ኛ ክፍል/ ለደረጃዉ የሰለጠኑ መምህራን ሽፋን ከ40.66% ወደ 100% ለማሳደግ ታቅዶ 89.81% ለማድረስ ተችሏል፡፡

ከሁለተኛ ደረጃ (9-10ኛ) መምህራን አንፃር የ2ኛ ደረጃ መምህራን ሽፋን ከ83.36% ወደ 98% ለማድረስ ታቅዶ 67.19% ብቻ ማሳካት ተችሏል፡፡

ከመሰናዶ (11-12ኛ) መምህራን አቅርቦት በ2007 ዓ.ም 0.96% የነበረውን ለደረጃው የሰለጠኑ መምህራን ሽፋን ወደ 21% ለማድረስ ታቅዶ 3.48% ብቻ መፈፀም ተችሏል፡፡

የክፍል-ተማሪ ጥምርታ በተመለከተ በትምህርት ቤት መሻሻል ትግበራ መሰረት ከ1-4ኛ ክፍል ከ1፡67 ወደ 1፡50፤ ከ5-8ኛ ክፍል ከ1፡56 ወደ 1፡50፤ ከ1-8ኛ ክፍል ከ1፡63 ወደ 1፡50 ለማድረስ ታቅዶ ከ1-4ኛ 1፡62፤ ከ5-8ኛ 1፡55 እንዲሁም ከ1-8ኛ 1፡59 ማድረስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ከ9-10ኛ ክፍል ከ1:65 ወደ 1:40 እና ከ11-12ኛ ክፍል ከ1:52 ወደ 1:40 ለማድረስ ታቅዶ እንደቅደም ተከተላቸዉ 1:66 እና 1:53 ማድረስ ተችሏል፡፡

የተማሪ መጽሀፍ ጥምርታን በስታንዳርዱ መሰረት አሳትሞ ለተማሪዎች ለማቅረብ በተደረገው ጥረት የተማሪ መጽሀፍ ጥምርታን በሁሉም የክፍል ደረጃ 1፡1 ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ በአማካይ 1፡2 እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በትምህርት ቤቶች ስታንዳርድ መሰረት 91.81% (ሀገራዊ 91.6%) የሚሆኑት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም 76.41% (ሀገራዊ 83.7%) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከደረጃ በታችና ለመማር ማስተማር ምቹ ያልሆኑ ናቸው፡፡ ደረጃ ሶስት የገቡት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 8.2% ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ 22.49 ከመቶ መሆኑን መረጃዉ ያሳያል፡፡

የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን ማሻሻል መርሀ ግብርን አጠናክሮ ከመተግበር አንፃር፡- ትምህርትን በፕላዝማ በመጠቀም ያስተምሩ የነበሩ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁጥር 2007 ዓ.ም 37 ብቻ የነበረ ሲሆን በ2012 ዓ.ም 42፣ የኮምፒዩተር ቤተመፅሐፍ ያላቸዉን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በ2007 ዓ.ም ከነበረበት 53 በ2012 ዓ.ም 145፣ በ2007 ዓ.ም አንድም ትምህርት ቤት የኢ-ለርንግ ማዕከል ያልነበረዉ ሲሆን በ2012 ዓ.ም በ52 ትምህርት ቤቶች ማዕከላትን ማቋቋም መቻሉና የሬዲዮ ትምህርት የሚያገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሽፋንን 73.4% ማድረስ መቻሉ በጥንካሬ የሚወሰዱ ናቸዉ፡፡

የተማሪ መጠነ ማቋረጥን በ2ኛው ዕ.ት.ዕ ዘመን የ1ኛ ክፍል ከ25.2% ወደ 14.5% ለመቀነስ ታቅዶ በ2011 ዓ.ም 14.5% ማድረስ ተችሏል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ (1-8 ክፍል) ከ13.6% ወደ 13% ለመቀነስ ታቅዶ 15.7%፣ ከ9-10 ክፍል ከ16.3% ወደ 7.3% ለመቀነስ ታቅዶ 8.3%፣ እንዲሁም ከ11-12 ክፍል ከ11.7% ወደ 3.4% ለመቀነስ ተችሏል፡፡ የተማሪ መጠነ መድገምን ከ1-4 ክፍል ከ8.68% ወደ 12.76% ከፍ ያለ፣ ከ5-8 ክፍል ከ11.36% ወደ 10.64% መቀነስ የተቻለ፣ ከ1-8 ክፍል ከ10.02% ወደ 11.70% ከፍ ያለ እና ከ9-10 ክፍል ከ8.11% ወደ 11.22% ከፍ ያለ እና ከ11-12 ከ1.2% ወደ 1.13% ዝቅ ያለ ሲሆን በ2ኛዉ ዕ.ት.ዕ ላይ መጠነ መድገምን ሁለት በመቶና በታች ለማስመዝገብ ግብ የተጣለ ቢሆንም ዕቅዱን ማሳካት አለመቻሉ ይታያል፡፡

### 4.1.3. ክህሎትና ቴክኖሎጅ ልማት አፈፃፀም

የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ጥራት ከሚወስኑ ጉዳዮች አንዱ ጥራት ያለው የሙያ ደረጃ በኢንዱስትሪው ባለቤትነት እንዲዘጋጅ ማድረግ ሲሆን በዚህም የጥ/አ/ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ አግኝተው ብቃታቸው በምዘና እንዲረጋገጥ ማድረግ የክልሉ ዕቅድ 8,390 ክንውን 392 አፈፃፀም 5.51% ብቻ ነው።

ኮሌጆች ባልተዳረሱባቸው አካባቢዎች ላይ 3 አዳዲስ የስልጠና ማዕከላትን ተደራሽ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል።

የቴክኖሎጂዎች የጥራት ደረጃ መለኪያ አሰራር ማዘጋጀትና መተግበር 5 ታቅዶ 3 ( 62.5 %) የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች (Industry Extension Leaders) በኢንድስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ማዕቀፍ ላይ ስልጠና መስጠት 98 ታቅዶ 178 ( ከ100% በላይ) ማከናወን ተችሏል። የዚህ አፈጻጸም የተሸለ መሆን ምክንያት በየ ፖሊ ቴክኒኮች የሚገኙ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ልምድ ያላቸውና ብቁ የሆኑ አሰልጣኞች በየክላስተራቸው የሚገኙ ተቋማት ውስጥ የሚገኙ አሰልጣኞችን (የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን መሪዎችን) ብቁ የሚያደርግ የአሰራር ስርዓትና ማዕቀፍ በተገቢው በማዘጋጀታቸው ሲሆን በአንጻሩም ከስልጠናው አስቀድሞ ወደ ድጋፍ መውጣትም እንደክፍተት ተወስዷል። ሰልጣኞች በትብብር ስልጠና ማሳተፉ ዕቅድ 80 ክንዉን 54 አፈፃፀም 67% በሀገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ስታንዳርድ መሰረት ግብዓት የተሟላላቸው ተቋማት 302 ታቅዶ 87 (28.9%)፣ ለትብብር ሥልጠና ማዕከልነት/መስጫነት የተባባሪነት ዕዉቅና ኢንዱስትሪዎች/ኢንተርፕራይዞች 228 ታቅዶ 150 (65%)፣ መካከለኛ 156 ታቅዶ 117 (75%)፣ አነስተኛ 72 ታቅዶ 70 (97.2%)፣ የስልጠና ፕሮግራሞች አዲት ማድረጊያ ማንዋል መከለስ 1 ታቅዶ ክንዉን 1 (100%)፣ የአጫጭርና ፕሮግራም ምዝገባ እና ዕውቅና ፍቃድ ለጠየቁ ተቋማት ግብረ መልስ መስጠት 80 ፐርሰንት ለማድረስ ታቅዶ 84.2 ከ100 በላይ መፈጸም ተችሏል።

የበቁ ኢንተርፕራይዞች 71 ለመፈጸም ታቅዶ 32 (45%)፣ በሁሉም ደረጃ በተቀዳ ቴክኖሎጂ ላይ የበቁ አንቀሳቃሽ 353 ለማከናወን ታቅዶ 115 (አፈፃፀም 32.6)፣ ለኢንተርፕራይዞች አዲስ ቴክኖሎጂ ማሸጋገር በቁጥር 30 ታቅዶ 16 (54%)፣ በአብገር ኢንተርፕራይዞች ቴክኖሎጂ ለገበያ ማቅረብ በቁጥር 148 ታቅዶ 27 (18 %)፣ በተዘጋጀ ሰነድ መሰረት በአሰልጣኞች አዲስ ቴክኖሎጂ መቅዳት 27 ታቅዶ (21 አፈፃፀሙም 77.78%)፣ በተዘጋጀ ሰነድ መሰረት በአሰልጣኞች የተቀዳ ቴክኖሎጂ ማሻሻል በቁጥር 2 ታቅዶ 8 (100%+) በላይ በሁሉም ቴክኖሎጂ ሀብት ማፍራት 6 ሚልዮን ብር ታቅዶ ክንውን 0.99 ሚልዮን ብር ሃብት

ማፍራት የተቻለ ሲሆን የአፈጻጸሙም ዝቅተኛ መሆን ዋንኛ ምክንያት የፈሩ ሃብቶች ሲለኩ የሃብት ልኬት ዘዴዎችን በአግባቡ ያልተከተለና በአብዛኛው ግምታዊ አሰራሮችን የተከተለ መሆኑ ትኩረት የሚያሻው ነው።

ተቋማት ከውጭ አገርና ከሀገር ዉስጥ ተቋማት ጋራ ትስስርና አጋርነት እንዲፈጥሩ ማድረግ በቁጥር፣ ዕቅድ 10 ክንዉን 3 አፈፃፀም 31.25% የቴክኖሎጂና የፈጠራ ውጤቶች ላይ አውደ ርዕይና የውይይት መድረኮች ማዘጋጀት በቁጥር፣ ዕቅድ 5 ክንዉን 2 አፈፃፀም 41.67% ከባለድርሻ አካላት ጋር ተዘጋጅቶ ተግባራዊ የተደረገ የስልጠና የመግባቢያ ሰነድ ዕቅድ 16 ክንዉን 14 አፈፃፀም 90% ማከናወን ተችሏል።

ተቋማት የICT መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው ማድረግ 5 ታቅዶ 18 (360%)፣ ደረጃውን የጠበቀ እና የተሟላ የደህንነት መጠበቂያ ያላቸው የማሰልጠኛ ወርክሾፖች ሟሟላት 12 ታቅዶ (25%)

ለ100 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ዕድሳት እና የቁጥጥር ስራ መስራት ታቅዶ 22 (22%)፣ በኢኮቴ ዘርፍ የተሰማሩ ለ25 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ፣ ፈቃድና ዕድሳት ቁጥጥር ስራ ለመስራት ታቅዶ 19 (76%) ተከናውኗል።

የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክህሎትና ግንዛቤ (ዲጂታል ሊትራሲ) ስልጠና የመንግስት ሠራተኞች፣ ሴቶችና ወጣቶች መስጠት 200 ታቅዶ 30 (15%)፣ የገጠር ሽቦ አልባ ስልኮች ተጠግነው ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግና የመረጃ ክትትል ማድረግ 65 ታቅዶ ክንውን 39 (60%) ተከናውኗል።

### 4.1.4. የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች የልማት ተሳትፎና ተጠቃሚነት አፈጻጸም

**የሴቶች ዘርፍ፡-**

የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ሴቶችንና ህጻናትን ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ለማዳን በተሰራው የግንዛቤ ሥራ 374,391 (48%) የህብረተሰብ ክፍሎችን ማሳተፍ የተቻለ ቢሆንም ካለዉ የሕዝብ ቁጥር አንጻር አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው። ሴቶች ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸትና ግንዛቤያዎችን በማሳደግ በተሰራው 397,146 (78%)

የህብረተሰብ ክፍሎችን ማሳተፍ ተችሏል። 312,897 (64%) ሴቶችን ስለመደራጀት ጠቀሜታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተሰርቷል። አፈጻጸሙ የተሻለ ቢሆንም በክልላችን መደራጀት ከሚገባቸው ሴቶች ቁጥር አንጻር ሰፊ ቀሪ ስራዎች እንዳሉ ያመላክታል።

የሴቶችን የኢኮኖሚ አቅም ከማሳደግ አንጻር ለሴቶች በተፈጠረላቸው የተለያዩ የግንዛቤ ሥራዎች 236,237 ሴቶች በተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ብር 23,623,700 (60%) ማስቆጠብ የተቻለ ሲሆን መቆጠብ ከጀመሩት 42,625 ሴቶች በተለያየ የገቢ ማስገኛ የሥራ መስኮች በመሰማራት ብር 350,643 የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል።

እንዲሁም የሴቶችን የመሬት ተጠቃሚነት መብት ከማረጋገጥ አንጻር 25,650 (10,300 እማወራ እና 40,000 ባልና ሚስት በጥምር) ሴቶች  የመሬት ባለቤትነት መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት አግኝተዋል። ከግብርና ስራ መስክ ውጪ 85,888 ሴቶች ተሰማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ተችሏል። ይሁን እንጂ በክልሉ ከሚገኙ ሴቶች ቁጥር አንጻር ገና ብዙ ቀሪ ስራዎች እንዳሉ ያሳያል። በተጨማሪም የሴቶች የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚነት ድርሻ 15 በመቶ ብቻ በመሆኑ ሴቶችን በግብርና ኤክስቴሽን አገልግሎት ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የሚያስችል ስልጠና፣ ግብአትና ቴክኖሎጂ ተደራሽ በማድረግ ረገድ ውስንነት ስላለ የሴቶችን እኩል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል። ካሉን የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች 843 የሴቶች ለብቻ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት በማደራጀት 106,500 ሴቶችን በአባልነት በማሳተፍ 5,325,000.00 ብር በማስቆጠብ ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ቢሆንም በክልሉ በገጠርና በከተማ ባሉን 843 ቀበሌዎች አንዳንድ የሴቶች ለብቻ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር ለማደራጀት ከተያዘው ግብ አንጻር ዝቅተኛ አፈጻጸም ታይቷል።

የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግ በተለያዩ ጊዜያቶች በተሰጡ የአቅም ግንባታ ስራዎችና በተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች በክልል ደረጃ የውሳኔ ሰጭነት በክልል ምክር ቤት በህግ ተርጓሚ በአስፈጻሚ አካላት እና በዞን ደረጃ ደግሞ በዞን ምክር ቤት፤ በህግ ተርጓሚ በአስፈጻሚ አካላት እንዲሁም በወረዳ ምክር ቤት፤ በህግ ተርጓሚ በአስፈጻሚ አካላት በተቀመጠው እስታንዳርድ መሠረት ተግባራዊ ያለሞሆን ችግር በስፋት ታይቶል ስለዚህ ቀጠይ በትኩረት የምሰራ ይሆናል፣ በተጨማሪም ሴቶች በልማት ቡድን ተደራጅተው በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ዘርፍ ባሉ ጉዳዩች በየጊዜው በመወያየትና ወደ ተግባር በመግባት ባሳዩት መሻሻል በቤት ውስጥም ያላቸው የውሣኔ ሰጪነት አቅም እያደገ መጥቷል።

በተለያዩ አካባቢዎች ከ140 በላይ የሆኑ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶችና ህጻናት ላይ ይፈፀማሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለእድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋ፣ በጋብቻ ላይ ጋብቻ፣ ግማ ማስፈልፈልና የነፍሰ ጡር ሴት ሆድ ማሸት በስፋት ይፈፀማሉ፡፡ ለአብነት እ.ኤ አ. በ2016 የስነ ህዝብና ጤና ጥናት መሰረት እድሜቸው 15-49 ባሉት ሴቶች ውስጥ የግርዛት ምጣኔ 65 በመቶ ነው፡፡ እንዲሁም ከ15 ዓመት በፊት የሚያገቡ ሴቶች በ2011 ከነበረበት 8 በመቶ በ2016 ወደ 6 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ በተለይም ድርጊቱ በከተማና በገጠር ሰፊ ልዩነት እንዳለ  መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የስርዓተ-ጾታ ማካተት ተቋማዊነት ከማረጋገጥ አንጻር በ2ኛው ዕ.ት.ዕ ሁሉም ሴክተሮች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን ተቋማዊ እንዲያደርጉ ለማስቻል የታቀደ ቢሆንም ማከናወን የተቻለው 22% ብቻ ሲሆን በአብዛኛዎቹ ሴክተሮች የስርዓተ ጾታ ጉዳይን በዓመታዊ ዕቅዳቸው የሚያቅዱ ቢሆንም ተግባራዊነቱን እየገመገሙና ማስተካከያ እያደረጉ ከመሄድ አንፃር ትልቅ ጉድለት ያለው ነው፡፡

**የህጻናት ዘርፍ፡-**

ህፃናት ድጋፍ፣ እንክብካቤ እና ጥበቃ አንጻር በገጠርና በከተማ ቤተሰብን ለማጠናከር የሚያስችሉ የምግብ ዋስትናና የስራ እድል ፈጠራ እንዲሁም የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ተግባራዊ በማድረግ በተደረገ ጥናት የሴት ልጅ ግርዛት 45 በመቶ፣ የህፃናት ጋብቻ 22 በመቶ እንዲቀንስ የተደረገ ሲሆን በህፃናት ጉልበት ብዝበዛ፣ ህገ ወጥ ዝውውርና በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ለመቀነስ የተለያየ ጥረቶች ቢደረጉም ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም፡፡

በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህፃናትን የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎት ለማጠናከር የማህበረሰብ አቀፍ፣ የማዋሀድና ማቀላቀል፣ የአደራ ቤተሰብ፣ የጉዲፈቻና የህፃናት ማሳደጊያ አገልግሎት ፕሮግራሞች ተቀርጸው ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን በነዚህ አማራጭ የህጻናት ድጋፍና እንክብካቤ ፕሮግራሞች 656,857 ህፃናት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

**የወጣቶች ዘርፍ፡-**

### 4.1.5. የሠራተኞና ማኅበራዊ ጉዳይ አፈጻጸም

የማህበራዊ ደህንነት ልማት ጥበቃን በማስፋፋት በችግሮች ተጠቂ የሆኑ ሰዎች የማህበራዊ ካሽ ትራንስፈር ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ቁጥር 64 ወደ 34 ለማድረግ ታቅዶ 53% ሰዎችን

የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። ለተለያዩ የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ 24,975 ዜጎች ለማህበራዊ አገልግሎት የሚሆን የገንዘብና ሌሎች ድጋፎችን በመስጠት የማህበራዊ ደህንነታቸዉን ለማረጋገጥ ታቅዶ 17,179 (69%) ዜጎች የተለያዩ ድጋፎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

ለአካል ጉዳተኞች በተሃድሶ ማዕከል የተቀናጀ አገልግሎት ከመስጠት አኳያ 1,446 አካል ጉዳተኞችን በማዕከሉ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 1,108 (77%) ዜጎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

የሥራ ክርክሮችን 100% በስምምነት ለመፍታት ወይም ዕልባት ለመስጠት ታቅዶ ከቀረቡ 802 ክርክሮች ውስጥ 680 (84%) የሥራ ክርክሮች በስምምነት በመፍታት በተከራካሪ ወገኖች መካከል የአሸናፊና ተሸናፊነትን መንፈስ በማስቀረት በአሠሪና ሠራተኛው መካከል መልካም ግንኙነት በመፍጠር በሥራ ክርክር አለአግባብ ሊባክን የነበረውን የምርት ጉልበት፣ ጊዜና ወጪ እንዲቀንስ ተደርጓል።

የሙያ ደህንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢ ጥበቃ ቁጥጥር አንጻር በ759 ድርጅቶች የሥራ ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ 532 (70%) የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር በማድረግ በልማት ድርጅቶች ውስጥ ያሉ የአፈፃፀም ችግሮችን የመለየትና የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

በ2,055 ድርጅቶች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ሥራ አመራር ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል ክትትል ለማድረግ እና የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት በታቀደው መሠረት በ1,121 (55%) ድርጅቶች ሥርዓቱን ለመዘርጋት የሚያስችላቸው ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል። 4,424 የሥራ ቦታዎችን (ድርጅቶችን) ለመመዝገብ ታቅዶ 2,540 በመከናወኑ አፈጻጸሙ 57% ነው።

በሀገር ውስጥ 157,718 ዜጎችን በሥራ እንዲሰማሩ ለማድረግ ከተያዘው ዕቅድ ውስጥ ለ143,774 (91%) ሥራ ፈላጊዎች ድጋፍ በመስጠት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል። ከውጭ ሀገር ስራ ስምሪት አንጻር በቤት አያያዝና ክብካቤ ሙያ 824 ዜጎችን፣በሀገር ውስጥ 500 በድምሩ 1,324 ዜጎችን በማሰልጠን በውጭ ሀገርና በሀገር ውስጥ ወደስራ ለማሰማራት ታቅዶ እንደየቅደም ተከተላቸው 9 (1%) እና 250 (50%) ስራ ፈላጊዎች ወደ ስራ ተሰማርተዋል። እነዚህን ዜጎች በዉጭ አገር እና በሀገር ዉስጥ የስራ ስምሪት ከመስጠት አንፃር ጉድለት ታይቷል። በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አስከፊነት ዙሪያ ለ95,504 (ሴት

47,752) የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ለመስጠት ታቅዶ 62,846 (31,423 ሴት) ግንዛቤ በመፍጠር ተችሏል።

### 4.1.6. የጤና ልማት አፈፃፀም

**የጤና አገልግሎት ሽፋን፡-**

የጤና አገልግሎት ለማህበረሰቡ ለማዳረስ በተከናወኑ ሥራዎች የጤና አገልግሎትን ለማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ባለፉት አስርት ዓመታት ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ሲሆን በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የጤና አገልግሎት ሽፋን በጤና ጣቢያ 88.6%፣ በጤና ኬላ 94%፣ በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል 30% እና በአጠቃላይ ሆስፒታል 80% ደርሷል።

**የእናቶችና ህፃናት ጤና አገልግሎት በተመለከተ**

የቅድመ- ወሊድ ምርመራ አገልግሎት አንድ ጊዜ እና ቢያንስ አራት ጊዜ ያገኙ እናቶች ሽፋን እንደ ቅደም ተከተላቸው 92% እና 62% መድረሱን ያሳያል። ሽፋኑ በዕቅድ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ከነበረው አንጻር ሲታይ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ዓመታት የተሻለ እድገት እያሳየ የነበረ ቢሆንም ባለፉት ዓመታት ከነበረው ክልላዊ ያለመረጋገት ጋር በተያያዘ የጎላ እድገት አልታየም። በሰለጠነ የጤና ባለሙያ የወለዱ እናቶች መጠን ዝቅተኛ አፈጻጸም /54%/ ማስመዝገብ ተችሏል። የእናቶች ማቆያ ቤት ግንባታ በሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች ካላቸው ጤና ተቋማት አንጻር ሽፋናቸው እኩል ባይሆንም በአሁኑ ወቅት 112 (82%) ጤና ተቋማት የእናቶች ማቆያ ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ድህረ ወሊድ አገልግሎት በተመለከተ በ48 ሰዓት ውስጥ የድህረ ወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች መጠን ባለፉት ዓመታት እየተሻሻለ የመጣ ሲሆን በመነሻው ዓመት (2008) 30.7% ከነበረበት በ2012 ወደ 72.3% እድገት አሳይቷል።

የእናቶች ሞት መጠን ከ100,000 በህይወት ከተወለዱ ህጻናት አንጻር ከ420 እናቶች በ2012 ወደ 199 ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም ወደ 401 መቀነስ ተችሏል። በክልሉ የአንድ እናት አማካይ የውልደት መጠን ብዛት ከ5.6 ወደ 4.1 የቀነሰ መሆኑን እና የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚነት /CPR/ መጠን በአራት ዕጥፍ ያህል (ከ11.9% ወደ 44.6%) ያደገ እንደሆነ ያሳያል። አንድ የገጠር እናት የመውለድ ብዛት በአማካይ 6 ከነበረበት ወደ 5.2 የቀነሰ መሆኑ የሚያበረታታ ቢሆንም በከተማ ከምትኖር እናት (2.3) በበለጠ ጊዜ የምትጸንስ መሆኑን ያሳያል። እንዲሁም ያልተማረች እና ሁለተኛ ደረጃና ከዛ በላይ በተማረች እናት

መካከል የአገልግሎት ተጠቃሚነት ልዩነት የሚታይ ሲሆን ይህም በአገልግሎት ፍትሃዊነት (Equity) ዙሪያ መሻሻል እንዳለበት ያሳያል።

በ2012 ዓ.ም ዕድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት የፔንታቫለንት 3 ክትባት ሽፋን 89% ማስመዝገብ ቢቻልም ከተያዘዉ ግብ /95%/ አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ ነዉ። በተመሳሳይ አመት መደበኛ የጤና መረጃ እንደሚያሳየው ዕድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት የኩፍኝ መከላከያ ክትባት ሽፋን 83% ሽፋን የተመዘገበ ቢሆንም ዉጤቱ ሲታይ ወደኋላ እየተመለሰ እንዳለ ያሳያል።እንዲሁም በ2012ዓ.ም ሁሉንም ክትባት ጨርሰው የወሰዱ 80% ማስመዝገብ ተችሏል።

የጨቅላ ህጻናት ሞት መጠን ከ36/1,000 ወደ 30/1,000፣ ከ1ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ከ85/1,000 ወደ 43/1,000፣ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ሞት ከ142/1000 ወደ 55/1000፣ ከእርግዝናና ወሊድ ጋር በተያያዘ የእናቶች ሞት ከ420/100,000 ወደ 401/100,000 መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን እንዲሁም እስከ አንድ ዓመት በህይወት ይኖራሉ ተብሎ ከሚገመተው ህፃናት አንጻር ከ12-59 ወራት የሆኑ ህፃናት ሞት መጠን 26/1,000 መሆኑን ያሳያል።

**ዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር**

የቲቢ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር በተመለከተ በክልሉ የቲቢ በሽታ ምርመራና ህክምና አገልግሎት ተደራሽነት ከማሳደግ አንጻር 100% ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች የመድኃኒት ክትትል አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት 78% የደረሰ መሆኑን ያሳያል። የምርመራ አገልግሎት በሁሉም ተቋማት እንዳይሰጥ የሚያደርጉ ምክንያቶች የላቦራቶሪ ባለሙያዎች እጥረት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽ ያለመሆን እና የማይክሮስኮፕ እጥረት ዋናዎቹ ናቸው። በክልላችን በየዓመቱ ከ4,669 በላይ ሰዎች በቲቢ በሽታ ሊጠቁ እንደሚችሉ ይገመታል። በ2012 ዓመተ ምህረት የቲቢ በሽታ መጠነ ልየታ የተጣለው ግብ 87% ሲሆን አፈፃፀሙ 78% ነው።

በክልሉ የወባ ሕመምተኞች በክልሉ በወባ ምክንያት የሚታመሙ መጠን 49/1000 የደረሰ ሲሆን ከተያዘው ዕቅድ (5/1000) አንጻር አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ከክልሉ የመጀመሪያው የጤና ሴክተር የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንጻር የወባ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ሥራዎች አፈጻጸም በአብዛኛው ከታቀደው በታች የተከናወኑ መሆኑን መረጃዎች አሳይተዋል። የአልጋ አጎበር ሥርጭትን በተመለከተ ወባማ በሆኑ አካባቢዎች ቢያንስ 2

የአልጋ አጎበር ያላቸው አባወራዎች በ2007 ዓ/ም ከነበረበት 56% በ2012 ወደ 100% ለማድረስ ታቅዶ 88% ማድረስ ተችሏል። የጸረ- ወባ ትንኝ ኬሚካል ርጭትን በተመለከተ በዕቅድ ዘመኑ የተረጨ አገልግሎቱ የሚገባቸው ቤቶች ሽፋንን ከ56% ወደ 100% ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም በ2012 ዓ.ም ለ80% ቤቶች ብቻ ርጭት ተከናውኗል።

የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ/ስርጭትን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንጻር የ2019 እ.አ.አ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጥናት መሰረት በክልላችን ጠቅላላ 15,724 ያህል ሰዎች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩና መጠኑም /HIV Prevalence/ 0.43% መሆኑን ያመላከተ ሲሆን አዲስ የቫይረሱ ስርጭት በሁሉም እድሜ ደረጃ 0.07% ይሆናል። ቫይረሱ በደማቸው ይኖራል ተብሎ የሚገመቱ ከ15 ዓመት እድሜ በላይ የሆኑ አዋቂ ሰዎች ላይ መጠኑ /HIV Prevalence/ በ2007 ዓ.ም ከነበረበት 0.6% ወደ 0.43% መቀነስ አሳይቷል።

የጤና ሁኔታን በተመለከተ የክልሉ የጤና ሁኔታ ሲታይ የአንድ ሰው በህይወት የመኖር እድሜ ከ64 ወደ 69 ዓመት ማድረስ የታቀደ ሲሆን በ2011 ዓ/ም አማካይ የእድሜ ጣሪያ 65.5 ዓመት ሲሆን ለሴቶች 67.3 ዓመት እና ለወንዶች ደግሞ 63.7 ዓመት መሆኑን የ2018 (እ.አ.አ) World Health Rankings ሪፖርት ያሳያል።

**የሃይጅንና የአካባቢ ጤና ማሻሻል፡-**

በመደበኛው የጤና መረጃ ሥርዓት ሪፖርት መሰረት የክልሉ የተሻሻለ መጸዳጃ ቤት ሽፋን 40.7% ሲሆን በጤና ሴክተር ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግብ 50% አንጻር ዝቅተኛ ነው። ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የወጡ ቀበሌያት ሽፋን 49.4% (የሀይጅንና አካባቢ ጤና ጎንዮሽ ሪፖርት) ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ከተቀመጠው ግብ 90% እና በመሬት ከሚታየው የአፈጻጸም ጥራት ችግር አንጻር ብዙ ስራ እንደሚቀር ለማየት ተችሏል።

# ምዕራፍ አምስት

# 5. የህዝብ አገልግሎት፣ ፍትህና መልካም አስተዳደር አፈጻጸም

## 5.1. የፍትህ ዘርፍ አፈጻጸም

### 5.1.1. ፍትህ ስራዎች ልማት አፈፃፀም

**የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች አፈጻጸም፡-**

የወንጀል መዛግብት የማጥራት ምጣኔን 99% ለማድረስ ታቅዶ የማጥራት ምጣኔን 92.3% ማድረስ ተችሏል፡፡ በመደበኛ ፍ/ቤት የተደረጉ የቀጥታ/መደበኛ ክስ ክርክሮች የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በማሰጠት የመንጠባጠብ ምጣኔ በአማካይ በ2.25% ለመቀነስ ታቅዶ 2.8% ለማድረስ ተችሏል፡፡ በዐቃቤ ህግ ይግባኝ የሚጠይቅባቸው መዝገቦች ውጤታማነት በአማካይ 95% ለማድረስ ታቅዶ 94% ማድረስ ተችሏል፡፡ በተከሳሽ የሚጠየቁ የይግባኝ ጉዳዮች የማፀናት አቅም በአማካይ 94% ለማድረስ ታቅዶ 90% ማድረስ ተችሏል፡፡

**የልዩ ልዩ ወንጀሎች የክልል ሰበር ጉዳዮች ክርክርና ክትትል ስራን በተመለከተ፣**

ዐቃቤ ህግ ሰበር የሚጠይቅባቸው መዝገቦች ውጤታማነት በአማካይ 87.6% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 67.2% ደርሷል፡፡ በተከሳሽ የሚጠየቁ የሰበር ጉዳዮች አለአግባብ እንዳይሻሩ የማፀናት አቅም በአማካይ 94% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙን 91.9% ማድረስ ተችሏል፡፡

**የፌደራል ሰበር ጉዳዮችን በተመለከተ፡-**

በዐቃቤ ህግ ሰበር የሚጠየቁ የሰበር ጉዳዮች የማስወሰን አቅም በአማካይ 90.2% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙን 76.3% ማድረስ ተችሏል፡፡ በተከሳሽ ሰበር የሚጠየቁ የሰበር ጉዳዮች የማፀናት አቅም በአማካይ 94% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 95.2% ማድረስ ተችሏል፡፡

**ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን በተመለከተ፡-**

ልዩ ትኩረት የሚሹ የህ/ሰብ ክፍሎች ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች የማጥራት ምጣኔ በዕቅድ ዘመኑ በአማካይ 99% ለማድረስ ታቅዶ  99.2% ማድረስ ተችሏል፡፡

**በቀላል ወንጀሎች የዕርቅ ስርዓትን አፈጻጸም በተመለከተ፡-**

የህዝብና የመንግሥት ጥቅም የማይነኩ ቀላል ወንጀሎች 95% በዕርቅ እንዲያልቁ ለማድረግ ታቅዶ 93% በዕርቅ እንዲያልቁ በማድረግ ተጎጂዎችን እንዲካሱ ተደርጓል፡፡

**የሙስና ወንጀል መዝገቦች አፈጻጸም፡-**

የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች ላይ ተጣርቶ የቀረበ መዝገቦች ክስ በመመስረት የሙስና ምርመራ መዝገቦች የማጥራት ምጣኔ 80% ማድረስ ተችሏል፡፡

**የታክስ ነክ ወንጀሎች አፈጻጸም በተመለከተ፡-**

የታክስ/ግብር/ ማጭበርበር ወንጀል ተገቢውን ምርመራ በማጣራት፣ ክስ በመመስረትና ውሳኔ በማሰጠት የማጥራት ምጣኔን በዕቅድ ዘመኑ በአማካኝ 95.6% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙን 92.42% ማድረስ ተችሏል፡፡

በታክስ ነክ ወንጀሎች ላይ ክስ በመመስረትና ክርክር በማድረግ የማስቀጣት ምጣኔ 96.4% ለማድረስ ታቅዶ 99% ማድረስ የተቻለ ሲሆን የመቋረጥ ምጣኔን ደግሞ ወደ 0.96% ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡ የዐቃቤ ህግ የይግባኝ መዝገቦች በአማካኝ 90.6% ውጤታማ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙ 97.5% ደርሷል፡፡ በተከሳሽ የሚጠየቁ የይግባኝ ጉዳዮች 94.3% ለማፀናት

ታቅዶ አፈጻጸሙን 97% ለማድረስ ተችሏል። የዐቃቤ ህግ የሰበር መዝገቦች በአማካኝ 90.2% ውጤታማ ለማድረግ ታቅዶ አፈጻጸሙን 87.8% ማድረስ ተችሏል። በተከሳሽ የሚጠየቁ የሰበር ጉዳዮች 94% ለማፀናት ታቅዶ አፈጻጸሙን 100% ማሳካት ተችሏል። የታክስ ነክ ፍትሐብሔር ጉዳዮች የማስወሰን አቅም 97% ለማድረስ ታቅዶ 99.6% ማድረስ ተችሏል።

**የፍትሐብሄር አስ/ር ጉዳዮች አፈጻጸም በተመለከተ፡-**

የማጥራት ምጣኔን 84.80% ማድረስ ተችሏል። የማስወሰን አቅም በአማካይ 63.53% ለማድረስ ታቅዶ 84.88% ማድረስ ተችላል።

**የህግ ማርቀቅ ስራን በተመለከተ፡-**

ከሚመለከተው የመንግስት ተቋማት የህግ ይረቀቅልኝ ጥያቄ የቀረቡ 2 መመሪያዎች ላይ አስተያየት ወይም የመጀመሪያ ረቂቅ በማዘጋጀት፣ በማረምና የህግ ቅርጽ በማስያዝ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ስራ ተሰርቷል።

**የጠበቆች፣ ሲቪክ ማህበራትና ሰነዶች ምዝገባ አፈጻጸም**

**የጠበቆች አስተዳደርን በተመለከተ፡-**

የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ በዕቅድ ዘመኑ 53 የህግ ባለሙያዎች የአንደኛ ደረጃ እንዲሁም 3 የሁለተኛ ደረጃ በድምሩ 56 ጠበቆች ተገቢውን መስፈርት ማሟላታቸው በማረጋገጥ የጥብቅና ፍቃድ እንዲሰጣቸው ተደርጓል። የጥብቅና ፈቃድ ዕድሳትን በተመለከተ ከተቋሙ የጥብቅና ፈቃድ ከወሰዱ 56 ጠበቆች መካከል 56ቱም ጠበቆች ወቅቱን ጠብቀው ፈቃዳቸው አሳድሰዋል።

በጠበቆች ላይ የሚቀርቡ የድስፕሊን ጉዳዮችን በተመለከተ በጠበቆች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በማጣራት ምላሽ ከመስጠት አንጻር በዕቅድ ዘመኑ 20 አቤቱታዎች ቀርበው 15ቱ የማያስከስሱ በመሆኑ እንዲዘጉ የተደረገ ሲሆን በ5 መዝገቦች ላይ ክስ በመመስረት ለጠበቆች ዲስፕሊን ጉባዔ ቀርቦ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቷል። በዚህም መሰረት በሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ 95% አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ታቅዶ አፈጻጸሙ 100% ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባዔ 95% ውሳኔ ለመስጠት አቅዶ 100% ደርሷል።

**የሲቪክ ማህበራት ፈቃድ አሰጣጥንና ዕድሳት በተመለከተ፡-**

ተቋሙ በዕቅድ ዘመኑ ለ62 ማህበራት የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሰጠ ሲሆን ሁሉም ፍቃዳቸውን አሳድሰዋል፡፡

### 5.1.2. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ስራዎች ልማት አፈፃፀም

**የክልሉ ፍርድ ቤቶችን ቅልጥፍና ማሳደግን በተመለከተ፡-**

በ2ኛው የዕ/ት/ዕ/ዘመን መጀመሪያ 57,947 የክርክር መዝገብ ለመቀበል ታቅዶ 56,148 (96.89%) መዝገብ ተቀብሎ መክፈት እንደተቻለ ሲያመለክት በጂቲፒ2 መጨረሻ ማጠናቀቂያ ወቅት ጠቅላላ ይከፈታል ተብሎ ከታቀደው 325,642 መዛግብት ዉስጥ 267,267 በመክፈት 82.07% አፈጻጸም ማስመዝገብ እንደተቻለ ያመለክታል፡፡

**የመወሰን አቅም አፈፃፀም፡-**

በክልላችን ፍርድ ቤቶች በ2ኛው የዕ/ት/ዕ/ መጀመሪያ ዓመት 2008 ላይ ከቀረቡት 17,220 የወንጀልና 38,714 የፍትሐብሔር በድምሩ 55,934 መዛግብት ውስጥ 16,487 የወንጀልና 37,297 ፍትሐብሔር በድምሩ 53,784 (96.15%) መዛግብት ላይ መወሰን የተቻለ ሲሆን በ262,991 መዝገቦች ላይ ዉሳኔ ለመወሰን ታቅዶ በ244,605 (93%) ላይ ዉሳኔ መስጠት ተችሏል፡፡

**የማጣራት አቅም አፈፃፀም፡-**

በትራንስፎርሜሽኑ መጨረሻም በድምሩ 253,638 መዝገቦች ላይ ዉሳኔ በመስጠት የማጣራት አቅምን 100.4% ለማድረስ ታቅዶ በድምሩ 248,983 (98.9%) ላይ ዉሳኔ ተሰቷል፡፡

**የፋይሎች መጨናነቅን በመቀነስ ረገድ የነበሩ አፈፃፀሞች፡-**

በትራንስፎርሜሽኑ መጨረሻም በድምሩ ከቀረቡት 262,978 መዝገቦች ዉስጥ በ 251,059ኙ ላይ ዉሳኔ በመስጠት የመዛግብት መጨናነቅን ወደ 0.9% ማዉረድ የተቻለ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ለመድረስ የተጣለዉን ወደ 1% ዝቅ የማድረግ ግብን ማሳካት ተሏል፡፡

**ፍትህ በሁለት ወር የመስጠት አቅም አፈፃፀም፡-**

በ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጀመሪያ 96.37% መዛግብት በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ የተሰጠባቸዉ ሲሆን በትራንስፎርሜሽኑ የዕቅድ ዘመን መጨረሻ ዉሳኔ ካገኙት 248,157 መዝገቦች ዉስጥ 231,442ቱ ወይም 93.3% በሁለት ወር ዉሳኔ ያገኙ መሆናቸዉ ሲታይ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

**የዳኛ መዝገብ ጥምርታ አፈፃፀም፡-**

በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ ደግሞ አንድ ዳኛ በበጀት ዓመቱ ውስጥ 300 መዝገቦች ላይ ውሳኔ አንደሚሰጥና በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ችሎት ደረጃ አንድ ዳኛ በዓመት ሁለት መቶ /200 መዝገቦች ላይ እንደሚወስን ታሳቢ ተደርጓል። ከዚህ አንጻር በትራንስፎርሜሽኑ የመጀመሪያ ዓመት በ2008 በየደረጃዉ የዳኝነት አገልግሎት ድምር አማካይ የዳኛ መዝገብ ጥምርታ ሲታይ አንድ ዳኛ በአማካይ 310 መዛግብት ላይ ውሳኔ መስጠቱን መመልከት የተቻለ ሲሆን በትራንሰፎርሜሽኑ የዕቅድ ዘመን መጨረሻ አንድ ዳኛ በአማካይ 213 መዝገቦች ላይ ዉሳኔ ሰጥቷል።

**የተገልጋይ እርካታ ማሳደግን በተመለከተ፡-**

በዕቅድ ዘመኑ መጀመሪያ 81% ከነበረበት በ2ኛዉ ትራንስፎርሜሽኑ የዕቅድ ዘመን መጨረሻ አፈፃፀሙ ወደ 83% ያመላክታል።

## 5.2. የሕዝብ አገልግሎትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ

### 5.2.1. የክልሉ ምክር ቤት አፈፃፀም

### 5.2.2. ፕቢሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት

የማስፈጸም አቅም ግንባታ የትኩረት መስክ፡- በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት ተቋማት የለውጥን አሰራር ስርዓቶች ትግበራ በማሳለጥ አገልግሎት በስታንዳርድ መሠረት እንዲሰጡና የተለመደ ተቋማዊ አሠራር እንዲያደርጉ የታቀደ ቢሆንም በስታንዳርድ አገልግሎት ከመስጠት አንጻር ክፍተት እንደሚታይ ተገምግሟል። የውጤት ተኮር ዕቅድ የአሠራር ሥርዓት በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት ተቋማት ስታንዳርዱን ጠብቆ እንዲተገበር፤ የሥልጠና ሰነድ ማዘጋጀት፣ ሥልጠና በመስጠት ሥርዓቱ የተሟላ የሥራ አመራር፣ የመለኪያ እና የግንኙነት መሳሪያ እንዲሆን እና የተቋማትን የዕቅድ አፈፃፀም ውጤታማነት ለማረጋገጥ አመራርና ፈፃሚዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ሥራ ተሰርቷል።

በአፈጻጸም ውጤት ላይ ተመስርቶ ለፈፃሚዎች ዕውቅና የተሰጠ ቢሆንም ከ2010 በጀት ዓመት ወዲህ በተፈጠረው ሀገራዊና ክልላዊ ነባራዊ ያለመረጋጋት ሁኔታዎች የተነሳ የዕውቅና አሰጣጡ ተቋርጦ ቆይቷል። በመሆኑም በቀጣይ ስትራቴጂክ ዘመን የአፈፃፀም ስራ አመራር ስርዓትን በማጠናከር የፈጻሚ፣ የስራ ክፍልንና የተቋምን አፈፃፀም የሚመጋገብበትንና የሚተሳሰሩበትን አግባብ በህግ ማዕቀፍ እንዲመራ ማድረግ ያስፈልጋል።

የመንግስት ተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥና ዕቅድ አፈጻጸምን ለማሻሻል ነባር አደረጃጀቶችን በመከለስና አዳዲስ አደረጃጀቶችን በመቅረጽ ተቋሟዊ ለውጥ ማምጣት በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ /ቢፒአር/ ጽንሰ ሀሳብ ላይ ለበርካታ ጊዜ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ከለውጥ ሠራዊት ግንባታ የአሰራር ስርዓት ዝርጋታና አተገባበር አንፃር በጥቂት ተቋማት ካልሆነ በስተቀር በአብዛኛው ተቋማት በሞዴልነትና በግንባር ቀደምትነት ሊፈረጁ የሚችሉ ተቋማት፣ አደረጃጀቶች እንዲሁም ፈፃሚዎች በሚፈለገው ልክ ተፈጥሯል ማለት አያስደፍርም፡፡

**የሰው ሀብት ስራ አመራር ልማት አንፃር፡-**

መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 47/94ን በአዋጅ ቁጥር 175/2011 በመተካት ሥራ ላይ እንዲውል መደረጉ፣ አዋጁን ተከትሎ የምልመላና መረጣ መመሪያና ማወዳደሪያ መሥፈርት፣ የክልሉ መንግሥት ሠራተኞች የዲስፕሊን መመሪያና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ፣ የክልሉ መንግሥት ሠራተኞች የድልድል አፈጻጸም መመሪያ፣ የመንግሥት ሠራተኞች የደንብ ልብስና የስራ መሣሪያ ዝግጅትና አሰጣት መመሪያ፣ የሰው ሀብት ልማት አፈጻጸም መመሪያ፣ የዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሥራ ሥምሪትና ምደባ መመሪያ፣ የክልሉ መንግሥት ሠራተኞች የሥራ ምዘና፣ ደረጃ ምደባና የደመወዝ ስኬል ደንብ፣ የመንግሥት ተሿሚዎች የሥራ ምደባና ጥቅማ ጥቅም ደንብ፣ ከኃላፊነት ተነስተው ወደ ሲቪል ሰርቪስ መደብ የሚመደቡ ኃላፊዎች የስራ ምደባና የደመወዝ አከፋፈል ሁኔታ የሚወስን ደንብ እና ወጣት ምሩቃንን በሰቪል ሰርቪስ የሥራ መደቦች በታሳቢ ስለሚቀጠሩበት ሁኔታ በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡

የሰው ሀብት ልማትና ስራ አመራር ብቃትን ከማሳደግ አንጻር የሰው ሀብት ልማት ስራዎችን ለመምራት የሚያስችል መመሪያና ማኑዋል የማዘጋጀትና የማስጸደቅ፣ የአፈፃፀም ክፍተት ዳሰሳ ጥናት የማድረግና ፍላጎት የመለየት ስራ ተከናውኗል፡፡ በዚህም መሠረት የክልሉን አቅም ለማሳደግ በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲና በሌሎች የውጭና የውስጥ ሀገር ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለአመራሩና ባለሙያ የሚሰጡ የትምህርት ዕድሎችን በማስተባበር 100% የዕድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ልዩ ትኩረት የሚሹ አካላትን በተመለከተ የሴት የመንግሥት አመራሮችን አቅም ለመገንባት በክልሉ በሚመደብ በጀት በሦስት ዙር የረጅም ጊዜ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከአርብቶ አደሮች አካባቢ አመራሮች 35 ታቅዶ 27ቱ የረጅም ጊዜ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ የቀበሌ ስራ አስኪያጆች

በመጀመሪያ ዲግሪ ለማስተማር 200 ታቅዶ 266ቱ የረጅም ጊዜ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የቅሬታና ይግባኝ ውሳኔዎችን ጥራትና ቅልጣፌ ከማሻሻል አንጻር ይግባኝ ውሳኔ አሰጣጥ በአስተዳደር ፍርድ ቤት ፍትሐዊ ውሳኔ መስጠትና ማስፈፀም፣ በይግባኝ አቀራረብና ውሣኔ አሰጣጥ ላይ የሥልጠናና የምክር አገልግሎት የመስጠት ሥራ ተከናውኗል፡፡ በሰው ሃብት ህጎች የክስና የይግባኝ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ደንብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቶ ስላልወረደ ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም፡፡

የአስተዳደር ፍርድ ቤትን አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምድብ ችሎት ባሉባቸው ሦስት ከተሞች ላይ ምድብ ችሎት ተቋቁሞ አገልግሎት እየሰጠ ቢሆንም ከጥራትና ከህግ ባለሙያዎች አንፃር ሰፊ ክፍተት መኖሩን ግምገማዎች ያመላክታሉ፡፡

የክፍያና የጥቅማ ጥቅም ስርዓት ማሻሻልን በተመለከተ ከሥራ ልዩ ባህርይ አንጻር ልዩ ጥቅማጥሞች የሚያስፈልጋቸው የሥራ መደቦችና የተሿሚዎች ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች በሚመለከተው አካል በቀረቡት ጥያቄዎች መነሻ ጥናት ተደርጎ የውሳኔ ሀሳብና አስተያየት የማቅረብ ሥራ ተከናውኗል፡፡

የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ማጠናከር በተመለከተ በነባሩ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሰሳሰን እና የነጥብ ሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ዘዴ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር በነባር አደረጃጀቶች ማሻሻያና በአዲስ አደረጃጀቶች ምክንያት የተፈጠሩ የሥራ መደቦች ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥያቄዎች 100 ፐርሰንት ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

ተቋማት በሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን የተፈቀዱላቸውን የሥራ መደቦች ደረጃና የክፍያ ሥርዓት በአግባቡ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የዴስክ ኦዲት ሥራ ተደርጎ ያለአግባብ የተፈጸሙትን የማረም ሥራ የተከናወነ ቢሆንም አንዳንድ ተቋማት ከአሰራር ሥርዓት ውጭ ለደረጃው ከተፈቀደ ክፍያ በላይ የሚከፍሉና በአንድ መደብ ደርበው በመመደብ የመንግስት ሀብት ያለ አግባብ የማባከንና የተሰጣቸውን ግብረ-መልስ ያለመቀበል ችግር የተስተዋለ በመሆኑ በቀጣይ የዴስክ ኦዲት ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ይሆናል፡፡

የሰው ሃብት ስራ አመራር ትግበራ ህጋዊነትን ለማረጋገጥ በመንግስት ተቋማት በመደበኛና ልዩ ምርመራ ኢንስፔክሽን በማድረግ ያለአግባብ የተፈጸሙ የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት ሥራዎች በግኝቱ መሰረት የእርምት ዕርምጃ የተወሰደ ቢሆንም አንዳንድ ተቋማት በተሰጣቸው ግብረ-መልስ መሰረት ተቀብሎ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ክፍተቶች ታይቷል፡፡

ሀሰተኛ የትምህርት፣ የሥራ ልምድና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃዎች ትክክለኛነት ከማረጋገጥ አንጻር የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግና በማጣራት እርምጃ የተወሰደ ቢሆንም አሁንም ከችግሩ መላቀቅ ባለመቻሉ በቀጣይም በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡
የመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የአሰራ ግድፈት ጥቆማዎችና ቅሬታዎችን በማጣራት የማስተካከያ ውሳኔዎች የተሰጡ ቢሆንም ተቋማት በውሳኔ መሰረት ከመተግበር አንጻር ችግሮች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
የመረጃ አያያዝና አቅርቦትን ማሻሻልን በተመለከተ የመንግስት ሰራተኞችን መረጃ በዘመናዊ የመረጃ ቋት ማደራጀትና ማጠናከር፣ ስታትስቲካል አብስትራክት ማዘጋጀት፣ የፔርሶኔል ፋይሎች በላተራል ፋይሊንግ ካቢኔት ማደራጀት፣ ለተገልጋይ በሚመችና በሚፈለገው መልኩ መረጃ ማቅረብ፣ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም የአሰራር ሥርዓት መዘርጋትና የማስተግበር ሥራ ተከናውኗል፡፡
የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ሥርዓት ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ በክልሉ 11,055 የሰው ሀብት መረጃ ኢንኮድ ለማድረግ የተቻለ ቢሆንም በስትራቴጂክ ዘመኑ በተከሰቱ የተለያዩ ችግሮች ምክንያት በሚፈለገው ደረጃ ለመተግበርና ወደ ትግበራ በገቡ 44 ተቋማት ላይ ትግበራን በአግባቡ ለመምራት አልተቻለም፡፡

**የመልካም አስተዳደር አፈፃፀም በተመለከተ፡-**

የመልካም አስተዳደር የትኩረት መስክ የህዝብ ተጠቃሚነትን፣ እርካታና አመኔታን ለማረጋገጥና ዘለቄታ እንዲኖረው ለማድረግ በባለቤትነት የሚመራና ባለድርሻ ሆኖ አፈጻጸምን የሚገመግም የህዝብ ክንፍ አደረጃጀት የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ለሚመለከታቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ የተሰሩ ቢሆንምከህዝብ ተጠቃሚነት፣ እርካታና አመኔታ አንጻር የተፈለገውን ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት አልተቻለም፡፡

**የህዝብ ክንፍ ተሳትፎን ከማሳደግ አንጻር፡-**

በሁሉም የአስተዳደር እርከን ተቋማት የህዝብ ክንፎቻቸዉን በመለየትና አቅም በመገንባት በዕቅድ ዝግጅትና በአፈጻጸም ግምገማ፣ በተቋም አፈጻጸም ምዘና በየተቋሙ በሚካሄዱ የአውደ ጥናት መድረኮች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ የህዝብ ክንፍ አደረጃጀቶች የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ከመፍታት አንፃር የራሳቸውን ሚና እንዲወጡ ቢደረግም የሚፈለገው ውጤት አልተመዘገበም፡፡

በየተቋማቱ የመልካም አስተዳደር ችግር መፍቻና ማምከኛ ስትራቴጂ መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ በተመለከተ በሁሉም ተቋማት የመልካም አስተዳደር ችግሮች ላይ የማምከኛ ስትራቴጂ የመቅረጽ ስራ የተሰራ ቢሆንም የተሻለ አፈፃፀም መለየት፣ መቀመርና የማስፋት ስራ አልተከናወነም፡፡ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እየጨመሩ በመሆኑ በመንግስት ተቋማት በሚሰጡ አገልግሎቶች ህብረተሰቡ እየተማረረ መሆኑን በገለልተኛ አካላት የተደረጉ ጥናቶች አመላክተዋል፡፡

### 5.2.3. የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች አፈፃፀም

በህትመት ሚዲያ የተከናወኑ ተግባራት በሚመለከት በ8ቱ ዕትም መጽሔት 10,000 ኮፒ፣ በ40 ዕትም የዜና መጽሔት 10,400 ኮፒ፣ በ120 ዕትም በራሪ/ብሮሸር ጽሁፍ በ108,000 ኮፒ፣ በ5ቱ ዕትም ካሌንደር በ5,000 ኮፒ እና 600 የትርጉም ስራዎችን ለማከናወን ተችሏል፡፡ መሠረታዊና በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ለክልሉ ሕብረተሰብ የተሟላ ኢንፎርሜሽን ለመስጠትና ያገኘውን ኢንፎርሜሽን ተጠቅሞ በአካባቢው፣ በአገሩ ጉዳይ ላይ ያለውን ተሣትፎ ለማጎልበት ስባል 16,500 የሬዲዮ ዜናዎች፣ 9,200 የሬድዮ ኘሮግራሞች፣ 516 የቴሌቪዥን ዜናዎች እና 150 የቴሌቪዥን ኘሮግራሞች ተዘጋጅተው በአካባቢ በኤፍ.ኤሞችና ሬዲዮ፣ በደቡብ ቴሌቪዥን ኘሮግራም እንዲሁም በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ለማሰራጨት ተችሏል፡፡
መንግሥት የሚያወጣቸውን የልማት ዕቅዶችን፣ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የመልካም አስተዳደር ፖሊሲዎችን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ ብሎም በአፈጻጸም ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት እንዲቻል 60 የልማት ሥራ ጉብኝቶች ተካሂደዋል፡፡ በሌላ በኩል በክልል ደረጃ ሕዝብና መንግሥትን ገጽ-ለገጽ የሚያገናኝ 16 የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት በልማት ዕቅዶችና አፈጻጸሞች፣ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ የማስጨበጥ ተግባር ተከናውኗል፡፡

ሕብረተሰቡ በዞኑ በመካሄድ ላይ ያሉ የልማት እንቅስቃሴዎችን በግልጽ እንዲገነዘባቸው በማድረግ ለቀጣይ ሥራ እንዲነሳሳና ለብሔራዊ መግባባት አይነተኛ መድረክ ለመፍጠር በልማት፣ በሠላምና በዴሞክራሲ ርዕሰ - ጉዳዮች ዙሪያ የፎቶግራፍ ኤግዚቢሽን ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት 32 የአዳራሽ፣ 300 የመስኮት እና 32 የአልበም የፎቶግራፍ ኤግዚቢሽኖች ተዘጋጅተው ለሕዝብ እይታ ውሏል፡፡

የሕዝብ ድምጽ በመንግሥት ዘንድ ተደማጭ እንዲሆን መንግሥትም አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ እንዲችል በአገራዊ እና በክልላዊ እንድሁም ዞናዊ ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ፣ በመልካም አስተዳደር፣ በመሰረተ ልማት፣ በማዳበሪያ ስርጭት፣ በመንግሥት ምሥረታ፣ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ፣ በኑሮ ውድነት፣ በሊዝ አዋጅና በመሣሰሉት ዙሪያ በዞኑ ከሚገኙ ወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደርና ሴክተር መ/ቤቶች በየዕለቱ የሕዝብ አስተያየት በአካል፣ በስልክና በፋክስ እየተሰበሰበና እየተጠናቀረ አገራዊ ጉዳዮችን ለክልል መንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ዞናዊ ጉዳዮችን ደግሞ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# 6. የሰላም ግንባታ አፈጻጸም

## 6.1. የሰላም ግንባታ አፈጻጸም

ክልሉ ውስጥና አጎራባች በሆኑ ክልሎች እና ዞኖች ተዋሳኝ ድንበር አከባቢዎች በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ግጭቶች የመከላከል ሲከሰቱም የመፍተት ስራዎችን በማከናወን በክልሉ ሰላምና ፀጥታ እንዲሰፍን የማድረግ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና የፀጥታ ስጋት መረጃዎች ቀድሞ በማግኘት አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የሁኔታ መከታተያ ክፍል እንዲዘጋጁ በማድረግ የክስተት፣ የሁኔታና የአመላካች

እንዲሁም የፀጥታ ስጋት መረጃዎችን ቀድሞ በመሰብሰብ፣ በመተንተንና በማደራጀት በአፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ በማድረግ ጉዳቶች እንዲቀንሱ ተደርገዋል፡፡

በክልሉ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ህብረተሰቡ በሠላም አብሮ የመኖር እሴት እንዲጎልበት ተከታታይነት ያላቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ የስልጠና መድረኮች በመጠቀም የሰላም እሴት ግንዛቤ ውይይቶችን ተደራሽ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከዚህም የተነሳ በህብረተሰቡ ውስጥ በተለይም ከመዋቅርና ከመልካም አስተዳደር፣ ጥያቄዎች መነሻ በተደጋጋሚነት ሲከሰቱ የነበሩ የፀጥታ ችግሮች የሰው ሞት አካል መጉደል የንብረት መውደም የሰዎች መፈናቀል ያስከተለ ቢሆንም ማህበረሰብ ክፍሎችና ባለድርሻ አካላት በቅንጅት የከፋ ጉዳት ዳግም እንዳይከሰት ጥረት ተደርጓል፡፡

ህብረተሰቡ በያለበት ግጭቶችን በመፍታት እና በመከላከል ተሳትፎ እንዲኖረው በቀበሌያት እና በየደረጃው ባሉ የትምህርት ተቋማት የሰላም ደረጃጀቶች እንዲቋቋሙ በመደገፍና በማጠናከር የሰላም ግንባታ ስራ በአደረጃጀት የተደገፈ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በሃይማኖትና እምነት ተቋማትና ተከታዮቻቸው መካከል የአብሮነት፣ የመከባበርና የመቻቻል እሴት ግንባታን ለማጎልበት የሚያስችሉ ሀገራዊ፤ ክልላዊና አካባቢያዊ ወቅታዊ ሁኔታዎችን መሠረት ባደረገ መልኩ በየደረጃው ለሚገኙ አስፈፃሚና ፈፃሚ አካላት፣ ለሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ መሪዎች፣ ለቤተ-እምነት መሪዎች ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ለመስጠት ተችሏል፡፡ በተለይም ሀገራዊ ለውጡን ምክንያት በማድረግ በክልላችን በአብዛኛው አካባቢዎች በሃይማኖት ሽፋን በተከሰቱ የፀጥታ ችግሮች መነሻ በየደረጃው የሚገኙ የሃይማኖት አባቶችና የአካባቢ ሽማግሌዎች ባደረጉት ሰፊ ትግል በሃይማኖት ተቋማትና ተከታዮቻቸው መካከል የሚፈጠረውን አለመግባባትና ግጭት በእርቅና በተለያዩ ባህላዊ ዜዴዎች በሰላማዊ መንገድ በመፍታት ወደ ቀድሞ አብሮነትና መከባበር እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የሀይማኖት ተቋማትን የመመዝገብና ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን ለፌዴራል የተሰጠ ተግባር ቢሆንም በየደረጃው ያለ መዋቅር ፌዴራል ባወጣው መመሪያ መሠረት የሚያቀርቡትን መረጃ በማጣራትና በማስተላለፍ ፈቃድ እንዲያወጡና እንዲመዘገቡ ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

# 7.የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ አፈጻጸም

## 7.1. የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ሥራዎች አፈፃፀም

የአካባቢ ደህንነት መብቶች፣ የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃና ተጠቃሚነት የሚረጋገጥባቸውን ስርዓቶች በነባሩ ክልል በማዘጋጀት መከበራቸውን በማረጋገጥ ረገድ የአካባቢና የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አሳታፊና ያልተማከሉ የአካባቢ መንከባከቢያ ሥርዓቶች እንዲዘጋጁ ተደርጓል። በሀገራችን የኢንዱስትሪና የከተሞች መስፋፋትና የኑሮ ለውጥን ተከትሎ እየመጣ ያለውን የአካባቢ ሃብቶች ብክነትና ብክለት በተገቢው ሁኔታ ለመከላከል በ16 ከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ የተደረገ ሲሆን

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ህግ ተከባሪነት ክትትልና ቁጥጥር ስራ ተሰርቷል። የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ተግባራትን በማስተባበር፣ በመደገፍና በመፈጸም ለአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን የሚቋቋም ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የተያዘውን ግብ ለማሳካት በአቅም ግንባታ፣ በአሠራር ስርዓት ዝርጋታ፤ በቴክኖሎጂ ልየታና ሽግግር የተለያዩ ስራዎችን ማከናወን ተችሏል። የልማት አጋሮች ለዘርፉ የሚያደርጉት የገንዘብ፣ የአቅም ግንባታና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። በዚህም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን በላቀ ደረጃ ለመፈፀም የሚያስችል የፋይናንስ ምንጭና አቅርቦትን በማስፋት ከተለያዩ ምንጮች ከፍተኛ ሀብት ማግኘት ተችሏል።

# ምዕራፍ ስምንት

# የካፒታል ፕሮጀክቶችና ስታትስቲካልና መልከአ ምድራዊ መረጃ አስተዳደር ስራዎች አፈፃፀም

### 8.1 የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈጻጸምን በሚመለከት

በሴክተር መ/ቤቶች ተግባራዊ የተደረጉ ፕሮጀክቶች የህዝቡን የመሠረተ ልማትና የማህበራዊ አገልግሎት በማቅረብ ረገድ አመርቂ ውጤት ያስመዘገቡ ቢሆንም በየደረጃው የተተገበሩ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥና ወጪ አለመጠናቀቁ፣ የግንባታ መዘግየት፣ ገሚሱ ተጀምረው ሳይጠናቀቁ የሚቆሙበት ሁኔታ መኖሩ፣ የግንባታ ጥራት ችግርና የዲዛይን መቀያየር፣ መ/ቤቶች ፕሮጀክቶችን ለመጀመር የሚያደርጉትን ርብርብ ያህል ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ ፕሮጀክቶችን ለዞኖችና ልዩ ወረዳ የሚደለድሉበት ሁኔታ

ኢፍትሃዊ መሆኑ፣ ፍትሃዊ ያልሆነ የሀብት ዝውውር የሚደረግ መሆኑ በመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ፍትሐዊነት ላይ በህብረተሰቡ ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ እያስነሳ መሆኑን ተገምግሟል፡፡ በመሆኑም ክልላዊ የልማት ፕሮጀክቶች በተለይም የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ለዞኖች በፍትሐዊነትና ወጥ በሆነ መንገድ ተግባራዊ የሚደረግበት፣ የክፍያ ስርዓት፣ ቅንጅታዊ የክትትልና ግምገማ አሰራር ሥርዓትን በመዘርጋት ውጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መጠቀም በሚያስችል ሁኔታ እንዲተገበር በቀጣይ መሪ ዕቅዱ ዘመን በሙሉ አቅም የመስራት ጉዳይ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

**የመንግስታት ትብብር ማዕቀፍ ከማሳደግ**

ባለፉት ዓመታት ቀጥሎ በግራፍ በተመለከተዉ መሠረት ለልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የሚዉል የዉጭ ሀብት በክልሉ ፈስሶ በርካታ የልማት ሥራዎች ተሠርቷል፡፡ በዚህ መሠረት የመንግስታት የልማት አጋርነትን የሚያጠናክሩና የሚያበረታቱ ዉጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ ስለሆነም የመንግስታትና የመልቲላተራል የልማት አጋርነት ወደ ክልል የሚፈሰዉ ሀብት በመጠንና በጥራቱ ይበልጥ እንዲሻሻል ቢደረግ ልማቱን ይበልጥ ለማጠናከር ስለሚያስችል በመሪ ዕቅዱ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

## 8.2 ስታትስቲካልና መልከአ ምድራዊ መረጃ አስተዳደር ስራዎች አፈፃፀም

የመረጃ አደረጃጀት ትንተና ሰርጭት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አማካይነት በመታገዝ መረጃ ለማሰራጨት የሶሽዮኢኮኖሚ መረጃዎችን በዴቭ.ኢንፎ /DEVINFO/ እና የመልከዓ-ምድር መረጃዎችንም በጀ.አይ.ኤስ /GIS Software/ በመጠቀምና በማደራጀት የዞኖችንና የልዩ ወረዳን መረጃ እና ነጠላ ካርታ በማዘጋጀት ለተጠቃሚ ተሰራጭቷል፤

የሶሽዮኢኮኖሚ መረጃዎችን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ለማደራጀትና ለማሰራጨት በተደረገ ጥረትና ሂደት በወረዳ ያሉ ባለሙያዎች በተከታታይ የDEVINFO, GIS የተሰጡ ሥልጠናዎች ብዙ ባለሙያዎች አቅም ለመገንባት ተችሏል፡፡

በፕላንና ልማት ቢሮና በሴክተር መ/ቤቶች ጥራት ያለውን መረጃ ለማደራጀት ያሉትን ባለሙያዎች በመረጃ አደረጃጀት፣ በአይ.ሲ.ቲ የሥልጠና ኘሮግራሞች አቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል፡፡

በGTPII መጀመሪያ ዓመታት አነስተኛ የነበሩት በመረጃ አደረጃጀትና በሶፍትዌር የሰለጠኑ ባለሙያዎች በመረጃ አደረዳጀት በልማት አመልካች መረጃ አዘገጃጀት በጂ.አይ.ኤስ. ሶፍትዌር

በጂፒኤስ አጠቃቀም በዶቪ ኢንፎ አጠቃቀም ዞን በርካታ ባለሙያዎች ሥልጠና እንዲወስዱ በማድረግ የመረጃ አደረጃጀት ሰራው በየዞኑና ልዩ ወረዳ በቴክኖሎጂ አንዲደገፍ ለማድረግ ጥረት ተደረጓል፡፡ ይህም የመረጃውን ተደራሽነት ወቅታዊነት ጥራት ለመጠበቅ ሁለት ዳታቤዝ ሶፍትዌር በዞን በወረዳ ደረጃ ጥቅም ላይ አንዲውል ሰራዎች ተሰረተዋል፡፡

ዞኖች የሚዘጋጁት ዓመታዊ የሶሽዮ ኢኮኖሚና ፕሮፋይልና የሰታቲስቲካል አብስትራክት በጥራትና ወቅቱን ጠብቀው ለሚመለከተው አካል የሚልኩ ዞኖች ከቀደሞው ሁኔታ ሲነጻጸር በአሁኑ ግዜ ብዛታቸው እየጨመረ መምጣቱ አበረታች የሰራ ውጤት ነው፡፡

ዳይሬክቶሬቶች የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት ባደረገው ጥረት የዞኖችንና ልዩ ወረዳ ሀገራዊ የልማት እንቅስቃሴውን ለመደገፍ የሚያስችል የጥናት ዶክመንቶች Regional unemployment study & rural facility with collaboration of CSA ለማዘጋጀት ተችሏል:: በዚህም በመጀመሪያ ደረጃ ጥናት /Survey/ ስልት መሰረት በዞኖችና በወረዳዎች ያሉ ሴክተሮችን በማሳተፍ መረጃ የማመንጨት ተግባር በባህሪው ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅና ተቋማዊ አሰራርና አደረጃጀት ለውጥ የሚያስፈልግ ቢሆንም በክልሉ አቅም አንድ ዙር /employment & unemployment survey/ የሥራ ስምሪት ጥናት ተዘጋጅቶ መረጃው ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ተደርጓል፡፡

ለሀብት ክፍፍል የሚያሰፈልጉ አመልካች የቀመር መረጃዎች ወቅቱ ከሚጠበቀው የመረጃ ጥያቄ አንፃር ማዘጋጀት ለሀብት ክፍፍል እንዲዘጋጅ ጥረት የተደረገ ሲሆን ለቀጣይም ልዩ ተኩረት ተሰጥቶ መሰራት ይገባል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ያለፉት ዓመታት ተግዳሮቶች እና የአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ አድማስ

## ምዕራፍ አንድ

# 1. ባለፉት ዓመታት ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶች እና መልካም አጋጣሚዎች

## 1.1. ያጋጠሙ የልማት ተግዳሮቶች

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ባለፉት እቅድ ዓመታት የልማት አፈፃፀም ዋነኛ ተግዳሮቶች ስንመለከት ሰፊ የመልማት አቅሞች ቢኖሩትም ውጫዊና ዉስጣዊ ተግዳሮች ሲፈታተኑት ነበር። በየመስክ ያጋጠሙት የእቅድ ዓመታት ተግዳረቶች ከዚህ ቀጥሎ በየዘርፉ ተመላክተዋል።

## 1.1. የኢኮኖሚ ዘርፍ ተግዳሮቶች

### 1.1.1. ግብርና ዘርፍ

ስነምህዳራዊ ተስማሚነት፣ በቂ ዝናብ ያለበት፣ በተፈጥሮ ሀብት የበለጸገ በግብርና ዘርፍ የትርፍ አምራችነት እምቅ አቅም ያለውና ክልሉ የኢኮኖሚ ማእከል መሆን የሚችል ሆኖ እያለ እያጋጠሙት ካሉ ዋናዋና ተግዳሮቶች ውስጥ፡

የግብርናው ዘርፍ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በሁለንተናዊ መልኩ ሲታይ ኋላቀር፣ ያልዘመነ (የምርምር ውጤቶችና ምርታማ ቴክኖሎጂዎች እጥረትና ተደራሽነት ችግሮች ያሉበት)፣ በዝቅተኛ ምርትና ምርታማነት ምክንያት በአስተማማኝ ሁኔታ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ያልቻለ፣ እሴት የማይጨምርና ደካማ የገበያ መር፣ የመዋቅራዊ ለውጥ ሽግግር ለማድረግ ያልበቃ እድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ፡፡

**ግብአት አቅርቦት ላይ የሚሰሩ የተደራጁ ተቋማት ያለመኖር፡-**

ለአየር ንብረት ለውጥ ከሌሎች ዘርፎች በበለጠ የተጋለጠ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን፣ በቂ ኢኮኖሚ የማያመነጭ በአስተማማኝ ሁኔታ የስራ እድል የማይፈጥር፣ ተደራሽነት ችግር፣ በመሰረታዊነት የአርሶ አደሩን ኑሮ ያልቀየረ፣ የስርዓተ-ፆታን እኩልነትና ፍትሐዊነት በተሟላ ሁኔታ ያላረጋገጠ መሆኑ፡፡ የባለሀብቶች ሚና ወሳኝ መሆኑ ቢታመንም የግብርና ኢንቨስትመንት ግልፀኝነት የጎደለው የመሬት ወረራን ታሳቢ ያደረገ፣ የክልሉን ልዩ ባህርይና ስርዓተ-ምህዳራዊ ሁኔታን ያላገናዘበ የግብርና ዘርፍ እቅድና አፈፃፀም፣ አርብቶ አደር ማህበረሰብ ተረጋግቶ አለማረስ፣ የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ የተቀናጀ ልማት አለመስፋፋት የተስተዋለበት መሆኑ፡፡

### 1.1.2. ኢንዱስትሪ ዘርፍ

የግብርናን ግብዓቶችና ሌሎች ጥሬ (የተፈጥሮ) ሀብቶችን ተጠቅሞ የሚሰራ አምራችና እሴት የሚጨምሩ እንዱስትሪዎችና ሌሎች የኢኮኖሚ ተቋማት (እንደ ኮንስራክሽን፣ ማእድን፣ ሆቴልና ቱሪዝም፣ እንዱስትሪዎችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት) በክልሉ አለመስፋፋት፡

የተመሰረቱ አነስተኛና ጥቃቅን አምራች ዘርፎች እንደ የሻይ ቅጠል ማቀነባበሪያ፣ የቡና ማጠቢያ፣ መቀሸሪያና ማቀነባበሪያ እሴት የማይቸምሩ ስራዎች መሆናቸው
የገበያ ትስስር ደካማ መሆናቸው፣ ለዘርፉ የማምረቻ፣ ምርት ማሳያ፣ የመሸጫ ቦታዎች ዝግጅትና አቅርቦት በቂ አለመሆን፣
የመሰረተልማት እንደ መንገድ፣ መብራት፣ ተሌኮም (ቴክኖሎጂ) ትስስር ደካማ መሆን፣
የካፒታል እጥረት፣ ተቋማዊ አቅም ችግርና በመስኩ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ዋና ዋና ችግሮች ናቸው።

### 1.1.3 የስራ አጥነትና ተጓዳኝ ማህበራዊ ችግሮች እየተስፋፋ መምጣት

የስራ ፈጠራ መስኮች አለመስፋፋት፣ ድጋፍና ክትትል፣ ክህሎት ስልጠና አለመኖርና ተሰማርተው ያሉትም በቀጣይነት ውጤታማነታቸውን እያረጋገጡ አለመቀጠል፣ የቁጠባ ችግር፣ ከቴክኒክና ሙያ የሚወጡት ወጣቶች በስራ ፈጠራ ክህሎት ያልተገነቡና ስራ ፈላጊ መሆን፣ ለስራ ክቡርነት ያለው አመለካከት ችግሮች ይጠቀሳሉ፡

### 1.1.4 ፋይናንስ፣ የገቢ ሀብት አሰባሰብና በቁጠባ ከመጠቀም አንፃር

ከፍተኛ የሆነ ፋይናንስ እጥረት መኖር (በተለይ ለካፒታል ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ) እና እዳ ውስጥ መግባት፣ ገቢ በማሰባሰብ የውስጣዊ አቅምን በማሳደግ በራስ አቅም ከድጋፍ በጀት ጥገኝነት የሚያላቅቅ አቅጣጫ ይዞ አለመስራት፣ በቂና ጥራት ያለዉ መረጃ የተደገፈ የገቢ ግመታና አሰባሰብ፣ ከሙስናና ብክነት የፀዳ የሀብት አሰባሰብ ስርዓት አለመዳበር፣ የተሰበሰበውን ገቢ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለህዝብ ልማት ስራ ላይ አለማዋል፣ የግብር ስወራዎች፣ የገቢ አሰባሰብ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆን የዘርፉ ተግዳሮቶች ናቸው።

### 1.1.5 ንግድና ገበያ ልማት

የወጪ ምርቶች ንግድ (እንደ ቡና) የተዛባ ህገወጥ ንግድና ግብይት መስፋፋት፣ የገበያ ሰንሰለት መራዘምና በምርት ሰንሰለት ውስጥ ፋይዳ የሌላቸው ተዋኒያን/ደላሎች/ ንግድ ማዛባትና አርሶ አደሮች የልፋታቸውን ዋጋ አለማግኘት፣ የአርሶ አደር ማህበራት አለመጠናከር (ክህሎት፣ የገበያ ትስስር ድጋፍ፣ የብድር አገልግሎት አቅርቦት ችግር፣ ወ.ዘ.ተ)፣ የገበያ

ምርቶች በመጠንና ዓይነት አለመስፋፋት፣ የአቅርቦትና አገልግሎት ጥራት ችግሮች፣ ያለተመጣጠነ ዋጋ መተመን፣ የገበያና የመረጃ መሰረተ ልማቶች አለመኖር/አለመስፋፋት፣ ደካማ የህግ የማስከበር ስራዎች ተግዳሮቶች በዘርፉ ይጠቀሳሉ፡፡

### 1.1.6 የመሰረተ ልማት አቅርቦትና የጥራት ጉድለት መኖር

የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ቴክኖሎጂያዊ መሰረተ ልማቶች አቅርቦች እጥረት፣ በሁሉም ደረጃዎች የሚለካ የመንገድ መሰረተልማት አለመስፋፋትና ያለው የጥራት ጉድለት፣ ፍትሐዊነትና የተደራሽነት፣ የግንባታዎች ያለመጠናቀቅ ችግሮች የህዝብ ለህዝብ ትሰስር፣ የምርት ዝውውር፣ ኢኮኖሚ እድገት ከማቀላጠፍ፣ ህዝባዊ አገልግሎቶችን እንደ ጤና ለማግኘት ማነቆ መሆን፣ የዲጂታል መሰረተልማትቶች እንደ ቴሌኮም፣ ኢንተርኔት /ብሮድ ባንድ/፣ ለፈጣን መረጃ ልውውጥ አስቸጋሪ መሆን፣ የከተማና ገጠር የመጠጥ ውሃ መሰረተልማቶች አቅርቦት እጥረት፣ ተደራሽነትና የጥራት ጉድለት፣ የእርሻ መስኖ መሰረተልማት ከአነስተኛ የውሃ ማሰባሰብና ግብርናውን በሚያሻግር መልኩ አለመሰራትና ጥናት፣ የዲዛይን፣ ግንባታ፣ የጥራትና ዘላቂነት ችግሮች፤ መሰረተ ልማት ተሳትፎ ላይ የህብረተሰቡ ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆንና ከህብረተሰብ የሚሰበሰብ ገንዘቦችና የተሰሩ ስራዎች ላይ ግልፀኝነት ያለመኖር፣ የተለያዩ መሰረተ-ልማት ግንባታዎች ተቀናጅተው አለመተግበር ተጠቃሾች ናቸው፡፡

### 1.1.8. ከተማ ልማትና የቤቶች ልማት

አብዛኛዎቹ ከተሞች ከአመሰራረታቸው ታሪክ አንፃር ወይም በሌላ ምክንያት በፕላን የማይመሩ፣ የግንባታ ጥራት ችግር፣ ለኑሮና ለስራ ምቹ አለመሆን፣ ከተሞችን መልሶ ማልማት ስራ በዕቅድ ያለመመራት፣ ጽዱና አሬንጓዴ ዘመናዊ ከተማ ልማት አካሄድን አለመከተል፣ የመሬት ወረራና አቅርቦት ችግር፣ የተለያዩ የህገወጥ ተግባራት፣ የግጭት፣ የማህበራዊ ችግሮችን የሚያስተናግዱና የስራ አጥነት መከማቻ መሆን፣ በቂ ኢኮኖሚ ያማያመነጩ፣ ከዙሪያ ገጠሮች ጋር ልማትና እድገትን፣ መልካም ትስስር ደካማ መሆን፣ ከፍተኛ የቤት እጥረትና የመሰረተ ልማት ችግር ያሉባቸው መሆን፣ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ችግር፣ በቂ የመዝናኛ ስፍራና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት አለመኖር፣ የገጠር ሞዴል ቤቶች ልማት (መንደሮች) ደረጃ ወጥቶላቸው ለነዋሪ ምቹ እንዲሆን ታቅዶ አለመተግበር ተግዳሮቶች ያሉበት ነው፡፡

**ቱሪዝም ልማት ዘርፍ**

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል በተፈጥሮ ሀብቶች ብዝሀነት፣ በባህልና በስነምህዳራዊ ገጽታዎች የታደለ ከፍተኛ የአሬንጓዴ ቱሪዝም እምቅ አቅም ያለው ሆኖ ሳለ የቱሪዝም ዘርፍ ትኩረት ያልተሰጠበት መሆን፣ በክልላችን ባሉ ፓርኮች ላይ በማኔጅመንት ፕላን መሰረት ባለመተግበሩ አርሶ አደሮች በፓርክ ክልል ውስጥ መግባት እና በሰው ላይ ጉዳት ማድረስ፤ የቱሪዝም ሀብቶች (ባህላዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ መስህቦች) አቅም በጥናት ያልተለዩ፣ የሚጠበቅባቸው የገቢ አቅም በውል ያልታወቀ መሆኑ እና የቱሪዝም ሀብቶችን የማስዋወቅ ስራ ዝቅተኛ መሆኑ፤የህግ ማዕቀፍ ድጋፍ የሚፈልጉ ርእሰ ጉዳችን ሙሉ ለሙሉ ለይቶ በህግ እንዲደገፍ ያለማድረግና ወጡትንም የህግ ማዕቀፎች በሚፈለገው ደረጃ ተፈፃሚ ያለመሆን፣ የቱሪዝም መሰረተ ልማቶች የሌሉባቸውና በቱሪዝም መረጃ/ግንኙነት መረብ ላይ ያልሰፈረ መሆኑ፣ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና የቱሪዝም ገበያ አለመስፋፋትና የመዳረሻዎች አለመልማት የባለፉት ትግበራ ዓመታት ችግሮች ናቸው፡፡

**የማዕድን ሀብት አጠቃቀም**

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል የተለያዩ የማዕድን ሀብቶች (ወርቅ፣ ብረት፣ የድንጋይ ከሰል፣ የኮንስትራክሽን ማእድናት...) እንዳሉት መረጃዎች ቢጠቁሙም በባህላዊ ዘዴ ብቻ የሚመረቱ ያልዘመኑና እሴት የማይጨምሩ መሆናቸውና ህገ ወጥ ንግድ መኖሩ፣ ለክልሉ/አካባቢው የሚያበረክተው አስተዋጽኦ አነስተኛና ለብክነት የሚዳረጉ መሆኑ፤

## 2.1. የማህበራዊ አገልግሎቶች ተግዳሮት

### 2.1.1. ትምህርት ልማት ውስጥ የነበሩ ተግዳሮቶች

ትምህርት ተቋማት በገጠርና ከተሞች የተስፋፉ ቢሆኑም የጥራት ችግር ያሉባቸው፣ የውስጥ ቁሳቁስ ያልተሟላላቸውና ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች ያልተደራጁ መሆናቸው፣ በተሟላ

ስብእና የተገነባ አገር ተረካቢ ዜጋ ከመፍጠር አንፃር፣ የተማሪ-ክፍል፣ የተማሪ-መምህራን እና የተማሪ-መፃህፍት ጥምርታዎች አለመጣጣም ይጠቀሳሉ፣ ለተግባር ተኮር ትምህርት የሰርቶ ማሳያ/መስክ ትምህርት፣ ላቦራቶሪ አደረጃጀትና ቁሳቁስ እጥረት፣ መጠነ ማቋረጥ መጨመር፣ የሴት ተማሪዎችን ልዩ ድጋፍ በማድረግ በትምህርት እንዲበቁ አለመስራት፣ በየትምህርት ቤቱ የተማሪዎች አገልግሎቶች እንደ ውሃ ንጽህና አገልግሎቶች በቂ አለመሆን፣ የት/ቤቶች ደህንነትና ጽዱና አሬንጓዴ ት/ቤት ከመፍጠር አለመፍጠር፣ የአዳሪና የታለንት ት/ቤት አቅርቦት እጥረት፣ የትምህርት ቤቶች ገቢ አቅም ማነስ፣ ከግል ትምህርት ተቋማት ቁጥጥር ዘቅተኛ መሆን ይጠቀሳሉ።

### 2.1.2.. በጤና ተቋማት ጥራት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

የህክምና አገልግሎት ሰጪ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በቢቂ ሁኔታ ያልተደራጁ መሆንና፣ ብቃት ያላቸው የጤና ባለሙያዎች እጥረት፣ የመድሀኒት አቅርቦት በበቂ ሁኔታ አለመገኘትና ተገልጋዩ ከግል ተቋማት እንዲገዙ እየታዘዙ ለአላስፈላጊ ብዝበዛ መዳረግና ለሙስና በር ከፋች መሆን፣ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ችግሮች፣ የጤና አገልግሎት ሀብት ብክነት የሚታይበት መሆን፣ የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ፓኬጆች መቀዛቀዝና ማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን በሚፈለገው መጠን ተግባራዊ ያለመደግ፣ በመከላከል ላይ የተመሰረተ ጤና ማፋፋት እየተቻለ በብቃት አለመተገበር የህ/ሰቡ የመሰረታዊ የጤና ክህሎት አለመዳበር፣ ታካሚዎች የተሟላ የጤና አገልግሎት ፍለጋ ሩቅ እየተጓዘ ለህልፈት መዳረግ፣ የግል ጤና ተቋማት አገልግሎት በቂ ቁጥጥር የማይደረግባቸው ተካሚዎችን ለእንግልትና ብዝበዛ የሚዳርጉ መሆናቸው፤

### 2.1.3. በስፖርት ልማት ውስጥ የነበሩ ተግዳሮቶች

በህ/ሰብ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ የስፖርት አገልግሎት አለመስፋፋትና የስፖርት ዘርፈብዙ አስፈላጊነት በህ/ሰብ ዘንድ ግንዛቤ አለመዳበር፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አለመኖርና ያሉትም የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው ለአገልግሎት እንዲውሉ አለማድረግ፣ የስፖርት ቢዝነስ ጽንሰ ሀሳብ ተይዞ አለመስራትና ስፖርት ለጤናና ማስ ስፖርት የተስፋፋ አለመሆን፣ የተለያዩ የስፖርት ተሰጥኦ ያላቸውን ወጣቶች መልምሎ አለማብቃትና አለመጠቀም፣ የተለያዩ ባህላዊ ስፖርቶች ዳብረው ለውውድር፣ ለመዝናኛ፣ ለገጽታ ግንባታና ለማንነት መገለጫ እንዲውል አለማድረግ ችግሮች ተስተውሏል።

### 2.1.4. ከአረጋዊያንና አካል ጉዳተኞች አንተሳር የነበሩ ተግዳሮቶች

ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚና ምቹ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሰረተ ልማቶች አለመስፋፋት እና የአረጋዊያንና ጧሪ የሌላቸው ወገኖችን በዘላቂነት የሚጦሩበትና የሚቋቋሙበት ተቋምና ስርዓት አለመኖር ችግሮች አሉበት፡፡

## 3. ባለብዙ ዘርፍ-ጉዳዮች /Cross Cutting Issues/ ተግዳሮቶች

### 3.1. ስርዓተፆታ ተጠቃሚነትን ከማመጣጠን አንፃር፡

በሁሉም ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማቶች የሴቶች እኩል ተጠቃሚነትና በሚያፈሩት ሀብት ተጠቃሚነት ፍትሐዊነትን ላይ ከማስፈን፣ በከተማም ሆነ በገጠር የመሬት የይዞታ ባለቤትነትና የልማት ፍትሐዊነት፣ ከማንኛውም ፆታዊ አድልዎች ተፈጥሯዊ ነፃነታቸው የተጠበቁ ከመሆናቸው አንፃር ገና ብዙ የሚቀረው መሆኑ፣

### 3.2. አካባቢ ጥበቃና አየር ንብረት ለውጥ ላየ የነበሩ ተግዳሮቶች

በተለይ በሁሉም የግብርና ዘርፎች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እያሳደረ መሆኑ፤ በማምረትና በመልማት ሂደት በውሃ ሀብት፣ በአፈር፣ በአየር የሚደርስ ብክለት እየተስፋፋ መቀጠሉ፤

### 4. ሠላም፣ ፀጥታ፣ የህዝብ ደህንነትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች ተግዳሮቶች

በክልሉ በተለያዩ መነሻ ምክንያቶች የሚከሰቱ የፀጥታ ችግሮች አሉ፡፡ እነዚህ ህዝብ በሠላም ወጥቶ መግባትን የመዘዋወር መብቶችን የሚገድቡ፣ ልማትን የሚያስተጓጉሉ ናቸው፡፡ መነሻ ምክንያት የሚሆኑት በዋነኛነት ድህነት፣ ከዚህ የመጣ የስራ አጥነት፣ ጎሳን መነሻ ያደረጉ ግጭቶች፣ የዘር ፖለቲካ፣ የሀሰት መረጃዎች/ማህበራዊ ሚዲያዎች/፣ የሀብት ሽሚያዎች፣ የድንበር ግጭቶች፣ የተደጋገመ የመልካም አስተዳደር እጦቶች፣ የልማትና አገልግሎቶች ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጥያቄዎች፣ የማህበረሰብ የንቃተህሊና እንደ ምቹ አጋጣሚ፣ ባህላዊ የሠላም ዳኝነትና እርቅ ተቋማት እየተሸረሸሩ መምጣትና ሚናቸው ተቀባይነት ማጣት ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

### 5. የመፈጸምና ማስፈጸም አቅም ውስንነቶች

የተሟላ አደረጃጀትና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት ፈጥሮ ተልእኮውን በብቃት የመፈጸም፣ የማስፈጸምና የመምራት ወስንነቶች፣ ቁርጠኛ፣ ታማኝ፣ ስራ ወዳድ፣ ችግር ፈቺ ባለሙያችን አለማብዛት፣ ከአቅም ጋር የተመጣጠነ እያደገና እየጎለበተ የሚቀጥል ከአንገብጋቢ የህዝብ

ልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ምላሽ እየሰጡ የመተግበርና ወደ ተገልጋዩ ቀርቦ ስሜቱን ተረድቶ በርህራሄ አገልግሎት አለመስጠት፣ ለእድገትም ለተገልጋይም ፋይዳ በሌላቸው የማይቆጠሩ ስራዎች (ስብሰባ) ላይ ጊዜ፣ ገንዘብ ጉልበትና ሀብት ማባከን ከተገልጋይና ከልማት አንፃር ሲታይ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው።

1.2. **መልካም አጋጣሚዎች**

**የፖለቲካ ሁኔታና ፖሊሲ መሻሻሎች፡-** በረዥም ጊዜ ጥያቄ ሆኖ የቆየው ክልል መመስረቱና ወደ ስራ መገባቱ፣ የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች የየአካባቢዎችን የመልማት አቅም የሚደግፍ መሆኑ፣ እየተሻሻለ የመጣ አዲሱን ክልል ለመምራትና ለማልማት የሚያስችል የተማረ ሀይል እየተበራከተ መምጣቱ፣ የክልሉን ሁለንተናዊ እድገት ሳይንሳዊ ቅርጽ የሚያስይዙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እየተስፋፉ መሆኑ፣

**ኢኮኖሚ አቅሞች፡-** መሰረተልማት በመስፋፋት ላይ መሆኑ፣ የኮይሻ የገበታ ለሀገር ፕሮጀክት የፈጠራቸው መነሳሳቶች፣ ትርፍ የማምረትና የመበልጸግ እምቅ አቅም ያለው ክልል መሆኑ፣ በክልሉ የከተማና ገጠር ኢንቨስትመንት ፍሰት የሚጨምር መሆኑ፣

**ማህበራዊ/የህዝብ ሁኔታ፡-** በስነልቦና የተሳሰረ ከፍተኛ የልማት ፍላጎቶች ያሉት ታታሪ ህዝብ ያለበት ክልል ነው፣ የተለያዩ የህዝብ የልማት አደረጃጀቶች እንደ የአርሶአደር የህ/ሰራ ማህበራትና ዩኒየኖች መኖራቸው፣ ህዝቦች ለዘመናት የዳበረ አብሮነትና ማህበራዊ መስተጋብር ያላቸው መሆኑ

**ሠላምና ፀጥታ፡-** አንፃራዊ ሠላም ያለው የተረጋጋ ክልል ነው፣ የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ተወያይቶ የመፍታት ባህልና ልምድ ያለውና በስነልቦና የተሳሰረ ህ/ሰብ ክፍሎች ያሉበት ክልል መሆኑ

**ተፈጥሮ ሀብት፡-** በዓይነተ ብዙ የተፈጥሮ ሀብት (ማዕድናትን ጨምሮ) የበለጸገ አረንጓዴ ክልል መሆኑ፣ ለሁሉም ዓይነት ልማቶች ተስማሚ የስነምህዳር እና የአየር ንብረት የአየር ንብረት ያለው መሆኑ፣ በርካታ ወንዞች፣ ጅረቶች፣ ሀይቆችና ፏፏቴዎች ያሉበት መሆኑ፣ ክልሉ የግብርናን ዘርፍ ለማሳደግ ለምና ሰፋፊ ተስማሚ የእርሻ መሬት ባለቤት መሆኑ፤

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ አስፈላጊነት እና ልዩ ባህርያት

## 2.1. የክልልችን የልማት ዕቅድ ዝግጅት ታሪካዊ ዳራ

አንድ የልማት መሪ ዕቅድ ሲዘጋጅ ከሚያካትታቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ለማመላከት ያህል የክልሉን ነባራዊ ሁኔታዎችን መገምገም፣ አሁን ያለንበት ደረጃን መለየት (where we are)፣ የት መድረስ እንዳሰብን ግብ መጣል (our Goal) እና ግባችንን እንዴት ማሳካት እንደምንችል /how to achieve our Goal/ ማመላከት መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው።

ምንም እንኳን ክልላችን አዲስ ቢሆንም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ውስጥ ባሉት ስድስት መዋቅሮች ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት በዕቅድ ለመምራት የሚያስችሉ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅዶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይተዋል። ከነዚህም ውስጥ ከ1988-1992 ዓ.ም የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ፣ ከ1993-1997 ዓ.ም የድህነት ቅነሳ ስትራተጂ ዕቅድ (Poverty Reduction Plan)፣ ከ1998-2002 ዓ.ም ዘላቂና ቀጣይነት ያለው ልማትና የድህነት ቅነሳ እቅድ (PASDEP) (Plan for Accelerated & Sustainable Development to End Poverty)፣ (የአምስት ዓመት የልማት መርሀ ግብር) ከ2003-2007ዓ.ም የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (Growth & Transformation Plan I /GTP I) እና ከ2008-2012 ዓ.ም የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (Growth & Transformation Plan II/GTP II) ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በመቀጠልም በተመረጡ ዘርፎች ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶች እንዲካሄዱ በማድረግና በግብዓትነት በመጠቀም "ኢትዮጵያ የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት" ለማድረግ የተቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይ ለማሳካትና ክልላዊ ድርሻውን ለመወጣት የሚያስችል የ10 ዓመት (2013-2022) ክልላዊ የልማት ዕቅድ ተዘጋጅቷል።

## 2.2. የረጅም ጊዜ (የአሥር ዓመት) ዕቅዱ አስፈላጊነት

ክልላዊ የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ ሚና በዋናነት ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ቀጣይ የስትራቴጂክ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ በየምዕራፉ በሚኖሩ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶች አማካይነት ሊተገበሩ የሚቀመጡ መሰረታዊ አቅጣጫዎችን፣ ዓላማዎችን፣ ግቦችንና የማስፈፀሚያ ስልቶችን በማስቀመጥ የዕቅዶችን ተፈፃሚነት በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ ለመምራትና ለመከታተል የሚያስችል ነው። ይህም ማለት የልማት ዕቅዱ ለክልላችን የኢኮኖሚ ዕድገት ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ቀጣይ የስትራቴጂክ አቅጣጫዎችንና ዓላማዎችን በማስቀመጥ፣ ክልላዊ የኢኮኖሚ ዕድገትንና ልማትን በረጅም ጊዜ ዕቅድ በመምራት፣ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የማምጣት ዓላማን ለማሳካት ብሎም ሀላፊነትንና ተጠያቂነትን በግልፅ በማስቀመጥ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና የጋራ ብልጽግናን ለማስፈን ያስችላል።

ከፍጹም ድህነት ወደ ማይቀለበስ ብልጽግና የሚደረግ ሽግግር የአንድና ከዚያ በላይ ትውልድ ዕድሜ ይጠይቃል። በዚህም መሠረት በአንድ ትውልድ ዕድሜ ብልጽግናን በራዕይ ደረጃ ማመላከት የሚቻል ሲሆን ስኬቱ በትክክለኛ ጎዳና መሆኑን ለማመላከት በቂ ጊዜ ያስፈልገዋል። በተለይም በልማት ሂደት

ውስጥ የዓመት፣ የአምስት ዓመት እና የአስር ወይም አስራ አምስት ዓመታት ዕቅዶች በእነዚህ ጊዜያት ሊፈጸሙ እንደሚገባቸዉ ጉዳዮች የተለያዩ ናቸው።

በዝቅተኛ የድህነት ምጣኔ፣ በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ ደረጃ የሚገለጽ የገቢ አቅም፣ በከፍተኛ የሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ፣ በዘላቂ የኢኮኖሚ መዋቅር፣ በዘላቂ የከተማ ልማት፣ በኑሮ ደረጃ መሻሻል፣ በፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና በመሳሰሉ ጉዳዮች የሚገለጹ ጥቅል የልማት ግቦች በአጭር ጊዜ የሚረጋገጡ ስላልሆኑ ከአስር ዓመት በማያንስ የጊዜ ሰሌዳ ይመላከታሉ። የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችም በረጅም ጊዜ ዕቅዱ የተመላከቱትን ግቦች ለማሳካት የሚተገበሩ ዝርዝር ዕቅዶች ናቸው።

የልማት ሂደትን የሀብት መፍጠሪያ አቅም መገንባት፣ ሀብት መፍጠር እና ሀብት በፍትሐዊነት መከፋፈሉን ማረጋገጥ በሚሉ ሦስት ደረጃዎች መከፋፈል ይቻላል። የሀብት መፍጠሪያ አቅም በኢንቨስትመንት ይረጋገጣል፤ ሀብት በኢኮኖሚ ዕድገት ይፈጠራል፤ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በፖሊሲ እውን ይሆናል። የእነዚህ ሂደቶች ትግበራም የተለያየ ጊዜ ይወስዳል። በአንድ ዓመት ዕቅድ ውስጥ ስለኢንቨስትመንትና ተያያዥ ጉዳዮች፣ ስለ ዝርዝር የዘርፎች ተግባር እና በፖሊሲ ደረጃም ስለ ጥቅል ኢኮኖሚ መረጋጋት ሊታቀድ ይችላል። በአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ ስለ መሠረተ ልማቶች ግንባታና ስለ ፈጣን የመካከለኛ ጊዜ የኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሊታቀድ ይችላል። ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል፣ ድህነትን ትርጉም ባለው ደረጃ መቀነስ፣ ዘላቂ ልማት እና ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጥራት ያለው ኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሁም መዋቅራዊ ለውጥ ከአስር ዓመት ባነሰ የጊዜ ሰሌዳ ማቀድ አይቻልም።

ከዚህ አንጻር አስርና ከዚያ በላይ ዓመታት የሚወስዱ የረጅም ዘመን ዕቅዶች አመላካችና አቅጣጫ ጠቋሚ ሲሆኑ የአምስት ዓመት ዓይነት የመካከለኛ ዘመን ዕቅዶች በረጅም ዘመን የልማት ዕቅድ የተመላከቱ ዋና ዋና ግቦችን ለማስፈጸም የሚታቀዱ ዝርዝር ጉዳዮች ይሆናሉ። በአስር ዓመት ሊደረስባቸው የሚገባቸውንና የሚችሉትን ግቦች ግምት ውስጥ ያላስገባ የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ በብዙ መልኩ ግቡን የሚያሳካ ዕቅድ ሊሆን አይችልም።

ይህን ጉዳይ በምሳሌ ለማስረዳት የቡና ልማት ችግኝ ከማፍላት እስከ ምርት ባለው ሂደት የአምስት ዓመት ጊዜ ሊያስፈልገው ይችላል። በአንድ ዓመት ውስጥ ሊታቀድ የሚችለው ችግኝ አፍልቶ ከመትከልና ችግኙ መጽደቁን ከማረጋገጥ አይዘልም። ቡና በመትከል ተጠቃሚነትን ግብ ላደረገ ገበሬ ግን ትልቁ ዕቅድ የአምሥት ዓመት ዕቅድ ይሆናል። ገበሬው ስለሚኖረው የቡና ምርት መጠን፣ የቡናው ምርት ተሸጦ ስለሚገኘው ገቢና በገቢው ስለሚሟሉ ፍላጎቶች ከአምሥት ዓመታት ባነሱ ጊዜያት እንደሚሟሉ አድርጎ ማቀድ አይቻለውም። ይልቁንም እነዚህ ግቦች በአምሥት ዓመት ዕቅድ

ከተመላከቱ በኋላ ዝርዝር አፈጻጸሞች የአምሥት ዓመት ግቦችን መሠረት አድርገው በአንድ ዓመት ተመጥነው ይታቀዳሉ።

## 2.3. የአሥር ዓመት ዕቅዱ ልዩ መለያ ባህሪት

**የልማት ዕቅድ ዝግጅቱ የዘርፎችን ትስስር ያማከለ እንዲሆን መደረጉ፦**

የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ አንዱ መለያ የዘርፎችን ትስስር ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ ነው። የዘመናዊ ግብርናን፣ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪንና የማዕድን ዘርፎችን አንዱ ለሌላው ግብዓትና ፍላጎት በመሆን እንዲደጋገፉ የንግድ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፎችን በማሳለጥ ምርትን ከገበያ ጋር የማገናኘት ሚና እንዲወጡ በልማት ዕቅዱ ዝግጅት ትስስር እንዲፈጠር ተደርጓል። በተመሳሳይ መሠረተ ልማቶች (መንገድ፣ ኢነርጂ፣ መስኖ፣ ሌሎች የትራንስፖርት መንገዶች፣ መገናኛዎች) ለሌሎች ዘርፎች መልማት መሠረት እንዲሆኑ እንዲሁም የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ የምርታማነት ወሳኝ ማረጋገጫዎች በመሆናቸው የሁሉንም ዘርፎች ልማት በሚያሳልጡበት አግባብ ታቅፏል።

የዘርፎች ትስስር ወሳኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ ምርታማነት፣ ከፍተኛ የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም እና ሌሎች ዘርፎችን የማነቃቃት አቅም ያላቸውና ለበርካታ ዜጎች የኑሮ ደረጃ መሻሻል መሠረት የሚሆኑ ዘርፎች በቀጣይ አስር ዓመታት የተለየ ትኩረት ይሰጣቸዋል። ዘመናዊ ግብርና፣ የአምራች ኢንዱስትሪና የማዕድን ዘርፎች በአምራች ዘርፍነት የተለየ ትኩረት የሚሰጣቸው ሲሆን እነዚህ ዘርፎችም በግብዓትና በፍላጎት የእርስ በእርስና ውስጣዊ ትስስር በሚደጋገፉበት አኳያ ታቅደዋል። በተጨማሪም የልማት ዕቅዱ ክልሉ ባለው የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ መስህቦች ምክንያት የቱሪዝም ዘርፍ ለአገልግሎት ዘርፎች መጠናከር እንዲሁም ለአምራች ዘርፎችና ለመሠረተ ልማት ግንባታ ወሳኝ የሆነውን የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት በማስገኘት ሊጫወት የሚችለውን ሚና ከግምት ያስገባ እንዲሆን ተደርጓል። በተመሳሳይ የአይሲቲ (ICT) ዘርፍ እንደ ተጨማሪ የዕድገት እና የሥራ ዕድል ምንጭ እንዲሁም የሰው ሀብት መገንቢያ ለማድረግ የተለየ ትኩረት ይሰጠዋል። እነዚህን ዘርፎች ለማልማትም መሠረተ ልማቶች ቁልፍ ሚና ስለሚኖራቸው የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች በአብዛኛው ከዘርፎች ትስስር ጋር የተቆራኘ ነው። በተጨማሪም የልማት ዕቅዶች ተፈጻሚ የሚሆኑት በዘርፍ ተቋማት እንደመሆኑ ተቋማቱ ስለዘርፎች የመልማት አቅም፣ መሠረታዊ ክፍተቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች የተሻለ ግንዛቤ አላቸው። በመሆኑም የልማት ዕቅድ ከላይ ወደታች የሚወርድ ሳይሆን በዘርፎች ተሳትፎ እንዲታቀድ ተደርጓል።

**አሳታፊና ክልላዊ የልማት ማዕከላትን የለየ መሆኑ፦**

በክልሉ በተለያየ ደረጃ በሚገኙ የመንግስት አስተዳደር አካላት ተግባራዊ የሚደረጉ የልማት ዕቅዶችን ክልላዊ የልማት ዕቅድ ጋር የሚያስተሳስር ጠንካራ የአሠራር ሥርዓት መኖር ለልማት ዕቅዱ ውጤታማነት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም በዞኖችና ከልዩ ወረዳዎች በታች ባሉ የመንግሥት አካላት የልማት ዕቅድን የሚመራ አቅምና በቂ ፋይናንስ እንዲኖር ማድረግ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። በተመሳሳይ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ አካባቢዎችን እምቅ አቅም በመለየት እነዚህን አቅሞች መሠረት ያደረገ የተደራጀ የኢንቨስትመንት ፍሠት ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ አካባቢዎች የተፈጥሮ፣ የሰው ኃይልና አቅሞችን በአግባቡ በመጠቀም ለልማት ዕቅድ መሳካት አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። በዚህም መሠረት በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ክልላዊ የልማት ዕቅዱና የዞን መዋቅር የልማት ዕቅዶች ያላቸውን የመልማት እምቅ አቅም በመቃኘትና በማጣጣም እንዲሁም ክልላዊ የልማት ማዕከላትን በመለየት የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ከተመረጡ የልማት ማዕከላት ጋር የተቀናጁበትን አግባብ ግምት ውስጥ እንዲያስገባ ተደርጓል።

**የሥርዓታትን ድክመቶች እንደ ዋና ተግዳሮት በመውሰድ ሁሉን አቀፍ ማሻሻያ የሚደረግበት አቅጣጫ መያዙ፦**

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ በመዋቅራዊ ለውጥ ረገድ ለተስተዋለው ዝቅተኛ አፈጻጸም አንዱና ዋናው ምክንያት የሥርዓታት ድክመት እንደሆነ ታምኖበታል። የተቋማት ዝቅተኛ የማስፈጸም አቅም፣ የፕሮጀክት አስተዳደር እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መላላት፣ የተጠያቂነት አለመስፈን፣ በግሉ ዘርፍ ያልተገቡ ባሕርያት መታየትና ከመንግሥት ተቋማት ብልሹ አሠራሮች ጋር መቆራኘት፣ እንዲሁም ክልላዊ የጋራ ስምምነቶች ይልቅ የተናጠል ፍላጎቶች ልቀው መገኘትና ለሠላም መደፍረስ መንስኤ መሆን የሥርዓታት ድክመት መገለጫ ሆነዋል። የአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ እነዚህን ክፍተቶች ከግምት በማስገባት የሥርዓታት መሻሻልና ለውጥ የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆን የለየ ሲሆን በዚህም የተሻሉ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂና የሕግ ማዕቀፎች ተግባር ላይ እንደሚውሉ ታሳቢ አድርጓል።

**የግሉ ዘርፍ ዋና የኢኮኖሚ ዕድገት ሞተር መሆኑን መቀበል የመንግሥትንና የግሉን ዘርፍ ትብብር የሚያጠናክር መሆኑ፦**

ባለፉት አሥራ አምሥት ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የመንግሥት ሚና ከፍተኛ ነበር። የመንግሥት የልማት ስኬቶች በአብዛኛው በኢኮኖሚና በማሕበራዊ መሠረተ ልማቶች ላይ የተንጸባረቁ ሲሆኑ ዋና የዕድገት ምንጮቹም ፍላጎትን የሚያበረታቱ እነዚህ ዘርፎች ነበሩ። ጥራት ያለውና ዘላቂ

የኢኮኖሚ ዕድገት መረጋገጥ የሚችለው በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ሲሆን በቀጣዮቹ አስር የልማት ዕቅድ የትግበራ ዓመታት የግሉ ዘርፍ በተለይም የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ በወሳኝ አምራች ዘርፎች ላይ እንደሚሰማራ ትልቅ ተስፋ ተጥሏል። ይህ ዕቅድ ዳር እንዲደርስም የግሉ ዘርፍ የመንግሥትን የልማት አቅጣጫ እንዲረዳና በምክክር ሲዳብርም እንዲገዛው እና መንግሥትም የግሉ ዘርፍ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች በተቀላጠፈ መንገድ እንዲፈታ የማድረግ ዓላማ ያለው ሲሆን በልማት ሂደቱ የመንግሥትና የግሉ ዘርፎች እውነተኛ ትብብር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

የታቀዱ ግቦችን ለማሳካት በሀገር ደረጃ ተግባራዊ የሚሆኑ የልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ፍላጎት ማዕቀፍ፣ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ማዕቀፍ፣ ሀገራዊ የተቀናጀ የልማት ማዕቀፍ እና የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት ማዕቀፍ እየተዘጋጁ መሆኑ እንዲሁም በክልል ደረጃ ዘመናዊና ዲጂታል የክትትልና ግምገማ ስርዓት ለመዘርጋት ትኩረት መሰጠቱ የልማት ዕቅዱን ልዩ ያደርገዋል።

# ክፍል ሦስት

# የአሥር ዓመት (2013-2022)

# የልማት ዕቅድ

# ምዕራፍ አንድ

# 1የልማት ዕቅዱ መነሻዎች እና የትኩረት አቅጣጫዎች

ምዕራፍ አንድ

1የልማት ዕቅዱ መነሻዎች እና የትኩረት አቅጣጫዎች

## 1.1. የልማት ዕቅዱ መነሻ ሀሳቦች

የልማት ዕቅዱ የተሳካ ይሆን ዘንድ ወደፊት ሊደረስበት የሚታሰበውን ደረጃ፤ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ፤ ወደፊት ሊከሠቱ የሚችሉ መልካም አጋጣሚዎችን እና ተግዳሮቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው። ከዚህ አንጻር ዕቅዱ የሀገራችን ርዕይ፣ እየተተገበሩ ያሉ እና በቀጣይ ተግባራዊ የሚሆኑ ሀገራዊ እና የዘርፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ በቅርቡ እየተካሄደ ያለው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም፤ ባለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የተመዘገቡ መልካም ውጤቶችና በትግበራ ሂደት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችና ያጋጠሙ ፈተናዎች፣ እንዲሁም ከባቢያዊ እና ዓለምአቀፋዊ ሁኔታዎችና ለውጦች በሀገራችን ኢኮኖሚ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሊያሳድሩ የሚችሉት አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ በልማት ዕቅዱ እንደ መነሻ ተወስደዋል። ዋና ዋና የዕቅዱ መነሻዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የአሥር ዓመት የልማት ዕቅዱ መነሻ ያደረገው ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ማድረግ ነው። ስለሆነም በቀጣይ ዓመታት የሚከናወኑ የልማት ተግባራትና የሚመዘገቡ የልማት ውጤቶች ወደዚህ ሀገራዊ ርዕይ በአስተማማኝ ደረጃ የሚያደርሱንና አማካይ ገቢን ብቻ ሳይሆን ብልጽግናን የሚያጎናጽፉን መሆን አለባቸው። በዚህም መሠረት ለብልጽግና ደረጃ መለኪያነት ሶሥት ዋና ዋና አመልካቾች የተመረጡ ሲሆን እነዚህም፡-

- የሰብዓዊ ልማት አመልካች (Human Development Index)፤
- የፈርጀ ብዙ ድህነት አመልካች (Multidimensional Poverty Index) እና
- ዜጎች በኑሮአቸው ላይ ያላቸው የእርካታ ደረጃ (Perception of Wellbeing) ናቸው።

## 1.2. የልማት ዕቅዱ ምሶሶዎች

በዚህም መሠረት የልማት ዕቅዱ የተመረጡ ቁልፍ ስትራቴጂካዊ ምሶሶዎች (strategic pillars) ያሉት ሲሆን እነዚህም (1)ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት እና የጋራ ብልጽግናን

ማረጋጋጥ፣ (2) የኢኮኖሚ ምርታማነት እና ተወዳዳሪነትን ማረጋጋጥ፣ (3) የቴክኖሎጂ አቅም እና ዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት፣ (4) ዘላቂ የዕድገት እና የልማት ፋይናንስን ማረጋገጥ፣ (5) የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት መሪነት ማረጋገጥ፣ (6) ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎችን የሚቋቋም አረንጓዴ ኢኮኖሚ በመገንባት፣ የሥርዓታት ለውጥን ማረጋገጥ፣ (7) የልማት ተጠቃሚነት እና ማህበራዊ አካታችነትን ማረጋገጥ፣ (8) የፍትሕ ተደራሽነት እና ውጤታማ የሕዝብ አገልግሎት ማስፈን እና (10) ዘላቂ የሰላም ግንባታና ማረጋገጥ ናቸው።

# ምዕራፍ ሁለት

# 2የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ

## 2.1 በማክሮ ኢኮኖሚ አመልካቾች ላይ ጥናት በማድረግ ለቀጣይ ዕቅዶች ግብአት እንዲሆኑ ማስቻል

በቀጣይ አስር ዓመት ሀገራዊ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን በመከተል በክልላችን ኢኮኖሚ ዉስጥ አዳዲስ የሚፈጠሩ አምራች ኢንዱስቲሪዎችን በክልሉ ሀብት ግመታ ማዕቀፍ ውስጥ በማካተት በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመፍታትና በቀጣይ 10 ዓመታት ውስጥ የክልሉን ኢኮኖሚዊና

ማህበራዊ ቀመሮችን ለመወሰን የሚያገለግሉ የማክሮ ኢኮኖሚ አመላካቾች ላይ የዳሰሳ ጥናት የሚካሄድ ሲሆን በዋናነት 2 የክልሉን የድህነት ምጣኔ ጥናት፣ 1 የስራ አጥነት ምጣኔ እና 1 የሃብት ገምታ የጥናት ዶክመንቶች የሚዘጋጁ ይሆናል። የጥናቱን ሰነድ ለባለድርሻ አካላት የማድረስ ሥራ ይሰራል።

## 2.2 የኢኮኖሚ ዕድገት እና የድህነት ቅነሳ

በክልሉ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ በተሰሩ ስራዎች ክልሉ ባለፉት አምስት ዓመታት 10.24 በመቶ አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን ከዚህም በመነሳት በሚቀጥሉት አስር ዓመታት (ከ2013 እስከ 2022) የክልሉ ኢኮኖሚ በአማካይ የ11.01 በመቶ ዕድገት እንዲመዘገብ ለማስቻል ይሰራል። የኢኮኖሚ ዕድገቱ በክፍላተ ኢኮኖሚ ሲታይ በሚቀጥሉት አስር ዓመታት የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል በአማካይ በየዓመቱ የ11.9፣ የ14.99 እና የ11.64 በመቶ ዕድገት እንዲያስመዘግቡ ታቅዷል።

**ሠንጠረዥ 5፡ የዘርፎች የዕድገት ምጣኔ (ከ2013-2022 በጀት ዓመት)**

| ዘርፍ/ንዑስ ዘርፍ | የተጨማሪ ዕሴት አማካይ ዕድገት ግብ በመቶኛ | | |
|---|---|---|---|
| | 2008-2012 | 2013-2017 | 2018-2022 |
| ግብርና ተዛማች | 9.03 | 13.4 | 11.90 |
| ኢንዱስትሪ | 10.87 | 22.5 | 14.99 |
| አገልግሎት | 12.41 | 8.3 | 11.64 |
| ጠቅላላ ምርት | 10.24 | 13.8 | 11.01 |

**ድህነት ቅነሳ በተመለከተ፡-**

ድህነት ማለት አንድ ሰው ለመኖር የሚያስፈልገው መሰረታዊ ነገሮች ከተቀመጠ ስታንዳርድ (ማለትም 2100 ካሎሪ) በመጠንም ሆነ በዓይነት በታች ሆኖ ሲገኝ ነው። ድህነት የሚሰላው የድህነት ወለል መሠረት ተደርጎ ሲሆን በተደረገው ጥናት የክልሉ የድህነት ምጣኔ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 19.0 በመቶ በ2022 ወደ 7 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ግብ ተቀምጧል።

## 2.1. የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ

የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ለማረጋገጥ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዘመን የግብርና ዘርፍ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 59.8 በመቶ ድርሻ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 42.0 በመቶ እንደሚቀንስ ታቅዷል። በአንጻሩ በዚሁ ጊዜ የኢንዱስትሪ ድርሻ ከ18.4 በመቶ ወደ 36.5 በመቶ ሲያድግ በተመሳሳይ የአገልግሎት ዘርፍ ድርሻ ከ24.3 በመቶ ወደ 21.5 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ታቅዷል።

**መዋቅራዊ ለውጥ**

| | የኢኮኖሚ ዘርፎች | አፈጻጸም | | ግብ |
|---|---|---|---|---|
| | | 2008 | 2012 | 2022 |
| 1 | ግብርና | 57.3 | 59.8 | 42.0 |
| 2 | ኢንዱስትሪ | 18.5 | 18.4 | 36.5 |
| 3 | አገልግሎት | 24.3 | 21.9 | 21.5 |

## 2.2. የፊሲካል ፖሊሲ

ለፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ምቹ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ከመፍጠር አንጻር የፊስካል ማዕቀፍ ትልቅ ትርጉም እንዳለዉ ይታወቃል። ባለፉት ዓመታት ተፈጻሚ የሆነዉ የፊስካል ማዕቀፍ ያሉትን የገቢ ዕቅዶችን በዉጤታማነት ከማስተዳደር፣ ገቢን ከማሳደግ እና የወጪ አመዳደብ በካፒታል እና ዕድገት ተኮር ዘርፎች ድህነትን በመዋጋት ረገድ ቁልፍ በሆኑ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ነበር። የፊስካል ማዕቀፉ ዓላማ የክልሉን የወጪ በጀትን በክልሉ ዉስጥ በሚሰበሰበዉ ገቢ በአጭር ጊዜ መሸፈን የሚከብድ ቢሆንም ከዓመት ወደ ዓመት በክልሉ የሚሰበሰብ ገቢን ማሳደግ፣ የፊዩራል ድጎማ እና የዉጭ ብድርና እርዳታ በሂደት በቅናሽ እያደገ እንዲሄድ ለማድረግ የክልሉ መንግስት ሚና ከፍተኛ መሆን አለበት። ሆኖም ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅና ከዓመት ዓመት በጀትን ከማሳደግ አንጻር ፈታኝ እየሆነ የሚሄድ በመሆኑ በግልጽ መታወቅ ይኖርበታል። ይህም በየፋይናንስ ምንጩ በክልሉ የሚቀጥሉት የ10 ዓመታት ፊስካል ማዕቀፍ አማካይ ዕድገት ትንበያዉ ያሳያል።

በልማት ዕቅዱ ዘመን የመንግስት ገቢና ወጪን ጤናማና ዘላቂ ለማድረግ ጠቅላላ የክልሉን ውስጥ ገቢን የሚያሳድግ አቅጣጫ ተቀምጧል። በዚህ መሠረት በታክስ ፖሊሲና ሕጎች ዙሪያ ማሻሻያ በማካሄድ፤ የታክስ አስተዳደር ሥርዓቱን በማዘመን፤ የታክስ መዋቅሩን በማሻሻልና ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴን በመከላከል ገቢን የማሳድግ ስራዎች ይሰራሉ።

በክልሉን የሚሰብሰብ የገቢ አቅም በ2012ዓ.ም ከነበረበት 1.292 ቢሊዮን ብር ወደ 14.058 ቢሊዮን ብር ለማድረስ ታቅዷል።

ከመንግስት በጀት አንጻር በዕቅድ ዘመኑ የበጀት ዕድገት በአማካይ በየዓመቱ 24 በመቶ እንዲያድግ ለማድረግ ግብ የተጣለ ሲሆን ጠቅላላ በጀት (ዕርዳታን ጨምሮ) በ2012 ከነበረበት ብር 4.932 ቢልዮን በቀጣይ 10 ዓመት መሪ ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት (በ2022) ወደ ብር 43.212 ቢሊዮን ከፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል። በ2022 ከሚጠበቀዉ በጀት ዉስጥ ብር 14.058 ቢሊዮን ከክልሉ ገቢ (በክልል ማዕከልና በአሰተዳደር እርኮኖች ከመንግስት ሠራተኞች ደመወዝ ስራ ግብር፣ ከጤና እና ትምህርት ተቋማት እንዲሁም ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢን ጨምሮ) በሌሎች ገቢ አይነቶች በጥረት እንደሚሰበሰብ ተተንብዮዋል።

ከመንግስት ወጪ አንጻር በቀጣይ አስር ዓመታት የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የመሠረተ ልማት፣ የማህበራዊ ልማት፣ የአካባቢ ጥበቃና ልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፍትሕና የዘላቂ ሰላም ግንባታ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ብር 40.433 ቢሊዮን የሚደርስ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ መደበኛ ወጪ ብር 21.377 ቢሊዮን እና የካፒታል ወጪ ብር 19.056 ቢሊዮን ይሆናል።

ዕድገትን በማፋጠን ድህነትን ለማስወገድ የሚረዱ የመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወጪ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ብር 28.503 (ቢሊዮን) የሚደርስ ሲሆን ይህም ከጠቅላላ የመንግስት ወጪ 70 በመቶ ድርሻ እንደሚይዝ ትንበያዉ ያሳያል። ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ድርሻ በመቶኛ ማየት ይቻላል።

የቀጣይ ተከታታይ ዓመታት የክልሉ በጀትና ወጪ ትንበያ

| ሠንጠረዥ 9፡ የቀጣይ ተከታታይ ዓመታት የክልሉ በጀትና ወጪ ትንበያ | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መነሻ አመት | የበጀት ትንበያ (በቢሊዮን ብር) | | | | | | | | | |
| ዝርዝ | የ2012 አፈጻጸም | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| በክልል የሚሰበሰብ ገቢ | 1.292 | 1.538 | 2.271 | 4.160 | 4.950 | 5.891 | 7.010 | 8.342 | 9.927 | 11.813 | 14.058 |
| ከፌደራል ድጎማ | 3.633 | 4.468 | 6.429 | 6.835 | 8.407 | 10.341 | 12.719 | 15.645 | 19.243 | 23.669 | 29.113 |
| ከዉጭ እርዳታ | 0.007 | 0.007 | 0.034 | 0.039 | 0.039 | 0.039 | 0.040 | 0.040 | 0.041 | 0.041 | 0.041 |
| ጠቅላላ በጀት እርዳታን ጨምሮ | 4.932 | 6.013 | 8.734 | 11.034 | 13.397 | 16.271 | 19.769 | 24.027 | 29.211 | 35.523 | 43.212 |
| ከጠቅላላ በጀት ለእድገት ተኮር ዘርፍ የተመደበ | 2.804 | 3.540 | 5.939 | 7.503 | 9.110 | 11.064 | 13.443 | 16.338 | 19.863 | 24.156 | 29.384 |
| መደበኛ በጀት | 4.401 | 5.856 | 4.454 | 5.627 | 6.832 | 8.298 | 10.082 | 12.254 | 14.897 | 18.117 | 22.038 |
| የካፒታል በጀት | 0.564 | 0.570 | 4.280 | 5.406 | 6.564 | 7.973 | 9.687 | 11.773 | 14.313 | 17.406 | 21.174 |
| ዝርዝር | መነሻ አመት አፈፃጸም | የወጪ ትንበያ (በቢሊዮን ብር) | | | | | | | | | |
| ጠቅላላ ወጪ | 4.803 | 6.089 | 6.418 | 10.324 | 12.535 | 15.225 | 18.498 | 22.482 | 27.332 | 33.239 | 40.433 |
| መደበኛ ወጪ | 4.390 | 5.546 | 4.321 | 5.458 | 6.627 | 8.049 | 9.780 | 11.886 | 14.451 | 17.573 | 21.377 |
| የካፒታል ወጪ | 0.413 | 0.542 | 2.097 | 4.866 | 5.908 | 7.176 | 8.718 | 10.596 | 12.882 | 15.666 | 19.056 |
| ከጠቅሊሊ ወጪ የዕድገት ተኮር ዘርፍ ወጪ | 2.918 | 3.433 | 5.939 | 7.278 | 8.836 | 10.732 | 13.040 | 15.848 | 19.267 | 23.431 | 28.503 |

# ምዕራፍ ሦስት

# 3 የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት ዕቅድ

### 3.1. የግብርና ልማት

የግብርናው ዘርፍ ለቀጣዮቹ አሥር ዓመታት የሚኖረውን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሀገሪቱን ሕዝብ የመመገብ፣ በመካከለኛ ጊዜ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ የማስገኘት፣ የመዋቅራዊ ሽግግርን እውን ለማድረግ፣ ለኢንዱስትሪውና ሌሎች ዘመናዊ ዘርፎች ርካሽ ምግብ፣ ግብዓትና የሰው ኃይል የማቅረብ፣ ለሌሎች ዘርፎች ምርቶች ገበያ ወይም ፍላጎት የማጎልበት እና በስፋት የሥራ ዕድል መፍጠር ከግብርናው ዘርፍ ይጠበቃል።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የግብርና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች**

**የመስኖ አቅምን በማጎልበት የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ፣**

ይህ አካሄድ የሚጠበቀውን የግብርና ትራንፎርሜሽን ለማምጣት በቂ ስላልሆነ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የመስኖ ልማት ላይ ኢንቨስት ማድረግ አለበት። ይህም ያሉንን የምርት ወቅቶች ከ3 እና 4 ጊዜ በማድረስ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ በላይ ለኢንዱስትሪና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ከማቅረብ አኳያ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያመጣል። የምንከተለው የመስኖ ልማት አካሄድ የጥቃቅንና የአነስተኛ መስኖ ልማት ሲሆን በአርሶአደር ደረጃ የሚከናወን ይሆናል። በመስኖ ስራ ላይ ትኩረት መስጠት በቤተሰብ ደረጃ የውሃን ተደራሽነት ከማረጋገጥ ባሻገር ተያያዥ ለሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች መጎልበት የራሱን አስተዋአ ያደርጋል።

**ክላስተር** Commodity based commercialization cluster **የተከተለ የአመራረት ዘይቤ ማጠናከር፣**

የተለያዩ ሥነ ምህዳር ያላቸው ዞኖች መኖራቸው  በየአካባቢያቸው ሁኔታ የላቀ ውጤት በሚያስገኝላቸው የግብርና ምርት ላይ እንዲያተኩሩ ቢደረግና ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችላቸው የቴክኖሎጂ ፓኬጅ መጠቀም ቢቻል የየአካባቢው ህዝብ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል። የሚመረጠው ሰብል በሀገርም ሆነ እንደ ክልል ያለው አንጻራዊ ጠቀሜታ ወይም የትኩረት ሰብል መሆኑ መለየት ያስፈልጋል። ለምሳሌ፣ ቤ/ሸኮ፣ ምዕ/ኦሞ፣ ኮንታ ፣ካፋና ሸካ ቆላማ አካባቢዎች የቅባት፣ የአገዳና ፍራፍሬ ሰብሎች ምርትን በከፍተኛ ደረጃ ማምረት ይቻላል። በተመሳሳይ በካፋና ዳውሮ  ሌሎች ዞኖች ... ደጋማ አካባቢዎች ስንዴ፣ ገብስና የደጋ ፍራፍሬ  አምራች ሆኖ የቆየ በመሆኑ የተሟላ ፓኬጅ በአግባቡ በመጠቀም በምርታማነትም ሆነ በጥራትም በገበያ ለመወዳደር የሚያስችል እድል አለው።

የቦሎቄ ሰብል ስንወስድ ሁሉም ዞኖች የቦሎቄ ክላስተር በጥራት በማምረት የውጭ ገቢያ በክፍተኛ ፍጥነት መጨመር ይቻላል፡፡

በስፔሻላይዜሽን ወይም በክላስተር አሰራር አ/አደሩ ወደ ኮሜርሻላይዜሽን ወይም በገበያ የተመራና ገበያ በሚፈለገው standard መጠን እንዲያመርት ይደረጋል፡፡ ስለሆነም ይህን ግብ ለማሳካት አሰራርና አደራጃጀቶችን ማስተካከል የዚሁ commodity-based commercialization cluster approach አካል ይሆናል፡፡ በክላስተር የሚመረጠው ምርት የገቢ ምርት የሚተካ በመሆኑ (import substitution) እንዲሁም የገበያ ሰብል አምርቶ ወደ ዓለም ገበያ ለመግባት በሚያስችል ጥራት ከፍተኛ ምርታማነት ለማረጋገጥ የድጋፍና ክትትል ስርዓት ይጠናከራል፡፡

**የከተማ ግብርና ስራዎች ማጠናከር፡-**

የከተማ ግብርና በከተማ ውስጥና በዙሪያው በአነስተኛ ቦታ ለምግብነትና ለሌሎች ጠቀሜታዎች ሊውሉ የሚችሉ ሰብል ልማት ስራን የሚያካትት ነው፡፡ በሌላ በኩል ምርት ማምረት፤ ምርት ውጤቶችን የማቀናባበር እና ለተጠቃሚው የማቅረብ ስራዎች ይሰራል፡፡ በተለይም በቤተሰብ ደረጃ በአነስተኛ ከሚከናወኑ የማምረትና ማቀነባበር/ እሴት ጭመራ እስከ ሰፋፊ የማምረትና ማቀነባበር ያጠቃልላል፡፡

**የበሽታና የተባይ ክስተት መከላከል ሥራን ማጠናከር፡-**

የተባይ ክስተት ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አሠራር ሥርዓት በመዘርጋት በክልላችን እየተስፋፉ የሚገኙ ዋና ዋና ተባዮች፣ የበሽታ ወረርሽኝ ክስተት ቀድሞ በመተንበይና አርሶ/አርብቶ አደሩን በቅድሚያ በማስጠንቀቅ ለመከላከል ዝግጅት ይደረጋል፡፡ መንግሥትም አስፈላጊውን ፀረ ተባይ፣ የመከላከያ ትጥቅ፣ የመርጫ መሣሪያና ሌሎች የሎጂስቲክስ አቅርቦት አስቀድሞ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

**የሜካናይዜሽን አገልግሎትን ማስፋፋት፣**

የሜካናይዜሽን አግልግሎት ማስፋፋት ግብርናን ለማዘመንና የምርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ለክልላችን መልከዓ ምድርና አግሮ ኢኮሎጂ ተስማሚ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀምና ተደራሽነትን ለአርሶ/አርብቶ አደር በማረጋገጥና አጠቃቀም ላይ የተመሰረተና የአርሶአደሩን አቅም ያገናዘበ ሀገር-በቀል የሜካናይዜሽን

ቴክኖሎጂዎች ፈጠራ፣ ማኑፋክቸሪንግና ስርጭት ስርዓት በማስፋፋት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የአርሶአደሩን ገቢ ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ ይቻላል፣ ምርታማነትና የምርት ጥራት በማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ የስራ እድል በመፍጠር ወጣቱን ትውልድ ወደ ግብርና መሳብ ያስችላል።

**የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሳደግ፡-**

በሁሉም ደረጃ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ቴክኖሎጂ አጠቃቀማችን ካለፉት ዓመታት ጋር ሲታይ ከፍተኛ የሆነ የአጠቃቀም ማነስ የታየበት እንደሆነ ለመገምገም ተችሏል። የቅድመና ድህረ ምርት አያያዝ እና አጠቃቀም ማሻሻል፣ በተለይም ከቴክኖሎጂዎች ውስጥ የማዳበሪያ መጠንና ጥምርታ እንዲሁም የሰብል ምርጥ ዘር አቀባበልና አፈጻጸም በሚፈለገው መጠን ለውጥ ያለመምጣቱ ሲታይ ምርትና ምርታማነት በቀጣይነት ለማሻሻል የቴክኖሎጂ አቀባበልና አጠቃቀም ማሻሻል ምርጫ የሌለው እንደሆነ በበቂ ደረጃ በሁሉም ተዋንያኖች ግንዛቤ መፍጠር እንደሚገባ እንደ አቅጣጫ መያዝ ይኖርበታል።

**የእንስሳት ሃብት ልማት፤ መኖ ልማትና ጤና ማሻሻል፦**

የእንስሳት ኃብት ልማትን መደገፍ የአረባብ ሥርዓትን ከማሻሻልና ገበያ መር ከማድረግ ይጀምራል። በተጨማሪም በእንስሳት ጤና አገልግሎት ውስጥ የግሉን ዘርፍ ሚና ማሳደግ፣ የመኖ ምርትን ማስፋፋትና የግብይት ማዕከላትን ማጠናከር ዋና ዋና ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች ናቸው። በተጨማሪም የኳራንቲን ማዕከላትን አጠናክሮ ወደ ሥራ ማስገባትና ሌሎች ከግብይት ጋር የተያያዙ መሠረተ ልማቶችን በመንግስትና የግሉ ዘርፍ ሽርክና ማሟላት፤ ዘመናዊ የምርት ዱካ ሥርዓት መተግበር፤ የፋይናንስና ኢንሹራንስ ስርዓቶችን ማሻሻል፤ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ከእንስሳት በሽታዎች የፀዱ ማድረግና ህገወጥ ንግድን ትርጉም ባለው መልኩ መቆጣጠር በቀጣይ ትኩረት የሚደረግባቸው ይሆናል። በተያያዘም በኤክስፖርት ቁራዎችና በአርቢዎች መካከል ቀጥታ የምርት ግብዓት ግንኙነቶችን ማዳበር ትኩረት ይደረግበታል።

**በግብርና ልማት የባለሀብቱን ተሳትፎ ማሳደግ፦**

ባለሃብቱ በዘርፉ ላይ ያለውን ተሳትፎ ለማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል። ይህም በምርምር፣ በኤክስቴንሽን፣ በፋይናንስና ኢንሹራንስ አቅርቦት፣ በግብዓት አቅርቦት፣ በግብርና ምርት፣ በግብይት መሰረተ ልማት ላይ የተሻሉ ድጋፍና ማበረታቻዎችን በመስጠት ዘርፉ ውስጥ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት ከሀገር በቀልና አለማቀፍ ባለሃብቶች ጋር በጥምረት የሚሰራ ይሆናል።

በተጨማሪም ባለሃብቱን የእሴት ጭመራ ስራዎች ላይ ለማሳተፍ በተለይም አግሮ ኢንዱስትሪዎችን መሰረት ያደረገ የእሴት ሰንሰለት ማጠናከር ስራ የሚሰራ ይሆናል።

**የሥራ ዕድል መፍጠር**

በገጠር የሚኖሩ ስራ ፈላጊ ዜጎች ፍትሃዊ፣ ዘላቂና ውጤታማ የስራ እድል ተፈጥሮላቸው የልማቱ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ በመሆን በ2022 ለሃገር እድገት እና ትራንስፎርሜሽን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

**የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት ሥራዎች ተግባራዊ ማድረግ፡-**

የሥነ-ሕይወታዊ ሥራዎች ስነ - ምህዳሩን ባማከለ መልኩ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ባላቸው የደን አግሮ ፎረስትሪ ችግኞች ላይ ትኩረት በመስጠት በአካባቢ፣ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አንጻር ውጤት ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ ልዩ ትኩረት ሰጥተን የምንሰራው ይሆናል። የአፈር ለምነት ችግርን ለመከላከል በክልላችን ያለውን የኮትቻና የአሲዳማ መሬት በመለየት የሌሎች ክልሎች ልምድን በመቀመር አርሶአደሩ ማሳውን ውጤታማ በሆነ ዘዴ እንዲጠቀምበት ለማስቻል የግብዓትና የብድር ሥርዓት የማመቻቸት ተግባር ይካሄዳል። የአፈር ምርምራ ሥራውን አጠናክሮ ለመቀጠል ያሉት ላብራቶሪ በሙሉ አቅሙ እንዲንቀስ ድጋፍ ይደረጋል።

**ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ዘላቂ ግብርና ልማት ማካሄድ፦**

የአየር ንብረት ለውጥ የዝናብን መጠን በማዛባት የግብርና ዘርፉን በመጉዳት የምግብ ዋስትና እንዳይረጋገጥ ከማድረጉም በላይ የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎችና ፀረ-ሰብል ተባዮች እንዲከሠቱ ያደርጋል። በመሆኑም በቀጣይ የግብርና ልማትን ዘላቂነትበማረጋገጥ ከግብርና ልማት የሚወጣውን የከባቢ ሙቀት ሳቢ ጋዞች ልቀትን መጠን በመቀነስ የዘርፉን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የግብርና ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል**

በልማት ዕቅዱ ዘመን በአጠቃላይ የግብርናው ዘርፍ ዓላማዎች ግብርናን ምርታማና ተወዳዳሪ በማድረግ የአርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ገቢ ማሳደግና ከድህነት ማላቀቅ፣ ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ በተለይም ግብርናን በማዘመን ሀገራዊ የምግብና ስርዓተ-ምግብ ፍላጎትን ማሟላት፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ማቅረብ፣ እሴት መጨመርና በገጠር በቂ የሥራ ዕድል መፍጠር ናቸው። እነዚህን ጥቅል ዓላማዎች ዕውን ለማድረግም ዋና ዋና ስትራቴጂክ ዓላማዎች የተቀመጡ ሲሆን እነዚህም

ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ገበያ ተኮር የእንሰሳትና ዓሣ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፣ እና ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀምን ማሻሻል ናቸው። በተጨማሪም የግብርና ግብዓትና ምርት ግብይትን ማሳደግና ማዘመን እንዲሁም በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ በግብርና ምርምር፣ በግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎትና በህብረት ሥራ ማኅበራት የሚገለጹ ቁልፍ የስኬት መስኮችም የዘርፉን ስትራቴጅክ ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ ቁልፍ የውጤት መስኮች ናቸው። የዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች በተለይም የምግብ ዋስትና የሥርዓተ-ምግብ ዋስትና እና የሥርዓተ-ፆታ ነክ ጉዳዮችን ማሻሻል፣ የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን መቀነስ፣ እንዲሁም የሥራ ዕድል መፍጠር ተጨማሪ ዓላማዎች ናቸው።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የግብርና ልማት ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል፥**

ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሰብል ምርትና ምርታማትን ለማሳደግ የሚንከተለው የአመራረት ስርዓት በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች ሲሆን የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች ሶስት የምርት ወቅት (መኽር፣ በልግና መስኖ) መሰረት አድርጎ የሚለማ ይሆናል። በዕቅዱ የተካተቱ ሰብሎች አዝርዕት እና ሆርቲካልቸር ይይዛል። በሁሉም የአመራረት ስርዓቶች (በልግ፣ መኽር፣ መስኖ) እና የሰብል ዓይነቶች የሰብል ምርትን ከ54.6 ወደ 117.03 ሚሊየን ኩንታል (በየዓመቱ በአማካይ 10% ዕድገት) ለማድረስ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን የአዝርዕት ምርትን ከ19.3 ወደ 36.25 ሚሊዬን ኩንታል (በየዓመቱ በአማካይ 8.2% ዕድገት) እና የሆርቲካልቸር (አትክልት፣ ስራስር እና ፍራፍሬ) ምርትን 35.3 ወደ 76.22 ሚሊዬን ኩንታል (በየዓመቱ በአማካይ10.1% ዕድገት) ምርትን ለማድረስ ዕቅድ ተይሏል።

**የአዝርዕት ሰብሎች ልማትን በተመለከተ**

የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች አጠቃላይ የአዝዕርት ሰብሎች ምርት በቀጣይ አስር ዓመታት የአዝርዕት ሰብሎች በበልግና በመኽር አሁን ከሚመረተው 19,314,957 ኩ/ል በየዓመቱ በአማካይ በ8.2% በማሳደግ ወደ 35,056,264 ኩ/ል ለማድረስ ታቅዷል። የአገዳ ሰብል ምርት በመነሻ ዓመት (2014) የነበረበት ከ12,521,053 ኩ/ል በመውሰድ በየዓመቱ በአማካይ በ7.7% በማሳደግ በ2022 ዓ/ም ወደ 22,173,920 ኩ/ል ማድረስ፤ የብርዕ ሰብል ምርት ከ3,802,442 ኩ/ል በየዓመቱ በአማካይ በ 9.1% በማሳደግ ወደ 7,271,624 ኩ/ል ማድረስ፤ የጥራጥሬ

ሰብል ምርት ከ 2,826,435 ኩ/ል በየዓመቱ በአማካይ በ 8.8% በማሳደግ ወደ 5,307,025 ኩ/ል እና የቅባት ሰብል ምርት ከ165,028 ኩ/ል በየዓመቱ በአማካይ በ9.2% በማሳደግ ወደ 303,695 ኩ/ል ለማድረስ ዒላማ ተይሏል፡፡ ከምርታማነት አንጻር በመነሻ ዓመት (2014) የነበረበት በመነሻነት በመውሰድ በ2022 የሚደረስበት ምርታማነት የአገዳ ሰብል ከ44 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 65 ኩ/ል በሄ/ር፣ የብርዕ ሰብሎች ከ27 ኩ/ል በሄ/ር ወደ 45 ኩ/ል በሄ/ር፣ በጥራጥሬ ሰብል ከ18 ኩ/ል /ሄ/ር ወደ 28 ኩ/ል በሄ/ር፣ በቅባት ሰብሎች ከ9 ኩ/ል/ሄ/ር ወደ 14.3 ኩ/ል በሄ/ር ምርታማነት ለማድረስ ታቅዶዋል፡፡

የተለየ ትኩረት ከሚሹ አዝርዕት ሰብል ውስጥ አነስተኛ ይዞታ እርሻ በመስኖ የሚመረተው የስንዴ ምርት አሁን ካለበት 16,426 ኩ/ል ወደ 31,338 ኩንታል ይደረሳል፡፡ በአጠቃላይ አነስተኛ ይዞታ የአዝርዕት ምርት በመነሻ ዓመት (2014) በመኽር ከነበረበት ከ6.67 ሚሊየን ኩንታል በ2022 ዓመት ወደ 12.66 ሚሊየን ኩንታል፣ (በ2014) ዓመት በበልግ ከነበረበት ከ 12.56 ሚሊየን ኩንታል ወደ 22.3 ሚሊየን ኩንታል ለማድረስ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን በ8 ዓመቱ መጨረሻ በመኽር ከተገኘው ከአጠቃላይ ምርት የ49.6 በመቶ እና በበልግ የ50.4በመቶ የምርት ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

በዋና ዋና በክላስተር የሚለሙ አዝርዕት ሰብሎች የኩታ ገጠም እርሻ በአነሰተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮች አጠቃላይ ከሚመረተው የማሳ ሽፋን 27.4 በመቶ ድርሻ ያለው ሲሆን በcommodity based commercialization cluster በተመሳሳይ ሰብል እንዲያለሙ ይደረጋል፡፡ በዚህም በዋናነት በቆሎ፤ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ ቦሎቄ፣ ሰሊጥ፣ አቮካዶ፣ ፓፓዬ፣ ሙዝ፣ አፕልና አናናስ በልዩ ትኩረት የሚመረቱ ሰብሎች ሲሆኑ በሁሉም አመራረት ሰርዓቶች (በልግና መኽር) በአዝርዕት ሰብሎች አሁን ከሚመረተው 4,872,786 ኩ/ል ምርት በየዓመቱ በ 8.6% በማሳደግ በ2022 ዓ/ም ወደ 12,516,282 ኩ/ል ለማድረስና የመሬት ሽፋኑን ከነበረበት 149,021 ሄ/ር በ2022 ዓ/ም ወደ 174,601 ሄ/ር መሬት በክላስተር ሰብሎች ለመሸፈን ታቅዷል፡፡

በተጠቃሚዎች ተቀባይነት ያለው የሰብል ቴክኖሎጅ ማቅረብ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ሁሉንም የእሴት ሰንሰለት ተከትሎ ማፍለቅ ተግባር በምርምር ተቋማት የሚካሄድ ሲሆን በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ምርት የሚሰጡና ተባይን መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎችን ወይም ምርታማነትን የሚያሻሽሉ ቴክኖሎጂን በመኮረጅ እና የአግሮ-ኢኮሎጂ ተስማሚነታቸውን በማጥናት የኤክስቴንሽን ተግባራትን በማጠናከር የበቆሎ ምርታማነትን አሁን ከሚገኝበት 40.2

ኩ/ል በሄክታር የሆነ ክልላዊ አማካይ ወደ 69 ኩ/ል በሄክታር፣ የስንዴን ከ40 ወደ 65፣ የጤፍ ከ14.3 ወደ 24፣ የገብስ ከ26 ወደ 41 እና የማሽላ ከ18 .4 ወደ 31፣ የቦሎቄ ከ17.3 ወደ 28፣ ሰሊጥ ከ5.1 ወደ 8.1 ለማድረስ እንደ ግብ ተቀምጧል። ይህም የምርታማነት ደረጃ የተወሰደው የተሻሻለ የሰብል ቴክኖሎጂን ተጠቃሚ ሞዴል አርሶ አደሮች በ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ላይ የደረሱበትን ከ10 ዓመት በኋላ የሁሉም አርሶ አደሮች ክልል አቀፍ አማካይ እንዲሆን የሚያስችል ከፍተኛ ጥረት በሁሉም የባለድርሻ አካላት እንደሚደረግ በታሳቢነት ተወስዶ ነው።

**የሆርቲከልቸር ምርትና ምርታማነት፤**

የአትክልት ሰብል መስኖን ጨምሮ ምርት በመነሻ ዓመት (2014) ከነበረበት 9,442,571 ኩ/ል ወደ 37,849,610 ኩ/ል ማድረስ፤ በፍራፍሬ ሰብል መስኖን ጨምሮ ምርት በመነሻ ዓመት (2014) ከነበረበት 5,639,057 ኩ/ል ወደ 13,640,435 ኩ/ል ማድረስ፤ የስራስር ሰብል ምርት በመነሻ ዓመት (2014) ከነበረበት 20,215,023 ኩ/ል ወደ 50,519,050 ኩ/ል እና በእንሰት ሰብል ምርት በመነሻ ዓመት (2014) ከነበረበት 7,224,474 ኩ/ል ወደ 17,361,509 ኩ/ል ለማድረስ ዒላማ ተይዟል።

በክላስተር የሚለሙ ሰብሎችን ፖቴንሻልን መሰረት ባደረገ መልኩ በሁለት ቀጠና ለመክፍል ታቅዷል። በዚህ መሰረት ቀጠና አንድ፡- ሸካ፣ ቤንች ሸኮና ም/ኦሞ ሲሆኑ በእነዚህ አከባቢዎችም በፖቴንሻል ደረጃ በዋናነት የሚለሙ ሰብሎች በአዝርዕት ሰብሎች (በቆሎ፣ ሩዝ፣ ሰሊጥ፣ ገብስ፣ አተር፣ ባቄላ) ሲሆኑ በሆርቲካልቸር ሰብሎች (አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ አናናስ፣ እንሰትና ስራስር፣ ቀ/ሽንኩርት እና ቲማቲም ወዘተ...) ሲሆኑ፤

ቀጠና ሁለት፡- በዚህ ቀጠና የተካተቱ አከባቢዎች ካፋ፣ ኮንታና ዳዉሮ ሥነ- ምህዳራቸዉ የሚያካልለው ከቆላ እሰከ ደጋ ሲሆን በእነዚህ አከባቢዎችም በፖቴንሻል ደረጃ በዋናነት የሚለሙ ሰብሎች በአዝርዕት ሰብሎች (ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ ዳጉሳ፣ በቆሎ፣ አተር፣ ባቄላ፣ ቦሎቄ) ሲሆኑ በሆርቲካለቸር ሰብሎች (አቮካዶ፣ ማንጎ፣ እንሰትና የስራስር ሰብሎች፣ ቀ/ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ጥቅል ጎመን ወዘተ...) ናቸው።

የተቀናጀ ተባይ መከላከል ዘዴን አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ በማሳደግ በ10 የተመረጡ ሰብሎችና ተባዮች ላይ መከላከል እንዲካሄድ በማድረግ ሊባክን የሚችለው የምርት መጠን በ1% ዝቅ እንዲል ይደረጋል፤ የድህረ ምርት ብክነት ዒላማ በዝርዝር ሰብሎች የተቀመጠ ሲሆን ለማሳያነት የስንዴ፣ የበቆሎ፣ የማሽላ እና የቦሎቄ ምርት ብክነት ከ13.5 በመቶ ወደ 5 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ታቅዷል።

የግብርና ግብዓቶች አቅርቦትና የምርጥ ዘር አቅርቦት በ2014 ከነበረው 135,227 ኩ/ል በየምርት ዘመኑ 15 በመቶ በማሳደግ በ2022 መጨራሻ 358,763 ኩ/ል ይደርሳል ተብሎ ታቅዷል። በክልላችን የአፈር ማዳበሪያ ሥርጭት ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ መጥቶ በ2014 ዓ/ም 414,190 ኩንታል የነበረው የአቅርቦትና ስርጭት መጠን በ2022 የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ሥርጭት 1,148,406 ኩንታል ለማድረስ ታቅዷል።

የተመሰከረለት ዘር አቅርቦትና ሥርጭት በተመለከተ፡- የብርዕና አገዳ ሰብሎች በ2015 ምርት ዘመን በ 1,296 ሄክታር ማሳን በመስራች ዘር በመሸፍን በአማካይ 30 ኩንታል በሄክታር በማገኘት እና በየዓመቱ በአማካይ 15 በመቶ በማሳደግ በ2022 ምርት ዘመን 103,410 ኩ/ል የተመሰከረ ዘር፣ የጥራጥሬ ሰብሎች በ2015 ከሚገኘው 1,560 ኩ/ል ለ2022 ምርት ዘመን በማምረት በአማካይ 17 ኩ/ል በሄክተር በማምረት 4,709 ኩ/ል የተመሰከረለት ዘር፣ የቅባት ሰብሎች በ2015 ምርት ዘመን የሚሰበሰበውን 363 ኩ/ል በየዓመቱ በአማካይ 10 በመቶ በማሳደግ በዕቅድ መጨራሻ ለ2022 ምርት ዘመን በአማካይ 14 ኩ/ል በሄክታር በማምረት 1232 ኩ/ል የተመሰከረለት ዘር፣ የወጥድንችና የጎደሬ በ2015 ምርት ዘመን የሚሰበሰበው 18,480 ኩ/ል በአማካይ 15 በመቶ በማሳደግ በዕቅድ መጨራሻ ለ2022 ምርት ዘመን በአማካይ 138 ኩ/ል በሄክተር በማምረት 56,580 ኩ/ል የተመሰከረለት ዘር በክልሉ ውስጥ ለማምረት ታቅዷል። የጓሮ አትክልት ምርጥ ዘር አቅርቦትን በተመለከተ በ2015 ምርት ዘመን 528 ኩ/ል ከነበረበት የጓሮ አትክልት ሰብሎች ምርጥ ዘር በየዓመቱ በአማካይ 15 በመቶ በማሳደግ በዕቅድ ዓመቱ መጨራሻ 2022 ምርት ዘመን 1,356.9 ኩ/ል ለማቅረብ ታቅዷል። በተጨማሪ ከኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን እንዲሁም የፓ ይነር ዘር አቅራቢ ድርጅቶችን በመጠቀም በ2015 የነበረው 85,455 ኩንታል አቅርቦት በየአመቱ በአማካይ 15 በመቶ በማሳደግ 2022 ወደ 227,312 ኩ/ል፣ የጥራጥሬ ሰብሎችን በ2015 የነበረው 9,242 ኩንታል አቅርቦት በየአመቱ በአማካይ 15 በመቶ በማሳደግ 2022 ወደ 24,584 ኩ/ል እና የቅባት ሰብሎች በ2015 ምርት ዘመን 175 ኩ/ል የነበረው ምርጥ በየአመቱ በአማካይ 15 በመቶ በማሳደግ 2022 ወደ 466 ኩ/ል ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በአገዳ ሰብሎች አባዝቶ ለማቅረብ እንቅስቃሴ እየተደረገ ካለው በመነሳት የተለያዩ ምንጮችን በመጠቀምና ዘር አባዥ ድርጅቶችን በመደገፍ በቀጣይ አመታት እንዲመረት በመድረግ በአገዳ፣ በብዕር፣ በጥራጥራና በቅብአት ሰብል በ2015 የነበረዉን 94,872 በየአመቱ በአማካይ 15 በመቶ በማሳደግ 2022 ወደ 252,362 ኩ/ል ምርጥ ዘር ለማቅረብ ታቅዷል።

የፀረ-ተባይ ኬሚካል አቅርቦትና ስርጭትን በተመለከተ በ2015 የነበረው 62,171 ሊተር አቅርቦት በየአመቱ በአማካይ 15 በመቶ በማሳደግ 2022 ወደ 165,363 ሊትር ለማቅረብ ታቀደ ሲሆን የአረም መከላከያ ኬሚካል በ2015 የነበረው 30,000 ሊትር አቅርቦት በየአመቱ በአማካይ 15 በመቶ በማሳደግ 2022 ወደ 79,801 ሊትር የበሽታ መከላከያ ኬሚካል በ2015 የነበረው 12,171 ሊትር አቅርቦት በየአመቱ በአማካይ 15 በመቶ በማሳደግ 2022 ወደ 32,362 ሊትር እና የተባይ መከላከያ ኬሚካል በ2015 የነበረው 20,000 ሊትር አቅርቦት በየአመቱ በአማካይ 15 በመቶ በማሳደግ 2022 ወደ 53,200 ኪ/ግ አግሮ-ኬሚካል ለማቅረብ ታቅዷል።

## የግብርና ሜካናይዜሽን ማስፋፋት

አርሶ/አርብቶ አደሩን ከጉላ ቀር የእርሻ መሳሪያዎች የአሰራር ዘዴዎች አላቆ ምርትና ምርታማነቱን ከፍ ለማድረግ፣ የኢኮኖሚ አቅሙ ለማሳደግና ምግብ ዋስትናው ለማረጋገጥ የማምረት ተግባሩ በተሻሻሉ የእርሻ ልማት መሳሪያዎችን /በግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን/ እንዲደገፍ ይደረጋል። በዚህ መሠረት በ2015 ከነበረው 4544 የቅድመ ምርት ቴክኖሎጂ እቅድ በአማካይ 15% በመጨመር በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 6,833 ይደርሳል። ድህረ ምርት ቴክኖሎጂ በ2015 በጀት ዓመት መጨራሻ ከደረስንበት 4033 በ15% በመጨመር በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 6,912 ይደርሳል። የትራክተር የኪራይ አገልግሎት በ2015 በጀት ዓመት ከደረስንበት 37 ትራክተር በ15% በመጨመር ወደ 102 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን የኮምባይነር የኪራይ አገልግሎት በ2015 በጀት ዓመት በእቅዱ መነሻ ዓመት አገልግሎቱ ባይጀምርም ባልነበረበት በ2022 6 ታቅዷል። እንዲሁም የትራክተር ግዥ ማመቻቸት በ2014 ከ 55 በመነሳት በ2022 ቁጥሩ 142 እንዲሁም በ2015 ከነበረዉ 2 የኮምባነር ገዥ በማመቻቸት በ2022 9 የሚደርስ ይሆናል ።

ተፋሰስን መሰረት ያደረገ የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራዎችን በማካሄድ ለአየር ንብረት ለዉጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ከፍተኛውን አስተዋጽኦ ማበርከት፤በ2014 በማህበረሰብ ተሳትፎ አግሮ ኢኮሎጂን መሰረት በማድረግ የለማዉን 110209 ሄ/ር በ2022 ወደ 220,717 ሄ/ር በማሳደግ ገቢ የሚያመነጭ የበለፀገ ተፋሰስ በመፍጠር ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ፣ በ2015 ምርት ዘመን ላይ የተለያዩ የውሃ አማራጮችን

በመጠቀም በአነስተኛ መስኖና በባህላዊ መንገድ ከሚለማዉ 46,291.3 ሄ/ር በ2022 በ 65,000 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችል ዉሃ ለማቅረብ ግብ ተጥሏል።

**የእንስሳት ዝርያን በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር**

የወተት ምርትን በ2015ዓ/ም ከዳልጋ ከብት ከ 164,835.67 ቶን ሊትር ዕቅድ ከነበረበት በዓመቱ መጨረሻ ወደ 365,648.856 ሊትር ማድረስ፤ የስጋ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የዳልጋ ከብት በ2015 ከነበረበት 44,037.24 ቶን በ2022 ወደ 122,518.94፣ በግ በ2015 ከነበረበት 17,455.09 በ2022 ወደ 43,667.76 ቶን፣ እና ፍየል በ2015 ከደረሰበት 12,529.92 ቶን ከነበረበት በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደ 33,179.86 ቶን እና ለማድረስ ይሰራል።

የዶሮ ስጋ ምርትን በ2015 ዓ.ም ከደረሰበት 5,828.03ቶን በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደ 24,655.40ቶን ለማድረስ ይሰራል። የእንቁላል ምርትን በ2015 ዓ.ም ከነበረዉ 6,274.01 ቶን እንቁላል በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደ 12,789.33 ቶን እንቁላል የማሳደግ ስራ ይሰራል።

**የዓሣ ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ**

በክልሉ ከሚገኙ ከሀይቆች፣ ግድቦች፣ ወንዞችና ሌሎች ትናንሽ የውሃ አካላት እንዲሁም አኳካልቸር በ2015 ዓ.ም ከተደረሰበት ከ 3,39.36 ቶን በየአመቱ በአማካይ ከሀይቆች፣\ ግድቦች፣ ወንዞችና ሌሎች ትንንሽ የውሃ አካላት እና በአኳካልቸር በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 9,55.27 ቶን ለማድረስ ይሰራል።

**የማር ምርትና ምርታማትን ለማሳደግ**

ለሀገር ውስጥ ፍላጎት እና ለኤክስፖርት የማር ምርት በ2015 ዓ.ም ከደረሰበት 52,070.67 ቶን ከነበረበት በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 79591.19 ቶን ለማድረስ ይሰራል። የሰም ምርትን ደግሞ ከ5206.27ቶን ከነበረበት በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 7962.2 ቶን ለማድረስ ይሰራል። የጨፈቃ ቀፎ ቁጥር በ2015 ዓ.ም ከነበረበት 48,980 በየዓመቱ በማሳደግ ወደ 101,398፤የሽግግር ቀፎ ቁጥር በ2015 ዓ.ም ከነበረበት 26,235 በየዓመቱ በማሳደግ በ2022 ዓ/ም 89009፤ እና ዘመናዊ ቀፎን በ2015 ዓ.ም ከነበረበት 10527 በየዓመቱ በማሳደግ 27,026 ለማድረስ ይሰራል።

**የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል**

በተመሳሳይ መልኩ ዝርያቸው የተሻሻሉ ዲቃላ የሥጋ ዳልጋ ከብቶች በ2015 ዓ.ም ከነበረበት 17098 በማሳደግ በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 58010 ለማድረስ ይሰራል። ዝርያቸው የተሻሻሉ ዲቃላ በጎች በ2015 ከነበረበት 173549 በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 566977 ለማድረስ:: ዲቃላ ፍየሎች በ2015 ከነበረበት 25941 በ2022 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 52684 ለማድረስ ይሰራል።

አዲስ የመኖ ማባዣ ጣቢያ ለማቋቋም በ2015 ዓ.ም ከነበረበት 177 በማሳደግ በ2022 ዓ.ም ወደ 229 ለማሳደግ የሚሰራ ሲሆን በመኖ ዘር ብዜት የሚሰማሩ ባለሀብቶችን በ2015 ዓ.ም ከነበረበት በቁጥር 139 በማሳደግ በ2022 ዓ.ም ወደ 310 የማድረስ ስራ የሚሰራ ይሆናል። የተሻሻለ የመኖ ዘርን ለአርሶ አደር ማሰራጨትን በ2015 ዓ.ም ከደረሰበት 596.98 ኩ/ል በማሳደግ በ2022 ዓም መጨረሻ ወደ 1053.32 ኩ/ል፣ የመኖ ሳር ግንጣይና ቁርጥራጭን በ2015 ዓ.ም ከደረሰበት 316.9 ቢሊየን በየአመቱ በማሳደግ በ2022 ዓ/ም መጨረሻ ወደ 787.52 ቢሊየን እንዲሁም የመኖ ችግኝ ተከላን በ2015 ዓ.ም ከደረሰበት 167.662 ሚሊየን በየአመቱ በማሳደግ በ2022 ዓም መጨረሻ ወደ 235.41 ሚሊየን ለማድረስ ይሰራል።

የቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ምርትና ምርታማነት ከማሳደግ አንተጻር የቡና ሰብል ምርታማነት በ2014 ምርት ዘመን ከደረሰበት 7.9 ኩ/ል በሄ/ር በ2022 ዓ.ም ወደ 12 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ፣ በቡና ልማት የተሸፈነ መሬት በ2014 ዓ.ም 559,038 ሄ/ር ከነበረበት በ2022 ዓ.ም ወደ 791,053 ሄ/ር ለማሳደግ፣ በ2014 ምርት ዘመን 239,021 ቶን የነበረዉን አጠቃላይ የቡና ምርት በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ወደ 544,001 ቶን ለማድረስ እቅድ ተይዟል። የሻይ ምርታማነት  በአውት ግሮወር ትስስር እና በባለሀብት እየለማ ያለውን በ2014 ዓ.ም ከነበረበት 34 ኩ/ል በሄ/ር በ2022 ዓ.ም ወደ 38 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ፣ በሻይ ልማት የተሸፈነ መሬት በ2014 ዓ.ም 2,276 ሄ/ር ከነበረበት በ2022 ዓ.ም ወደ 4,789 ሄ/ር ማሳደግ፣ እቅድ ተይዟል። በዋና ዋና እና በአነስተኛ የቅመማ ቅመም ሰብሎች ልማት የተሸፈነ መሬት በ2014 ዓ.ም 73,190 ሄ/ር ከነበረበት በ2022 ዓ.ም ወደ 125,224 ሄ/ር ማሳደግ፣ በመነሻ ዓመት 271,759 ቶን ምርት ይገኝ ከነበረበት በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ወደ 648,253 ቶን ለማድረስ ታቅዷል።

የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ምርቶች የገበያ አቅርቦት ከማሳደግ አንጻር በቀጣይ አስር አመት የቡና ምርት የኤክስፖርት አቅርቦት መጠን በ2014 ዓ.ም 63,470.3 ቶን ከነበረበት በ2022 ዓ.ም ወደ 99,085 ቶን ማድረስ፣ የሻይ ምርት አቅርቦት መጠን በ2014 ዓ.ም 5,180.9 ቶን ለገበያ ይቀርብ ከነበረበት በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ወደ 10,881 ቶን ማድረስ፣ የቅመማ ቅመም ምርት የገበያ አቅርቦት በ2014 ዓ.ም 39,163.8 ቶን ለገበያ ይቀርብ ከነበረበት በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ወደ 66,521 ቶን ለማድረስ ዕቅድ ተይዟል።

የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉና አርሶ/አርብቶ አደሩን በገበያ ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን፣ የአሰራር ዘዴዎችንና መረጃዎችን በፍጥነትና በተከታታይነት በማፍለቅ/ በማበልፀግ እንዲሁም በሌሎች ምርምር ተቋማት የፈለቁ ተክኖሎጂዎችን በማላመድና ማቅረብን፤ ዋነኛ የትኩረት መስኮች በማድረግ የሰብል ቴክኖሎጂዎችን ተያያዥ ከሆኑ ዕውቀቶችና መረጃዎች ጋር በማላመድና በማፍለቅ ማቅረብ በሰብል ምርምር ዘርፍ በየዓመቱ 1(አንድ) ቴክኖሎጂን በማፍለቅና 9 ያለቀላቸውን ዝርያዎች፣ በማስገባት በማላመድ፣ 128 ተጨማሪ በማቅረብ በ2014 ቀርበው የነበሩትን 168 የሰብል ቴክኖሎጂዎች፤ ወደ 196 ለማሳደግ፣ የእንስሳት ቴክኖሎጂዎችን ተያያዥ ከሆኑ ዕውቀቶችና መረጃዎች ጋር በማላመድ በማፍለቅ ማቅረብን በተመለከተ 128 ተጨማሪ በማቅረብ በ2012 ዓ.ም 67 የነበረውን የእንስሳት ቴክኖሎጂ፤ መረጃና ዕውቀት አቅርቦት በ2022 ወደ 195 ለማድረስ ግብ ተጥሏል። ሁሉንም የግብርና ሥነ-ምህዳሮች ያማከለ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በማስተዋወቅ ፍላጎት እንዲፈጠር ለማድረግ በሰፋፊ ኩታ ገጠም የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ ስራ በእቅድ ዓመቱ መጨረሻ 16 (አስራ ስድስት) በ8 ፓኬጅ የተደገፈ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ይከናወናል። የክልሉን የመነሻ ዘር ፍላጎት መሠረት በማድረግ የአዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎች መነሻ ዘር ለማባዛት እስከ 2013 ዓ.ም 1,054 ኩ/ል ዘር የነበረውን በአመት በአማካይ ወደ 382 ኩንታል በማባዛት እስከ 2022 ዓ.ም. 3,056 ኩንታል ለማቅረብ፣ በጥራጥሬ ሰብሎች ዘር ብዜት እስከ 2013 ዓም 350 ኩንታል የነበረውን በ2022 ዓ.ም 1,128 ኩንታል፣ በቁርጥራጭ/ግንጣይ መልክ የሚባዙ የስራስር ሰብሎች በ2013 15 ሚሊዮን የነበረውን በ2022 ወደ 48 ሚሊዮን ለማቅረብ፣ በሙዝ መነሻ ዘር ብዜት እስከ 2014 ዓ.ም 3,200 ችግኝ የነበረውን በ2022 ዓ.ም 17,064 ችግኞች ለማቅረብ የእንስት ኮርም ብዜት እስከ 2013 ዓ.ም 1200 የነበረውን በ2022 ዓ.ም

ወደ 9,600 ለማድረስ፣ በስናር ዘር ብዜት እስከ 2013 ዓም 12 ኩንታል የነበረውን በ2022 ዓም ወደ 96 ኩንታል ዘር ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

ብቁና ውጤታማ የሆኑ የጎ/ሥ/ማህበራት መፍጠር፣ አቅርቦትና ሥርጭት በማሻሻል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፣ የላቀ የጎብረት ሥራ ማህበራት የገበያ ድርሻ እና የላቀ ቁጠባና ኢንቨስትመንት እንዲኖራቸው ማድረግ፣ የጎብረት ሥራ ማህበራት ደህንነትና ህጋዊነትን ማርጋገጥ ዋና የትኩረት አቅጣጫ በማድረግ የተጣለው የህብረት ስራ ማህበራት የትኩረት አቅጣጫ ሲሆኑ ጎብረት ሥራ ማህበራትን ማደራጀትና ማጠናከርን በተመለከተ አሁን ያለውን 2,369 የመሰረታዊ ጎብረት ሥራ ማህበራት በ28% በማሳደግ 3,032 ለማድረስ፣ 19 ዩኒየኖች ቁጥር በ17% በማሳደግ 23 ለማድረስ፣ በነባረና አዲሰ የጎብረት ሥራ ማህበራት አባላት ቁጥርን አሁን ካለበት 205 ሺህ ወደ 100,920 አባላት ለማሳደግ፣ የገ/ቁ/ብ ጎብረት ሥራ ማህበራት ቁጠባ በ2014 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ብር 87 ሚሊዮን ወደ ብር 1,481,343,809 ለማድረስ፣ የጎብረት ሥራ ማህበራትን በማጠናከርና በማደራጀት በመሰረታዊ ጎብረት ሥራ ማህበራትና በዩኒየኖች አሁን ያለውን ካፒታል በ150% ማሳደግ፣ የግብርና ግብይት ብድር አቅርቦት በማመቻቸት በ2014 ከነበረዉ የዓመቱ አፈጻጸም መነሻ ብር 52,000,000 አቅርቦት ወደ 1,502,125,812.32 ብር ማሳደግና የብድር አመላለስን ከ95 በመቶ በላይ እንዲሆን ማድረግ፣ የምርት ማሳደጊያ ግብዓት ብድር አቅርቦትን በ2014 ከነበረዉ 45,000 ኩንታል ወደ 5,271,321.19 ኩንታል ለማድረስ ግብ ተጥሏል። የጎብረት ሥራ ማህበራትን የኢንስፔክሽን ሽፋን በ2014 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ከ26 ከመቶ ወደ 80 በመቶ በዓመት ማሳደግ፣ የአዲት አገልግሎት ሽፋን ከ31 በመቶ ወደ 100% በማሳደግ 2,369 ማህበራት ላይ አዲት ማድረግ፣ የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ የአገልግሎት ሽፋን ከደረሰበት ከ6 ከመቶ ወደ 75 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል።

**የአደጋ ሰጋትና ቅደመ ማስጠንቀቂያ የቀጣይ አስር አመት ግብ**

የአደጋ ተጋላጭነትን በመቀነስና የመቋቋም አቅምን በመገንባት የምግብና የስነ-ምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ማረጋገጥና የህብረተሰቡን ገቢ ማሳደግ ሲሆን፤ በአደጋ ክስተት ስጋት አመልካቾች ላይ ከዞኖችና ወረዳዎች መረጃ በማሰባሰብ፣ በመተንተንና በማደራጀት ለባለድርሻ አካላት 416 ሣምንታዊና 96 ወርሃዊ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሪፖርቶች ተደራሽ ይደረጋሉ። በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ የምግብ ክፍተት የሚያጋጥማቸውን ቤተሰቦችን ለመለየት በየዓመት 2 ጊዜ የተካሄደ የበልግና የመኸር ዳሰሳ ጥናትና የምግብ ምላሽ የተሰጣቸው 250,000

ቤተሰቦች እና ከተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ አደጋዎች ጉዳት መነሻ መልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ የተደረገላቸው 86,000 ቤተሰቦች የኖራሉ፡፡ በ16 ዙር በመደበኛና በተጋላጭነታቸው በትኩረት አንድ በጥና ተለይተው የቀረቡና 3344 ሜ/ቶን የአልሚ ምግብና ዘይት የቀረበላቸው ከ5 አመት ዕድሜ በታች ለሆኑ 105,600 ሕጻናት፣ 151,680 አጥቢና ነፍሰ ጡር እናቶች፣ በጠቅላላው 257,280 ተጠቃሚዎች፣ ከልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በቅተው የወጡ 16,568 ተጠቃሚዎች ይኖራሉ፡፡ በተለያዩ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች ከተሰራጨው ገንዘብ 10,000,000.00 ብር እንዲሰራጭ፣ የብድር ገንዘብ 12,500,000.00 ብር እንዲመለስ፣ እና 5,528,000.00 እነዲቆጠብ ይደረጋል፡፡ ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ ተደርጎላቸው ሰላማቸው ተረጋግጦ 48,632 ተፈናቃዮች በምግብ ራሳቸዉን እንዲችሉ ደረጋል፡፡

በ2022 ዓ.ም ሁሉም ወረዳዎች የአደጋ ተጋላጭነት ፕሮፋይል ይኖራቸዋል፤ ጥናቱን መሰረት በማድረግም ሁሉም የአደጋ ስጋት ቅነሳና የመጠባበቂያ እቅድ ይዘጋጅላቸዋል፡፡ 13 ወረዳዎች አስቸኳይ የጤናና የሥርዓተ ምግብ ዳሰሳ ጥናት (Rapid Health and Nutrition Assessment) ይካሄዳል፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋዎች ክስተት ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው የሚረዱ ቤተሰቦች ከነበረው አሁን ከነበረን 240,491 ቤተሰቦች በየዓመቱ በ10 በመቶ በመቀነስ በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ (በ2022) ወደ 93,000 እንዲቀንስ ይደረጋል፡፡ በአደጋ የተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎችን በዘላቂነት ከማቋቋም አንጻር በየአመቱ 2,500 ቤተሰቦች መልሶ በማቋቋም በዕቅድ ዘመኑ በጠቅላላው 20,000 ቤተሰቦችን ለማቋቋም ትኩረት ተሠጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡ የአምስተኛው ምእራፍ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ትግበራ በገጠር የሚኖሩ 23,669 የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ከምግብ ዋስትና ችግር በማላቀቅ በዘላቂነት የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ ማስቻል፡፡

**የእቅዱ የማሰፈጸሚያ ስልቶች**

የልማት ዕቅዱ ለማሳካተ የያዛቸውን ራእይና ዓላማ፣ ለመፈጸም የታቀዱ ግቦች ላይ ከዞኖችና ወረዳዎች ጋር የጋራ ማድረግ፣ በየደረጃው አስፈላጊ የሆኑ ችሎታን፣ ዕውቀትና ክህሎት፣ የአመራር ብቃትና ስልትን ማዳበርና መለወጥ፣ ቅንጅታዊ አሰራርን መተግበርና ማጎልበት፣ የተሻሻሉ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን መተግበር፣ የተረጋገጡ የስኬት ሞዴሎችን ለማሳደግ የሚረዱ አቀራረቦችን ማጎልበት (Cluster approach)፣ ምርታማነትና የገበያ ትስስሮችን ለማሳደግ የሚረዱ አሠራሮችን ማጎልበት፣ በልማትና ግብይት ዘርፍ ለተሰማሩና ለሚሰማሩ የግል ባለሃብቶች አስፈላጊ የሆነ ድጋፍ ማድረግ፣ የምርት ማዘጋጃና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ በማድረግና እሴት የሚጨምሩ አገልግሎቶችን በማስፋፋት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሕብረተሰቡ ያላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ከመሠረቱ ለማስረጽ እንዲሁም የራሳቸውን እና የአባላትን ምርቶች እና አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ ላይ ተቀናጅተው እና ተጠናክሮ እንዲሰሩ የኅብረት ሥራ ሴክተር የኮሚዩኒኬሽን እና የሕዝብ ግንኙነት አሰራርን ማጠናከር፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት መረጃዎችን ጥራት እና ወቅታዊነት ጠብቆ ለሕብረተሰቡ እንዲደርስ ትኩረት ተሰጥቶ መስራት የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ምርትና አገልግሎቶቻቸውን ለተጠቃሚዎች እንዲያስተዋውቁ ለማድረግ ተከታታይነት ያለው የኅብረት ሥራ ማህበራት ኤግዚብሽን፣ ባዛርና ሲምፖዚየሞች በራሳቸው እንዲያዘጋጁ ማድረግና በኅብረት ሥራ ማህበራትና እና በሸማቾች መካከል ቀጣይነት ያለው ግብይት ትስስር እንዲኖር ለማድረግ የማስተዋወቂያ እና ግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮች እንዲዘጋጁ ለማስቻል የግንዛቤ መፍጠሪያ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀትና በእቀዱ ላይ ግንዛቤዎችን መስጠት፣ እቅዱን የሚደግፉ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ግቦቹን ለማሳካተ ይሰራል።

### 3.2. አርብቶ አደር ልማት ስራዎች

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የአርብቶ አደር ልማት ሥራዎች የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፣**

ከክልል እስከ ቀበሌ የተዘረጉ መዋቅሮች በአደረጃጀት፣ በአሰራርና በሰው ኃይል ተጠናክረው በራሳቸው አቅም የሚፈጽሙ እንዲሆኑ በማድረግ በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ እና ልዩ ድጋፍ በሚሹ አካባቢዎች የተጀመረውን ሁለገብ ልማትን ማስቀጠል እና ብልጽግናን ማረጋገጥ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ ተወስዷል።

የአርብቶና ከፍል አርብቶ አደርን የአኗኗር ዘይቤ ማዕከል ያደረገ የመሰረተ ልማት ስራዎችን በማስፋፋት ተደራሽነትና ጥራታቸውን ማረጋገጥ፤ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራምን ማጠናቀቅ፤ መንደሮች በፕላን የሚመሩ፣ ጽዱ፣ ለኑሮ ምቹና አረንጓዴ እንዲሆኑ መሥራትና ወደ ፊት የከተማ ማዕከል እንዲሆኑ ማድረግ ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ነው።

በአርብቶና ከፍል አርብቶ አደሩ እና ልዩ ድጋፍ በሚሹ አካባቢዎች የእንስሳትንና የሰብልን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የግሉ ባለሀብት በራሱና ከመንግስት ጋር በቅንጅት በግብርናውና በአግሮ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በስፋት እንዲሳተፍ ማድረግ እና የገበያ ትስስር በመፍጠር ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፤

በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢ በቂ የፋይናንስ አገልግሎት አንዲኖር በማድረግ የባንክና ኢንሹራንስ እንዲሁም የገጠር ማይክሮ-ፋይናስ እንዲስፋፋ ማድረግና ህብረተሰቡ እንስሳቱን በዋስትና አስይዞ የሚበደርበትን ሁኔታ እንዲመቻች፣ ሕዝቡ በብድርና ቁጠባ ህብረት ሥራ ማህበራት እየተደራጀ ብድር የሚያገኝበትና የቁጠባ ባህል እንዲዳብር ይደራጋል፡፡

በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢ የውሃ አቅርቦት፣ የጤና እና የትምህርት ፍትሃዊነትና ተደራሽነት በማሻሻል የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

የህዝቡን ምርታማነት ለማሳደግ አዳዲስ ቴክኖሎጆችና ግብአቶች የማቅረብ፣ የድርቅ ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ዘላቂ ልማት እና የአካባቢ ጥበቃና አየር ንብረት ለውጥ ማላመድ ሥራዎች በሁሉም ተግባራት ትኩረት አግኝቶ እንዲታቀዱና እንዲፈፀሙ ይደረጋል፡፡

የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ማህበራዊ ሃብት በመገንባት፣ የሰላም አደረጃጀቶችንና አሰራሮችን በማጠናከር አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድና በራሳቸው አቅም የሚፈቱበትን ስርአት በመዘርጋት፣ ተጎራባች ማህበረሰቦችን በልማትና መልካም አስተዳደር በማስተሳሰርና በመካከላቸው ዘላቂ ሰላም እንዲፈጠር ይደረጋል፤

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የአርብቶ አደር ጉዳይ ዓላማ እንደሚከተለው ተለይቷል፣**

በአርብቶ አደርና ልዩ ድጋፍ በሚሹ አካባቢዎች የልማትና መልካም አስተዳደር ስራዎችን በተቀናጀ ሁኔታ በመተግበር የህዝቡን የልማት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የአርብቶ አደር ጉዳይ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች፣**

በአርብቶ እና ከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢዎች ግንዛቤዉ ያደገ፣ ልማትን ማፋጠን የሚችል ማህበረሰብ እና የሰለጠነ የሰዉ ሀብት በማፍራት የማስፈጸም አቅም ችግርን ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀነስ በአማካይ ከ40% በታች የሆነዉን የሰለጠነ የሰዉ ኃይል ወደ 85% የማሳደግ፣ በአካባቢዉ የሚታየዉን የሰለጠነ የሰዉ ሀይል እጥረት ለመቀነስ የአጭር ጊዜ ሥልጠና በመነሻ 191 የነበረ ሲሆን 420 ማሰልጠን፤ እንዲሁም የረጅም ጊዜ ስልጠና ለ388 የመስጠት፣ በአካባቢዉ ያለዉን የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ አንድ ደረጃውን የጠበቀ አዳሪ ት/ቤት በመገንባት እና በመነሻ 3,756 የነበረዉን በ2022 ለ4,976 ተማሪዎች ትምህርት ለመስጠት ታቅዷል፡፡

በመነሻ ከነበረዉ 705 የተለያዩ የመጠጥ ዉሀ ተቋማት አዳዲስ 80 የውሃ ተቋማትን በቅንጅት በመገንባት ወደ 785 በማሳደግ የንጹህ መጠጥ ውሀ ተደራሽነት ይረጋገጣል

በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢ የመንገድ ተደራሽነት ከመነሻው ከነበረው 1,123 ኪ/ሜ ወደ 1,353 ኪ/ሜትር ለማድረስ ይሰራል፡፡

በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የመንደር ማሰባሰብ በመነሻ 5,364 የነበረዉን 4,960 የቤተሰብ ኃላፊዎችን በአዲስ መልክ በማሰባሰብ፤ 72 አዳዲስ ማህበራዊ ተቋማት በመንግስትና የህብረተሰቡ ተሳትፎ በመገንባት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 10,324 የቤተሰብ ኃላፊዎች ጽዱና ለመኖሪያ ምቹ በሆኑ መንደሮች ይሰበሰባሉ፤

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ግጭቶች እንዲቀንሱና እንዲወገዱ 112,185 ለሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ በመስጠት ልማዳዊ ድርጊቶች ተወግደው፤ በውስጥና በተጎራባች ሀገሮች ድንበር የሚስተዋሉ ግጭቶችና አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ይሰራሉ፤

አርብቶ አደሩ ከእንስሳት እርባታ ጎን ለጎን የሰብል ልማትን በማካሄድ በዓመት ሁለት ጊዜና ከዚያ በላይ በማምረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ነባርና አዲስ የመስኖ ፕሮጀክቶች እና ሌሎች የዉሀ አማራጮችን በመገንባትና እና ሌሎች የዉሀ አማራጮችን በመጠቀም 30,000 ሄ/ር ማሳ በዘመናዊ መስኖ እንዲለማ ይደረጋል፡፡

**የእንስሳት ሀብት ልማት ስራዎች፡-**

አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ ከእንስሳት ሀብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ከሚመለከተዉ ሴክተርና ከልማት አጋሮች ጋር በመቀናጀት የእንስሳቱን ጤና እና መኖ በማሻሻል፣ እንዲሁም ምርታማነቱን በማሳደግ ከዚህ ጋር በተያያዘ የገበያ መሰረተ ልማት እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡ የአርብቶ አደሩ አካባቢ ከፍተኛ የእንሰሳት ሀብት የሚኖርበት በመሆኑ ከዚህ ጋር ተያይዞ የእንሰሳቱን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ፤ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ድርቅን ለመቋቋም እንዲያስችል 50 ኩ/ል የእንስሳት መኖ ዘር በማቅረብ፣ 500 ሄ/ር መሬት የእንስሳት መኖ ባንክ እና 350,000.00 ሳር እስር (ቤል) ማዘጋጀት፣ በስምንቱም የአርብቶ አደር ወረዳዎች እና ቆላማ አከባቢዎች በቁጥር 16,200 እንስሳቶችን ማዳቀልና በቁጥር 32,144,071 እንስሳቶችን በማስከተብ ማህበረሰቡ ከእንስሳት ሀብቱ በበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚሰራ ይሆናል፡፡

**በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና እንክብካቤ ስራዎች፡-**

564ሄ/ር መሬት መከለል፣ 2,402 ሄ/ር መሬት ተበይ ካልሆኑ እፅዋቶች ማፅዳት፣ 648 ሄ/ር መሬት ፊዚካል የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን ማከናወን፤ 250 ሄ/ር ስነ ህይወታዊ ስራዎችን መስራት፣ 5 ሚሊዮን የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸዉን ችግኞች መትከል፣ በአየር ንብረት ለዉጥ ላይ አዎንታዊ ሚና አንዲኖራቸው ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ

ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመሆን አርብቶ አደሩ ከተፈጥሮ ሀብት ልማት ተግባራት ተጠቃሚ እንድሆኑ በትኩረት ይሰራል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የአርብቶ አደር ጉዳይ ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀምጠዋል፣**

አርብቶ አደሮችና ልዩ ድጋፍ በሚሹ አካቢዎች በመንደር ማሰባሰብ ጠቀሜታ፤ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አወጋገድ፣ ከዘላቂ ሠላም ግንባታ፣ በእንስሳት ዝሪያ ማሻሻል፣ በመስኖ ልማት፣ በእንስሳት መኖ ልማት፣ በሰብል ልማትና በተለያዩ ዘርፎች የተሻለ ተሞክሮ ባለባቸዉ ወረዳዎችና ክልሎች ምርጥ ተሞክሮ ላይ ልምድ ልውውጥ ቀስመው እንዲተገብሩት ተገቢው ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደር በየአካባቢያቸው የሚያስመዘግቡትን መልካም ተሞክሮዎች በጋራ ተገናኝተው መለዋወጥ እንዲችሉ እና ለመንግስት አስፈጻሚ አካት ያላቸውን የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ 1 የሀገር አቀፍ በዓል እና 5 ክልላዊ የአርብቶ አደር ቀን በዓል ይዘጋጃል፡፡

በመንደር ማሰባሰብና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊትና ግጭት መከላከል ዙሪያ ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ሰፊ የሞብላይዜሽን ተግባራት በየደረጃዉ ለማካሄድ፣ የህዝብ ንቅናቄ መድረኮችን በግብዓትነት ለመጠቀም፣ ከሚመለከታቸዉ ባድርሻ አካት ጋር በቁርኝነትና በቅንጅት ለመስራት፣ በክልልና በዞን ስትሪንግ እና ቴክኒክ ኮሚቴ ዕቅዱ እንዲመራ ለማድረግ፣ እንዲሁም ከዚህ በፊት የተሰጡት የትምህርትና ስልጠናዎች ያስገኙትን ውጤቶችንና የነበረበትን ክፍተት በዳሰሳ ጥናት መለየትና ለዕቅድ ትግበራዉ ያላቸዉን ሚና ለማሳደግ ይሰራል፡፡

### 3.3. ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት ኢንተርፕራይዞችና ኢደስትሪ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፣**

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የኢኮኖሚ ድርሻ በፍጥነት ማሳደግ እንዲቻል ነባር ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋትና በማሻሻል የማምረት አቅማቸውን ማሳደግ እንዲሁም ከአምራች ዘርፉ ውጭ ያሉ ባለሀብቶችን ወደ ዘርፉ እንዲቀላቀሉ በማድረግ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችና የምርት ዓይነቶችን ማስፋፋት፣ የተለያዩ የኢንዱስትሪ ክላስተር ማዕከላት እንዲፈጠሩ እንዲሁም በኢንዱስትሪዎች መካከል የገበያ፣ የቴክኖሎጂና የማኔጅመንት ዕውቀት ሽግግር መፍጠር የሚያስችል ትስስር እንዲኖር በትኩረት ይሰራል፡፡

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዕድገት የሁሉንም ህብረተሰብ በተለይም ወጣቶች፣ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነትን (equitable and inclusive growth) ማረጋገጥ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ ነጻ ውድድርን የሚያሰፍን፣ ማህበራዊ ልማትን የሚደግፍ፣ የአካባቢ ተጽእኖን የማያስከትል አረንጓዴ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገትን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚመሩበት የድጋፍ ማዕቀፎች የልማቱ እድገት ፍላጎት እና ከሚጠበቀው ውጤት አንጻር ተጣጥሞ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

የክልሉ ሥራ ፈላጊ ወጣቶችን በመለየት በተለያዩ ገቢ ማስገኛ መስኮች በማሰማራት በሀገሪቱ እየተመገዘገበ ያለውን ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስቀጠል ድህነትን በመቀነስ ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል፡፡

የቢዝነስ መፈልፈያ ማዕከል (BIC) በማደራጀት የስራ ፈጣሪነትን ባህል በማዳበር ዘርፉ የአዳዲስ ስራ ፈጠራ ማፍለቂያ እንዲሆን የማድረግ፣ ሰፊ የስራ ዕድል ለሚፈጥሩ ተቋማት የማበረታቻ ስርዓት የመፍጠር፣ የቁጠባ ባህላቸው የሚዳብርበትን፣ የጥቃቅን አነስተኛ መለስተኛ ኢንተርፕራይዞች ባንክ ማቋቋም እና የአነስተኛ ብድር ተቋማትን የሚዘምንበት አቅጣጫ ለመከተል ታቅዷል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፣**

የኢንዱስትሪ ልማት ምርታማነት፣ ጥራትንና ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ፣ የማኑፋክቸርንግ ኢንዱስትሪው መሠረቱን በማስፋት በሂደት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ መሠረት እንዲጥል በማድረግ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ከኢንዱስትሪና ግብርና ጋር በማስተሳሰር የክልሉ ህዝቦች ብልፅግናን ማረጋገጥ፤

በገጠር አካባቢዎች ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተመረቁና ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች አቋርጠው ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶችን መጠነኛ ቁጠባ በመነሻነት እንዲቆጥቡ በማድረግና ከመንግስትና አበዳሪ ተቋማት የብድር አገልግሎት በማቅረብ በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው የሥራ ዕድል እንዲያገኙና ሀብት ፈጥረው ለራሳቸውም ሆነ ለአገር ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማስቻል ነው፡፡

የስራ ፈጠራ ክህሎትና የስራ ፈጣሪነት አመለካከትን በማጎልበት፣ በከተሞች ሰፊ የስራ አማራጮችን በመፍጠርና የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ለኢንዱስትሪ መሰረት የሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች በማፍራት ስራ አጥነትን በመቀነስ ለክልላችን ብሎም ለሀገራችን ብልፅግና ዘርፉ የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ እንዲወጣ ማድረግ ነው፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተለይተዋል፣**

**በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፡-** በክልሉ የማኑፋክቸርንግ ኢንዱስትሪው አሁን ለኢኮኖሚ እድገት ያለውን ድርሻ ከ18.4 በመቶ በ2022 ወደ 25.3 በመቶ ድርሻ ማሳደግ፣

በክልሉ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን መሠረት ለማስፋት 1,072 አዳዲስ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም ለ17,368 ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር እና 1,640 ነባር ኢንዱስትሪዎችን በማጠናከር 25,016 በድምሩ ለ42,384 ዜጎች የሥራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን በድምሩ 136 እንዱስትሪዎች ከዚህም ውስጥ 104 ከአነስተኛ ወደ መካከለኛና እና 32 ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡

የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠንና ለማስፋፋት እንዲያግዝ ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጭ ለተሰማሩ ባለሀብቶችና ለዩኒቨርስቲ ምሩቃን ለ16,500 ዜጎች እንዲሁም ከአከባቢ ብክለት የጸዳ የአምራች ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት እንዲያግዝ በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ  በአጠቃላይ ለ63,620 (16,500 ሴት) ለኢንዱስትሪያሊስቶች ዜጎች ግንዛቤ ይፈጠራል፡፡ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ያሉባቸውን የማምረቻ ማሽነሪ እንዲሁም የሥራ ማስኬጃ ክፍተቶቻቸውን ለመሙላት እንዲያግዝ ለ368 አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የብር 400,000,0000 ብር ማሽነሪዎችና የ32,0000,000 ሚሊየን የሥራ ማስኬጃ ብድር እንዲመቻችላቸው ይደረጋል፡፡

አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ያላቸውን ውስን ካፒታል በግንባታ ላይ በማዋል የካፒታል እጥረት እንዳያጋጥማቸው ለምርት ማምረቻ የሚሆን 788 ሄክታር መሬት እንዲዘጋጅ በማድረግ 24 የምርት ማሳያና መሸጫ ህንጻ በመገንባት 164 ኢንዱስትሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በጥራት፣ በዋጋና በጊዜ በገበያ ላይ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት እንዲያመርቱ በ1,400 አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ይመቻቻል፡፡

የአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በገበያ ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ በመሆን ገቢ ምርቶችን በመተካትና በወጪ ምርቶች ላይ በአይነትና በብዛት እንዲያሳድጉ ለማስቻል 240 ባዛርና ኤግዝብሽን በማዘጋጀት ኢንዱስትሪዎችን በማሳተፍ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሀገር

ውስጥ እና ውጭ ሀገር ገበያ ትስስር ይፈጠሮላቸዋል፡፡ በክልሉ ካሉት የስራ አጥ ቁጥር ለ20 በመቶ የስራ እድል ፈጥራል በተጨማሪም 5.55 ቢሊዮን ብር የተመዘገበ ካፒታል እንዲኖር ታቅዷል፡፡

**በገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራ ዘርፍ፡-** የስራ ፈላጊ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ 749,225 ሥራ ፈላጊ ዜጎች እንዲለዩና እንዲመዘገቡ በማድረግ 390,535 በግብርና ዘርፎች፣ 7,500 በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፎች፣ 17,045 በአገልግሎት ዘርፍ፣ 80,213 በቋሚ ቅጥር በድምሩ 495,292 እና በኮንስትራክሽ ዘርፍ 22,480፣ በማዕድን ዘርፍ 74918፣ በተለያዩ ተቋማት በጊዜያዊ ቅጥር 156,535 በድምሩ 253,933 በጊዜያዊ የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ይደረጋል፡፡

አዲስ ለሚደራጁ ለኢንተርፕራይዞች 136,682 ሜ/ር መሬት ማዘጋጀት፣ ለኢንተርፕራይዞች 30,882 ቢዝነስ ፕላን ዝግጅት ድጋፍ ማድረግ፣ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተደራጅተው ከሚሰማሩ ብር 399,996,989 ቅድመ ብድር ቁጠባ በማስቆጠብ እና ለመነሻ ካፒታል የሚሆን ብድር ብር 1,391,742,274 እንዲቀርብ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

በነባር ኢንተርኘራይዞች ከተሰራጨው የብድር ገንዘብ ውስጥ ጊዜው የደረሰና ውዝፍ ብድር ብር 1,863,078,137 በማስመለስ፣ ድህረ ብድር ቁጠባ ብር 1,138,546,458 በማስቆጠብ፤ ለ65,809 አደረጃጀቶች የሂሳብ ዝርጋታ እና ለ32,903 አደረጃጀቶች የአዲት አገልግሎት እንዲያገኙ እንዲሁም የደረጃ ሽግግር ከጊዜያዊ ወደ ቋሚ 3,061 ከመስራች ወደ ታዳጊ 1,445 እና ከታዳጊ ወደ የበቃ 638 በማሸጋገር ድጋፍ ይደረጋል፤

የገበያ ልማት እና የቴክኖሎጂ ተደራሽነትን በማሳደግ ለ68,072 ኢንተርፕራይዞች ላመረቷቸው ምርቶችና አገልግሎት የገበያ ትስስር ከአገር ውስጥ በሚገኙ መንግስታዊ ተቋማት፣ በአካባቢ ገበያ፣ በዩኒየኖችና ህ/ሥራ ማህበራት ጋር ሽያጭ በማከናወን ብር 2,671,076,735 ገቢ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ለ890 አደረጃጀቶች ምርጥ ተሞክሮ የመቀመርና የማስፋፋት አሰራርን በማሳደግ በዞኖች፣ ወረዳዎች እና በክልል ደረጃ የምርት ማስተዋወቂያ ባዛርና ኤግዚቪሽን በማዘጋጀት እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

**በከተማ ስራ እድል ፈጠራ ዘርፍ፦**

አጠቃላይ ለ373,134 ዜጎች/በዕድገት ተኮር ዘርፎች 298,507 ዜጎች ቋሚ፣ በከተሞች መሰረተ ልማት፣ ሰፊ የመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች፣ በግል ሰፋፊ ድርጅቶችና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለ74,627 ዜጎች ጊዜያዊ/የሥራ ዕድል ይፈጠራል። የ497,512 ሥራ ፈላጊዎች መረጃ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር /የሴቶችና ወጣቶች አደረጃጀቶችን/ በመቀናጀት በንቅናቄ ቤት ለቤት ምዝገባ ይካሄዳል፤ የአንድ ማዕከል ባለሙያዎችም መረጀውን በተደረጀ መልኩ ወደ ባህር መዝገብ በጊዜ እንዲገለበጥ ይደረጋል፤ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ስልጠናዎችን ለ70,669 አንቀሳቃሾች ለመስጠት ታቅዷል።

ለ373,164 አንቀሳቃሾች አጫጭር የክሎት ክፍተት መሙያ ስልጠና ይሰጣል። ነባርና አዲስ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ አቅማቸውን ለማጠናከር ብር 2,482,792,927 እንዲቆጥቡ በማድረግ የብር 2,911,907,927 የፋይናንስ/ብድር ድጋፍ ማድረግ፣ 2,329,526,336 ከብድር ተመላሽ እንዲሆን ማድረግ ኢንተርፕራዞች ያለባቸዉን የማምረቻና መሸጫ ችግር ለመቅረፍ 236 ሄ/ር የለማ መሬት የማምረቻና መሸጫ ቦታ ድጋፍ እንዲሁም 1,225 ሼድ ይቀርባል የ2,843,765,631 ብር የገበያ ድጋፍ ይመቻቻል

ለ1,115,482 በተለያዩ ደረጃ ላሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ፈጠራ ስልጠና ይሰጣል 22,492 ኢንተርፕራይዞችን የሂሳብ ዝርጋ አገልግሎት በመስጠት የ21,418 ኢንተርፕራይዞችን ሂሳብ ምርመራ ይደረጋል፣ ለኢንተርፕራይዞች ዝግጁ የሆኑና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድባቸው 107 የምርትና የማምረቻ መሳሪያ ቴክኖሎጂ ፕሮቶታይፖች ዝግጁ እንዲሆኑ ይደረጋል። ለ339,213 ተጠቃሚዎች የመረጃና አንድ ማዕከል አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣል ፣

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀምጠዋል፣**

የስራ ዕድል ፈጠራን የሚያበረታቱ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በማውጣትና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ተግባራዊ ይደረጋል። የስራ እድል ፈጠራ በተሻለ ብቃት መምራትና መተግበር የሚያስችል የማስፈጸም አቅም በመፍጠር በሁሉም የአስተዳደር እርከን ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

የሥራ ዕድል ፈጠራን በተጠናከረ መንገድ ለመተግበር ሁለንተናዊና የተቀናጀ ድጋፍ እንዲሰጥ ይደረጋል። በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ የሚሳተፉ ዜጐች በግል፣ በማህበር በኢንተርፕራይዞችና

ሌሎች አደረጃጀቶችና ስራዎች ተሰማርተው ውጤታማ ለማድረግ ቀጣይነት ያላቸው ዘርፈ-ብዙ የአንድ ማእከል አገልግሎትና በከላስተር ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

የሥራ ዕድል አማራጮችን የማስፋት፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት አስተዋጽኦ ሊያበረክት የሚችል፣ ከአነስተኛ ካፒታል እና የቴክሎጂ አቅም በመነሳት በልማታዊ ጥረት እያደገ የሚሄድ የካፒታልና የቴክኖሎጂ አቅም እንዲገነባ፣ እንዲሁም ለተዋናዮች አስፈላጊው የግብዓት አቅርቦት የማመቻቸትና የገበያ ትስስር እንዲጎለብ ይደረጋል፡፡

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ከአጭር ጊዜ አኳያ ካፒታልን ቆጥቦ ፈጣን እድገት በማረጋገጥ ከልማቱ ሕዝቡ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያደርግ ሲሆን፣ ከመካከለኛና ረዥም ጊዜ አኳያ ልማታዊ ባለሀብት የሚፈራባቸው ምንጮች ሆነው ከማገልገላቸው ባሻገር ሀገራችን ባላት ውስን ካፒታልና ቴክኖሎጂ በመጀመር ደረጃ በደረጃ የካፒታልና ቴክኖሎጂ አቅምን በማጠናከር በማያቋርጥ የፈጠነ እድገት ኡደት ውስጥ ለመግባት የሚያስችል እንዲሆን ይደረጋል፡፡

አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን የማያቋርጥ የኢንደስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ አሟጦ እንዲጠቀሙ የተለያዩ አማራጮች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ የመሸጫ ማዕከላትን በተመጣጣኝ ኪራይ እንዲጠቀሙ ገንብቶ የማቅረብ፣ የማምረቻ ማሽንና ስራ ማስኬጃ ብድር ከማቅረብ ረገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፡፡

### 3.4. ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ልማት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የከተማና ኮንስትራክሽን የትኩረት አቅጣጫዎች፣**

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለመምራት የሚችል አቅምና የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋት፣ ለኮንስትራክሽን ኢንዳስትሪ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን የመፈተሽ፣ የማላመድና የማስረጽ ሥራዎች በስፋት በማከናወን፣ የፕላን ስምምነትና ይዞታ ማጣራት ስራዎችን በማገናዘብ እና ዲዛይን በመገምገም በልዩ ትኩረት ይፈጸማል፡፡ ለግንባታ ፕሮጀክቶች የቅደመ ዲዛይን ጥናትና ምርምር ስራዎችን በማካሄድ ከአካባቢ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋዊያን ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ እና ግንባታዎች ደረጃቸውን ጠብቀው በጥራትና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ማስቻል የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

ክልላዊ ፈጣን እድገትን ተከትሎ የሚፈጠሩ የገጠር አገልግሎት ማዕከላት እድገታቸውን በስኬች ፕላን በመምራት ህጋዊ ሰውነት በመስጠት እና ከተሞች ከደረሱበት እድገት አኳያ በመስፈርት ላይ በተመሰረተ አግባብ በመፈረጅ ከነዋሪው አዳጊ ፍላጎት ጋር የተጣጣመ አገልግሎት በማቅረብ ያልተማከለ፣ የተመጣጠነ እና ፍትሃዊ የአከታተም ሥርዓት የመገንባት አቅጣጫ መከተል፣ እንዲሁም ክልል አቀፍ ስፓሻል ፕላን ጋር የተቀናጀ የተለያየ ዓይነት የከተማ ፕላን ጥራቱን የጠበቀ በማዘጋጀት የከተማ-ከተማ እና የከተማ-ገጠር ትስስርን በማጠናከር እና የዕቅድ ትግበራ ክትትልና ግብረመልስ ስርዓቱን በማዘመን ነዋሪው ንቁ ተሳታፊና ባለቤት የማድረግ አቅጣጫ መከተል ነው።

አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩን በከተሞች መስፋፋት ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግና በከተሞች መሬትን በቁጠባ መጠቀምን የሚያጠናክር በቂ የካሳና መልሶ ማቋቋም ድጋፍ በመስጠት ለልማቱ መሬት በበቂ መጠን በቀጣይነት የሚቀርብበት አቅጣጫ መከተል በዋናነት ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎን በመረጃ ላይ የተመሠረተና ዘመናዊነትን የተላበሰ የመሬት አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት በመሬት ዙሪያ ያሉ የሌብነት ምንጮችን የመለየትና የማድረቅ ስራ መስራት ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ነው።

በከተሞች የመኖሪያ ቤት ፍላጎት መጨመርና የአቅርቦት ማነስ ችግርን ለመቅረፍ የተለያዩ የቤት ልማት አማራጮች መጠቀም፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ለዜጎች ሥራ ዕድል የሚፈጥር፣ ቅንጅታዊ አሰራር በመከተል፣ የቁጠባ ባህል በማሳደግ፣ የዜጎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ያረጋገጠ እና በገጠር የልማት ማዕከላት የተሻሻሉ መኖሪያ የቤቶች ግንባታ ፕሮግራሞች በማስቀጠል ደረጃ ማስጠበቅ፣ የቤት አቅርቦትን ከባለቤትነት በተጓዳኝ የኪራይ አማራጭንም እንዲያድግ መስራት፣ በቤት ልማት የግል ዘርፉ ሚና ማጎልበት፣ የቤቶች መረጃና አስተዳደር በማዘመን ህገወጥነትን መከላከል እና የመንግሥት ቤቶች የይዞታ ዋስትና በማረጋገጥ የቤት ልማትና አስተዳደር ሥርዓት ቀጣይነት ማረጋገጥ ይሆናል።

**የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፣**

- በክልሉ አለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ የኮንስትራክሽ ኢንዱስትሪ በመገንባት ኢንዱስትሪው በክልሉ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትንና መዋቅራዊ ለውጥን ለማፋጠን የሚኖረውን ሚና ከፍ ለማድረግ እና በየምዕራፉ ለሚዘጋጁት የኮንስትራክሽ ዘርፍ የመካከለኛ ዘመን የልማት ዕቅዶች ዝግጅትና ትግበራ አቅጣጫ ቀያሽ ወይም ፍኖተ ካርታ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል።

- በክልሉ እየተመዘገበ ያለውን የኢኮኖሚ እድገት ሊሸከሙ የሚችሉ ተወዳዳሪ እና በፕላን የሚመሩ ከተሞችን መፍጠር፡፡ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ አዳጊ፣ተናባቢና ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ ካዳስተር ሲስተም በማስደገፍ፣ የመሬት ይዞታ ምዝገባውን በሃገር አቀፍ ስታንዳርድ መምራት እና በዕቅድ ዘመን ዘርፉ የዜጎችን የንብረት ዋስትና በማረጋገጥ የከተሞችን የኢኮኖሚ ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ እንዲያግዝ ማድረግ፡፡
- ፍላጎትን መሰረት ያደረገ፣ ልማትን የሚያፋጥን፣ ወጪን የሚያስመልስና ፍትሀዊነትን የሚያሰፍን የመሬት ዝግጅትና አቅርቦትን ማረጋገጥ፡፡
- በክልሉ በሚገኙ ከተሞችና የገጠር ማዕከላት እያደገ የመጣውን የቤት ፍላጎት ደረጃውን የጠበቀና ተደራሽነትን ሊያረጋግጥ የሚያስችል የአሰራር ስርዓትና አቅም በመፍጠር ዘላቂነት ያለው የመኖሪያና መስሪያ ቤት አገልግሎት ተጠናክሮ እንዲቀርብ ማድረግ፡፡
- በተደራጀና በነቃ የከተማ ህዝብ ተሳትፎ የከተሞች የአካባቢ ልማት፣የመሰረተ ልማትና አስተዳደር፣ የቆሻሻ አስተዳደር፣ የአረንጓዴ መሰረተ ልማትና አስተዳደር እና የከተማ ውበት በማሻሻል፣ እንዲሁም በከተማ ነክ ሙያዎች የሰው ሃይል ልማትን በማጠናከር ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን በማዘመን የተገልጋይ እርካታ ማረጋገጥ ነው፡፡

**የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች፣**

**የኮንስትራክሽን ስራዎች፡-**

የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ተቋማት የ793 ግንባታ ፕሮጀክቶች ሲጠኑ የተፈጥሮ አካባቢ ተፅዕኖን ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆኑን ክትትል ይደረጋል፣ በአማካሪ የማይሸፈኑ 2,160 መካከለኛና አነስተኛ ግንባታዎች የተፈጥሮ አካባቢ ተፅዕኖን ግምት ውስጥ ያስገቡና 100% ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋዊያን ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገው የተሟላ ዲዛይን የማዘጋጀት ስራ ይሰራል፡፡ 105 ከፍተኛ ደረጃ ላላቸው የግንባታ ፕሮጀክቶች የአማካሪ ግዥ የሚሆን ሰነድ በማዘጋጀት የከፍተኛ ፕሮጀክቶች ዲዛይን ዝግጅትና ጥራት ክትትል ስራዎች በቅንጅት በማድረግ በግንባታዎቹ ለሚሳተፉ የግንባታ ሰራተኞች ደህንነት መጠበቂያና መከላከያ አልባሳትና መሳሪያዎች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ተጀምረው ሳይጠናቀቁ የቀሩ እና የግንባታ ሂደታቸው የተጓተቱ የግንባታ ፕሮጀክቶች የውለታ አስተዳደር ተግባር 100% በአዲስ መልክ ውለታ በመግባት ወደ ስራ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

የክልሉ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የአከባቢ የግንባታ ግብዓት ፍላጎት 80 በመቶ የሚሆነው በክልል ውስጥ ምርት እንዲሸፈን ይደረጋል። የክልሉን የአካባቢ የግንባታ ግብዓት ክምችት የሚያሳይ 10 የጥናት ሰነድ በማዘጋጀት እና በክልሉ ውስጥ የሚለሙ 40 የካባ ቦታዎች ለግንባታ ተስማሚነታቸው በላብራቶሪ ፍተሻ ይረጋገጣል። በተጨማሪም በተመረጡ 16 የመንግስት ፕሮጀክቶች ላይ የኮንስትራክሽን አዲት በማድረግ የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪው ውጤታማነቱ ይረጋገጣል።

ለ1,921 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ባለሙያዎች፣ 56 ተቋራጮች እና 10 አማካሪዎች አዲስ ፈቃድ በመስጠት በዘርፉ የሚኖራቸው ሚና ከፍ እንዲል እና በክልሉ በሚለሙ የግልና የመንግስት ግንባታዎች 24,000 ለሚሆኑ ዜጎች (9,600 ሴት) የሥራ እድል እንዲያገኙ ይደረጋል።

**የከተሞች ፕላን ስራዎች፡-**

የከተሞችን ፈርጅ መሠረት ያደረገ የተለያየ ዓይነት 159 ፕላን በሕብረተሰቡ ተሳትፎና ባለቤትነት የመሬት አጠቃቀም ምጣኔ ተከትሎ የሚዘጋጅ ሲሆን ፕላኑን ለመተግበር እንዲያመች 64 የሰፈር ልማት ፕላን፣ በ20 ከተሞች አርባን ዲዛይን እና የገቢ መሠረታቸውን ለማሳደግ የሚረዳ ለ383 ከተሞች የቦታ ደረጃ ፕላን ጥናት ይዘጋጃል። የገጠር አገልግሎት ማዕከላት በጅምሩ እድገታቸውን በፕላን ለመምራት የሚያስችል 907 ስኬች ፕላን ይዘጋጃል። የተዘጋጁ ፕላኖች በአግባቡ መውረዳቸውን የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል።

ክልላዊ የከተሜነት ደረጃ ቀደም ሲል ከነበረበት 25.6 ከመቶ ወደ 36 በመቶ እንዲያድግ ይደረጋል። ለ42 የገጠር አገልግሎት ማዕከላት የከተማነት እውቅና ጥናት፣ ለ48 ከተሞች የፈርጅ ለውጥ ጥናት፣ ለ16 ከተሞች ነባራዊ ሁኔታ ጥናት (Urban Base Line Study) እና ለ24 ከተሞች መሠረታዊ መረጃ ፕሮፋይል ጥናት ይዘጋጃል። በተጨማሪ ለ5 ከተሞች እህትማማች ግንኙነት እንዲፈጥሩ ይደረጋል።

**መሬት ልማትና ማኔጅመንት ስራዎች ፡-**

የመሬት ፍላጎቱን ቢያንስ 75 በመቶ እንዲዘጋጅና እንዲቀርብ በማድረግ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል 4,300 ሄ/ር የለማ የከተማ መሬት እና 3,709 ሄ/ር መሬት ለተለያዩ አገልግሎቶች እና በልማት ምክንያት ከይዞታቸዉ ለሚነሱ ባለመብቶች ምትክ ቦታ ባንክ የሚደረግ በድምሩ 322 ሄ/ር መሬት ተዘጋጅቶ ለልማት ይተላለፋል።

በሁሉም ከተሞች ሽንሻኖ አልባ (ቅርጽ የሌላቸዉ)፣ ከደረጃ በታችና በላይ የሆኑ ይዞታዎችን በየከተማዉ በጥናት በመለየትና የጥናት ሰነድ ዉጤት መረጃዎችን በማጠቃለል ይዞታዎች

ላይ LDP/በሰጥቶ መቀበል መርህ/ የማስተካከያ ዉሳኔ እየተሰጠ በከተማዉ ፕላን ስታንዳርድ መሰረት ማስተካከያ እርምጃ ተወስዶ ወደ ልማት እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

ለ16,380 የከተማ መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት /certificate/ በአግባቡ መሰጠቱ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፤ ከመሬት አስተዳደርና ጋር ተያያዥነት ላላቸው 8,400 ቅሬታና አቤቱታዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡ ከፊርጅ 2 እስከ 5 ባሉ ከተሞች ለ 24,000 አርሶአደሮች ጊዜያዊ መጠቀሚ ሰነድ በመስጠት በማስፋፊያ አካባቢዎች ላይ የሚገኝ የአርሶአደር መሬት ተለይቶ እንዲታወቅ ይደረጋል፡፡ የ48,000 ጊዜያዊ የመጠቀሚያ ሰርተፍኬት ህትመት ማከናወን በከተማው አስተዳደር ክልል በማስፋፊያ አካባቢዎች ለሚገኙ አርሶ አደሮች/አርብቶአደሮች 24,000 ጊዜያዊ የመጠቀሚያ ሰርተፍኬት ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

**መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ስራዎች፡-**

የካዳስተር እና የመሬት ይዞታ ማረጋገጥና ምዝገባ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ተናባቢ፣ ወጥና ተመጋጋቢ ሆኖ እንዲገነባ በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን 30 ከተማ አስተዳደር ከተሞችን ወደ ካዳስተር ሥርዓት ለማስገባት የሚያስችሉ የኦርቶፎቶ ዝግጅት እና የጂአይቲክ መረብ ማስፋፊያ ስራዎች ይሰራሉ፡፡

በከተሞች የመሬት ላይ መቆጣጠሪያ መረብ ለማስፋፋት 1,020 ሞንመንት በማዘጋጀትና በመትከል መረጃ ይሰበሰባል፡፡ ለመሬትይዞታ 58,000 ማህደራት ልዩ መለያ ኮድ በመስጠት ከኦርቶ ፎቶጋር ይተሳሰራል፤  የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዘጋጅላቸዋል፡፡ 46,000 የከተማ መሬት ይዞታ መብት ምዝገባ ይደረጋል፡፡ በካዳስተር ሲስተም ልማትና አስተዳደር በ1 ከተማ የመሬት መረጃ ማዕከል እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ በ20 ከተሞች የካዳስተር ሲስተም መሠረተ ልማት ግባዓቶች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡ በ11 ከተሞች  የመሬት ይዞታ ምዝገባ በሀገራዊ ካዳስተር ምዝገባ ሶፊትዌር እንዲታገዝ ይደረጋል፡፡

**ቤቶች ልማትና አስተዳደር ስራዎች፡-**

በከተሞች የቤት አቅርቦት መጠን አሁን ካለበት ወደ 65 በመቶ እንዲያድግ 16,328 ቤቶች እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት 3,000፣ ለአነስተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው ወጪ ቆጣቢ 1,904፣ በግለሰቦች 9,600፣ በመንግስትና በግል ባለሀብት አጋርነት 400፣ በተቋማት ፍላጎትና ፋይናስ 224 እና የደሃ ደሃ ቤት አቅርቦት 1200 ቤቶች እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡

በገጠር ማእከላት 1,446 ደረጃቸውን የጠበቁ ቤቶች እንዲገነቡና አሁን ያሉ 30 ከመቶ ቤቶች ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲሻሻሉ ማድረግ፣ በከተማና በገጠር ማዕከላት ነዋሪዎች ወጪና መሬት ቆጣቢ 5 አማራጭ ዲዛይኖች ይዘጋጃሉ፣ በአጠቃላይ በከተማና በገጠር ማዕከላት 21,363 ቤቶች ግንባታ ለ13,400 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና 0.114 ቢሊየን ብር በማስቆጠብ 17,041,000 የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

**የማስፈጸም አቅም ግንባታና አካባቢ ልማት ስራዎች፡-**

በ6 ከተሞች ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ በቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡ እንዲዘምን በማድረግ የነዋሪው እርካታ አሁን ካለበት 50 በመቶ ወደ 85 በመቶ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ በዘርፉ ለተሰማሩ 100 ኢንተርፕራይዝ አባላት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

የከተማ ነዋሪ ህብረተሰብ፣ መንግስትና አጋዥ ድርጅቶች በገንዘብ፣ በጉልበትና በእውቀት የሚሳተፉበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የነዋሪው የልማት ተሳትፎ አደረጃጀት በሁሉም ከተሞች የሚከናወን ሲሆን ለመሰረተ ልማትና አካባቢ ልማት የሚያስፈልገው በጀት በየአመቱ 35% በህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡

በከተሞች የተቀናጀ የመሠረተ ልማት አቀርቦት 6,356.5 ኪ.ሜ መንገድ በመገንባት ሽፋኑን ወደ 80%፣ 1,620 ኪ.ሜ የመንገድ መብራት በመዘርጋት ሽፋኑን ወደ 73% እንዲሁም 2,722 ኪ.ሜ የውሃ መስመር በመዘርጋት ሽፋኑ ወደ 80% እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ የመሰረተ ልማት ሃብት ቆጠራን በሁሉም ከተሞች የማካሄድ ግብ ተጥሏል፡፡ ለመሰረተልማት ግንባታ ከተለያዩ ምንጮች ብር 660 ሚሊዮን ይመቻቻል፣ በ7 የከተማ አስተዳደር ከተሞች የመሰረተልማት ግንባታ ማሻሻሪዎች እንዲሟሉ ይደረጋል፣ የ14.25 ኪ.ሜ የአዲስ አስፋልት መንገድ ግንባታ፣ የ15.006 ኪ.ሜ የኮብልስቶን ንጣፍ መንገድ ግንባታ፣ 1,956 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ ግንባታና 4,117 ኪ.ሜ አዲስ መንገድ ከፈታና ጠረጋ ይከናወናል፡፡ ከመንገድ ድንነት ማሻሻል አንጻር የ7.5 የነባር አስፋልት መንገድ ጥገና፣ 13.5 ኪ.ሜ ኮብልቶን መንገድ ጥገና፣ 1,607.6 ኪ.ሜ የነባር ጠጠር መንገድ ጥገና ይከናወናል፡፡

የፍሳሽ አወጋገድ ስረዓት ለማሻሻል 171.5 ኪ.ሜ የጎርፍ መከላከያ ክትር፣ የ852 ኪ.ሜ የጎርፍ መውረጃ ቦይ ግንባታ፣ 303 ድልድይና ካልቨርት፣ በቁጥር 316 የውሀ ቦኖ ይገነባል፡፡ በ44 ከተሞች ፈርጃቸውን ያገናዘበ ከፍተኛ፣መካከለኛና አነስተኛ ቁራ ግንባታ ይከናወናል

ሽፋኑም 50 እንዲደርስ ይደረጋል፣ ደረጃውን የጠበቀ የተሸከርካሪ ማቆሚያ በ16 ከተሞች እንዲሠራ ይደረጋል።

በከተሞች የአረንጓዴ ልማት ሽፋንን ካለበት 19 ከመቶ ወደ 30 በመቶ እንዲያድግ ይደረጋል፣ በዚህ 802,903 ሜትሪክ ቶን ሙቀት አማቂ ጋዝ ከከባቢ አየር ስቦ የማስቀረት ስራ ይከናወናል። በከተሞች እና በዙሪያቸው ማክሮክላይሜት ለውጥ ሚቋቋሙ 214,000,000 ችግኞች ተከላና እንክብካቤ ይደረጋል:: 400 የመንደር፣ 44 የቀበሌና 52 ከተማ አቀፍ መናፈሻ ፓርኮች ይለማሉ። 2 ደረጃውን የጠበቁ የእጽዋት ፓርክ /ቦታኒክ ጋርደን/ ይለማል፤ በ 6 ከተሞች ዘላቂ ማረፊያ ቦታ በስታንዳርድ በማልማት መታሰቢያ ፓርክ እንዲሆኑ ይደረጋል፡ በሁሉም ከተሞች ዘላቂ ማረፊያ እንዲዘጋጅ ይደረጋል። ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ሽፋን ከነበረበት 64 ከመቶ ወደ 90% የማሳደግ ስራ ይሰራል።

**የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀምጠዋል፣**

ምቹ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሁኔታ ለመፍጠርና ለማጠናከር የተሳለጠ የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋት፣ የአሰራርና ሥነ ምግባር ኮድ የማዘጋጀት፣ ተቋማዊ አደረጃጀትና የኮንትራት አስተዳደርን የማጠናከር፣ የተጠያቂነት አሰራርን የማስፈን እንዲሁም የህብረተሰቡንና የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤና ተሳትፎ በማሳደግ ለብልሹ አሰራር ተጋላጭነት የመቀነስ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

ከዲዛይን ዝግጅት ጀምሮ እስከ ፕሮጀክቱ ፍጻሜ ድረስ ያለውን የቁጥጥር ሥርዓት የሚያጠናክር የኮንትራት አስተዳደርና የፕሮጀክት ማኔጅመንት አሰራርን የማዘመን ሥራ ተግባራዊ ይደረጋል። የአቅም ግንባታና የመንግስትና የግል አጋርነትን በማጠናከር የግሉን ዘርፍ ሚና የማሳደግ ጥረቶች በስፋት ይከናወናሉ።

በከተማና በገጠር ማዕከላት ተደራሽና ደረጃውን የጠበቀ የመኖሪያ ቤት አቅርቦትን ለማሳደግ የሚያስችል የቤት ልማት የፋይናንስ ሥርዓት ይዘረጋል። በተጨማሪም የመኖሪያ ቤት አቅርቦት አማራጮችን የማስፋት ሥራ በአዳዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶች ማኔጅመንት ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ይደረጋል። የመንግሥት ቤቶች መረጃን በአግባቡ ከቴክኖሎጂ አንጻር የቤቶች መረጃና አስተዳደር የማዘመን፣የመንግሥት ቤቶች መረጃ የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ ተጠናክሮ የሚከናወን ይሆናል፡

ከመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ አንፃር የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ በዘርፉ የሚታየውን የባለሙያ ዕጥረት ከዩኒቨርሲቲዎችና ከሌሎች የትም/ት ተቋማት ጋር በቅንጂት በመስራት እንዲፈታ ይደረጋል፡፡ የፈጻሚው የክህሎት ክፍተት በሥልጠና እንዲሟላ ይደረጋል፡፡

### 3.5. የንግድና ኢንቨስትመንት ልማት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የንግድና ኢንቨስትመንት ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች፣**

የህግ ማዕቀፎችን ከወቅታዊ ተለዋዋችጭ ሁኔታዎች ጋር በማሻሻል የመቅረጽ፣ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት የማዘመን ስራ አጠናክሮ በመቀጠል አገልግሎት አሰጣጥን ግልጽና ቀልጣፋ የማድረግ፣ የንግድና የግብይት ህጎችን በማስከበር ህጋዊ የንግድ ውድድርን በማጎልበት ለኢኮኖሚ ዕድገት ዘርፉ የበኩሉን እንዲያበረክት የማድረግ፣ በህጉ መሰረት የሸማቾችን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲቻል የሚመለከታቸውን አካላት ግንዛቤ፣ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር የማጠናከር ስራ በትኩረት ይሰራል፡፡

የንግድ ግብይትና የገበያ መረጃ ለማዘመን መሰረተ-ልማት አቅርቦቶችን ማስፋፋትና ማጠናከር፣ የግብርና ምርት ግብይት የውጭ ምንዛሬ እንዲያስገኙ በብዛት፣ በዓይነትና በጥራት ለገበያ እንዲቀርቡ ገበያ የማመቻቸት፣ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስራዎች፣ እንዲሁም ህገ-ወጥ ንግድንና ግብይት መከላከል የሚያስፈልግ የክትትል፣ መረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

የክልሉን ተወዳዳሪና ተነጻጻሪ የኢንቨስትመንት ሀብት በጥናት በመለየት የክልሉን እምቅ ሀብትና ምቹ ሁኔታዎች በማስተዋወቅ እና የተለያዩ የኢንቨስትመንት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት እንዲሁም የተዘጋጁ መድረኮችን በመጠቀም የማህበረሰቡን፣ የአስፈጻሚውን እና ፈጻሚውን ብሎም የባለሀብቱን ግንዛቤ በማዳበር የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር እና እንዲስፋፋ በማድረግ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሚናውን በአግባቡ እንዲጫወት ይደረጋል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የንግድና ኢንቨስትመንት ልማት ዓላማዎች፣**

- በንግድና በግብይት ዘርፍ ህጋዊና ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ምቹ የንግድ ስርዓት እና ጤናማ የገበያ ውድድርን በመፍጠር የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ልማትን ማፋጠን፣
- ዘመናዊ የግብርና ምርት ግብይት መሰረተ-ልማት በማስፋፋት የከተማ፣ የገጠር እና የከተሞች የእርስ በርስ ትስስር እንዲፈጠር ማድረግ እንዲሁም ለውስጥና ለውጭ የገበያ

ትስስርን በመፍጠር የግብርና ምርቶችን በዓይነት፣ በጥራትና በመጠን በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት

○ መሠረታዊ የፍጆታ ምርቶች አቅርቦትና ስርጭት ፍትሃዊና ወቅታዊ በማድረግ የሸማች ህብረተሰብ ተጠቀሚ እንዲሆኑ ማስቻል እና በሕግ መሰረት ለሸማቹ ጥበቃ ማድረግ

○ የንግዱ ማህበረሰብንና የሸማቹን ኅብረተሰብ አደረጃጀቶችን በመደገፍና በማጠናከር የህዝቡንና የነጋዴውን ተሳትፎ በማሳደግ ለዘርፉ ዕድገት አጋዥነታቸውን እንዲረጋገጥ ማድረግ የተቀመጡ የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

○ በክልሉ የኢንቨስትመንት አማራጭ ዕድሎችና ንጽጽራዊ ጠቀሜታ ላይ ያነጣጠረ የማስተዋወቅ ስራ በመስራት የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በመሳብ የክልሉን የግል ኢንቨስትመንት በማስፋፋት የተፈጥሮ ሀብታችንን ጥቅም ላይ በማዋልና በማልማት፣ የወጪ ምርቶች ገበያን በማዳበር፣ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲፈጠር በማድረግ፣ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር የክልሉን ህዝቦች የኑሮ ደረጃ ማሻሻልና ለአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት የበኩሉን ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ ዋና ዓላማ ተደርጎ ተለይቷል።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የንግድና ኢንቨስትመንት ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች፣**

**ንግድ ዘርፍ፡-**

በክልሉ ባሉ ነባር መዋቅሮችና አዲስ በሚፈጠሩ መዋቅሮች የኦን-ላይን የንግድ ሥርዓት እንዲጀመርማስቻል። በክልሉ 103,737 የንግድ ምዝገባ፣ 118,202 አድስ የንግድ ፈቃድ እና 623,632 የንግድ ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎቶችን መስጠት፤ ክልሉ የተለያየ መጠን ያላቸው 40 ድርጅቶች/ግለሰቦች የካፒታል ዕቃዎች ውል ስምምነት ምዝገባ ማካሄድና መረጃቸውን ማደራጀት፤ ሸማቾች በግብይት ወቅት ሆነ በሌላ በተዘዋዋሪ መንገድ ባጋጠማቸው ሸማቹን በሚጎዱ ድርጊቶች ላይ የሚቀርቡ 32,635 ቅሬታዎች /አቤቱታዎችን/ በመቀበል በ100% ተገቢውን ድጋፍና መረጃ በመስጠት መፍትሔ እንዲያገኙ ማድረግ፣ 380,741 ነጋዴዎች ለሸጧቸው ምርቶች ወይም አገልግሎት ለሸማቹ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ መወጣቱን 16 ጊዜ ክትትል ማድረግ።

**መሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች፡-**

በክልሉ 70,380 ቶን ስኳር፣ 76,678.6 ቶን ስንዴ እና 68,428,288 ሊትር ዘይት መሰረታዊ የንግድ ዕቃዎች እንዲቀርቡና እንዲሰራጩ ማድረግ፣ መሠረታዊ የፍጆታ ምርቶች ወይም ሸቀጦች ወይም አገልግሎቶች ስርጭት በተገቢው መንገድ ለተጠቃሚዎች መድረሱን በ72 ዙር በ56 አሰራጮች ላይ ክትትል በማድረግና ማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ቅሬታ የሚቀርብባቸውን አሰራጮች ወደ 2% መቀነስ፡፡

የሀገሪቱ የንግድ ውድድር ህግን በተላረረ መልኩ በንግድ ዕቃዎች ላይ የዋጋ የመጨመር ድርጊት ለመከላከል 96 ዙር በ567,064 ንግድ ድርጅቶች ላይ ክትትል ማድረግና ማስተካከያ እርምጃ በማስወሰድ ችግር የሚታይባቸውን ድርጅቶችን በ5% መቀነስ፡፡

195,848 በግብይት ላይ የዋሉ የሥነ-ልኬት መሣሪያዎች በመደበኛና በድንገተኛ ፍተሻ በማረጋገጥ ሸማቹን ህብረተሰብ ብዝበዛ መቀነስና በተገኙ ጉድለቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ መድረግ፡፡ በ54 ነባርና አዳዲስ የነዳጅ ማደያዎች ላይ 32 ጊዜ መደበኛና 16 ጊዜ በድንገተኛ የምርመራ ስራ ይሰራል፡፡

37 ነባርና ዘመናዊ የመጀመሪያ ደረጃ የግብርና ምርት ግብይት ማዕከላትን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ማጠናከር፣ 106 የገበያ ማዕከላት የይዞታ ማረጋገጫ እንዲያገኙ በቅንጅት ድጋፍና ክትትል ማድረግ ለባዛርና ኤግዚብሽን ዝግጅት 184 ፍቃድ መስጠት፡፡

**ግብይት፤-**

623,460 ቶን የአገዳ፣ 556,083 ቶን ብርዕ፣ 42,449 ቶን የቅባት፣ 731,692 ቶን የጥራጥሬ ሰብል፣ 333,522 ቶን ፍራፍሬ እና 402,279 ቶን የአትክልት 16,735 ቶን የጫት፣ 57,340 ቶን የእንሰት እና  176,432 ቶን የስራስር 8,721.5 ቶን ሰሊጥ፣ 2,245 ቶን ቀይ ቦሎቄ፣ 745.7 ቶን ማሾና 143.28 ቶን አኩሪ አተር ምርቶችን በመጠን፣ በፍላጎትና የገበያ ዋጋ መረጃዎችን መሰረት ባደረገ መልኩ የሀገር ውስጥ የገበያ ትስስር መፍጠር፡፡

በቁጥር 1,668,145 የዳልጋ ከብት፣ 2,493,055 በግ፤ 1,219,916 ፍየል፣ 4,002,005 ዶሮዎች እና 3,977.39 ቶን ዓሳ፣ 70,842.27 ቶን ማርና ሰም፣ 2,175,640 ሊትር ወተት እና 23,273.33 ቶን ቅቤ ምርቶች በመጠን፣ በፍላጎትንና የገበያ ዋጋ መረጃዎችን መሰረት ባደረገ መልኩ የገበያ ትስስር ይፈጠራል፡፡ በቁጥር 59,881 ከብት፣ 40,093 በግ፣ 39,518 ፍየልና 11,855.42 ቶን ማርና ሰም፣ 432,115 ከብት ቆዳ፣1,629,050 ሌጦ ጥራታቸውንና ደረጃቸውን ጠብቀው ወደ ውጭ ሀገር እንዲላኩ ለኤክስፖርት ቄራና ለተለያዩ ላኪ ድርጅቶች

እንዲሁም ለፋብርካዎች እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

**ኢንቨስትመንት ማስፋፋት፤-**

274 ባለሀብቶችን በቀጥታ በግንባር በመገናኘት፣ 2,006 ደግሞ የህትመትና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ እና ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም የፕሮሞሽን ስራ በመስራት በጠቅላላው 2,280 ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ገብተው በኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ይሠራል፡፡ በግብርና 1,017፣ በኢንዱስትሪ 494፣ በአገልግሎት 769 በጠቅላላው 2,280 ባለሀብቶች በ10 አመት ውስጥ ፈቃድ በማውጣት ወደ ኢንቨስትመንት ይሰማራሉ፡፡ 356 ባለሀብቶች የማስፋፊያ ፈቃድ የሚሰጥ ሲሆን ከሚሰጡ የፈቃድ አገልግሎቶች ብር 161.18 ቢሊዮን ካፒታል በመመዝገብ 653,882 የስራ እድልም ይፈጠራል፡፡ 893 ባለሀብቶች ፈቃዳቸውን ያድሳሉ፡፡ ከሚሰጡ የፈቃድ አገልግሎቶች ብር 2,933,627.14 ገቢ ይገኛል፡፡

አዲስ ፈቃድ ያወጡ 2280 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በመረጃ ቋት በማደራጀት ፣የፕሮጀክቶችን መረጃ 43,539 ጊዜ ውቅታዊ የማድረግ ስራ በመስራት 3,260 የተተነተነ መረጃ ለተጠቃሚ የመስጠት ስራ ይሰራል፡፡ በጋይድ ማፕ ተደግፎ የተዘጋጀ 53,350.82 ሄ/ር አዲስ የገጠር የኢንቨስትመንት መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ 109,785.9 ሄ/ር መሬት በመለካት ከይዞታ ማረጋገጫ ካርታና ከምስክር ወረቅት ጋር የማሰረከብ ስራ ይከናወናል፣ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለ36,748 ቋሚና ለ917,134 ጊዜያዊ በድምሩ ለ953,882 ዜጎች የስራ እድል እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

የክልሉን የኢንቨስትመንት ፖቴንሻል በየዓመቱ አንደ ማለትም በዕቅድ ዘመኑ 10/አስር/ ጥናት ይደረጋል፡፡ በክልሉ በኢንቨስትመንት በልዩ ልዩ የሥራ መስክ ተሰማርተው ለሚገኙ በግብርና 4,471፤ በኢንዱስትሪ 3,171፤ በአገልግሎት ሰጪ 2,247 በድምሩ 9,891 ፕሮጀክቶችን 23,545 ጊዜ/ዙር ክትትልና ድጋፍ በማድረግ፤ ከቅድመ ትግበራ ወደ ሙሉ በሙሉ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ደረጃዎች እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የንግድና ገበያ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች፣**

የንግዱ ዘርፍ በአሠራር፣ በሰው ኃይልና በአደረጃጀት እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ ከዚህም አንጻር ቅንጅታዊ አሰራርን የማጎልበት፤ የሥራ አመራርና የቴክኖሎጂ አቅምን የመገንባትና የንግድ

አሠራር ምቹነትና የሪፎርም ሥራዎችን ውጤታማ የማድረግ ሥራዎች ተፈጻሚ ይደረጋሉ። በተጨማሪም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎትን የማዘመንና በጥናት ላይ የተመሠረተ የግብይት ሰንሰለትና የጥራት ቁጥጥር ሥራዎች ይካሄዳሉ። ህገ ወጥ ንግድን በተጠናከረ መልኩ ለመቀነስ የተሻሻለ የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል። አስተማማኝና ዘመናዊ የንግድና ገበያ መረጃ ሥርዓት ይገነባል።

ንግድን ለመጀመር የሚያስፈልጉ ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታዎች እንዲዘምኑ፣ ዲጂታል መር የሆነ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት እንዲሰፍንና መሰረታዊ የሆኑና ለንግድ እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉ አስፈላጊው ፋይናንስ እንዲቀርብ፣ እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራር እንዲጠናከር ይደረጋል።

የለውጥ ስራዎችን ማስቀጠል፣ ዘመናዊ የመረጃና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ የኢንቨስትመንት መማክርትና ምክክር መድረኮችን ማጠናከር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፣ የኢንቨስትመንት ግንዛቤ ማስጨበጥ እና የፀረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ትግል እንዲጠናከር ይደረጋል።

### 3.6. የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ልማት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች፣**

የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ለመገንባት በዘርፉ የተሠማራውን የሰው ኃይል በዕውቀት እና በክህሎት ማብቃት፣ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋት፣ ሕዝባዊ አደረጃጀቶችን ማጠናከር፣ ዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ፣ ዘመናዊና ለአጠቃቀም ምቹ የሆኑ መተግበሪያዎችን የማልማት ሥራ በትኩረት ይሰራል።

የመሠረተ ልማት አቅርቦቶችን ለማስፋፋት የባህል ማዕከላት፣ የዕደ-ጥበባት መንደር፣ የቴአትርና ሙዚቃ ሥፍራዎች፣ የቱሪስት መረጃ ማዕከል፣ የቱሪስት መዳረሻዎች (መንገድ፣ ውሃ፣ መብራት፣ ስልክ፣ ኢንተርኔት አገልግሎት)፣ ህጋዊ በማድረግና በማዘመን፣ በማልማትና ለሥራ ምቹ ለማድረግ በትኩረት ይሰራል።

በዘርፉ ልማት ውስጥ የግል ዘርፍ ሚና ለማሳደግ የባለሀብቱን ተሳትፎ ማጎልበት፣ አማራጭ የሥራ ዘርፎችን መለየትና እንዲተገበሩ ድጋፍ መስጠት፣ የግሉን ዘርፍ አጋርነት ማጠናከር ትኩረት ይሰጣቸዋል።

ስፖርትን ለልማት ለማዋል የሚያስችል አደረጃጀትና ስርዓት በመፍጠር፣ ስፖርትን በዘላቂነት ችግሮችን በመፍታት ስፖርት ለማህበራዊ ልማትና ለአገር ብልጽግና፣ ህዝቦችን ለማቀራረብ፣ ለክልላዊ ገጽታ ግንባታ እና ለስፖርት ቱሪዝም ዕድገት፣ እንዲሁም ከአጎራባች ክልሎች ጋር አንድነትን ለማምጣት መሳሪያ ሆኖ እንድያገለግል ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል፡፡

**ባህል ቱሪዝም ዓላማዎች**

- የብሔሮችና ብሔረሰቦችን ቋንቋ፣ ሥነ ጥበብ፣ ባህል፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶችን በማጥናት፣ በዘለቄታዊነት በመጠበቅ፣ በመሰነድና በማልማት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳቸውን ማሳደግና ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ፣
- የማህበረሰብ ስፖርትን በየደረጃው እንዲስፋፋ በማድረግ፣ ጤናው የተጠበቀ አምራች ዜጋንና ብቁ ስፖርተኞችን በማፍራት ዘርፉ ለሰላም፣ ለአንድነትና ለብልጽግና የሚኖረውን ፋይዳ ማጎልበት ነው፡፡

**ባህል ቱሪዝም ዋና ዋና ግቦች**

**ባህል ዘርፍ፡-**

ክልላዊና ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ ሽፋን በመቶኛ ከ 85 ወደ 90 ማሳደግ፣ ሁለት በመጥፍት አደጋ ላይ ያሉ ቋንቋዎች እንዲያገግሙ፣ ስርአተ ፅህፍት የተዘጋጀላቸው ቋንቋዎች 11 ከነበረበት ወደ 13 ማሳደግ፣ 4 የነበረውን ሰዋሰው የተዘጋጀላቸው ቋንቋዎች ወደ 7 ማድረስ፣ 4 ባህላዊ መዝገበ ቃላት የተዘጋጀላቸውን ቋንቋዎች ወደ 8 ማድረስ፣ 6 ተጠንተው የታተሙ ቃላዊ ተረኮች ስነ-ቃሎችና ወጎችን ወደ 13 ማድረስ፣ የባህል ሳምንት፣ ፌስቲቫልና አውደ ርዕይ በክልሉና በታችኛዉ መዋቅሮች ማዘጋጀትና ማክበር አሁን ካለበት 2 ወደ 24 ማሳደግ፣ የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸው በማህበር የተደራጁ የዕደ ጥበብ ሙያተኞች ማህበራት አሁን ካለበት 6 ወደ 24 ማሳደግ፣ የስዕል፣ ፎቶግራፍና ኤግዚብሽንና የሥነ ጥበብ ውድድር 6 ወደ 68 ማሳደግ፣ ለህዝብ እይታ የቀረቡ የትውን ጥበባት በቁጥር አሁን ካለበት 30 ወደ 512 ማሳደግ፣

**ቱሪዝም ዘርፍ፡-**

የተመዘገቡ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎችን ቁጥር አሁን ካለበት 190 ወደ 336 ማሳደግ፣ የተጠበቁ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች ቁጥር አሁን ካለበት 21 ወደ 288 ማሳደግ፣ የተቋቋሙ የዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎች ቁጥር አሁን ካለበት 2 ወደ 4 ማሳደግ፣ የማካለልና ዳግም ማካለል በማካሄድ ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸው የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ቁጥር አሁን ካለበት 2 ወደ 4 ማሳደግ፣ ነባርና አዳዲስ የብሔራዊ ፓርክ ውስጥ ለውስጥ መንገዶች ግንባታ በኪ.ሜትር አሁን ካለበት 42 ወደ 240 ማሳደግ፣ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎችን ለማልማት የተገነቡ የመሰረተ ልማት ስራዎች ብዛት አሁን ካለበት 6 ወደ 24 ማሳደግ፣ የአገር ውስጥ ቱሪዝምን በማስተዋወቅና የጉብኝት ባህል እንዲዳብር በማድረግ የጎብኚዎችን ቁጥር አሁን ካለበት 1,500,000 ወደ 19,065,000 ማሳደግ፣ ጥራት ያለው የሴክተሩ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብዛት ከ1400 ወደ 5,280 ማሳደግ፣ በ12 ነባርና በ11 አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችና መስህብ ልማቶችን ማጎልበት፣ የክልሉን የቱሪዝም ሀብቶች በሀገርና ዓለም አቀፍ ተደራሽነት ባላቸው የማስተዋወቂያ መንገዶች በመጠቀም 8 ጊዜ የግብይትና ፕሮሞሽን ሥራዎችን መስራት፣ ዘርፉን በማልማትና በማሳደግ ለዜጎች የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል ወደ 640,000 እና የሚሰበሰበውን ገቢ 750,000 ወደ 11,839,374 ብር ማሳደግ፣

**ስፖርት ዘርፍ፡-**

የህዝባዊ እና መንግስታዊ ስፖርት ተቋማት ሰብዓዊ ሀብትን በማልማት የተዘጋጁ የህግ ማዕቀፎችን ወደ 12፣ ስታንዳርዶች ወደ 8 እንዲሁም ዘመናዊ ቴክኖሎጆዎችን ወደ 5 በማሳደግ የአሰራር ስርዓቶችን ማሻሻል፣ ከህብረተሰብ ወደ 35,996,083 ብር፣ ከስፖርት ልማት ፈንድ 3,500,000 ሚሊየን ብር፣ ከስፖርት ማህበራት ወደ 800,000 ብር፣ ከስፖርቱ ቱሪዝም 121,961,000 ብር እንዲሁም ከስፖርት ቦታዎችና ተቋማት 1,000,000 በመሰብሰብ ተቋማዊ የፋይናንስ አቅምን ማሳደግ፣ የስፖርት ማዘዉተሪያ ስፍራዎችን ብዛት ወደ 8 በማሳደግ ህጋዊነታቸዉን በማረጋገጥና 30% ተደራሽ ማድረግ፣ አገልግሎት መስጠት የጀመሩትን ወደ 4፣ የተገነቡ 1ኛ ደረጃ 2፣ 2ኛ ደረጃ ወደ 12፣ 3ኛ ደረጃ ወደ 288 የስፖርት ማሰ/ማዕከላትና ተቋማትን ቁጥር ማሳደግ፣ በየደረጃዉ የማህበረሰብ አቀፍ ስፖርትን በማስፋፋት የሚሳተፈዉን የህብረተሰብ ቁጥር ወደ 1,145,888 ማሳደግ፣ በስፖርት ለሁሉም መዝናኛና በባህል ስፖርቶች የህብረተሰቡን ተሳትፎ ወደ 1,200,000 ማሳደግ፣ በትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም የአማተር ባለሙያዎች ቁጥር ወደ 480 ማሳደግ፣ የታዳጊ ወጣቶች ስልጠና ልማት ፕሮግራም የተተኪ ስፖርተኞችን በግለሰብ የማበልፀጊያ ማዕከላት ወደ 50 እና

በመንግስት ማበልፀጊያ ማዕከላት ወደ 845 ቁጥር ማሳደግ፣ የኤሊት (የአዋቂ እና የላቁ) ስፖርተኞችን ቁጥር ወደ 270 ማሳደግ፣ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ በ23 የስፖርት አይነቶች ስፖርተኞችን በማሳተፍ ውጤት ማስመዝገብ፣ በክልል ደረጃ ክልል አቀፍ 151 የዉድድር መድረኮችን ማዘጋጀት፣ የስፖርት ኢንዱስትሪዉን በማስፋፋት በዘርፉ የሚሰራዉን የባለሀብት ተሳትፎን ወደ 15 ማሳደግ።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ስልቶች ተቀምጠዋል፣**

በአሥር ዓመቱ የዘርፍ ዕቅድ ላይ ከአመራር፣ ከሰራተኛ፣ ከባለድርሻ አካላት፣ በዘርፉ ካሉ ማህበራት፣ ፌዴሬሽኖችና ከግል ባለሃብቶች ጋር የጋራ መግባባት መፍጠር እና ዕቅዱን በየደረጃው ማውረድ፣ እንዲሁም እቅዱን መሰረት ያደረገ የለውጥ አስተዳደር በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል።

የዘርፉ የሰው ሀብት ልማት፣ የገበያና ፕሮሞሽን፣ የቱሪዝም አገልግሎቶችና መረጃ ስርጭት፣ የመዳረሻ አካባቢ ማህበረሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፤ በቱሪዝም ልማት የመንግስትና የግል ዘርፍ አጋርነት፣ ፍትሃዊ የቱሪዝም ንግድን ማረጋገጥ፤ የቱሪስት ደህንነትና ጥበቃ ማቋቋም፤ ቱሪዝም ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው የሚያስችሉ ሥራዎች የሚከናወኑ ሲሆን የማስፈፀሚያ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሰራር ማስተካከያዎችን ማውጣትና መተግበር እንዲሁም በዘርፉ የሚካሄዱ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች የማስፈፀሚያ ስልት ይሆናሉ።

የስፖርት ፖሊሲ እና የስፖርት ሕግ እንዲሁም የስፖርት ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች፣ የማህበረሰብ ስፖርት ማስፋፊያ ፕሮግራም እና የፀረ አበረታች ቅመሞች ስትራቴጂ እና ልዩ ልዩ ሰነዶች ይተገበራሉ።

# ምዕራፍ አራት

# 4 የመሠረተ ልማት ዕቅድ

## 4.1. የትራንስፖርት ልማት

### የቀጣይ አሥር ዓመታት የትራንስፖርትና መንገድ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች

የማስፈፀም አቅም በማሳደግ ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ አገልግሎት መስጠት፣ የትራንስፖርትና መንገድ መሰረተ-ልማት አቅርቦቱን ማሻሻል፤ ደህንነቱ የተጠበቀና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የትራንስፖርት የአገልግሎት አሰጣጥን ማስፈን፤ በሥራ ዕድል ፈጠራ የህብረተሰቡን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፡፡

### የቀጣይ አሥር ዓመታት የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ዓላማዎች

የትራንስፖርትና መንገድ መሰረተ ልማት ፍትሃዊ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ (የመንገድ ልማት ዲዛይን አቅርቦትን ማሳደግ፣ የመንገድ ልማት ግንባታ አቅርቦትን ማሳደግ፤ የመንገድ ጥገናና ደህንነትን ማሳደግ፣ የመንገድ ልማት ደረጃን ማሻሻል) ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣ የትራንስፖርት አገልግሎቱ የተቀናጀ፣ ፍትሃዊና ተደራሽ ማድረግ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርትና መንገድ መሰረተ ልማት እና አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ፣ የመፈጸም አቅም መገንባት የዘርፉ ውጤታማነትን ማሳደግ ናቸው፡፡

### የቀጣይ አሥር ዓመታት የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ዋና ዋና ግቦች

**የትራንስፖርትና መንገድ መሰረተ ልማት ፍትሃዊ ተደራሽነትን ማረጋገጥ፡-**

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና መስጫ /ትራፊክ ኮምፕሌክስ /በአንድ ዞን ላይ በመገንባት ከ 0 ወደ አንድ ማድረስ፤ ጋራጮች በጥገና ወቅት የሚወጣውን አከባቢ በካይ ጋዝ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለመከላከል እንዲቻል በሁለት ዞኖች ውስጥ የሚገኙ ጋራጮችን በኢንደስትሪ ዞን ማደራጀት፣ የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን በመገንባት አሁን ከነበረበት 34 ወደ 40 ማድረስ፣ የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን ከደረጃ 2 ወደ ደረጃ 1 ለማሻሻል ከ 0 ወደ 5 ማድርስ፣ የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን ከደረጃ 3 ወደ ደረጃ 2 ለማሻሻል ከ 3 ወደ 14 ማድረስ፣ በከተሞች የከተማ ታክሲ መናኸሪያዎችን በመለየት 0 ከነበረበት ወደ 20 ማድረስ፣ የስምሪት መስመሮች አሁን ካለበት ከ439 ወደ 520 ማድረስ፣ በከተሞች ውስጥ የስምሪት መስመሮች ላይ 0 ሼዶች ከነበሩበት 20 ማድረስ፣ የመኪና ማቆሚያ ፓርኪንግ አሁን ከነበረበት 0 ወደ 2 ማድረስ፣ የሳይክል መንገድ ለይቶ ተግባራዊ ለማድረግ 0 ከነበረበት

በዋና ዋና ከተሞች ወደ 4 ማድረስ፣ የጭነት ትራንስፖርት መናኸሪያ ግንባታ አሁን ካለበት ከ 0 ወደ 6 ማድረስ፡፡

የመንገድ ጥናትና ዲዛይን አሁን ካለበት 3,863.3 ኪ.ሜ ወደ 7,800 ኪ.ሜ ለማሳደግ፣ በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም 3,863.3 ኪ.ሜ ወደ 7,800 ኪ.ሜ.ማሳደግ፣ የድልድይ ጥናትና ዲዛይን አሁን ካለበት 86 ወደ 129 ለማሳደግ፣ በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም ከ 86 ወደ 180 ማሳደግ::

መንገድ ግንባታ አሁን ካለበት 1,642.12 ኪ.ሜ ወደ 4,215.145 ኪ.ሜ ለማሳደግ፣ በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም አሁን ካለበት 1,642.12 ኪ.ሜ ወደ 4,215.145 ኪ.ሜ ማሳደግ፣ የመንገድ ደረጃን ከማሻሻል አንፃር አሁን ካለበት DC2 ወደ DC3 ሲሆን፣ በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም 24 ኪ.ሜ. ወደ 624 ማሳደግ ነው፣

የድልድይ ግንባታ አሁን ካለበት 30 ወደ 60 ለማድረስ፣ በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም የድልድይ ከ 30 ወደ 60 ማድረስ፣ የመንገድ ጥገናና ደህንነት አሁን ካለበት 1,530 ኪ.ሜ ወደ 12,570 ኪ.ሜ ለማሳደግ፣ በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም ከ12,570 ኪ.ሜ መጠገን፡፡ በሁሉ አቀፍ ገጠር ተደራሽ መንገድ ልማት ፕሮግራም የሥራ እድል የተፈጠረላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች 67,777 ወደ 210,108 ማድረስ፡፡

**የትራንስፖርት አገልግሎቱ የተቀናጀ፣ፍትሃዊና ተደራሽ ማድረግ፡-**

ቦሎዎችን በጥራዝ ማሳተምና ማሰራጨት 165 ከነበረበት ወደ 709 ማድረስ፣ ሰሌዳዎችን ማሳተምና ማሰራጨት 25,000 ከነበረበት ወደ 42,000 ማድረስ፣ የተሽከርካሪ ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ/ ማሳተምና ማሰራጨት ከ18,000 ወደ 42,000 ማድረስ፣ 42,000 የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ላምኔትድ አድርጎ ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤ የከተማና የገጠር የስምሪት መስመሮችን አሁን ከነበረበት 419 ማድረስ ወደ 520፣ በክልሉ የህዝብ የንግድ ማመላለሻ የሚሰጡ ማህበራትን ቁጥር ከ10 ወደ 15 ማድረስ፣ በተለየ መስመር የብስክሌት ትራንስፖርት አገልግሎት ተግባራዊ የተደረገባቸው ዋና ዋና ከተሞች ብዛት ከ0 ወደ 6 ማድረስ፣ በወንዞችና ሀይቆች ላይ የሚሰሩ ባለሞተር ጀልባ ኦፕሬተሮችን አሁን ካለበት 0 ወደ 2 ማድረስ፡፡

**የትራንስፖርት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፦**

በስታንዳርዱ መሠረት አገልግሎት የሚሰጡ ማሰልጠኛ ተቋማትን ድርሻ ከ 75 ወደ 100 % ማድረስ፣ በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት የሚሰጡ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማትን ድርሻ ከ 0 ወደ 50 % ማድረስ፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማትን ቁጥር ከ 13 ወደ 30 ማድረስ፣ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማትን ቁጥር ከ 0 ወደ 4 ማድረስ፣ ተሽከርካሪዎች ላይ ድንገተኛ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ ማድረግ ከ1,200 ወደ 2,000 ማድረስ፣ የተሽከርካሪዎች አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ 0 ከነበረበት 4 ማድረስ፣ የትራፊክ አደጋ አሁን ከነበረበት 296 በ5% በየዓመቱ በመቀነስ በ2022 ወደ 178 ማውረድ፤ ሞት የሚያስከትል አደጋ 97 ከነበረበት በ5% በመቀነስ ወደ 58 ማድረስ፣ የንብረት ዉድመት ከብር 7,188,979 ከነበረበት በ5% በመቀነስ ወደ ብር 4,313,387 ማድረስ፣ በሰው ህይወት ላይ ይደርስ የነበረውን ሞት ከ108 በየአመቱ በ5% በመቀነስ ወደ 64 ማድረስ፣ የፍጥነት መገደቢያና GPS መሳሪያ የገጠሙ የንግድ ተሽከርካሪዎች ቁጥር በየአመቱ በ20% በማሳደግ 90% ማድረስ::

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፥**

ሞተር አልባ መካከለኛ ትራንስፖርት ዘዴ አፈፃፀም መመሪያ መጠቀም፣ የብዙሃን ትራንስፖርት ማስፋፊያ ስትራቴጂ፣ የትራፊክ ፍሰት ቁጥጥር ስትራቴጂ፣ ፕብሊክ ትራንስፖርት ደንብ፣ የዘርፉን የአደረጃጀት ማሻሻያዎች፣ የወርሃዊ ድርጊት መረሃ-ግብርና መናኸሪያ ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ ማሻሻል፤ የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም፣ ሁሉ አቀፍ መንገድ ግንባታ አተገባበር መመሪያና ደንብ እና የትራንስፖርት ኢንፎርሜሽን ሶፍትዌር ግንባታ ማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው።

**4.2. የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጅ ልማት**

**የውሀ፣ ማዕድንና ኢነርጅ የትኩረት አቅጣጫዎች**

የንጹህ መጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን አቅርቦት ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች ማዳረስ፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ማስፋፋት፤ የተገነቡ የመጠጥ ውኃ ተቋማትን አገልግሎት በዘላቂነት እንዲቀጥል ማስቻል፤ የታዳሽ ኃይል የመጠጥ ውኃ አቅርቦት አማራጭን ለገጠር መጠጥ ውኃ ተቋማት እንደ አንድ የኃይል ምንጭ መጠቀም፤ የከተሞች

ፍሳሽ አወጋገድ ሥርዓትን ማጠናከርና አስፈላጊ የመሠረተ ልማት አውታሮችን መገንባት፤ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማትን ማሳደግ በልማት ዕቅዱ ዘመን ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል። በተጨማሪም በሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለሚደርስባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ንጹህ የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ሃይጅን የአቅርቦት ድጋፍ ሥራን በትኩረት ማከናወን፤ ልዩ ድጋፍ በሚሹ የክልሉ  አካባቢዎች ወጥነትና ዘላቂነት ያለውን ድጋፍ ማድረግ በቀጣይ በልማት ዕቅዱ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ።

**የቀጣይ የዕቅድ ዘመኑ የውሃ ልማት ዓላማዎች**

የክልሉን የመጠጥ ውኃ፣ ሳኒቴሽንና ኃይጂን አቅርቦቱን በማስፋፋት የአገልግሎቱ ተደራሽ ያልሆነውን ሕዝብ ተጠቃሚ ማድረግ፤ ንፁህ፣ አስተማማኝና በቂ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት የልማት ዕቅዱ ማጠናቀቂያ ለሁሉም ዜጎች ማዳረስ፤ የከተሞችና ገጠር ሳኒቴሽን አገልግሎት አቅርቦትን ማሳደግ፤ የትምህርትና የጤና ተቋማትን ቅንጅታዊ አሠራር በማጠናከር የመጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን አገልግሎትን ማስፋፋት፤ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የውኃ ጥራት ደረጃ ማስጠበቂያ መንገዶችን ተግባራዊ በማድረግ የመጠጥ ውኃ ጥራትን ማረጋገጥ፤ የዋሽና የተፋሰስ ዘመናዊ መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት፤ በዘርፉ የሚሰሩ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ አለመኖሩን ማረጋገጥና የውኃ ሀብት አስተዳደርን ማስፋፋትና ማጠናከር ዋና ዋና አላማዎች ናቸው።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የውሃ ልማት ዋና ዋና ግቦች**

የመጠጥ ውሃ ተቋማት ጥናትና ዲዛይን፣ አፕሬሳልና ይሁንታ ስራዎችን ጥራትና ቅልጥፍናን ማሻሻል፣ ለ3,079,695 የገጠር ነዋሪ ህዝብ በ1 ኪ/ሜ ክልል ውስጥ በነፍስ ወከፍ በቀን 25 ሊትር ውሃ በማቅረብ የገጠር ንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በዕቅድ ዘመኑ መነሻ 2014ዓ.ም ከነበረበት 33.3% በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 2022 ዓ/ም ወደ 100% ማሳደግ፣ ለ533,360 የከተማ ነዋሪ ህዝብ በነፍስ ወከፍ በቀን ለደረጃ 3 ከተሞች 60 ሊትር፣ ለደረጃ 4 ከተሞች 50 ሊትር እና ለደረጃ 5 ከተሞች 40 ሊትር ውሃ በማቅረብ በዕቅድ ዘመኑ መነሻ 2014ዓ.ም ከነበረበት 39.2% በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 2022 ዓ/ም ወደ 100% ማሳደግ፣ ለ3,613,055 የክልሉ የከተማና ገጠር ነዋሪ ህዝብ በተቀመጠው መለኪያ የንፁህ መጠጥ ውሃ በማቅረብ የክልሉን አማካይ ሽፋን በዕቅድ ዘመኑ መነሻ 2014 ዓ.ም ከነበረበት 34.2% በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 2022ዓ.ም ወደ 100% ማሳደግ፣ አገልግሎት የማይሰጡ የመጠጥ ውሃ ተቋማትን በመጠገንና መልሶ በመገንባት የመጠጥ ውሃ ተቋማትን የብልሽት መጠን በዕቅድ

ዘመኑ መነሻ 2014 ዓ/ም ከነበረበት 38.8% በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 2022 ዓ.ም ወደ 0 መቀነስ፡፡ የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር ውሃ አለኝታ ጥናት ማካሄድ፣ የውሃ ሀብት አጠቃቀም በህጋዊ ስርዓት ላይ የተመሰረተ እንዲሆንና ፍትሃዊና የተቀናጀ የውሃ ሀብት ልማትና አስተዳደር ስርዓት ማስፈን፣ የውሃ ብክለትና ብክነት መቀነስ እና የውሃ አቅርቦት ጥራትን ማረጋገጥ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የመጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽን እና ሃይጅን መረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀት እና ስርጭት ሥርዓት መፍጠር፤

**የውሃ ልማት ዓላማዎችና ግቦች ለማሳካት የማስፈጸሚያ ሥልቶች**

የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በሚመለከት ፍላጎትን፣ አቅምንና ቁጠባን መሠረት በማድረግ ውጤታማ፣ አስተማማኝና ዘላቂ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖር ይደረጋል፤ ለገጠሩ ህብረተሰብ ውሃ አቅርቦት ሽፋን እንዲስፋፋ ለማድረግ በአነስተኛ ወጪ ሊገነቡ የሚችሉ አማራጭ ዲዛይኖችን ዘላቂና አዋጭ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

በነባር ውሃ ተቋማት ውስጥ የበቃ አስተዳደርና አሠራር እውን በማድረግ አዳዲስ የውሃ ልማት ፕሮጀክቶች ከመገንባታቸው በፊት ቁጠባን መሠረት ያደረጉ እርምጃዎች ለመውሰድ ሚያስችሉ ሥልቶች ይመቻቻሉ፣ ነባር የውሃ ተቋማትን መንከባከብና ውሃን በቁጠባ መጠቀም፣ በቤተሰብ ደረጃ መሠረታዊ የውሃ ፍላጎቶችን ማሟላትና ከመሰረታዊ ፍላጎቶች ባሻገር የሚኖረው ውሃ ክፍፍልና አጠቃቀም ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን በሚያመጡ መመዘኛዎች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ፣ ባልተማከለና በዝቅተኛ ደረጃ ያሉትን ውሃ አስተዳደር ተቋማት ጨምሮ ለተሻሻለና ለቀልጣፋ የውሃ ሀብት አስተዳደር አቅም ግንባታ ማካሄድ፣ በከተሞች ዋጋ ማስመለስ መርህን መሰረት ባደረገ መልኩ በአነስተኛ ወጪ በብድር ለሚገነቡ ውሃ ተቋማት ቅድሚያ መስጠት፡፡

## 4.3. የማዕድንና ኢነርጂ ልማት

**የቀጣይ ዓመታት የማዕድንና ኢነርጅ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች፣**

በአማራጭ ኢነርጂ ልማት ዘርፍ የህብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ እንዲቻል የኢነርጂ ምንጮችን በማልማት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ከማድረግም ባሻገር የወቅቱ አለማቀፍ እና ሀገር አቀፍ የትኩረት መስክ የሆነውን የአካባቢ አየር መዛባትና የደን መመናመንን በመቀነስ ጉልህ ድርሻ ያለው በመሆኑ በቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን መሠረት በማድረግ በስፋት የሚተገበር ይሆናል፡፡

የክልሉን የማዕድን ሀብት አለኝታ ጥናት በወርቅ፣በኢንዱስትሪ እና በጌጣጌጥ ማዕድናት ላይ ትኩረት በመስጠት ጥናት የሚደረግ ይሆናል። በማዕድኑ ዘርፍ በፌዴራል ደረጃ ሲተገበሩ የነበሩ ነገር ግን በክልል ደረጃ እንደሚተገበሩ የተለዩትን የነዳጅ ማደያ ብቃት ማረጋገጥና ቁጥጥር፤ የወርቅና የብር ንግድ ብቃት ማረጋገጥና ቁጥጥር ሥራዎች ታሳቢ ተደርጎ አደረጃጀት ማሻሻያው ላይ የሚታይ ይሆናል። ከኢነርጂ ሥራዎች ጋር በተያያዘ የባዮ ፊዩል ልማትና አጠቃቀምን፤ የኢነርጂ ሥራዎች ብቃት ማረጋጫ እና ቁጥጥር እንዲሁም የኢነርጂ ምርምር ማዕከልን በተመለከተ ለክልሉ የተለዩ ተግባራትን መፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት እንዲፈጠር ይደረጋል። የክልሉን የማዕድን ሀብት በጥናት እንዲለይ ቅድሚያ በመስጠት የተገኘውን መረጃ ለአልሚዎች በማቅረብ ኢንቨስትመንትን መሳብ ሌላው ዋነኛው የትኩረት አቅጣጫ ሊሆን ይገባል። በዚህም የማዕድኑን ንዑስ ዘርፉን መሰረት አድርገው ለሚቋቋሙ የማኑፋክቸሪንግ አንዱስትሪዎች እና የግብርና ግብዓት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ለወደፊት ኢንቨስትመንት አቅጣጫ አመላካች የሆነ ፍኖተ ካርታ እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

**የቀጣይ ዓመታት የማዕድን ልማት ዓላማዎች እንደሚከተለው፣**

በልማት ዕቅዱ ዘመን በአጠቃላይ የዘርፉ መሪ ዕቅድ ዓላማ የክልላችንን የማዕድንና የአማራጭ ኢነርጂ ተፈጥሮ ሀብታችንን በተገቢው ደረጃ በማወቅ ለማልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ የሀገራችንን ብሎም የክልሉን ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጡን ለማፋጠን ዘርፉ ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ለማስቻል ነው።

**የቀጣይ የእቅዱ ዘመን የማዕድን ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች፣**

**ከአማራጭ ኢነርጂ ዘርፉ አንፃር፡-**

የተሻሻሉ ማገዶ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ ቤተሰብ በ2014 ከነበረበት 41,083 ወደ 292,083 ማድረስ፣ የባዮጋዝ ግንባታ ተጠቃሚ ህዝብ በ2014 ከነበረበት 695 ወደ 2,735 ማሳደግ፣ የሶላር ተጠቃሚ በቤተሰብ በ2014 ከነበረበት 81,892 ወደ 328,895 ማሳደግ፣ ሶላር ማሾ (እስከ 15 ዋት) በ2014 ከነበረበት 282,230 ወደ 400,000 ማሳደግ፣ የሶላር ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ተቋማት ቁጥር በ2014 ከነበረበት 5 ወደ 119 ማሳደግ፤ (በትምህርት፣ በጤና፤ በመጠጥ ውሀ፣ በመስኖና በሌሎች ተቋማት)፣ ፒኮ/ ሀይድሮ ፓወር ሀይል ማመንጨት የሚችሉ ወንዞችን 9 በማጥናትና በመለየት 3 መገንባት።

**ከማዕድን ሀብት ጥናት እና አስተዳደር አንፃር፡-**

ለብሄራዊ ባንክ የሚቀርበውን የወርቅ መጠን አሁን ከደረሰበት 4,783 ኪሎ ግራም ወደ 12,133 ኪሎ ግራም ማሳደግ፣ ከውጭ የሚመጣውን የኢንዱስትሪ (የድንጋይ ከሰል ማዕድናት ምርት አሁን ከደረሰበት 26,100 ቶን ወደ 1.8 ሚሊዮን ቶን ከፍ ኢንዲል ማድረግ፣ የክልሉን የማዕድን ሃብት አለኝታ አመላካች ሽፋን አሁን ካለበት 10% ወደ 50% ማድረስ፣ በማዕድን ፍለጋ እና ማምረት ሥራ ላይ ኢንቨስት የሚያደርጉ ባለሃብቶች ቁጥር አሁን ከደረሰበት 25 ወደ 100 ማሳደግ፣ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆኑ የግንባታ ማዕድናት ምርት አቅርቦትን አሁን ከደረሰበት 2,907,977 ሜ.ኩብ ወደ 6,431,977 ሜ.ኩብ ማሳደግ፣ የማዕድኑ ዘርፉ ለሥራ-አጥ ዜጎች የሚፈጥረውን የሥራ-ዕድል አሁን ካለበት 16,628 ወደ 73,000 ማሳደግ፣ ከማዕድኑ ዘርፍ ለክልሉ የሚሰበሰበውን የውስጥ ገቢ አሁን ከደረሰበት 22,992,770 ብር ወደ 260,000,000 ብር ከፍ እንዲል ማድረግ፡፡

**የቀጣይ የእቅድ አመታት የማዕድን ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ፣**

የማዕድን ኢንቨስትመንት ሥራ ከአካባቢ ብክለት የፀዳ እንዲሆን ለማድረግ የአረንጓዴ ልማት ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ ማድረግና በሚለማው ማዕድን አካባቢ የሚገኘውን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የተቀመጡ ግቦች እንዲሳኩ ይደረጋል፣

ከከፍተኛ ትምህርትና ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በመተባበር ለዘርፉ ጥናት፣ ልማትና ዕድገት የሚያስፈልጉ የተለያዩ ባለሙያዎችን የማፍራት እንዲሁም ብቁና በቂ ባለሙያዎችን በዘርፉ ማቆየት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

**4.4. የመስኖ ልማት**

**የመስኖ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች**

ክልሉ በመስኖ የመልማት አቅም ያለዉ ቢሆንም ገና ብዙ መስራት የሚጠይቅ ሰፊ መሬትና የዉሃ ሀብት ያለዉ ነዉ፡፡ የቤተሰብ መስኖ ሳይጨምር በአነስተኛ በመካከለኛና በከፍተኛ ማልማት የሚያስችል 303,209.51 ሄ/ር ያልለማ መሬት ያለዉ ሲሆን ይህንን ወደ ልማት ለማስገባት አሁን ካለበት 0.8% በዕ.ት.ዕ ዘመን መጨረሻ ወደ 126,904 ሄ/ር መሬት በማልማት ወደ 41.85% ማሳደግ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫችን ነዉ፡፡ ለዚህም መሳካት በቂ የማስፈፀሚያ ሀብት፣ አጋዥ ቴክኖሎጂዎች፣ የባለድርሻ ተቋማትን ተሳትፎ ማሳደግ፣

መለስተኛ ፕሮፌሽናሎችን በማህበር ማደራጀትና ወደ ስራ ማሰማራት፣ የአቅም ግንባታ ስራዎች እና በቂ ድጋፍና ክትትል ሥራዎችን እንደ ዋነኛ ግብ ማሳኪያ መሣሪያ ተወስዷል።

**የቀጣይ የእቅድ ዓመታት የመስኖ ልማት ዓላማዎች፣**

በክልሉ በተመሳሳይ ተግባር የተሰማሩት ተቋማትን አቅም አሟጦ መጠቀም ፤ጥናትና ዲዛይን፤ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ ላይ መለስተኛ ፕሮፌሽናሎችን በማህበር በማደራጀት ወደ ስራ ማሰማራት፤ በዘርፉ ልምድና ብቃት ያላቸዉን የግል ተቋራጮች በመለየትና በማሳተፍ የመስኖ ግንባታ ስራዎች እንዲሰሩ ማድረግ፤ የመስኖ ተቋማት አስተዳደር የአሰራር ስርአት መዘርጋትና አቅም መፍጠር።

**የቀጣይ የዕቅድ ዓመታት የመስኖ ልማት ዋና ዋና ግቦች፣**

በቀጣይ የዕ.ት.ዕ ዘመን በገፀ-ምድር እና በከርሰ ምድር ዉሃ ሀብት በአነስተኛ በመካከለኛና በከፍተኛ ማልማት የሚያስችል 303,209.51 ሄ/ር ያልለማ መሬት ያለዉ ሲሆን ይህንን ወደ ልማት ለማስገባት እንዲሁም የተገነቡና ሚገነቡ የመስኖ ተቋማትን በሙሉ አቅም እንዲያለሙ ማድረግ፤

128,541 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 149 አነስተኛ፣ 28 መካከለኛ፣ 12 ከፍተኛ እና የ38 የጥልቅ የከርሰ ምድር የመስኖ ፕሮጀክቶች በአጠቃላይ 265 የመስኖ ተቋማት ጥናትና ዲዛይን ስራዎችን መሥራት፣ እንዲሁም 38 ነባር የመስኖ ተቋማት መልሶ ግንባታና ማስፋፊያ ጥናት ማካሄድ ። 126,904 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 153 አነስተኛ፣ 28 መካከለኛ፣ 13 የግድብ መስኖ እና የ38 የጥልቅ የከርሰ ምድር የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ በማካሄድ መስኖ ተቋማቱ አሁን ካለበት 64 ተቋማት በ2022 ዓ.ም ወደ 270 የመስኖ ተቋም ማድረስ፣ እንዲሁም 270 አዲስ የመስኖ ተጠቃሚ ማህበራትን ማደራጀት እና 64 ነባር የመስኖ ተጠቃሚ ማህበራትን ማጠናከር እና በመስኖ ግንባታ ወቅት እና ከግንባታ በኃላ ለ18,900 ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የመስኖ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የማስፈጸሚያ ስልቶች**

ከክልል ጀምሮ እስከ ዞንና ወረዳ ያለዉን የመስኖ መዋቅር የሎጂስቲክስና የሰዉ ሀይል አቅም በመገንባትና የሰዉ ሀይል በማሟላት በራስ ሀይል የሚከናወኑ ስራዎች በስፋት እንዲተገበሩ ማድረግ፤

የመንግስት የልማት ድርጅቶች /አማካሪና ተቋራጭ/ የሚሰሩትን ስራ በኮንትራት አስተዳድር ህግ እንዲፈጸም በማድረግ የስራ ጥራትና ጊዜ እንዲጠበቅ ማድረግ፤ የግል አማካሪዎችና

ተቋራጮችን በስፋት በማሳተፍ ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ፤ በዘርፉ ካሉ የከፍተኛ ትምርት ተቋማትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋራ በቅንጅት መስራት፤ የመስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ሥራዎች የተጠቃሚውን ባህላዊ እሴቶች ጠብቀው ለማከናወን እንዲቻልና ህብረተሰቡ ችግሩን ከመለየት ጀምሮ እስከ ግንባታና ምርት ሂደት ጉልህ ተሳትፎ እንዲያደርግ ማስቻል፣ ይህንንም በተሳትፎአዊ መስኖ ልማትና አስተዳደር አሰራር/PIDM/ መሰረት መፈጸም፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5 የማህበራዊ ዘርፍ ልማት

# ዕቅድ

## 5.1. የሥነ-ሕዝብና የሰው ኃብት ልማት

### 5.1.1. የሥነ-ሕዝብ ልማት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች**

ከኢኮኖሚ ልማት ጋር ያልተመጣጠነ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መኖር፣ የተፈጥሮ ሀብት መመናመንና የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ውስንነት መኖር፣ የምርትና ምርታማነት ማነስና የምግብ ዋስትና በቤተሰብ ደረጃ ያለመረጋገጥ፣ የትምህርት ፍትሀዊነት፣ ጥራትና ተደራሽነት ችግር መኖር፣ የሕብረተሰብ የተዋልዶ ጤና እና አጠቃላይ የጤና ሁኔታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት፣ የሴቶች፣ የአረጋዊያን፣ የአካል ጉዳተኞችንና ልዩ ድጋፍ የሚሹ የማህ/ሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ተሣታፊነትና ተጠቃሚነት ዝቅተኛ መሆን፣ ዋና ዋና የሥነ-ህዝብና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት ዓላማ እንደሚከተለው ተለይቷል**

የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔን ከክልሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ምጣኔና የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ጋር በማጣጣም በሂደት የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል ማድረግ ነው። ለዚህም በሥነ-ህዝብና ልማት ጉዳዮች ዙሪያ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ሊያሳድጉ የሚችሉ የተለያዩ ሥልቶችን በመጠቀም አማካይ ክልላዊ የውልደት ምጣኔና የሞት ምጣኔ እንዲቀንሱ በማድረግ አጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔንና በክልሉ የሚታየውን የሥራ አጥነት ምጣኔን መቀነስ፤ የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን በሚመለከታቸው ሴክተሮች፣ የሐይማኖት ተቋማትና ሲቪክ ማህበራት የልማት ዕቅዶች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግና ተግባራዊነታቸውን መከታተል የቀጣይ አሥር ዓመት የሥነ ሕዝብና ልማት ጉዳዮች ዓላማ ነው።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት ዓላማን ለማሳካት የታቀዱ ዋና ዋና ግቦች**

የሕዝብ ዕድገት ምጣኔን ከክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ ጋር ማጣጣም፣ የቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚዎችን ምጣኔ አሁን ካለበት 45% በ2022 ወደ 80% እንዲሁም አንዲት በመውለድ የዕድሜ ክልል (15-49) ያለች እናት የምትወልዳቸው ልጆች መጠን /TFR/ አሁን ካለበት አማካይ 4.4 ልጆች በ2022 ወደ 3.1 ልጆች በማድረስ አጠቃላይ የክልሉ ህዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ አሁን ካለበት 2.9% ከአሥር ዓመት በኋላ በ2022 ዓ.ም ወደ 2.3% ማድረስ።

በክልሉ ዲሞግራፊያዊ ባህሪያት ዙሪያ ልዩ ልዩ ጥናቶችን በማድረግ ለሥነ-ህዝብ ፖሊሲ ማሻሻያ የሚረዱ ሃሳቦችን ማቅረብና የፖሊሲውን ዓላማና ግቦች ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ ፕሮግራምና ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀትና ተፈፃሚነታቸውን ማረጋገጥ፤ የተፈጥሮ አካባቢን በመጠበቅና በማልማት፣ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፤ የምግብ ዋስትና በቤተሰብ ደረጃ እንዲረጋገጥ በማድረግ አጠቃላይ የሕብረተሰቡ ጤና እንዲሻሻል የግንዛቤ ሥራዎችን በልዩ ትኩረት መስራት፣ በክልሉ ፍትሀዊና ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ እንዲሆንና በተለይ የሴት ልጆች መማር ለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስፋፋት ከፍተኛና የማይተካ ሚና ስላለው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ተሳትፎአቸውን ማሳደግ፣ ሴቶች፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞችንና በአጠቃላይ ልዩ ድጋፍ የሚሹ የማህ/ሰብ ክፍሎች ልዩ ጥበቃ እንዲደረግላቸውና በክልሉ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጉዳዮች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የግንዛቤ ሥራዎችን በተጠናከረ ሁኔታ ለመስራት ታቅዷል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሥነ ሕዝብ ልማት ዓላማና ዋና ዋና ግቦች ለማሳካት የምንከተላቸው ማስፈጸሚያ ስልቶች፤**

የሥነ-ሕዝብና ልማት ችግሮችንና መፍትሔዎችን እንዲሁም የሥነ-ህዝብ ሥራዎች ዓላማን ለሕ/ሰቡ ለማስተዋወቅ፣ ለማስተማር፣ ለማስረፅና ለመቀስቀስ እንዲሁም የአመራር አካላትን የማሳመን /IEC/BCC and Advocacy ሥራዎችን የማከናወን እና የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን በየደረጃው ባሉ ሴክተር መ/ቤቶች ዓመታዊ የሥራ ዕቅዶችና ስትራቴጂክ ዕቅዶች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ፡፡

በት/ቤቶች የሥነ-ህዝብ ክበባትን በማቋቋምና በማጠናከር የሥነ-ህዝብ መልዕክቶችን ለተማሪ ወጣቶችና ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲያደርጉ የመደገፍ እና የሴቶች መማር ለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስፋፋት የማይተካ ሚና ያለው በመሆኑ የሴት ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ እንዲያድግ የግንዛቤና የቅስቀሳ ሥራዎችን መስራት፡፡

የሥነ-ሕዝብ ፕሮግራም ከክልል እስከ ወረዳ እንዲዘጋጅና በየወቅቱ አፈፃፀሙ እንዲገመገም በማገዝ፣ በየደረጃው ለሚገኙ የስነ ህዝብ የስራ ሂደቶች የቴክኒክ፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ አቅም መገንባት፡፡ የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችንና የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚነትን በመጠት መርህ መሰረት ማስፋፋት፡፡ ማሕበረሰቡን በማንቀሳቀስ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን በማፋጠን ለጥቃት፣ ለመገለል፣ ለመድልዎና ለበደል ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ

ክፍሎች የሕግ ጥበቃ እና የማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ማጠናከር ይሆናል።

### 5.1.2. የትምህርትና ሥልጠና ልማት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የትምህርት ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች፤** የትምህርት ልማቱ ሰባት ዋና ዋና የትኩረት መስኮች ያሉት ሲሆን ያልተማከለ የትምህርት ሥርዓት ማጠናከር፣ በመልካም ሥነ- ምግባር የታነፀ ዜጐችን ማፍራት፤ አካታች የሆነ የትምህር ስርአትን በመገንባትና ውስጣዊ ብቃት በማሳደግ ሀገራዊ እሴቶች እና ብዝሃነት ለብሔራዊ አንድነት ማጠናከር፣ የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ለገበያ ተወዳዳሪነት፣ የትምህርት ዘርፉን በዲጂታል ቴክኖሎጂ ማበልጸግ፣ መደበኛ ያልሆነ የወጣቶች እና የጎልማሶች ትምህርት መርሃ-ግብር፤ የትምህርት ሥርዓት፣ አስተዳደርና ተጠያቂነትን ማጠናከር፣ የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ላይ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የትምህርት ልማት ዓላማዎች፤** ጥራት ያለው የግዴታ ትምህርትና ሥልጠና ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ መካከለኛ እንዲሁም ነፃ በሳይንስና ተስማሚ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ትምህርት ለሁለተኛ ደረጃ ማቅረብና በብቁ አመራር የሚመራና ውስጣዊ ብቃቱ የተረጋገጠ ትምህርት ለሁሉም በፍትሀዊነት በማዳረስ የዜጎችን አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እንዲሁም መልካም እሴቶችን በማጐልበት ለሀገራችን ብሎም ለክልላችን ነባራዊ ሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጡ፣ የሀገሪቱን የብልጽግና ጉዞ ማሳካት የሚችሉና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ብቁ ዜጐችን ማፍራት ነው።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የትምህርት ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት ዋና ዋና ግቦች፤**

ያልተማከለ የትምህርት አስተዳደርና የተጠያቂነት ሥርዓትን ማጠናከር፤ አቅምን ያገለበተና ተጠያቂነት የሰፈነበት ያልተማከለ የትምህርት አስተዳደርን ለማጠናከርና በ2022 100% ለማድረስ በየደረጃዉ ያለዉን የትምህርት አመራር ለውጡን መሠረት ያደረገ ግንዛቤ በመፍጠር ጥራትና ተዓማኒነት ያለው የትምህርት መረጃን በመጠቀም የትምህርት ሥርዓቱን ውጤታማነት ማሳደግ፣ የትምህርት አስተዳደር አቅም ግንባታና የተጠያቂነት ሥርዓትን በመዘርጋት ውጤታማነትን ማሳደግ ያስፈልጋል። በሁሉም ወረዳ የተደራጀ የወላጆችንና የማህበረተሰቡን ተሳትፎን ለማስተባበር የተቋቋመ የተማሪ ወላጅ ማህበር እና የብቃት ደረጃውን ያሟሉ የትምህርት አመራሮች ድርሻ 100% ማድረስ፣ ያስፈልጋል።

በመልካም ሥነ ምግባራቸው የተመሰገኑ ተማሪዎችንና መምህራንን ማፍራት፤ ሥርዓተ ትምህርቱን በመከለስ የግብረ-ገብነትና የዜግነት ትምህርት እንዲካተትና እንዲሰጥ በማድረግ ተማሪዎች በግብረ-ገብነትና በዜግነት ትምህርት ታንፀው በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዕድገት ጉልህ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ እንዲችሉ በእውቀት፣ በፈጠራ፣ በትብብርና ተግባቦት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር የታነፁ እንዲሆኑ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ ለማህበረሰቡ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ተማሪዎችና መምህራነ ተሳትፎ 100%፣ የትምህርት ቤቱን ሕገ-ደንብ በሚገባ የሚተገብሩ ትማሪዎችና መምህራንን ቁጥር 100%፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰጡና የሚያስተባብሩ መምህራን ተማሪዎችን 100% ማድረስ፡፡

ሥርዓተ-ትምህርቱን የጥራት ደረጃውን ጠብቆ ማዘጋጀት፣ መተግበርና መገምገም ሥርዓተ ትምህርቱ የሚጠበቅበትን ድርሻ መወጣት እንዲችል ግብረ ገብነትን፣ ሀገር በቀል ዕውቀቶችን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን (ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና ስነ-ጥበብ እና ሂሳብ)፣ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎቶችን እንዲሁም የሙያና የቴክኒክ ትምህርቶችን ማካተት ይጠበቅበታል፡፡ በቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ በሁሉም የትምህርት አይነቶች አካታች ሆነው የተዘጋጁና የተከለሱ የመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍትን 100% ማድረስ፡፡ በቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ- መጻህፍት ጥምርታን እንዲሁም የመምህር- መጻህፍት ጥምርታ 1፡1 ማድረስ፡፡

የመምህራንና የትምህርት አመራሩን አቅርቦት፣ ተነሳሽነት እና ብቃት ማሳደግ፤ የትምህርት አመራርነት ሥራን ሙያዊ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓትን መዘርጋትና መተግበር እንዲሁም ብቃትና የስራ አፈጻጸምን መሠረት በማድረግ የሚሠራ ይሆናል፡፡ ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራን አሁን ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራን በ2014 ከነበረበት 28.3% ወደ 90% ማድረስ፣ የአንደኛ ደረጃ መምህራንን በ2014 ከነበረበት 6% ወደ 75%፣ የመካከለኛ ደረጃ መምህራንን በ2014 ከነበረበት 12.2% ወደ 85%፣ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን በ2014 ከነበረበት 7.4% ወደ 75% ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ ለደረጃዉ የሰለጠነ የተማሪ መምህር ጥምርታን በተመለከተ በአንደኛ ደረጃ በ2014 ከነበረበት 1፡165 በ2022 ወደ 1፡55 በሁለተኛ ደረጃ በ2014 ከነበረበት 1፡318 በ2022 ወደ 1፡50፣ ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ ር/መምህራን ሚሟላትን በተመለከተ የቅድመ አንደኛ በ2014 ከነበረበት 0 በ2022 ወደ 50%፣ የአንደኛ ደረጃ በ2014 ከነበረበት 40% በ2022 ወደ 100%፣ የሁለተኛ

ደረጃ ር/መምህራን በ2014 ከነበረበት 34.2% በ2022 ወደ 100% ለማሳደግ በትኩረት ይሰራል፡፡

ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ በ2014 ከነበረበት 79.4% በ2022 ወደ 100% ሱፐርቫይዘሮች ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች በ2014 ከነበረበት 71.4% በ2022 ወደ 100% ለማደግ ታቅዷል፡፡

የሒሳብ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት ከቅድመ አንደኛ ጀምሮ በልጆች አዕምሮ ላይ እየሰረጸና በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ እየተተገበረ እንዲሄድ፣ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ማድረግ የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጥ ባሻገር አጠቃላይ የትምህርት ዓላማዎችን ለማስፈጸምና በክልል እና በሀገር ደረጃ የታለመውን ራዕይ ለማሳካት ሚናው የጎላ ነው፡፡ ለSTEAM ፕሮግራም የሳይንስ ላብራቶሪ የተሟላላቸው በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማትበ2014 ከነበረበት 10% በ2022 ወደ 50%፣ በሁለተኛ ደረጃ በ2014 ከነበረበት 50% በ2022 ወደ 100% ፣ የልህቀት ማዕከላትበ2014 ዜሮ ከነበረበት በ2022 ወደ 6 ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በተከታታይነት በማሻሻል ለመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹ ማድረግ፣ በሀገራችን በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ተቋማት በአብዛኛው ትምህርት ቤቶች ከሚጠበቀው ደረጃ በታች የሚገኙ ናቸው፡፡ በዚህም የትምህርት ተቋማት ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ተገቢው ግብዓት ሊሟላላቸውና ያላቸውንም የቁሳቁስ፣ የሰውና የፋይናንስ ሀብት በአግባቡ እንዲጠቀሙ ወደ ሚያስችሉ ተቋማት ደረጃ መቀየር ይገባቸዋል፡፡ ስለሆነም ትምህርት ቤቶች ተገቢው ግብዓት እንዲኖራቸው በመሥራት አቅማቸውን በማጎልበት ለመማር ማስተማር ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥሩ በማድረግ የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል ይቻላል፡፡

ደረጃ 3 የደረሱ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ2014 ከነበረበት 0% በ2022 ወደ 70% የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ2014 ከነበረበት 8.2% በ2022 ወደ 70% የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ2014 ከነበረበት 22.49% በ2022 ወደ 80% ለማሳደግ፣ ደረጃ 4 የደረሱ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ2014 ከነበረበት 0% በ2022 ወደ 30%፣ የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ2014 ከነበረበት 0% በ2022 ወደ 30%፣ የሁለተኛ ደረጃ በ2014 ከነበረበት 0% በ2022 ወደ 30% ለማድረስ ታቅዷል፡፡

በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ የትምህርት ተደራሽነትና ውስጣዊ ብቃትን ማሳደግን በተመለከተ ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ቅበላ በ2014 ከነበረበት 46.5% ወደ 100%፣ ንጥር የቅድመ አንደኛ ደረጃ ሽፋን በ2014 ከነበረበት 36.4% ወደ 100%፣ ጥቅል የ1ኛ ክፍል ቅበላ በ2014 ከነበረበት 99.5% ወደ 100%፣ ንጥር የ1ኛ ክፍል ቅበላ በ2014 ከነበረበት 64.6% ወደ 100%፣ ጥቅል ከ1ኛ-6ኛ ክፍል አማራጭን ጨምሮ በ2014 ከነበረበት 78.7% ወደ100%፣ ንጥር ከ1ኛ-6ኛ ክፍል አማራጭን ጨምሮ በ2014 ከነበረበት 69.3% ወደ 100%፣ ጥቅል የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል ቅበላበመቶኛ በ2014 ከነበረበት 68.4% ወደ 100%፣ ንጥር 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ቅበላ በ2014 ከነበረበት 68% ወደ 100% ጥቅል ከ9ኛ-12ኛ ክፍል በ2014 ከነበረበት 45.4% ወደ 76፣ ንጥር ከ9ኛ-12ኛ ክፍል በ2014 ከነበረበት 36.7 ወደ 62 ለማድረስ ይሰራል፡፡ በእቅድ ዘመኑ መነሻ 2014 መጠነ መድገም 1ኛ ክፍል 11.7% የነበረውን ወደ 3%፣ ከ1-6ኛ ክፍል 9.7% የነበረውን ወደ 2% 7-8ኛ ከ9.8% ከነበረበት ወደ 4% ከ9-12 11.7 % ከነበረበት ወደ 5 % ዝቅ ለማድረግ፤ እንዲሁም መጠነ ማቋረጥ 1ኛ ክፍል ከ10.4 ወደ 4፣ ከ1ኛ-6ኛ ከ11.1% ወደ 4%፣ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ከ17.6% ወደ 3%፣ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል21.4% የነበረውን ወደ 5% ዝቅ ለማድረግ፤ የማጠናቀቅ ምጣኔ (6ኛ ክፍል) በ2014 ከነበረበት 66.3% ወደ 82.5%፣ 8ኛ ክፍል 85.1% ከነበረበት ወደ 97%፣ እንዲሁም የ7ኛ ክፍል የመዝለቅ ምጣኔ 40.9% ከነበረበት ወደ 88.9% ለማሳደግ እቅድ ተጥሏል፡፡

የትምህርት ፍትሃዊነትና አካታችነትን ማሻሻልን ለማሳካት የታቀዱ ግቦችን በተመለከተ በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የጾታ ምጥጥንን በ2014 ከነበረበት 0.9 ወደ 1፣ ከ1-6ኛ ክፍል 0.87 ከነበረበት ወደ 1 ከ7-8ኛ ክፍል 0.95 ከነበረበት ወደ 1 ከ9-12 ክፍል 0.99 ወደ 1 ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ የልዩ ፍላጎት ትም/ት ተሳትፎ ለማሻሻል ጥቅል ከ 1ኛ-6ኛ ክፍል በ2014 ከነበረበት 50.5% ወደ 57.5%፣ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል በ2014 ከነበረበት 47.6% ወደ 52.5%፣ ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል በ2014 ከነበረበት 22.5% ወደ 30% እቅድ ተጠሏል፡፡

የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት መርሀ ግብሮችን ከገበያ ፍላጐት ጋር በማስተሳሰር ተደራሽነቱንና ፍትሀዊነቱን ማሳደግ፣ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ያጠናቀቁ ጎልማሶች በ2014 ከነበረበት 56.8% ወደ 100% ድህረ-የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ያጠናቀቁ ጎልማሶች በመቶኛ በ2014 ከነበረበት 79.6 ወደ 100%፣ የሰለጠኑ አመቻቾች ቁጥር 501 ከነበረበት ወደ 1480 ለማሳደግ ታቀዷል፡፡

ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የትምህርት ስርዓቱን ማሻሻል፣ አሁን ባለንበት ዘመን ማንኛውም የትምህርትና ስልጠና፣ የትምህርት አመራርና አስተዳደር እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በመረጃ ላይ የተመሰረተ የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓቶች ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት የዲጂታል ቴክኖሎጂን በማስፋፋት እና በአግባቡ መጠቀም ሲቻል ነው፡፡ ስለዚህ ፈጣን በሆነ የብሮድባንድ ኔትዎርክ መሰረተ ልማት ተሳስረው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶ በ2014 ዓም 29.2% የነበረውን በ2022 100%፣ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደግፈው የተካሄዱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ምዘና ሥርዓቶችና ሀገር አቀፍ ፈተናዎችን፣ ዲጂታላዝድ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት ተጠቃሚ የሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ድርሻ በመቶኛ ከ0% ወደ 100% ለማረስ የስራል፡፡ የኮምፒዩተር ማዕከላት የተደራጀላቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 66.21 ከነበረበት ውድ 100%፣ እንዲሁም የልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም መድረስ የቻሉ በየደረጃው ያሉ ተቋማት 15.4 ከነበረበት ወደ 100% ለመድረስ እቅድ ተጠሏል፡፡

የትምህርት ሥርዓቱ በመልካም ሥነ ምግባር የታነፁና ለሥራ ዝግጁ የሆኑ ተማሪዎችን ማፍራቱን ማረጋገጥ፤ በክልል ደረጃ የትምህርት ተደራሽነትንና ፍትሐዊነትን ከማረጋገጥ አኳያ የተቀናጀና ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ በማካሄድ በተደራሽነትና ፍትሃዊነት ላይ ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የተዘረጉ መርሀ ግብሮች፣ የተቀየሱ ስልቶችና የተከናወኑ ተግባራት ቢኖሩም የተፈለገውን ያህል ርቀት መጓዝ እንዳልተቻለ በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ ግምገማዎችና የምዘና ውጤት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዚሁ መሠረት ይህን ችግር ለመፍታት ትምህርት ቤቶች ያሉበትን የብቃት ደረጃ በኢንስፔክሽን ለማረጋገጥ ተግባሩ የሚከወነዉ በየሶስት ዓመቱ ሆኖ በአራተኛ ዓመት ላይ በሶስቱ ዓመታት ምዘናዉን ወስደዉ ያላለፉት የዳግም ምዘና የሚሠጥ ይሆናል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የትምህርት ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የማስፈጸሚያ ስልቶች፡-**

የግብረ-ገብ እና የዜግነት ትምህርትን በሚፈለገዉ ደረጃ እንዲተገበር ማድረግ፣ ተማሪዎችና መምህራን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲሰጡ ተገቢውን አደረጃጀት በመፍጠር የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ማጠናከር በስፋት የሚከናወን ይሆናል፡፡ የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ የትምህርት ዓይነቱ የይዘት ፍሰት፣ አጥጋቢ የመማር ብቃትና መርሀ ትምህርትን

ለመጽሐፍት ዝግጅት ስራ በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ፣ የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች ምልመላ፣ አሰለጣጠንና ስምሪት በተመለከተ የፖሊሲ፣ የትምህርት ህግ ማዕቀፍና ሌሎች ማዕቀፎች፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮፋይል፣ የምልመላ፣ የስራ ላይ ስልጠና፣ የማትጊያ ሥርዓትና መመሪያዎችን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ።

STEAM መምህራንን የፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ የትምህርት ህግ ማዕቀፍ፣ መመሪያዎችን ክልላዊ በማድረግ መተግበር፣ በየደረጃው ላሉ የትምህርት ተቋማት ሊተገበሩ የሚችሉ እና አግባብነት ያላቸው የትምህርት ቴክኖሎጂ መረጣ የሚካሄድበት ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር።

ትምህርትን ተደራሽ ማድረግና ውስጣዊ ብቃትን ለማሻሻል የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ለማሳደግ የተለያዩ ስልቶችና ስርዓቶችን መንደፍ፣ የትምህርት ቤቶችን ስርጭት (School Mapping) መሠረት በማድረግ ፍትሃዊና ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ለሁሉም ዜጎች ትምህርትን በፍትሀዊነት ለማዳረስ የሚያስችሉ ስልቶችን ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ፣ የሴቶች፣ ልዩ ድጋፍ የሚሹና፣ የአርብቶ አደርና ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የአዎንታዊ ድጋፍ ስርዓት መዘርጋትና በግብዓትና በሰው ኃይል የማደራጀት ስልቶችን ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ።

በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰጡ ትምህርቶች ከአካባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞና ተለማጭ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ፤ መደበኛ ባልሆነው የትምህርት ፕሮግራም ወጣቶችን እና ጎልማሶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፖሊሲና ስትራቴጂ መዘርጋት፣ የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ፕሮግራሞችን ተደራሽ ለማድረግ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላትን ማስፋፋት፣የትምህርት ዘርፉን ያልተማከለ ሥርዓት ለማዘመን የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራተጂዎች እና የአሠራርና የአደረጃጀት ሰነዶችን ክልላዊ በማድረግ በየጊዜው እየፈተሹ ተግባራዊ የማድረግ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

### 5.1.3. ክህሎትና ቴክኖሎጅ ልማት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት ክህሎትና ቴክኖሎጅ የትኩረት አቅጣጫዎች**

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አግባብነት፣ ጥራት፣ ተደራሽነትና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ፣ ተቋማዊ አቅምና ብቃት ማጎልበት፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና የሳይንስ ባህል ግንባታ ማጠናከር፣ ኢኖቬሽን፣ ጥናትና ምርምር እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ፣ መሰረተ ልማትና ፋሲሊቲ ማሳደግ ናቸው።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት ክህሎትና ቴክኖሎጅ ዓላማዎች**

ገበያው የሚፈልገውን ብቃት ያለው፣ ተነሳሽነትን የተላበሰና ከሥራ ፍላጎት ጋር ራሱን የሚያስማማ፣ ስራ ፈጣሪ በመሆን የኢኮኖሚውን ዕድገትና ልማት የሚያራምድ የሰው ኃይል መፍጠርና አዋጭ ቴክኖሎጂ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማሸጋገር የክልላችንና የሀገራችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና አስተዋጽኦ ማድረግ፣

**የቀጣይ አሥር ዓመታት ክህሎትና ቴክኖሎጅ ግቦች**

**የሰው ኃይል ልማት፡-**

የገበያ ፍላጎት መሰረት ያደረገ ዓመታዊ የመደበኛ ሰልጣኝ ቅበላ አሁን/2012 ዓ.ም ካለው 268 በ2022 ወደ 66,586 ለማሳደግ፣ የገበያ ተኮር አጫጭር ስልጠና ዓመታዊ ስልጠና ከ818 ወደ 93,181 ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ በትብብር ስልጠና የሚሳተፉ ኢንዱስትሪዎች፣ የልማት ድርጅቶችና ጥ/አ/ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ከ8 ወደ 36 በማሳደግ ጥራቱ የተጠበቀ የትብብር ሥልጠና ሽፋንን አሁን ካለበት ከ24 በመቶ ወደ 87 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በትኩረት ዘርፎች የበቃ የኢንዱስትሪና የተቋማት አሰልጣኞችን አሁን ከሚታየው እጥረት በበቂ ደረጃ ለመቅረፍ በA ደረጃ ከ10 ወደ 179፣ በB ደረጃ ከ195 ወደ 821 ለማድረስ ይሰራል፡፡ ቴክኖሎጂን የመቅዳትና የማሻሻል አቅም የተረጋገጠላቸው 147 የተቋም ውስጥ አሰልጣኞች ወደ 591 ለማድረስ ይሰራል፡፡

**ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተደራሽ ማድረግ፡-**

በወረዳዎች ተደራሽነቱ የተረጋገጠ የመንግሥት ቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት ከ39 ወረዳዎች ወደ በሁሉም ወረዳዎች መቶ በመቶ ለማዳረስ ይሠራል፣ እንዲሁም ዕውቅና አግኝተው ወደ ፖሊ-ቴክኒክ ያደጉ የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከ3 ፖሊ ተቋማት በስታንዳርዱ መሰረት ወደ 7 ፖሊ ተቋማት እንዲደርሱ ይደረጋል፡፡ የቴ/ሙ/ት/ስልጠና ዞኒንግ ስልጠና መነሻ በማድረግ በቴክኒካል ዩኒቨርስቲ ደረጃ ስልጠና የሚሰጡትን መለየት በቁጥር 0 ከነበረበት በ2022 ወደ 4 ማድረስ፣

ለመንግስት የቴ/ሙ/ት/ስ/ ተቋማት የተለያዩ የስልጠና ፕሮግራሞች ከአካባቢ የልማት ኮሪደር እና ወቅቱ ከሚፈልገው የገበያ ፍላጎት አንጻር በመቃኘት አሁን ካለበት 47 በ2022 ዓ.ም ለ79 የስልጠና ፕሮግራሞች በተጨማሪም የፕሮግራም ምዝገባ፣ እውቅናና የእውቅና እድሳት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዷል፤ እንዲሁም ለግልና እና ለመያድ የቴ/ሙ/ት/ስ/ ተቋማት አሁን ካለበት

25 በ2022 ዓ.ም ለ49 የስልጠና ፕሮግራሞች በተጨማሪም የፕሮግራም ምዝገባ፣ እውቅና የእውቅና እድሳት ፈቃድ ይሰጣል፡፡

**የቴክኖሎጂ ሽግግርና ኢንደስትሪ ኤክስቴንሽን በተመለከተ፡-**

ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከምርምር ተቋማትና ከኢንዱስትሪዎች ጋር በመተባበር አዲስ ተፈላጊ ቴክኖሎጂዎችን መለየትና መቅዳት አሁን ካለበት 32 ወደ 197 ለማሳደግ እና የተለዩና የተቀዱ ቴክኖሎጂዎች ላይ አብዝር ኢንተርፕራይዞችን ማብቃት አሁን ካለበት ከ115 ወደ 394 ለማድረስ ይሰራል፡፡

ለነባርና በአዲስ ተደራጅቶ ወደ ሥራ ለሚገቡ የጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾች የሚሠጥ የኢንዳስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ የሚደረግላቸው ነባር የኢንተርፕራይዞች አንቀሳቃሾች ከ1,370 ወደ 45,854 ለማድረስ ይሰራል፡፡ በተሰጠ ኢንደስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍና በተሸጋገረ ቴክኖሎጂ የተፈጠረ ሀብት ከ.99 ሚሊዮን ብር ወደ 19.67 ሚሊዮን ብር እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

**የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጥ፡-**

የምዘና መሳሪያ አዘጋጅ ባለሙያዎችን ከ2 ወደ 4 ለማድረስ፣ የምዘና መሳሪያ (ተጨማር አዳዲስ ቨርሽን) ዝግጅት ከ50% ወደ 100% ለማሳደግ፣ የድህረ ምዘና ጥናትን ምርምር ሰነድ ከ0 ወደ 1 ለማሳደግ እና በአዲስ ዕውቅና ያገኙ የኢንዱስትሪ ምዘና ማዕከላት ከ 7 ወደ 12 ለማድረስ ይሰራል፡፡

**የአይ.ሲ.ቲ መሰረተ ልማት ዝርጋታና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሻሻል፤**

ለሁሉም ስልጠና ተቋማት የኔትዎርክና ብሮድ ባንድ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማድረግ በመቶኛ፣ ከ18.4% በ2022 ወደ 90 ማድረስ፣ ዲጂታል ስቱዲዮ ያደራጁ ተቋማት/Digital Studio በቁጥር፣ ከ 0 በ2022 ወደ 14 ማድረስ፣ ዲጂታል ስቱዲዮ በማቋቋም ብለንድድ ለርኒንግ የተገበሩ ተቋማት/Blended Learning በመቶኛ፣ ከ 0 በ2022 ወደ 72 ማድረስ፣ ዲጅታል ቤተ መጻህፍት የተሟላላቸው ተቋማት/Digital Library በመቶኛ፣ ከ 1 በ2022 ወደ 75 ማድረስ፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም የገቢ አቅማቸውንና አጠቃቀማቸውን ማጎልበት ከ 5% በ2022 ወደ 68% ለማድረስ ታቅዷል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት ክህሎትና ቴክኖሎጅ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል**

የውጤት ተኮር ስርዓቱን ዘላቂነት ማረጋገጥ፣ የአመራርና አሰልጣኝ ልማት፤ የተቋማት አቅም ግንባታ ስልጠና ኮሌጆችን በሁሉም ወረዳዎች በማዳረስ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ፣ የትምህርት መሳሪያዎች አቅርቦት ከመንግስት ግምጃ ቤት ከሚመደበው በተጨማሪ በተለያዩ ተቋማት/መ/ቤቶች፣ የህብረተሰብ ንቅናቄ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ማስተባበር፣

የሰልጣኝ ልማት (መደበኛ እና ገበያ-ተኮር አጫጭር ስልጠና) ከኢንዱስትሪው ፍላጎት በመነሳት ብቃት ያለው ሙያተኛ ማፍራት፤ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት ከ4ቱ የድጋፍ ማዕቀፎች (በቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት፣ ኢኮኖሚ መሰረተ ልማት፣ ፋይናንስ መሰረተ ልማትና ገበያ ትስስር) አንጻር ያሉባቸውን ክፍተቶች በማሟላት በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፣ የህብረተሰብ እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ማሳደግ፤

ምርጥ ተሞክሮዎችን ማስፋፋት /Scaling up/ ከክልሎችና ከተቋማት የተገኘውን ምርጥ ተሞክሮዎችን በማስፋት ሂደት በየደረጃው በዘርፉ ግቦች አፈፃጸም ላይ የተመዘገቡ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለሌሎች በማስተላለፍ በስፋት እንዲተገበር ይደረጋል።

የትምህርትና ሥልጠና ጥራትን ለማስጠበቅና ለማጠናከር የንድፈ ሀሳብና የተግባር ሥልጠናን በጠበቀ መልኩ Curriculum እና TTLM ይሰራል። የአካባቢ ጥበቃ (Green TVET) ተቋማቱ የተፈጥሮ አካባቢ ብክለትን ለማስወገድ ካይዘንን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ። እንዲሁም በትምህርትና ሥልጠና ዘርፉ የዲጅታል ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ሥራ ይሰራል።

### 5.1.4. የጤና ልማት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የጤና ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች**

ውጤታማ፣ ጥራት ያለውና ፍትሐዊ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት አቅርቦትና ሽፋንን ለማረጋገጥ የሚሰራ ሲሆን የጤና አገልግሎት ወጪም የፋይናንስ ስጋትን ለመቅረፍ የሚደረገውን ትግበራ ማፋጠን ላይ እንዲያተኩር ይደረጋል፤ እንዲሁም የጤናውን ሥርዓት በየግዜው ለሚቀያየረው የህብረተሰቡ ጤና ፍላጎት ምላሽ ሰጪ የማድረግ ሥራዎች ይሰራሉ። በተጨማሪም በሽታ መከላከል፣ የፈውስ ህክምና፣ የተሃድሶና የህመም ማስታገስ የጤና አገልግሎቶች ዜጎችን ለፋይናንስ ችግር ሳያጋልጡ ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ሽፋንን ማሻሻል ትኩረት ይሰጠዋል።

በተመሳሳይ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች፣ በማህበረሰብ ግጭቶች፣ ባልተጠበቁ የበሽታ ወረርሽኞች እና በአዳዲስ የጤና ስጋቶች ምክንያት የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን በፍጥነት በመለየት፣ ዝግጁነትና ምላሽ ሰጭነትን በማጠናከር የዜጎችን የጤና ደህንነት መጠበቅ አዕኖት

ይሰጣቸዋል። የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ አካታችነት እና ባለቤትነትን በማጠናከርና በማሻሻል በጋራ ጤና ነክ ችግሮችን እየለዩ መፍትሄ በመስጠት የተሻለ የጤና ስኬት እና ፋይዳ የማምጣት ሥራዎች ይሰራሉ። ቤተሰቦች በጤና ፕሮግራሞች ዙሪያ በተለይም በሃይጅንና አካባቢ ጤና ሥራዎች፣ የእናቶች እና ህጻናት ጤና አገልግሎቶች የአጠቃቀም ሽፋን እና የጤና መድን ሽፋን ላይ የሚያደርጉትን ተሳትፎ ለማሳደግ ትኩረት ይደረጋል። የመድሀኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች አቅርቦት በማሻሻል የህክምና ተቋማት የሚፈልጉትን ጥራት ያላቸውን መድሃኒቶችን፣ የላቦራቶሪና የምርመራ መሳሪያዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ማቅረብ ትኩረት ይሰጠዋል። የጤናው ዘርፍ የቁጥጥር ሥርዓትን በማሻሻል ለህብረተሰቡ የሚቀርበውን ጤና ነክ ምርት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲሻሻል የማድረግ ሥራዎች ይሰራሉ።

የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን ማሻሻል ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን ይህም የግሉ ዘርፍ በጤናው ላይ ያለውን ተሳተፎ በተለይም ደግሞ ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት በመስጠት እና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ከሚደረገው ጥረት አኳያ ድርሻቸውን እንዲወጡ የሚደረግ ይሆናል።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የጤና ልማት ዓላማዎች**

ጤና ማበልጸግና በሽታ መከላከል ላይ ያተኮረ የማይበገር የጤና ሥርዓት በመገንባት የህብረተሰቡን ጤና ማሻሻል እና ለኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጸኦ ማበርከት፣ ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋንን ማረጋገጥ፤ ዜጎች በጤና ችግር ምክንያት ለኢኮኖሚ ቀውስ ሳይዳረጉ የጤና አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤ መከላከል በሚቻሉ ምክንያቶች የሚደርሱ የእናቶችና ህጻናት ሞትን መግታት፤ ተላላፊ እና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ሳቢያ የሚደርሱ ህመምና ሞትን መከላከልና መቀነስ፣ ዜጎችን ከድንገተኛ የጤና አደጋዎች መጠበቅ፣ የወረዳ ትራንስፎርሜሽንን ማምጣት እና ተገልጋይ ተኮር እና ተዓማኒነት ያለው የጤና ሥርዓትን መፍጠር የዘርፉ የልማት ዕቅድ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የጤና ልማት ዓላማዎችን ለማሳካት የታቀዱ ዋና ዋና ግቦች**

ከወሊድ በኋላ በህይወት የመኖር የእድሜ ጣሪያን አሁን ከደረሰበት 65 ወደ 70 እድሜ ለማድረስ፣ ሁሉ አቀፍ የጤና ሽፋን ጠቋሚን (UHC Index) ከ0.43 ወደ 0.7 ማሳደግ፣ በመጨረሻው የጤና አገልግሎት ጉብኝታቸው (የደንበኛ እርካታ መጠን) በአገልግሎቱ መርካታቸውን የገለጹ ደንበኞች ምጣኔን ከ46% ወደ 80% ለማሳደግ ታቅዷል።

**የእናቶች ጤና አገልግሎት /MCH-MNH በተመለከተ**

የእናቶች ሞት ምጣኔ ከ401/100,000 ወደ 140/100,000 ዝቅ እንዲል፣ የቅድመ ወሊድ ክትትል ቢያንስ አራት ጊዜ ያገኙ ነፍሰ ጡር እናቶች ሽፋን ከነበረበት ከ62% በ2022 ወደ 95% ማሳደግ፣ በሰለጠነ ባለሙያ የሚሰጥ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን ከ52% ወደ 95%፣ የድህረ ወሊድ እንክብካቤ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን ከ80% ወደ 98%፣ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ምጣኔን (CPR) ከ44.6% ወደ 60% የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡

**የጨቅላ ህጻናትና ህጻናት ጤና አጠቃላይ /MCH Overall፡-**

እድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት ሞት ምጣኔ ከ55/1000 ወደ 35/1000፣ እድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሞት ምጣኔ ከ43/1000 ወደ 20/1000፣ የጨቅላ ህጻናት ሞት ምጣኔ ከ30/1000 ወደ 15/1000 ዝቅ እንዲል ይሰራል፡፡ እንዲሁም ከ5 ዓመት እድሜ በታች ያሉ ህፃናትን የመቀጨጭ ምጣኔ ከ6.30% ወደ 3% እና ከ5 ዓመት እድሜ በታች ያሉ ህፃናትን የመቀንጨር ምጣኔ ከ36% ወደ 18% ዝቅ እንዲል ይሰራል፡፡ በተጨማሪም ሁሉንም ክትባቶች ጨርሰው የወሰዱ ህጻናት ሽፋንን ከ88% ወደ 95% ማሳደግና ኤች.አይ.ቪን ከእናት ወደ ጽንስ/ልጅ የመተላለፍ መጠንን ከ13.4% ወደ 5% የመቀነስ ስራ ይሰራል፡፡

**ዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች፡-**

የቲቢ ልየታ መጠንን ከ78% ወደ 90% ማሳደግ፣ አዲስ በተለዩ የስጋ ደዌ ህሙማን ላይ የደረጃ 2 የጉዳት መጠንን ከ12% ወደ 4% መቀነስ፣ አዲስ በኤች.አይ.ቪ የመያዝ መጠንን ከ0.03 ወደ 0.01% መቀነስ እና የወባ በሽታ ክስተት መጠንን ከ41/1000 ወደ 0 መቀነስ፡፡ እንዲሁም በወባ ምክንያት የሚከሰተውን የሞት መጠን ከ 3.6/100,000 ወደ 0 የማውረድ ስራ ይሰራል፡፡

**የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም / Health extension program /HEP**

የሞዴል አባ/እማወራዎች ሽፋንን ከ31% በ2017 ወደ 60% እና በ2022 ወደ 90% ማሳደግ፣ የድንገተኛ ቀዶ ህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ጣቢያዎች እና የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ሽፋንን ከ5% በ2017 ወደ 17% እና በ2022 ወደ 25% ማሳደግ፣ ከፍተኛ አፈጻጸም ያላቸዉ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሀድ ሽፋንን አሁን ካለበት 18% በ2017 ወደ 45% እና በ2022 ወደ 70% ማሳደግ፣ አጠቃላይ/የተሟላ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ኬላዎች መጠን ካለበት 0% በ2017 ወደ 15% እና በ2022 ወደ 50% ማሳደግ፣

**ሃይጅን እና የአካባቢ ጤና** መሰረታዊ የሳኒቴሽን ፋሲሊቲዎች ያሏቸዉ አባ/እማወራዎች ሽፋንን በ2014 ካለበት 40.7% በ2017 ወደ 70% እና በ2022 ወደ 100% ማሳደግ፣ ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነጻ የወጡ ቀበሌዎችን ሽፋን ከ49.4% በ2017 ወደ 80% እና በ2022 ወደ 100% ማሳደግ፣ በግቢያቸው/በቤታቸው ውስጥ የእጅ መታጠቢያ ውሃ እና ሳሙና ያላቸው አባ/እማወራዎች ሽፋንን ከ8% በ2017 ወደ 60% እና በ2022 ወደ 94% ማሳደግ

**ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን /DPC-NCD በተመለከተ፡-**

በዋና ዋና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች አማካኝነት የሚከሰት ያለዕድሜ ሞት መጠንን ከ18% ወደ 10% ለመቀነስ፣ የማህጸን ጫፍ ካንሰር ልየታ የተደረገላቸው እድሜያቸው ከ30-49 ከሆኑ ሴቶች ሽፋንን ከ8.8% ወደ 65% ለማሳደግ፣ የደም ግፊት ከፍ ካለባቸው እድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎች መካከል የደም ግፊት ልኬታቸውን መቆጣጠር የተቻለ ታካሚዎች መጠን ከ95% ወደ 100% ለማሳደግ እና በደማቸው የስኳር መጠን ካለባቸው ሰዎች መካከል በደማቸው የስኳር መጠንን መቆጣጠር የተቻለ ታካሚዎች መጠን ከ91% ወደ 100% ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

**የህክምና አገልግሎቶች አንጻር፡-** ዓመታዊ አማካይ የተመላላሽ ህክምና ጉብኝት/የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት መጠንን ከ0.9 ወደ 3 ለማሳደግ፣ በጤና ተቋማት የመሞት ምጣኔን (ከጠቅላላ ሞት) ከ1.4% ወደ 0.8% ለመቀነስ፣ ከጠቅላላ ከተሰበሰበ የደም መጠን የደም ተዋጽኦ የተሰራላቸው መጠን ከ65% ወደ 100% ለማሳደግ እና የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን የአባ/እማወራ የአባላት ምጣኔን 39% ወደ 100% ለማሳደግ ይሰራል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የጤና ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የተመረጡ የማስፈጸሚያ ሥልቶች፣**

በጤና ማጎልበት፣ በሽታ መከላከል እና ተገቢ የፈውስ ህክምና አገልግሎት ላይ ያተኮረ ፍትሃዊና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፣ የስነ-ተዋልዶ፣ የእናቶች፣ የጨቅላ ህፃናት፣ የልጆች፣ የወጣቶች እና የአፍላ ወጣቶች ጤና፣ ኤች አይ ቪ፣ ወባ፣ ቲቢ፣ ስጋ ደዌ እና ሄፓታይተስ ያሉ ተላላፊ በሽታዎች የመከላከል ስራ የጤና ሴክተር በቂ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን እንዲሁም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን (NCDs) ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣ የጤና ኤክስቴንሽን እና የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

የጤና ድንገተኛ እና የአደጋ ስጋት አስተዳደርን ማሻሻል፣ የማህበረሰቡን የጤና ባለቤትናትንና ተሳትፎን ማሳደግ፣ የፋርማስትካል እና የህክምና ቁሳቁሶች አስተዳደር ማጠናከር፣ የቁጥጥር

ስርዓቶችን ማሻሻል፣ የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደርን ማሻሻል፣ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ አሰጣጥን ማሻሻል (መረጃ፣ ምርምር እና የእውቀት አስተዳደር)፣ የጤና ፋይናንስ ማሻሻል፣ የጤና አመራር እና መልካም አስተዳደርን ማጠናከር፣ የጤና መሠረተ-ልማት ማሻሻል፣ ዲጂታል ጤናን እና ፈጠራዎችን ማሻሻል፤ የባህል ህክምናን ማሻሻል ተጠናክሮ ይሰራል።

ጤናን በሁሉም ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ውስጥ ማካተት፣ የጤና እና ከጤና ጋር የተዛመዱ እይታዎችን በሁሉም የሚመለከታቸው የዘርፍ ፖሊሲዎች እና ህገ ደንብ ውስጥ እንዲካተት ማድረግ፣ ለጤና መጠበቅ እና በማህበራዊ የጤና ጠንቅ በሆኑ ጉዳዮች የህዝብ ንቅናቄ ማድረግ፣ የግሉን ዘርፍ የጤና ተሳትፎን ማሻሻል፣ በጤናው ዘርፍ የግሉን ሴክተር ተሳትፎ ለማጠናከር ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጂዎችን እንደገና ማሻሻል፣ የመንግሥት-የግል ሽርክና/አጋርነት ማጠናከር፣ የህክምና ምርቶችን እና አቅርቦቶችን ማምረት እና ስርጭት ውስጥ የግሉ ሴክተር ተሳትፎ ማጎልበት፣ በጤና እና ከጤና ጋር በተዛመዱ አገልግሎቶች እና ምርቶች የቁጥጥር ሥርዓት ውስጥ የግሉ ሴክተር ተሳትፎ በማድረግ የሚሰራ ይሆናል።

### 5.2. የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ልማት

#### የቀጣይ አሥር ዓመታት የሴቶች፣ የሕጻናትና ወጣቶች ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች

ሴቶች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፍ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት እንዲያድግ ማድረግ፤ የሴቶችና የህፃናት ጉዳይ ተቋማዊነት እንዲጎለብት ማድረግ፤ የሴቶችና የህፃናት ጉዳይ የተመለከቱ አሉታዊ የስርዓተ-ጾታ ወግ/አመለካከቶችና ተግባራት በመቀየር የአመለካከት ለውጥ ማምጣት፤ የሕጻናት ስብዕና ልማት ማጎልበት፤ የህጻናትን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ የመፈጸምና የማስፈፀም አቅምን መገንባት።

ሁሉንም ሴክተር መ/ቤቶች በማስተባበር፣ እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ንቅናቄ በመፍጠር፣ የአመለካከት ለውጥ በማምጣት፣ የአስፈጻሚ አካላትን አቅም በመገንባት፣ ተግባርና ሃላፊነትን መሰረት ያደረገ ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ፣ ሊያሰሩ የሚችሉ ደንቦች፤ መመሪያዎችንና የአሰራር ማኑዋሎችን በማዘጋጀትና አፈጻጸማቸውን ማጎልበት፣ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በአግባቡ የልየታ ሥራ በመስራት ከአጠቃላይ ተጠቃሚዎች ውስጥ 50 በመቶ ተጠቃሚዎች ሴቶች እንዲሆኑ ይሰራል።

ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትን ህይወት ለመታደግ አማራጭ የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ማጠናከር፣ በተለይም ለአካል ጉዳተኛ፣ ለስደተኛና ተፈናቃይ ህፃናት ልዩ ትኩረት በመስጠት መብቶቻቸውን ማስጠበቅ፣ የተሀድሶ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ማቋቋም፣ የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት (One Stop Center)፣ የአደጋ ጊዜ የስልክ ጥሪ አገልግሎት (Hot line)፣ ቤተሰብን ለማጠናከር የሚያስችሉ የኢኮኖሚ፣ የስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎቶች የማስፋፋት ሥራዎች ይሰራሉ፡፡

የአስፈፃሚ አካላት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞችን አንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጥ በመከታተል የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት ማሻሻያ እንዲደረግባቸው በማድረግ፣ በባለድርሻ አካላት መካከል ጠንካራ የቅንጅታዊ አሰራር እንዲጎለብት ማድረግ፣ ለሁሉም ህፃናት የቀዳማይ ልጅነት ዘመን አገልግሎቶች ማነቃቂያ፣ የመማርና የመጫወት ዕድልን በማስፋፋት፣ የትምህርት ቤቶች ምቹነትና ተስማሚነት ማረጋገጥ፣ ህፃናት በእውቀት እንዲጎለብቱና በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ይሰራል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሴቶች፣ የሕጻናትና የወጣቶች ልማት ዓላማዎች**

በክልላችን ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና በባህል መስኮች እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት የተረጋገጠባት፣የህፃናት መብትና ደህንነት የተከበረባት፤ የህፃናትና መልካም ስብዕና የጎለበተባት እና የስርአተ-ጾታ እኩልነት የሚሰፍንበት ይሆናል ::

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሴቶች፣ የሕጻናትና ወጣቶች ልማት ዋና ዋና ግቦች፡-**

**የሴቶችና ህፃናት ተጠቃሚነት ማሳደግ፡-**

የሚመለከታቸውን ሴክተር መ/ቤቶችን በማስተባበር እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ንቅናቄ በመፍጠር ከአጠቃላይ ተጠቃሚዎች ውስጥ 50 በመቶ ሴቶች እንዲሆኑ ለማድረግ ይሰራል፡፡ በተመሳሳይ በከተማ የስራ እድል እንዲፈጠር በንግድና በአገልግሎት ዘርፍ የሴቶች ተጠቃሚነት 35% ወደ 50% ለማድረስ እና የሴቶች የስራ ክፍያ ልዩነት ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር በፋብሪካ፤ በግንባታና በኮንስትራክሽን ዘርፍ በአማካይ 60% ከነበረበት ልዩነቱን ለመቀነስ ታቅዷል፡፡ እንዲሁም ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በመስራት ሴቶችን ለአመራር ብቁ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

በገጠር የሴቶች የመሬት ባለቤትነት ተጠቃሚነት ሰርተፊኬት ያገኙ ሴቶች ከ130,281 ወደ 255,350 ለማድረስ እንዲሁም ባልና ሚስት በጥምር ከ451,340 ወደ 844,000 ሴቶች በማድረስ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

ሴቶች በግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እንዲቻል እማወራ ሴት አርሶ አደሮች 100% በግብርና ፓኬጅ (በእርሻና እንስሳት ልማት) ተጠቃሚ እንዲሆኑና ባለትዳር ሴቶች 50 በመቶ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

ሴቶች ለብቻቸው በህብረት ስራ ማህበር ተደራጅተው ተጠቀሚ ለማድረግ 480 ከነበረበት በሁሉም ከተማና ገጠር ቀበሌዎች በማደራጀት ወደ 859 ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በዚህም የገንዘብ ቁጠባና ብድር የሕብረት ሥራ ማህበራት የሴቶች ተጠቃሚነትና ተሳታፊነትን በማሳደግ አሁን ከነበረበት የአባላት ቁጥር ከ17,153 ወደ 33,620 አባላት ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም በአካባቢ ጥበቃ የሴቶችን ተሳትፎ አሁን ከነበረበት 335,384 ወደ 657,352 ለማድረስ ታቅዷል፡

የሴቶችን የገበያ ትስስር ተጠቃሚነት 35,906 ከነበረበት ወደ 70,375 በማሳደግ ብሎም 30,356 ሴቶች በአነስተኛ ግብርና ምርቶች ማቀነባባር (agro processing) ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል፡፡ የተለያዩ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ 88,528 ከነበረበት ወደ 173,541 የሆኑ ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሰራል፡፡

የሴቶችን የገበያ ትስስር ተጠቃሚነት ከ137,640 ወደ 195,448 በማሳደግ በአነስተኛ ግብርና ምርቶች ማቀነባበር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሰራል፡፡ እንዲሁም 1 የሴቶች የገበያ ማዕከል በመገንባት የሴቶችን የግብይት ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

የሴቶች የማምረቻና ኢንቨስትመንት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር የትብብርና የቅንጅት ስራዎችን በማጠናከር፣ በማንፋክቸሪንግ ዘርፍ የሴቶችን ባለቤትነት ከ6 በመቶ ወደ 30 በመቶ እና በኢንቨስትመንት ዘርፍ ደግሞ ከ9.4 በመቶ ወደ 40 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡

ለ391,304 ያህል የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤና ንቅናቄ ስራዎችን በመስራት እንዲሁም ከፋይናንስ ተቋማት ጋር አጋርነት በመፍጠር የሴቶች በተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ቁጠባን አሁን ካለበት 1,011,758 ወደ 1,821,164 ብር በማስቆጠብ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችን አሁን ከነበረበት ከ403,557 ወደ 726,403 ከፍ በማድረግ፣ የሴቶች የብድር አገልግሎት ምጣኔ ከብር 363,201,500 ወደ 653,762,700 ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ ተካቶ እንዲሰጥ የሚያስችል ስርዓት እንዲዘረጋጅ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ለመስራት ታቅዷል፡፡

የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግና ከማነኛውም ጥቃት ለመከላከል በተቋቋሙ አዳሪ ትምህርት ቤቶች/ሆስቴሎች/ ለሚማሩ ሴት ተማሪዎች ድጋፍ ለማድረግ እና በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የሴቶችን ተጠቃሚነት አሁን ካለበት 520,893 ወደ 1,173,913 ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

እንዲሁም ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ማገገሚያ ማዕከላትን በማቋቋምና በቁሳቁሶች በማሟላት የተሀድሶ አገልግሎት ሴቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ለማስቻል እስካሁን ምንም የተሠራ ባይሆንም በቀጣይ ስምንት አመታት 8 በማቋቋም የታቀደ ሲሆን በእነዚህም ተቋማት 1565 ሴቶች ማዕከላት አገልግሎት አንዲያገኙ ለማድረግ፣ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ችግር ለደረሰባቸው 2609 ሴቶች ምላሽ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል።

በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የሀይል ጥቃቶች እንዲሁም ህገወጥ ዝውውር እንዲወገዱ እንዲቀንሱ በሴቶች እና በአጠቃላይ 1,043,478 ህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የማያቋርጥና ተከታታይነት ያለው የአመለካከት ለውጥ የሚያመጡ ስራዎችን በማከናወን።

36,867 የሴቶችና ህፃናት ህግ ድጋፍና ምክር አገልግሎት፤ 23,347 የተለያዩ ማህበራዊና አስተዳደራዊ በደሎችና ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶችና ህፃናት የስነ-ልቦና ምክር አገልግሎት፤ 6,317 የተለያዩ ጥቃት ስለደረሰባቸውና ድጋፍ ስለሚሹ የሴቶችና ህፃናት በማሳደጊያ ተቋም ፕሮጀክቶች እና ግለሰቦች ባደረሱት በደል በፍርድ ቤት ጉዳዮቻቸውን የመከታተል፤ 4,145 ድጋፍ ተደርጎላቸው የፍርድ ቤት ውሳኔ ላገኙ ሴቶችና ህፃናት እንደፍርድ እንዲፈፀምላቸው የአፈፃፀም ክስ ማዘጋጀትና ውጤቱንም መከታተል፤ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶችና ህፃናት የነጻ ጥብቅ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚደረግ ይሆናል ።

የህፃናት ልደት ምዝገባን አሁን ካለበት 12 በመቶ ወደ 75 በመቶ ማሳደግ፣ በተስማሚ ችሎቶች ተጠቃሚ የሚሆኑ ህፃናት 100% ማድረስ፣ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ከ51 በመቶ ወደ 5% በመቶ እንዲቀንስ ማድረግ፣ የህፃናት ከጥቃትና ህገ-ወጥ ዝውውር ከነበረበት ወደ 10 በመቶ መቀነስ፤ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ዜሮ ማድረስ እንዲሁም 2,608 ህፃናት በህግ አባትነትን የማወቅ መብታቸው እንዲረጋገጥላቸው ማድረግ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው። በህፃናት ፓርላማ በንቃት የሚሳተፉ ህፃናት 100 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፣ የሴቶች ልማት ቡድን አደረጃጀት ከማጠናከርና ከመደገፍ አንጻር አሁን ካለበት 15,610 የሴቶች ልማት ቡደን አደረጃጀትን በቀጣይ ስምንት ዓመታት ወደ 28,098 የሴቶች ልማት ቡድን በማደራጀት የክልሉ በገጠርና በከተማ ያሉ ሴቶችን በማህበራዊ፣ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታቅዷል።ለሴት

የልማት ቡድኖች የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት 13,045 የልማት ቡድኖች ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ለማድረግ እቅድ ተይዟል፡፡

**የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ከማሳደግ አንፃር**

በተለያዩ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች የሴቶችን አቅም በመገንባት በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች፣ አስፈጻሚ እና ህግ ተርጓሚ አካላት 50 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በምርጫ ዙሪያ በመራጭነት ሁሉም ሴቶች እንዲሳተፉ፣ በአስመራጭነት 50 በመቶ እንዲሁም በተመራጭነት ወይም በእጩነት 50 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም የሴቶችን የቤት ውስጥ የውሳኔ ሰጭነት ሚና ጥናት በማድረግና በጥናቱ ግኝቶች ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመስራት 50 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡

**የወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ፡-**

በክልሉ በሚካሄዱ የተለያዩ የኢኮኖሚያዊ መስኮች ወንድ 441,096 ሴት 441,096 በድምሩ 882,192 በከተማና በገጠር የሚገኙ ወጣቶችን፤ በ6 ከተሞች ልዩ ትኩረት የሚሹ ተጋላጭ ወንድ 1,424 ሴት 1424 በድምሩ 2,848 ወጣቶችና በምግብ ዋስትናና በሴፍትኔት ፕሮግራም ወንድ 94,006 ሴት 94006 በድምሩ 188,012 ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሰራል፡፡

ለወጣቶች የስራ ዕድል ፈጠራና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት አጋዥ የሆኑ የተለያዩ ድጋፎችን ማለትም፡- የወጣቶች የልማት ፈንዶችን በማቋቋም፣ ወንድ 303,253 ሴት 303,253 በድምሩ 606,506 ወጣቶች በቁጠባ ላይ እንዲሳተፉና የግንዘቤ ማስጨበጫ ስራዎች ይሰራል፤ እንዲቆጥቡ የቁጠባ ባህልን የማጎልበት ስራዎችን በመስራት፣ለወንድ 577,171 ሴት 577,171 በድምሩ 1,154,342 ወጣቶች ገበያ ተኮርና ተወዳዳሪነትን የሚያሳድጉ የክህሎት ስልጠናዎችን በማመቻቸት፣ የፋይናንስ ተደራሽነትና አቅርቦትን በማሻሻል የተቀላጠፈ እንድሆን ከተለያ ተቋማት ጋር የተዘዋዋሪ የብድር ገንዘብ በማመቻቸት ወንድ 268,986 ሴት 268,986 በድምሩ 537,972 ወጣቶች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማመቻቸት፣ ለወንድ 127,367 ሴት 127,367 በድምሩ 254,734 ወጣቶች የገበያ ትስስር በማመቻቸት ለወንድ 145,561 ሴት 145,561 በድምሩ 291,122 ወጣቶች የማምረቻና መሸጫ ቦታ አቅርቦትንና በገጠር የመሬት አቅርቦትን በማሻሻል የወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያስችሉ ድጋፎች የማመቻቸት ጉዳይ በቀጣይ የዕቅድ ዘመናት በትኩረት ይሰራል፡፡

ወንድ 677,036 ሴት 677,036 በድምሩ 1,354,072 ወጣቶች በመደበኛ የክረምትና የበጋ የበጎ ፈቃድ የአገልግሎት በ14 መስኮች በብሔራዊ አገልግሎት /Non military/ አገራዊና ክልላዊ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች በስፋት እንዲሳተፉ በማድረግና ወንድ 1,031,108 ሴት 1,031,108 በድምሩ 2,062,216 የክልላችንን ህ/ሰብ በሚሰጧቸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲጠቅሙና በመንግስትና በህ/ሰቡ ሊወጡ የሚችሉ 2,474,659,200 ብር የማዳን ተግባራት በቀጣይ የዕቅድ ዘመናት የሚሰሩ ይሆናል፡፡

ለወንድ 413,527 ሴት 413,527 በድምሩ 827,055 ወጣቶች በህይወት ክህሎት /Life Skill ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር ከአሉታዊ የአቻ ግፊቶች ራሳቸውን በመከላከልና ዕለት ዕለት በህይወታቸው የሚገጥማቸውን ፈተናዎች በአሸናፊነት እንዲወጡ ማስቻል፣ በሠላም መቻቻልና አገር ግንባታ ወጣቶች በሚኖራቸው ሚና ላይ ወንድ 735,160 ሴት 735,160 በድምሩ 1,470,321 ወጣቶች ግንዛቤ እንዲፈጠር ማድረግ፣ 150 ምክንያታዊ የውይይትና የክርክር መድረኮችን በማመቻቸት ወንድ 643,265 ሴት 343,265 በድምሩ 1,286,531 ወጣቶች እንዲሳተፉ በማድረግ፣ በየደረጃው የወጣቶች የንቅናቄና ተሳትፎ ኮንፈረንስ መድረኮችን በማዘጋጀት ወንድ 808,676 ሴት 808,676 በድምሩ 1,617,353 ወጣቶች በችግሮቻቸው ዙሪያ ከከፍተኛ አመራሮች ጋር እንዲወያዩ ማድረግ፤

ወጣቶች በሀገራችን በሚካሄዱ ሁሉን አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት፣ በህግ አውጪው አካላት የወጣቶችን ድርሻ ከ15% ወደ 30%፣ በአስፈጻሚ አካላት ወደ 30% እንዲሁም በህግ ተርጓሚ አካላት ወደ 30% በማድረስ፣ በሚካሄዱ አገራዊና ክልላዊ ምርጫዎች ወጣቶች 90% በመራጭነት፣ 30% በአስመራጭነትና 25% በዕጩነት እንዲሳተፉ በማመቻቸት ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን ማስጠበቅ፡፡

ለወጣቶች ስብዕና ግንባታ መጎልበት የወጣት ማዕከላት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወቱ የሚታመን ሲሆን በመጪው ስምንት ዓመታት በሁሉም የክልሉ አከባዎች፣ 195 አዲስ ሁለገብና መለስተኛ የወጣቶች ስብዕና ልማት ማዕከላትን መገንባት፣ 328 ማዕከላትን በቴክኒክና በማቴሪያል ማጠናከርና አገልግሎታቸው ለአካል ጉዳተኛና ሴት ወጣቶች ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡ አገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል ወንድ 639,145 ሴት 639,145 በድምሩ 1,278,290 ወጣቶች በማዕከላቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑና 104,673,612 ብር ለወጣት ማዕከላት ግንባታና የውስጥ ቁሳቁስ ማሟያ ከመንግስት፣ መንግስታዊ ካሆኑ ተቋማትና ከህ/ሰቡ ሀብት የማሰባሰብ ስራ የሚሰራ ይሆናል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሴቶች፣ የሕጻናትና ወጣቶች ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተለይተዋል፤**

በየደረጃው ከላይኛው እስከ ታችኛው የመንግስት አስተዳደር እርከን ያለውን የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ተቋማዊ አቅም በመገንባት በአደረጃጀት፣ በአሰራር እና በሰው ሃይል አቅሙን በተሻለ መልኩ በማሻሻል የልማት እቅዱ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈጸም ይደረጋል። በዚህም መሰረት በሁለቱም ዘርፎች የተቀመጡ የመፈጸምና የማስፈጸም የአቅም ግንባታ ግቦች አፈጻጸሞችን በማስተሳሰርና በማቀናጀት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈጸሙ ይደረጋል። የሴቶች የልማት ፍላጎት ለማሟላት በራሳቸው በሴቶች የተቋቋሙ አደረጃጀቶችን ያለባቸውን የአደረጃጀት፣ የአሰራርና የሰው ሃይል ችግር በመፍታት አቅማቸውን ወደ ላቀ ደረጃ በማሳደግ የእቅዱ ባለቤት እንዲሆኑ በማድረግ እቅዱን በተቀላጠፈና በተናበበ መልኩ የተፈጻሚነቱ ዋና ሃይሎች እንዲሆኑ ይደረጋል። ልዩ ልዩ የማህበረሰብ አደረጃጀቶችን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም በመገንባት በሁሉም ዘርፎች ሚናቸውን እንዲወጡ በማስቻል ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸው የሚረጋገጥ ይሆናል።

የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ የሁሉንም አካላት ዘርፈ ብዙ ምላሽ የሚሻ እንደመሆኑ መጠን የልማት እቅዱ ዋና ፈጻሚዎች ሴክተር መ/ቤቶችና በተዋረድም የሚገኙ የዞን፤ የወረዳና የከተማ መስተዳደር አስፈጻሚ መ/ቤቶች እንደመሆናቸው መጠን የትብብር፣ ቅንጅት እና ህብረ- ኃይልን የማጠናከር ስራ የሚከናወን ሲሆን የተቀናጀ አሰራር እንዲኖር የሚያስችሉ ፎረሞችን፣ ኔትዎርኮችን፣ ጥምረቶችና አደረጃጀቶች እንዲሁም የሁለትዮሽና ባለ ብዙ የትብብር ስምምነቶች የመመስረትና የማጠናከር ስራዎች እንዲከናወኑ ይደረጋል።

### 5.3. ሠራተኛና ማህበራዊ ልማት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች፡-**

ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋና ለዜጎች ምቹ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ፣ አሠሪዎችና ሠራተኞች በሕግ የተደነገጉ መብቶችና ግዴታዎችን አክብረው የጋራ ራዕይ በመሰነቅ ለክልሉ ልማት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ፣ መሠረታዊ የሥራ ላይ መብቶች እንዲከበሩ፣ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግና ተወዳዳሪነት እንዲጨምር፣ የኢንዱስትሪ ሰላም በዘላቂነት እንዲሰፍን፣ ከሚኒስተር መ/ቤት፣ ከልማት አጋሮችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበርና በመቀናጀት ለእነዚህ ጉዳዮች ምላሽ ሊሰጥ የሚችል ፍትሃዊ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አስተዳደር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይሆናል።

የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ የትኩረት መስኮች (ልማታዊ ሴፍቲኔትን ማስፋፋት፤ የሥራ ዕድልን ማስፋፋት እና የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል፤ የማህበራዊ መድንን ማስፋፋት፤ የመሠረታዊ አገልግሎት ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ እና ለጥቃትና ለበደል ተጋላጭ ለሆኑ ዜጎች የሕግ ጥበቃ እና ድጋፍ መስጠት) ላይ ርብርብ ይደረጋል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት ዓላማዎች**

ሠላማዊ የኢንደስትሪ ግንኙነትን በዘላቂነት ማሻሻልና በመከላከል መርህ የተቃኘ የሕግ ተፈጻሚነትን ማረጋገጥ፤ የመረጃ ሥርዓት መዘርጋትና ማጠናከር፤ ፍትሃዊና ዘመናዊ የሥራ ስምሪት አገልግሎቶችን ማስፋፋት፣ የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓትን በመዘርጋትና በማስፋፋት የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች ተካታችነት፣ ተደራሽነት እና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይልማት ዋና ዋና ግቦች**

**የአሠሪዎችና ሠራተኞች የመደራጀት ምጣኔን ማሳደግ፣**

የአሠሪዎች በማህበር የመደራጀት ምጣኔን ከ5.1% ወደ 25.7% እና የሠራተኞች በማህበር የመደራጀት ምጣኔን ከ13% ወደ 35% ለማድረስ ይሰራል፡፡ እንዲሁም በማህበር የመደራጀት መብታቸውን እንዲጠቀሙ ግንዛቤ በመፍጠር የአሠሪ ማህበር አሁን ካለበት 23 ወደ 135 ለማድረስ ታቅዷል፡፡ አሰሪዎች እና ሰራተኞች በማህበር የመደራጀት መብታቸው እንዲከበርና ማህበር ባልተደራጀባቸው ድርጅቶች ዉስጥ የህግ ተፈጻሚነትን ሊያረጋግጥ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አሁን ካለበት 2,722 ድርጅት ወደ 7,778 ለማድረስ ታቅዷል፡፡

**የማህበራዊ ምክክርና የሥራ ቦታ ትብብር ሥርዓትን ማጠናከርና ማስፋፋት፡-**

በድርጅት ደረጃ የሁለትዮሽ የሥራ ቦታ ትብብርና ማህበራዊ ምክክር ሥርዓት መዘርጋት አሁን ካለበት ከ23 ድርጅቶች ወደ 135 ለማድረስ፣ አንድ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድን የማቋቋም፣ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶችን ከ1 ማዕከላት ወደ 2 የማድረስ ስራ ይሰራል፡፡

ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ከሚቀርቡ የሥራ ክርክሮች መካከል በስምምነት የተፈቱ አሁን ካለበት 24.9% ወደ 100%፣ ለአስማሚ ቀርበው በስምምነት የተፈቱ የሥራ ክርክሮችን

ከ84% ወደ 100%፣ በአሠሪዎችና በሠራተኛ ማህበራት መካከል የተደረጉ የህብረት ስምምነት ሽፋን ከ30% ወደ 100% የማድረስ ስራ ይሰራል።

**የሥራ ሁኔታዎች ቁጥጥር አገልግሎት ማስፋፋትና ማሳደግ፡-**

በሥራ ላይ የሚደርስ የሞት አደጋዎችን አሁን ካሉበት 51/100,000 ሠራተኞች በመቀነስ ወደ 29/100,000 ሠራተኞች ለማድረስ፣ በሥራ ላይ ሞት ያላደረሱ አደጋዎች አሁን ካሉበት 4,987/100,000 ሠራተኞች በመቀነስ ወደ 777/100,000 ሠራተኞች ለማድረስ፣ የሥራ ሁኔታዎች ቁጥጥር አገልግሎት ሽፋንን በድርጅት አሁን ካለበት ከ532 በማሳደግ 29,702 ላይ ለማድረስ እና የሙያ ደህንነትና ጤንነት ቁጥጥር አገልግሎት ላይ ለ23 የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና ዕድሳት ለመሥጠት ይሰራል።

**የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን መከላከልና መቆጣጠር፡-**

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ለመከላከል በሥራ ቦታ ቁጥጥር በማድረግ አስከፊ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን አሁን ካለበት 78,038 12,392 ለበመቀነስ፣ አስከፊ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲያስችል በክልሉ በሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአቻ ለአቻ ውይይት ማድረስ፣ አስከፊ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን ለመከላከል የማህበረሰብ ውይይት ማካሄድን አሁን ካለበት 42 ቀበሌዎች ወደ 868 ቀበሌዎችን ማድረስ፣ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን ለመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጥን አሁን ካለበት 1,641,489 (ሴት 820,744) ላይ ማድረስ ነው።

**የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ማጠናከርና ማስፋፋት፡-**

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎትን በ532 ድርጅቶች ሥርዓት በመዘርጋት የሥራ ሁኔታዎች ማሻሻል፣ የቁጥጥር አገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል የሚያግዝ አንድ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ላቦራቶሪ ማቋቋም፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች 50% ተደራሽ ለማድረግ።

**የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፡-**

አንድ የሥራ ገበያ መረጃ ቋት በማዘጋጀት እና በየደረጃዉ ጥቅም ላይ በማዋል የሥራ ገበያ መረጃዎችን ጥራት እና የቅብብሎሽ ስርዓት ለማሻሻል፣ የሥራ ገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብ እና በመተንተን 8 ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ፣

ከቀጣሪ ድርጅቶች ጋር የትብብር አሰራር ስርዓት በመዘርጋት ክፍት የሥራ ቦታዎችን የሚያሳዉቁ ድርጅቶችን ቁጥር ወደ 1,220 በማድረስ ጥቅም ላይ እንድዉል ለማድረግ እና በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ሥራ ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል አስመልክቶ 2 ክልላዊ ጥናቶችን ለማካሄድ ታቅዷል።

**የሥራ ስምሪት አገልግሎቶችን በማስፋፋት የዜጎች ተጠቃሚነትን ማሳደግ፡-**

ሞዴል የሥራ ስምሪት አገልግሎት ማመቻቻ ማዕከላትን በ2 ማዕከላት ላይ በማቋቋም አገልግሎቱን ለማሳደግ፣ ለ2,927,278 ሥራ ፈላጊዎች የሙያ ምክር እና የሥራ አመራር አገልግሎት ድጋፍ በመስጠት የሥራ ሥምሪት ግንኙነቶችን ለማጠናከር እና የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም የሥራ ባህል ለማሳደግ የሚያግዙ የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት ለ300,000 (50% ሴቶች) የህ/ክፍሎች በመስጠት የስራ ስምሪት ተጠቃሚነትን ለማሻሻል ታቅዷል።

በአገር ውስጥ የሥራ ስምሪት ድጋፍ አግኝተው በሥራ ላይ የሚሰማሩ ዜጎች ቁጥር በአገር ውስጥ የሥራ ስምሪት አሁን ከደረሰበት 25,774 ወደ 200,000 እና በአገር ውስጥ በወቅት ስራዎች ላይ የሚሰጥ የሥራ ስምሪት አሁን ካለበት 118,000 ወደ 380,000 በማሳደግ ሥራ አጥነትን የመቀነስ። በዉጭ አገር ስራ ስምሪት ለመሰማራት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ያሟሉ ሥራ ፈላጊዎችን 100% ወደ ሥራ እንዲሰማሩ በመደገፍ በዉጭ አገር የስራ ስምሪት ተጠቃሚነት ለማሳደግ ታቅዷል።

መስፈርቱን አሟልተዉ ለሚቀርቡ የአገር ዉስጥ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች 100% ፍቃድ በመስጠትና ህገወጥ የሰራተኛ ምልመላ እና ስምሪት የሚሰጡ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ የመዉሰድ ምጣኔን ከ80% ወደ 90% በማድረስ ህገ-ወጥነትን ለመከላከል።

**መደበኛ ያልሆነ የሰዎች ዝውውር በመከላከል ተጋላጭነትን መቀነስ፡-**

የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ፍልሰትን ለመከላከል የሚያስችል ግንዛቤ ያገኙ ዜጎችን ቁጥር ከ62,846 ወደ 4,100,000 ለማድረስ፣ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር 100% የሚሆኑት ከስደት ተመላሾች የስነ-ልቦና ምክር አገልግሎት እንዲያገኙና 60% የሚሆኑ ስደት ተመላሾች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ በማመቻቸት በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚነታቸዉን ለማሳደግ ታቅዷል።

**የማህበራዊ ጥበቃ ስርዓትን በመዘርጋትና በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፡-**

የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ተጠቃሚዎችን መረጃዎች አደራጅቶ ለመያዝ የሚያስችል የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ስርዓት 64 መዋቅሮች በማድረስ ለዜጎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ፍትሃዊነትና ተደራሽነትን፣ እንዲሁም 64 የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤቶችን በማቋቋም፣ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞችን አስተማማኝና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አንድ ክልላዊ የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ በማቋቋም የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ታቅዷል። ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ የሚውል ሀብት አሰባሰብ አሁን ካለበት 12,750,000 ወደ 112,147,000 በማሳደግ ተጠቃሚ ማድረግ

**የአካል ጉዳተኞችን ተካታችነትና እና ተደራሽነት ማሳደግ፡-**

ለ7,081 አካል, ጉዳተኞች የሥነ ልቦና እና ማህበራዊ የተሃድሶ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የማመቻቸት፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እና በመምራት የተሃድሶ አገልግሎት ከ1,108 ወደ 25,239 ለማድረስ፣ እንዲሁም 399,195 ለሚሆኑት አካል ጉዳተኞች የመሰረታዊ አገልግሎት አቅርቦት ተደራሽነትን እና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ታቅዷል። በተጨማሪም ለ20,252 አካል ጉዳተኞች የስራ ዕድል የማስፋት፣ በስራ ቦታ የሚደርስባቸውን መገለልና መድሎ የማስቀረት እና በስራ ቦታ ተመጣጣኝ ማመቻቸትን ለማሳደግ ይሰራል። በገጠርና በከተማ የሚኖሩ የመስራት አቅም የሌላቸውና እና የድሃ ድሃ የሆኑ አካል ጉዳተኞች የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች እና የሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን ተጠቃሚነት ሽፋንን አሁን ካለበት 133 ወደ 11,556 ለማድረስ ታቅዷል።

**የአረጋዊያንን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት ማሳደግ፡-**

ለ16,914 አረጋውያን የማህበራዊ የተሃድሶ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የማድረግ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በተለያዩ የሥራ መስኮች መሳተፍ ከሚችሉ አረጋውያን መካከል 14,000 የትምህርት፣ የስልጠና እና የሥራ ስምሪት እንዲያገኙ የማድረግ፣ እንዲሁም 8 አዲስ አረጋዊያን ማዕከላትን በመገንባት የአረጋዊያን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነታቸውን ማሳደግ፣ አረጋዊያን ላይ የሚደርሱ የመብቶች ጥሰቶችን 100% በማስከበር የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውን እና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ታቅዷል።

**የኢኮኖሚያዊ እና የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፡-**

በክልሉ ከተሞች በከፋ ድህነት ውስጥ ከሚገኙት የህብረተሰብ ክፍሎች 30,363 ተጠቃሚ ማድረግ የሥነ-ልቦና እና ማህበራዊ የተሃድሶ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ እና

የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር በዋና ዋና ከተሞች በከፋ ድህነት ውስጥ ከሚገኙት የህብተረሰብ ክፍሎች ውስጥ 15,182 የመሰረታዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚነታቸውን በማሳደግ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ካደረጉ የህረተሰብ ክፍሎች (Urban Destitute) ውስጥ 40% ዜጎችን የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም እና ሌሎች መሠረታዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ በማድረግ ችግሩን መቀነስ፡፡

የአደገኛ ዕጾችና መድሃኒቶች ተጠቃሚ ከሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ለ6,871 ለሚሆኑት የተሃድሶ አገልግሎት በመስጠት

## የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን የማስፈጸሚያ ሥልቶች

በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ አዋጆች፣ ፖሊሲዎችና የተለያዩ ስትራቴጂዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ ለዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ ሳይንሳዊ መረጃዎች ዘመናዊ በሆነ መንገድ ተሰብሰበው፣ ተደራጅተውና ተተንትነው ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

በሁሉም ተቋማት በፕሮግራሞቻቸውና በእቅዳቸው ውስጥ የሴቶችን፣ የወጣቶች፣ የአረንጓዴ ልማት፣ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን፣ በሥራ ቦታዎች ኤች አይ ቪ እና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎችን የመከላከልና የመቆጣጠር፣ በሚፈለገው ደረጃ አገልግሎቱን ተደራሽ እንዲያደርጉ ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን ተግባራዊነት ለማሳለጥ የተቋቋሙ ፕላት ፎርሞች፣ የማህበረሰብ ድጋፍና እንክብካቤ በማቋቋም፣ አቅማቸውን በመገንባት ከህብረተሰቡ ሀብት በማሰባሰብ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ይደረጋል፤ በህብረተሰቡ ዘንድም መረዳዳት ባህል እንዲጎለብት ቤተሰብ ተኮር ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

በሥራ ቦታ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በአማራጭ የመፍቻ መንገዶች (የሁለትዮሽና የሶስትዮሽ ሥርዓት) እንዲዘረጉ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም ሠራተኛው በተገቢው ሁኔታ የመደራጀት መብቱን እንዲጠቀም አስፈላጊው እና ውጤታማ የሆኑ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ተከታታይነት ባለው መንገድ ሥርዓት በመዘርጋት እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡

የሴክተሩ ተግባርና ኃላፊነት ዘርፈ-ብዙና ሴክተር ዘለል እንደመሆናቸው መጠን ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት፣ የግሉ ዘርፍ፣ አለም-አቀፍና ሀገራዊ የልማት አጋሮችና ማህበራዊ ተጓዳኞች ለዘርፉ ልማት የሚጠበቅባቸውን የጋራና የተናጠል ኃላፊነታቸውን መወጣት የሚችሉበት የትብብርና የቅንጅት አሰራሮች በየደረጃው እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# 6የሕዝብ አገልግሎት፣ ፍትህ እና የህዝብ አገልግሎት ልማት ዕቅድ

## 6.1. የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ

### የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች

ነፃ ገለልተኛና ብቃት ያለዉ የመንግስት አገልግሎት ሥርዓት በመገንባት፣ የሰዉ ሃብት ሥራ አመራርና ዘመናዊ የሰዉ ሃብት መረጃ አያያዝ ሥርዓት በማሻሻል፣ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ የአፈፃፀም ሥራ አመራር ሥርዓት በማጠናከር፣ ሥነ-ምግባር ዕሴት ግንባታና መልካም አስተዳደርን በማሻሻል በፐብሊክ ሰርቪሱ ዘርፍ መሠረታዊ ለውጥ በማምጣት በክልሉ የልማት ጉዞ ጉልህ ሚና መጫወት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

### የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ዓላማዎች

የመንግስት አገልግሎት ዘርፍ ዋናው ዓላማ ብቁ፣ ገለልተኛና ነጻ የመንግስት አገልግሎት ስርዓት/ሲቪል ሰርቪስ/ በመገንባት የመንግስትን የመፈጸም ብቃት ማጎልበትና በመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዜጎችን እርካታ ማሳደግ ነው።

### የቀጣይ አሥር ዓመታት የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል

የመንግስት ተቋማት የአደረጃጀት ውጤታማነት በ2014 በጀት ዓመት ከነበረበት 60% በ2022 ወደ 100% ማሳደግ፣ በየደረጃው የሚገኙውን አመራር የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም በ2014 በጀት ዓመት 45 በመቶ ከነበረበት በ2022 ዓ/ም ወደ 100% ማሳደግ እንድሁም የአፈጻጸም ሥራ አመራር ሥርዓትን በማጠናከር የመንግስት ተቋማት የዕቅድ አፈፃፀም ውጤታማነት በ2014 በጀት ዓመት 60 በመቶ ከነበረበት በመሪ ዕቅዱ መጨረሻ ዓመት ወደ 100% እንዲያሳድጉ ለመደገፍ ታቅዷል።
የሰው ሀብት ሕጎች አተገባበር ውጤታማነት በ2014 በጀት ዓመት 60 በመቶ ከነበረበት በ2022 ዓ/ም ወደ 100% ለማሳደግ፣ በ2014 በጀት ዓመት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት 60 በመቶ ከነበረበት በ2022 ወደ 100% ለማሳደግ፣ የሰው ሀብት ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ትግበራን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 100% ተግባራዊ ለማድረግ፣ ተቋማዊ የተደረገ የሰው ሀብት ሥራ አመራር የአሰራር ስርዓት በ2014 በጀት ዓመት ከሚገኝበት 60% በ 2022 መጨረሻ ወደ 100 % ለማሳደግ፣ የሰው ሀብት አቅም ማሳደግ ተደራሽነት በ2014 በጀት ዓመት 30 በመቶ ከነበረበት በ2022 ወደ 100 % ለማሳደግ፣ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት በ2014 በጀት ዓመት ከነበረበት 47% በ2022 ወደ 100 % ለማሳደግ፣ ሂደት ተኮር አደረጃጀት ትግበራ በ2014 በጀት ዓመት ከነበረበት 45% ወደ 100 % ለማሳደግ ታቅዷል።

ዘመናዊ የቅሬታና አቤቱታ ሥርዓት ተደራሽነት በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት ከ 45 በመቶ ወደ 100% ለማሳደግ፣ የመንግሥት ሠራተኞችን ሥነ-ምግባርና እሴት ግንባታ በማሳደግ በ2014 በጀት ዓመት የመንግስት ሰራተኞች የስራ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት 35 በመቶ ከነበረበት ወደ 100 % ለማሳደግ፣ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት ተቋማት የመልካም አስተዳደር ችግሮች በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበሩበት 75 በመቶ በዚህ መሪ ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ወደ 0 በመቶ ለመቀነስ ታቅዷል፡፡

### የቀጣይ አሥር ዓመታት የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች

የተቋማትና ዜጎች ዕርካታ ጥናት፡- የተቋማት እርካታ በየዓመቱ እንዲሁም ዜጎች ዕርካታ ማረጋገጫ ጥናት በየሁለት ዓመቱ የሚከናወን ሲሆን ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል እንደ አስፈላጊነቱ የዕቅድ ክለሳ ይከናወናል፡፡

የመንግስት ተቋማት ማወዳደሪያ/ሽልማት ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፡- በስፋት የሚሰራበት ሲሆን የሽልማት ስርዓቱም ተቋማት ክፍተታቸውን በመለየት በቀጣይ የሚሻሻሉበት አሰራር ይዘረጋል ተግበራዊም ይደረጋል፡፡

የካይዘን ትግበራ፡- ይህ ስልት በዋናነት በመንግስት ተቋማት ያሉ ብክነቶችን መቀነስ እና ምቹ የሥራ ቦታ መፍጠር ላይ አትኩሮ በመስራት ተቋማትን በቀጣይነት እንዲሻሻሉ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማድረግ እና የዜጎችን እርካታ በማረጋገጥ የጎላ አስተዋጽዖ ይኖረዋል፡፡

## 6.2. የፍትህ ዘርፍ

### 6.2.1. ፍትህ ልማት

#### የቀጣይ አሥር ዓመታት የፍትህ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች

የተጀመረውን የለውጥ ሂደት ለማስቀጠል የማስፈፀም አቅምን በማሳደግ የመንግስትና ህዝብን ጥቅም በማስከበር ይህንን መሪ ዕቅድ በማሳካት የተጀመረውን የልማት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታን ለማሳደግ የህግ የበላይነትን በማስከበር፣ የህብረተሰቡ ሠላምና ደህንነት የተረጋገጠ እንዲሆን በማድረግ በተቋሙ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ፍትሃዊ፣ ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፤

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የፍትህ ዘርፍ ዓላማዎች**

የተቋሙን የመፈፀም አቅም በማሳደግ የመንግስትና የህዝብን ጥቅሞችን በማስከበር የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ማስቻል፣ ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ፣ ዘላቂ ሰላምና መልካም አስተዳደር በመገንባት የተጀመረውን የለውጥ ሂደት በማስቀጠል የህግ የበላይነትን በማክበርና በማስከበር የሕብረተሰቡን ሠላምና ደህንነት የተረጋገጠ እንዲሆን በማድረግ በፍትህ አስተዳደሩ ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን ደረጃ በደረጃ በመቅረፍ ተቋሙ በስትራቴጂክ እቅድ ዘመኑ መጨረሻ ተልዕኮውን በአግባቡ መወጣት እንዲችል ለማድረግ ያለመ ነው።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የፍትህ ዘርፍ ዓላማዎች ለማሳካት የታቀዱ ዋና ዋና ግቦች**

በተቋሙ የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት 100% እንዲፈቱ ማድረግ፣ ለህዝብ ክንፍ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ግምገማ ዙሪያ ለማሳተፍ 32 መድረኮችን ማመቻቸት፤ የፍትህ አገልግሎት በተዘዋዋሪ ችሎት 100% ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፣

**የወንጀል ጉዳዮች አስተዳደር ጥራት እና ውጤታማነት ማሳደግ**

ከፖሊስ ጋር በጋራ ሊጣሩ በሚገቡ የወንጀል ጉዳዮች ምርመራ ምጣኔ ወደ 100% ማድረስ፣ የመዝገብ የማጥራት ምጣኔን በ2014 ዓ/ም 89.6% ወደ 99.75% ማድረስ፣ የመዝገብ የመንጠባጠብ ምጣኔን በ2014 ዓ/ም 4.1 ከነበረበት ወደ 1% መቀነስ፣ መዝገብ የመቋረጥ ምጣኔ በ2014 ዓ/ም 10% ወደ 3% መቀነስ፣ በመዝገብ የማስቀጣት ምጣኔን በ2014 ዓ/ም 88.7% ከነበረበት ወደ 99% ማድረስ፣ በተከሳሽ የማስቀጣት ምጣኔን 87% ማድረስ፣ የዐቃቤ ህግ ክስ መዝገቦች እንዳይሻሻሉ 99% በጥራት ማዘጋጀት፣ በዕርቅ ማለቅ የሚገባቸው ቀላል የወንጀል መዝገቦች 95% ማድረስ፣ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን የማስፈጸም አቅም 95% ማሳደግ፣ በጠቋሚዎችና በምስክሮች የሚቀርቡ የከለላ ጥያቄዎች ምላሽ የመስጠት ምጣኔን ወደ 100% ማሳደግ፣ ዐ/ህግ ይግባኝ በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ ምጣኔ በመዝገብ 99% ማድረስ፣

ዐ/ህግ ይግባኝ በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በተከሳሽ 90% ማድረስ፣ ተከሳሾች ይግባኝ የጠየቁባቸው ጉዳዮች በመዝገብ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም 99% ማድረስ፣ ተከሳሾች ይግባኝ

የጠየቁባቸው ጉዳዮች በተከሳሽ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም 90% ማድረስ፣

ዐ/ህግ ሰበር በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በመዝገብ 99% ማድረስ፣ ዐ/ህግ ሰበር በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በተከሳሽ 90% ማድረስ፣ ተከሳሾች ሰበር የጠየቁባቸው ጉዳዮች በመዝገብ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም 99% ማድረስ፣ ተከሳሾች ሰበር የጠየቁባቸው ጉዳዮች በተከሳሽ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም 90% ማድረስ፣

በሴቶችና ህጻናት አረጋውያንና በአካል ጉደተኞች የመዝገብ የማጥራት ምጣኔን 100% ማድረስ፣ የመዝገብ የመንጠባጠብ ምጣኔን ወደ 0.5% መቀነስ፣ ክስ የመቋረጥ ምጣኔ ወደ 4% መቀነስ፣ የማስቀጣት ምጣኔን በመዝገብ 99% ማድረስ፣ የማስቀጣት ምጣኔን በተከሳሽ 95% ማድረስ፣ ዐ/ህግ ይግባኝ በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በመዝገብ 99% ማድረስ እና በተከሳሽ 95% ማድረስ፣ ተከሳሾች ይግባኝ የጠየቁባቸው ጉዳዮች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም በመዝገብ 99% ማድረስ እና በተከሳሽ 95% ማድረስ፣

በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ዐ/ህግ ሰበር በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በመዝገብ 99% እና በተከሻሽ 95% ማድረስ፣ ተከሳሾች ሰበር የጠየቁባቸው ጉዳዮች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም በመዝገብ 99% እና በተከሳሽ 95% ማድረስ፣ የፍርድ ውሳኔዎችን የማስፈጸም አቅም ወደ 100% እነዲሁም የፍታብሔር የመርታት ምጣኔን 100% ማድረስ።

በሙስና የተመዘበረ የመንግስት ሀብትና ንብረት የማስመለስ ምጣኔ 99% ማሳደግ፣ በታክስ ማጭበርበር የተመዘበረ የመንግስት ሀብትና ንብረት የማስመለስ ምጣኔ 100% ማሳደግ፣ 20,390 በዐቃቤ ህግ መዝገቦች ላይ የህግ አዲትና ኢንስፔክሽን ማድረግ፣ ለሚቀርቡ ወንጀል ነክ አቤቱታዎችና ጥቆማዎች የመጀመሪያ ደረጃ ውሣኔ የመስጠት ምጣኔ 100% ማሳደግ፣

**የይቅርታ አሰጣጥ ጥራትና ውጤታማነት ማሳደግ፡-**

የይቅርታ ተጠቃሚ የህግ ታራሚዎች ምልመላና መረጣ አፈፃፀም ጥራት ወደ 99% ማሳደግ፣ ለህግ ታራሚዎች የሚሰጠው የውሳኔ አስተያየት ጥራት 95% ማድረስ፤ በይቅርታ አሰጣጥ ፋይዳ ላይ የተደረገ 4 የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ።

**የመንግስትና የህዝብ የሚመለከቱ የፍታብሔር ጉዳዮች ውጤታማነትን ማሳደግ**

የውል ምርመራ ሽፋንና ጥራት ምጣኔን 100% ማድረስ፣ መንግስት ከሳሽ በሆነበት ፍታብሔር ጉዳዮች የመርታት ምጣኔን 96% ማሳደግ፣ መንግስት ተከሳሽ በሆነበት የፍታብሔር ጉዳዮች የመርታት ምጣኔ 90% ማሳደግ፣ በፍትሀብሄር ጉዳዮች የተሰጠ የህግ ምክር ሽፋን ምጣኔ 100% ማሳደግ፣ በውል ክፍተቶች የሚከሰቱ ክርክሮችን ወደ 2% መቀነስ፣ በፍታብሄር አፈጻጸም ክስ ገቢ የተደረገ የመንግስት ሀብት 95% ማስመለስ፣ የፍታብሔር ጉዳይ ከክስ በፊት በድርድር 15% ሀብት እንዲመለስ ማድረግ፣ ተከሳሾች ይግባኝ የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር መዝገቦች ውሳኔ እንዲጸኑ የማድረግ አቅም 95% ማሳደግ፣ ዓቃቤ ህግ ይግባኝ የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር መዝገቦች ውጤታማነት 99% ማድረስ፣ ተከሳሽ ሰበር የጠየቁባቸው መዝገቦች ውሳኔ እንዲጸኑ የማድረግ አቅም 95% ማድረስ፣ ዓቃቤ ህግ ሰበር የጠየቁባቸው መዝገቦች ውጤታማነት 99% ማድረስ፤

**የህግ ጥናትና ማርቀቅ ስራን ጥራትና ውጤታማነትን ማሳደግ፡-**

98% ጥራቱ የጠበቀ የህግ ማርቀቅና ቅርጽ የማስያዝ ስራን መስራት፣ በተመረጡ የህግ ጉዳዮች ላይ 16 ጥናት ማድረግና ለሚመለከተው አካል የውሣኔ ሀሳብ ማቅረብ፣ በህግ ጥናት ላይ በክልሉ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችን በማሳተፍ በቅንጅት መስራት፣ የተዘጋጁ ህጎችን 95% ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ወደ እንግሊዘኛ መተርጎም፣

**የህብረተሰቡን ንቃተ ህግ ማሳደግ**

ለህብረተሰቡ የንቃተ ህግ ለመስጠት የሚያስችል 8 የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማድረግ፣ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጡ 200 የንቃተ ህግ ግንዛቤ መስጫ ማንዋሎችን በማዘጋጀት የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ለ6,520,000 የህብረተሰብ ክፍል የንቃተ ህግ ግንዛቤ ትምህርት መስጠት

**የህግ ምክርና አስተያየት በመስጠት የመፈጸምና ማስፈጸም አቅምን ማሳደግ**

የክልሉ መንግስትንና ሴክተር መስሪያ ቤቶችን 100% የሕግ ምክር አገልግሎት መስጠት፣

**ጠበቆች ለፍትህ ሥርዓቱ አጋዥነታቸውን ማጠናከር፣**

ጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች የፍትህ ስርዓቱ አጋዥ ኃይል ለማድረግ ከሙያቸውና ከሥራቸው ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ሥልጠና መስጠት፣ ፈቃድ የመስጠትና የማደስ አገልግሎት ውጤታማነትን ማሳደግ፣ በሚሰጡት የጥብቅና አገልግሎት ላይ ክትትልና

ቁጥጥር ማድረግ፣ በነሱ ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ 100% ውሳኔ መስጠት፣ የሥነ-ምግባር ጉድለት በሚያሳዩ ጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ላይ የሚቀርቡ ክሶችን በድስፕሊን ጉባኤ 100% ውሳኔ መስጠት፣ ለህብረተሰቡ በሚሰጡት አገልግሎትና ከፍትህ አካላት ጋር ባላቸው መሰተጋብር ዙሪያ የዉይይት መድረክ ማመቻቸት፣ ጠበቆችና ነጻ የህግ ድጋፍ ማዕከላት አቅም ለሌላቸው ዜጎች የሚሰጡትን ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ውጤታማነት ማሳደግ፤ ለጠበቃ የመክፈል አቅም ለሌላቸው ሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞችና ለአረጋውያን ነጻ የጥብቅና አገልግሎት 100% እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

**የቅሬታ አቀራረብና አፈታትን ሥርዓት ማሻሻል፡-**

የቅሬታ ማቅረቢያ ስርዓትን መዘርጋት፤ በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ የቀረቡ አቤቱታዎችና ቅሬታዎች 100% ምላሽ መስጠት፣

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የፍትህ ዘርፍ ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተቀምጠዋል**

የማስፈፀም አቅምን በመግንባት ተቋማዊ ለውጥ ለማምጣት የለውጥ መሳሪያዎችንና የአሰራር ስርዓቶችን መተግበር፣ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር መርሆችን በመከተል በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ሲቪል ማህበራት፣ ባለድርሻ አካላት እና የህዝብ ክንፍ በማሳተፍ የራሳቸውን ሚና እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

በሙስና፣ በታክስ እና በከባድ ወንጀሎች ምርመራ ከፖሊስ ጋር አብሮ በመስራት ቅንጅታዊ አሰራርን በማጎልበት፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከር አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፣ የህዝብና የመንግስት ጥቅም ያለባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ከሴክተር መ/ቤቶች በቅንጅትና በትኩረት ይሰራል፡፡ የህብረተሰቡን የንቃተ ሕግ ደረጃ በማሻሻል ሕግና ሥርዓት የሚያከብርና የህግ ማስከበር ስራውን በንቃት የሚደግፍ አደረጃጀት በመፍጠር ሕጎች ለህብረተሰቡ በልዩ ልዩ መንገድ እንዲታወቁና እንዲሠራጩ ይደረጋል፡፡

ጠበቆች ለፍትህ ሥርዓቱ አጋዥ የሚሆኑበትን ስርዓት በመዘርጋት፤ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ጥቅሞች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ፣ እንዲሁም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመረጃ አያያዝ  ስርዓቱን እንዲሻሻል የማድረግና ምርጥ ተሞክሮዎችንና የላቁ ውጤቶችን ቀምሮ ማስፋት አንደ ማስፈጸሚያ ስልት ተወስደዋል፡፡

## 6.2.2. ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች**

የሰው ሀብት ማልማትና ማሟላት፤ የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትን ማሳደግ፤ ቅልጥፍናን ማጐልበት፤ የዳኝነት ነፃነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ማረጋገጥ፤ተደራሽነትን ማረጋገጥ፤ የለውጥ መሣሪያዎችን አጠናክሮ መጠቀም፤ የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ሥራ ማጠናከር፤ የፋይናንስ ፍላጎትን ማሟላት የአደረጃጀትና የመረጃ አጠቃቀም ሥርዓትን ማጠናከር

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዘርፍ ዓላማዎች ፡-**

የፍርድ ቤቶችን ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን ተከትሎ ተልዕኮን መወጣት የሚያስችሉ ተግባራትን አከናውኖ መልካም እሴቶችን በመከተል በመሪ ዕቅድ ዘመኑ የሚደረስበትን ግብ ማሳካት ነዉ፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የፍትህ ዘርፍ ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች**

**የክልሉን ፍርድ ቤቶች ቅልጥፍና ማጐልበት፡-**

ቅልጥፍና ማጐልበት ስንል በፍርድቤቶች ለቀረቡ ጉዳዮች በጊዜ ያለ እንግልት ውሳኔ እንዲያገኙ የማድረግ አቅም ማጐልበትን ይመለከታል፡፡ ይህም የሚገለጸው በሚከፈቱት የክርክር ፋይሎች ብዛት፣ውሣኔ በሚያገኙ መዝገቦች መጠን፣በሚተላለፉ መዝገቦች መጠን፣በፍርድ ቤቶች መዛግብት የማጣራት አቅም፣ የመዝገቦች የመጨናነቅ ሁኔታ፣በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት የመወሰን አቅም እና ዳኛ መዝገብ ጥምርታትን የሚያጠቃልል ነው፡፡

ስለሆነም የጉዳዮችን አካሄድ አመራር በማጥናትና በመተግበር፣ የዳኞችን አቅም በማጐልበትና ቁጥር በመጨመር በቀጣይ ዕቅድ ዓመታት ውሳኔ የሚያገኙ መዝገቦች ቁጥር ከፍ ይደረጋል፡፡ የማጣራት አቅም ይሻሻላል፤ የመዝገቦች መጨናነቅ ሁኔታ ይቀንሳል፤ የዳኞችና መዝገብ ጥምርታ ይሻሻላል፡፡ በእነዚህ መነሻዎች ቅልጥፍናን ለማጐልበት የሚከተሉት ተግባራት ይከናውናሉ፡፡ በዚህ መሠረት በቀጣይ ስምንት ዓመታት የዕቅድ ዘመን የሚከፈቱ ፋይሎች

ከክልሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ቴክኖሎጂያዊ ሁኔታዎች በማገናዘብ የሚስተዋሉ አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ከግንዛቤ በማስገባት የክርክር ፋይሎችን መክፈት 2014 ዓ/ም 60452 ከነበረበት በ10% በየዓመቱ በማሳደግ በ2022 ወደ 129,585 ማድረስ፡፡

**የመወሰን አቅምን ማሳደግ፡-**

በቀጣይ የመሪ ዕቅድ ዓመታት በክልሉ ፍርድ ቤቶች የዳኛን ቁጥር በመጨመር፣ የክርክር ሂደቱን እና የመወሰን አቅምን የሚጨምሩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፣ ተደራሽነትን በማስፋት፣ በተጠና ሁኔታ የዳኞችን ክህሎት ክፍተት የሚደፍኑ ሥልጠናዎችን በመስጠትና ቅንጅታዊ ሥራዎችን በማጠናከር እንዲሁም የጉዳዮች አካሄድ አመራርን በመተግበርና ልዩ ዕውቀት ለሚፈልጉ ጉዳዮች ልዩ ችሎት በማደራጀት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የመወሰን አቅም 92% ከነበረበት በየአመቱ አፈጻጸሙን በ0.5% በመጨመር በ2022 ዓ/ም መጨረሻ 96.5% ማድረስ

**የማጣራት አቅምን ማሳደግ፡-**

በአዲሱ ክልል የታቀፉ ፍርድ ቤቶች አማካይ የማጣራት አቅም 94% ከነበረበት በየአመቱ አፈጻጸሙን በ0.5% በመጨመር በ2022 ዓ/ም መጨረሻ 98.5% ለማድረስ ታቅዷል፡፡

**የመዛግብት መጨናነቅ ሁኔታን መቀነስ፡-**

የመዛግብትን የመጨናነቅ ሁኔታ 1.06 ከነበረበት በየዓመቱ በ0.01 መቀነስ በ2019 ዓ/ም ወደ 1 ለማምጣት እና በየዓመቱ በ1.01 መቀነስ በ2022 ዓ/ም መጨረሻ ወደ 1 ዝቅ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

**በስታንዳርዱ መሠረት የመወሰን አቅምን ማሳደግ፡-**

በፍርድ ቤቶች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት መሠረት ከግብ ስኬትነት ከተወሰዱት ጉዳዮች አንዱ የመዛግብት ዕድሜ በአማካይ ከሁለት ወር መብለጥ የለበትም የሚል ነው፡፡ ይህም የሚለካው በአመቱ ውስጥ ከተወሰኑት ጉዳዮች በ2 ወር ጊዜ ውስጥ የተወሰኑ መዛግብት ብዛትን ለመለየት በሚያስችል መልኩ በማስላት ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የመወሰን አቅም 83% በየአመቱ በ2% እየጨመረ እንድሄድ በማድረግ በ2022 ዓ/ም መጨረሻ ላይ 100% ለማድረስ ታቅዷል፡፡

**የዳኛ መዝገብ ጥምርታ ማሻሻል፡-**

የዳኛ መዝገብ ጥምርታ ስንል አጠቃላይ በአመቱ ውስጥ የተወሰኑ መዛግብትን ለዳኞች ብዛት በማነጻጸር የመለካት ዘዴ ነው፡፡ ከዚህ መነሻ የዳኛ መዝገብ ጥምርታ 1፡101 ከነበረበት በየዓመቱ በ5% እየጨመረ ሄዶ በ2022 ዓ/ም መጨረሻ ላይ 1፡155 ማድረስ፡፡

**የሚሻሩ መዛግብትን መቀነስ፡-**

ዳኞች የቀረቡትን ክርክሮችና ማስረጃዎች ሰምተው በመመርመርና በመመዘን አግባብ ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ የሚሰጡት ውሳኔ እውነት ላይ የተመሰረቱ፣ ፍትሐዊና የሚፈጸሙ ከሆነ የሚሻሩ መዝገቦችን መቀነስ ይቻላል ፡፡ ከዚህ መነሻ የማጽናት አቅም 80% ከነበረበት በየዓመቱ በ3% እየጨመረ እንዲሄድ በማድረግ በ2022 መጨረሻ ላይ የማጽናት አቅምን ወደ 100% ለማድረስ ታቅዷል፡፡

**ተገማችነት ያለው ውሳኔ መስጠት፡-**

የክርክር ሂደቱንና የውሳኔ አሰጣጡን ተገማችነት ለማረጋገጥ የሚረዱ የጉዳዮች አካሄድ፤ አመራርና የቀጠሮ ፖሊሲን በማጥናት መተግበርና የፌዴራል ሰበር ውሳኔዎችን በተጠናከረ ሁኔታ ለአተረጓጎም መጠቀምና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የክርክሩን ሂደት ግልጽነት የማጐልበት ሥራዎች በቀጣይ የእቅድ ዘመን ይሠራሉ፡፡

**የተገልጋዩን እርካታ ማሳደግ፡-**

የተገልጋይ እርካታ ደረጃ 80.36% ከነበረበት በ የዓመቱ በ1% እያደገ እንዲሄድና በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 86.4% ለማድረስ ታቅዷል፡፡ 87.02

**የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የአሠራር ሥርዓትን ማጠናከር ፣**

የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ህገ መንግሥታዊ መሠረት ያለው የዳኝነት ነጻነት ግልጽነትና ተጠያቂነት አሠራርን በማጐልበት ረገድ ቁልፍ ኃላፊነት ያለው አካል ነው፡፡ ስለሆነም በቀጣይ የዕቅድ ዓመታት ጉባኤውን በሰው ኃይል፣ በበጀትና በማቴሪያል በማደራጀት የዳኝነት ነጻነት ግልጽነትና ተጠያቂነት አሠራር የማስፈን ተግባርን ከዞን ዳኞች አስተዳደር ጉባኤዎች ጋር

በመቀናጀትና የንዑስ ጉባዔዎችን ዉሳኔ የመስጠት አቅምን በማጎልበት የተጠናከረ ሥራ ይሠራል ።

**ፍትህን በግልጽ ችሎት የመስጠት መርህን ማጠናከር፡-**

ግልጽነት የተጠያቂነት መርህ አንዱ መገለጫ ሲሆን ይህ መርህ በፍርድ ቤቶች ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው ፍርድ ቤቶች በግልፅ ችሎት ማስቻል ነው። በመሆኑም ፍርድ ቤቶች ግልጽ ችሎቶች እንዲኖሩ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ግዴታ አለባቸው። በመሆኑ በቀጣዩ የዕቅድ ዓመታት ፍርድ ቤቶች አስፈላጊዉን ግብዓት በማሟላት በህግ በግልፅ ችሎት እንዳይታይ ከተከለከሉ ጉዳዮች ዉጭ ያሉትን በሙሉ በግልጽ ችሎት የዳኝነት አገልግሎት የመስጠቱ ሥራ ተጠናክሮ የሚሰጥ ይሆናል።

**ፍርድ ቤቶችን በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያ ማደራጀት፡-**

ፍትህ በችሎት በሚሰጥበት ጊዜ ህግን እና የሥነ ምግባር መርሆችን በተከተለ መንገድ መሆን ይገባዋል። ይህንን መከታተል የሚያስችል ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል። በመሆኑም በቀጣይ የዕቅድ አመታት በክልሉ ፍርድ ቤቶች ለዳኝነት ሥራ ቅልጥፍናና ግልጽነት የሚያግዙ አግልግሎቱን የተሟላና የተጠናከረ ማድረግ የሚያስችሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን የማሟላት ስራ ታቅዶ ተግባራዊ ይደረጋል።

**የይግባኝና የሰበር አቤቱታ ሥርዓት ማጠናከር፡-**

በፍርድ ቤቶች በሚሰጥ ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኝ የመጠየቅና አቤቱታውን ስልጣን ላለው ለበላይ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት አለው። የሰበር አቤቱታውንም ስልጣን ላለው ሰበር ችሎት በማቅረብ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ እንደሆነ እንዲታረም የሚያስችል የተዘረጋ የአሰራር ስርአት አለ። በመሆኑም በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች በቀጣዩ የዕቅድ ዓመታት የይግባኝ ቅሬታዎችና የሰበር አቤቱታዎች አፋጣኝ ምላሽ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲፈጠር ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል።

**የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፡-**

የፍርድ ሥራ ምርመራ ወይም የኢንስፔክሽን ሥራን መተግበር የዳኝነት ነጻነትና ተጠያቂነትን በማጐልበት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል። በተለይም የዳኞችን ከመዝገብ ሥራ ጋር በተያያዘ

ዋና ሕጎችን (substantive laws) እና የሥነ-ሥርዓት ህጎችን መሰረት በማድረግ በአግባቡ ክርክሮችን የመሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የፍ/ቤት ማሻሻያ ስርአት፣ የመረጃ ስርአት፣ የተጠያቂነትና ግልፅነትን ለማረጋገጥ የሚሰሩ ስራዎች ለመደገፍ፣ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል በባለሙያ የተደራጀ የክትትልና ግምገማ ስራ የሚሰራ ይሆናል፡፡

**በፍርድ ቤቶች ለተገልጋይ ምቹ የችሎት ሥፍራን ማዘጋጀት፡-**

በፍርድ ቤቶች የማስቻያ ሥፍራዎችን ወይም ችሎቶችን ለማደራጀት በተደረገዉ ጥረት በአንዳንድ ፍርድ ቤቶች ውጤት የተገኘበት ቢሆንም አሁንም በአብዛኞቹ ፍርድ ቤቶች ለተገልጋዮች ምቹ የማስቻያ ሥፍራ ያልተዘጋጀላቸው ሲሆን የተዘጋጀላቸውም ቢሆን የአካል ጉዳተኞችንና አረጋዊያንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ምቹ የችሎት ስፍራን ከማዘጋጀት አንፃር ውስንነት ይታያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የባለጉዳይ ማረፊያ፣ የመረጃ ክፍል እና ሌሎች አቅጣጫ ጠቋሚ ፅሑፎች ያልተሟላላቸዉ ስለሆነ ከላይ በዝርዝር የተመለከቱትን ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን በቀጣይ የመሪ ዕቅድ ዓመታት በትኩረት ይሠራል፡፡

**የርቀት ሙግት ሥርዓት (E- litigation) ማጠናከር፡-**

የርቀት ሙግት (E- litigation) ቴክኖሎጂ ከሳሽ ባለበት ሆኖ ኢንተርኔት በመጠቀም ክስ የሚመሠረትበት፣ ማስረጃ የሚያቀርብበት፣ ከፍርድ ቤትም ጋር አስፈላጊውን ግንኙነት የሚያደርግበት በቴክኖሎጂው አማካይነት የሚከናወንበት አሠራር ነው፡፡

**የምድብና የተዘዋዋሪ ችሎቶችን ማጠናከር፡-**

በክልሉ በየደረጃው በተቋቋሙ ፍርድ ቤቶች ምድብ ችሎቶችን እና የተዘዋዋሪ ችሎቶችን በማደራጀት የባለጉዳዮችን ጊዜ ገንዘብና ጉልበት ብክነት ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ሲሆን የተገልጋይ ተጠቃሚነትን ለማሳደግም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ስለሆነም የክልሉ ፍርድ ቤቶች ተዘዋዋሪና ምድብ ችሎቶች የመዛግብት የመቀበል አቅምን 38,694 መዛግብት በየአመቱ በ5% እያደገ እንድሄድ በማድረግ ወደ 49,573 መዛግብት ለማድረስ ታቅዷል፡፡

**አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓትን ማመቻቸት፡-**

በ2014 ዓ/ም አፈፃፀሙ 25,846 መዛግብትን በአማራጭ ሙግት ስርዓት ለመጨረስ ግብ ተጥሎ 19,160 ወይም 74.13% መድረሱ ሪፖርቱ ያመላክታል፡፡ በመሆኑም 74%ን በመነሻነት በመውሰድ ዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (25,748) 99.62% ለመድረስ በዕቅድ ተይዟል፡፡

**በክልሉ ፍርድ ቤቶች የቋንቋ ትርጉም ክፍል ማደራጀት፡-**

የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ፍርድ ቤቶች ተገልጋዩ በሚናገረውና በሚሰማው ቋንቋ የመዳኘት መብቱን ሊያከብሩለት ይገባል፡፡ በዚህም መሠረት በሚቀጥለው የልማት ዕቅዱ አመታት በክልሉ ውስጥ ባሉ ፍርድ ቤቶች እንደ አስፈላጊነቱ የቋንቋ አስተርጓሚና የዉሳኔ ትርጉም ስራ በሰው ኃይልና በማቴሪያል ተደራጅቶ እንዲዋቀር ይደረጋል፡፡

**የክልሉ ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ተደራሽነት፡-**

በ2014 ዓ.ም ከቀረቡት 4,841 ጉዳዮች 4,653 ወይም 96.6% መዛግብት መወሰን የተቻለ በመሆኑ ይህንን በሚቀጥሉት ዓመታት እንደመነሻ በመዉሰድ በየዓመቱ የመወሰን አቅማቸውን በ0.5% በማሳደግ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 7,219 መዛግብት እንዲወሰኑ ታቅዷል፡፡ 119251.3

**የፍርድ ቤቶችን አሳታፊነት ማሳደግ፡-**

በሀገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማጠናከር፣ መልካም አስተዳደርን ለማጐልበት፣ ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈንና የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሁሉንም ኅብረተሰብ የተቀናጀ ተሣትፎ ይጠይቃል፡፡ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለው፣ ተደራሽ፣ ወጭ ቆጣቢና ተገማች እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ከዕቅድ ዝግጅቱ ጀምሮ እስከ አፈጻጸም ግምገማ ድረስ የኅብረተሰቡ ተሳትፎ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው፡፡ በዚህ መሠረት በሚቀጥሉት የዕቅድ ዓመታት በሁሉም ፍርድ ቤቶች በህዝብ ክንፍ አደረጃጀት ማኑዋል ላይ በተቀመጠዉ መሰረት በየሩብ ዓመቱ ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ እስከ አፈፃፀም ምዘና ድረስ ባለዉ ሂደት ባለድርሻ አካላትንና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ የህብረተሰቡን ተሳትፎ የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡

**የፍርድ ቤቶችን የሥራ እንቅስቃሴ ለኅብረተሰቡ በየጊዜው ማሳወቅ፡-**

ፍርድ ቤቶች ሊሠሩ ስላቀዷቸው ሥራዎች ስለአፈፃፀማቸውና ስለ አሰራራቸው ወቅታዊ መረጃዎችን ለኅብረተሰቡ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም የዜጐች መረጃ የማግኘት መብትን የሚያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ በፍርድ ቤቶች የገጽታ ግንባታ ላይም ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት የዕቅድ ዓመታት በየደረጀው ያሉ ፍርድ ቤቶች የተለያዩ የህተመትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች/ በማህበራዊ ድረ ገፅ፣ በደቡብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ዜጐች ቻርተር፣ ዕቅድ እና አፈጻጸም ለህብረተሰቡ የማሳወቅ ሥራ አጠናክረው እንዲሠሩ ይደረጋል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ግቦችን ለማሳካት የታቀዱ ዋና ዋና ግቦች**

በዕቅዱ አተገባበር ረገድ የሁሉም የስራ ድርሻና ኃላፊነቶች በግልጽ መለየታቸዉን ማረጋገጥ፤ ለስራዉ አግባብንት ያለዉ የሰዉ ኃይል፤ የፋይናንስና ሌሎች ግብዓቶች በበቂ ሁኔታ መመደባቸዉን በማረጋገጥ፤ የእቅዱ ተግባራዊነት ከጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ጀምሮ በየደረጃዉ ባሉ የፍርድቤቶች ፕሬዝዳንቶች ጥብቅ ክትትልና ኃላፊነት ይመራል፡፡ የዋና ስራሂደቶችን ዳሬክቶሬቶች የዕቅዱን የዕለት ተዕለት አተገባበር የማስተባበር የማቀድ፤ የመከታተል፤ የመገምገም፤ አቅም እንዲገነባ የማድርገና ዕቅዱን ለመፈጸም የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋሉ፡፡ ዕቅዱ ወደ እያንዳንዱ በየደረጃዉ ወዳሉ ፍርድ ቤቶችና ወደ ፈጻሚዎች እንዲወርድ ይደረጋል፡፡ የዕለት ተዕለት ተግባራቸዉንም ከዕቅዱ ጋር በማስተሳሰር ይተገብራሉ፡፡

## 6.3. የዴሞክራሲ ሥርአት ግንባታ

### 6.3.1. የክልል ምክር ቤት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት ክልል ምክር ቤት የትኩረት አቅጣጫዎች፤**

በክልሉ ምክር ቤት የህግ አወጣጥ ሂደት ጥራትና ብቃት ማሳደግ፣ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር፣ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም መገንባት እና የህዝብ ግንኙነትና የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ማጠናከር እንደ ትኩረት አቅጣጫ ተወስደዋል፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት ክልል ምክር ቤት ዓላማዎች፤**

የምክር ቤቱ የቀጣይ አስር ዓመታት ዕቅድ ዋና ዓላማ ባለፉት አስር ዓመታት እንደ ምክር ቤት ታቅደው የተፈፀሙ የህግ ማውጣት፣ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች እና የውክልና ተግባራት በማጠናከር፣ የአባላቱን በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሊኖራቸው የሚገባውን

ዋነኛ ተልኮ ሊያሳኩ እንዲችሉ ተቋማዊ አደረጃጀቱን በማጎልበት እንደ ክልልም ሆነ እንደ ሀገር የተያዙ የልማት ዕቅድ በማሳካት የህዝቡን የዴሞክራሲ፣ የልማትና መልካም አስተዳደር ተጠቃሚነት እና የስልጣን ባለቤትነት ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሸጋገር ማድረግ ነው፡፡

**የቀጣይ አስር ዓመታት ክልል ምክር ቤት ዓላማዎችን ለማሳካት የታቀዱ ዋና ዋና ግቦች፤**

በየደረጃው ያሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤቶችን ሕግ የማውጣትና የመቆጣጠር አቅምን ማሳደግ፣ በህገ መንግስቱ መሠረት የም/ቤቱ መደበኛና እንደ የአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ጉባኤዎች 100% ወቅቱን ጠብቀው ማካሄድ፣ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት በግልጸኝነትና በተጠያቂነት መርህ መሥራታቸውን ማረጋገጥ፣ ሕግ አውጪው እና ሕግ አስፈጻሚው በክልሉ በሕገ መንግስትና ሕጎች መሠረት በግልጽ የስልጣን ክፍፍል መሥራት የሚያስችላቸው ቁመና ለመፍጠር ይሰራል፡፡

የህዝብ ተሳትፎን በማጠናከር፣ የስልጣን ባለቤትነት የማረጋገጥ እና የአሠራር ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና ውጤታማነት የሠፈነበት የመንግስት አሠራርና መልካም አስተዳደርን ማጠናከር፣ የተደነገጉ የሰብዓዊ መብቶች እና ጥቅሞች በአስፈፃሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ የሕግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ ጥራት፣ ቅልጥፍና እና ግልጽነት ያለው የመንግስት አስተዳደር እንዲሰፍን ለማድረግ ይሰራል፡፡ እንድሁም ለዜጎች ሁሉን አቀፍ እና ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ለማከናወን ታቅዷል፡፡ ለሙስና ወንጀል የሚያጋልጡ አሠራሮችንና የሕግ ክፍተቶችን በመለየት የመንግስትም ይሁን የግል ተቋማት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡ የምክር ቤቶች የጋራ ምክክር መድረኮችን አጠናክሮ በማስቀጠል በክልልና በየደረጃው ባሉ ምክር ቤቶች ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ምክክር ለማካሄድ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

በየደረጃው የሚገኙ ምክር ቤቶች የሚያከናወኗቸው ተግባራት በሚዲያ እንዲታጀቡና የምክር ቤት መረጃዎች በአግባቡ ለማደራጀት፣ የሴት ተመራጮች ኮከስ አደረጃጀትን በማጠናከርና የአባላቱን አቅም በማሳደግ በፖለቲካ፣ በልማትና በመልካም አስተዳደር ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሰራል፡፡

### 6.3.2. *መንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች*

**የቀጣይ አስር ዓመታት የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች የትኩረት አቅጣጫዎች፣**

የመንግስት ኮሚዩኒኬሽንና ሚዲያ ግንኙነት ማጠናከርና መዘርጋት፤ የሚዲያ ሞኒተሪንግና ጥናት ምርምር ማድረግ፤ እንዲሁም የዘመነ የመረጃ አስተዳደር የማልማትና በመረጃ የረካ ተገልጋይ መፍጠር የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡

**የቀጣይ አስር ዓመታት የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዓላማ፡-**

በክልላዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የህብረተሰቡን ሁለ ንተናዊ ተሳትፎ የሚያነሳሳ፣ የሚያጎለብትና ተጠቃሚ የሚያደርግ የኮሚዩኒኬሽን ስርአት በማጎልበት ተአማኒና ጥራቱን የጠበቀ መረጃ በማድረስ የሚዲያ ሞኒተሪንግና የህዝብ አመለካከት ጥናት ስራዎችን በማከናወን እንዲሁም የመንግስት መረጃ ማዕከልና ዲጂታል ሚዲያዎችን በማልማት በመረጃ የበለጸገ ህብረተሰብ መፍጠር እና የክልሉን ገጽታ መገንባት ነው።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ዓላማዎች ለማሳካት የታቀዱ ዋና ዋና ግቦች**

የመንግሥት ኢንፎርሜሽን አገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናን ማሻሻል፤ በኮሙኑኬሽን የአሰራሮች፤ የግንኙነት ብቃትና ዉጤታነትን ማሳደግ፤ ወቅታዊ መረጃን ለመድረስ ዜና፤ ፕሮግራም፤ ዶክመንተሪ፤ የአቋም መግለጫ አዘጋጅቶ ማስተላፍና ተደራሽ ማድረግ፤ የሚዲያ ሞኒተሪንግ ተደራሽነትን ማሳደግ፤ የሕዝብ አስተያየት ጥናትና ምርምር አገለግሎት ተደራሽነት ማሳደግ፤ የቤተመፅሐፍትና ዶክመንተንሽ ሚዲያ አገለግሎት አሰጣጥ ተደራሽነትን ማሳደግ፤ የዳታ ቤዝ አድሚንስቴር አገለግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ፤ የዌብሳይት አስ/ርና ማህበራዊ ሚዲያ አሰጣጥ ተደራሽነትን ማሳደግ፤ ለህትመትና ማስታወቂያ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የመስጠት አገለግሎት ማሳደግ፤ መረጃ አደረጃት ሥርዓትና አጠቃቀምን ማሻሻል፤

**የቀጣይ አስር ዓመታት የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ግቦችን ለማሳካት የተለዩ የማስፈጸሚያ ስልቶች፤**

የሚዲያና ኮሚዩኒኬሽን ስትራቴካዊ አጋነትናትና ግንኙነት አሰራር መመሪያ፤ የሴክተር መስሪያ ቤት ከሚዩኒክሽን ግንኙነት መመሪያ፤ የመረጃ ነጻነት አዋጅ፤ የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ፤ የህዝብ አስተያየት ጥናት አሰራር መመሪያ፤ የኢዲቶሪል ፖሊሲ፤ የሚዲያ ሞኒቶሪንግ አሰራር ማንዋል፤ የመንግስት መረጃ እና ዲጅታል ሚዲያ ልማት አስተዳደር መመሪያ፤ የቤተ-መዛግብትና ቤተ-መጻህፍት አሰራር መመሪያ፤ የዳታ ቤዝ አሰራር መመሪያ መጠቀም የማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው።

### 6.3.3. ሥነ- ምግባርና ጸረ-ሙስና

**የቀጣይ አሥር ዓመታትሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የትኩረት አቅጣጫዎች**

የተቋም አቅም ግንባታ፣ የስነምግባር ግንባታ፣ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ጥናት እና የሙስና መረጃ አስተዳደርና አገልግሎት የእቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

**የቀጣይ አሥር ዓመታት ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓላማዎች**

የዚህ ስትራቴጅክ ዕቅድ ዓላማ የኮሚሽኑን ስትራቴጂያዊ ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችንና ስትራቴጅያዊ ጉዳዮችን አንጥሮ በማውጣት ኮሚሽኑ በቀጣይ ስምንት ዓመታት የሚመራበትን ዕቅድ በማዘጋጀትና ከፈፃሚዎች ጋር በማስተሳሰር ኮሚሽኑ የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት በላቀ ደረጃ እንዲወጣ ማስቻል ነው፡፡

**የቀጣይ አሥር ዓመታት ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል**

የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ተልዕኮ ለመወጣት አሠራር ሥርዓት፤ ስትራቴጂና አደረጃጀት በተከታታይ ማሻሻልና ብቃት ማረጋገጥ፤ በሥነምግባር የታነጹ፣ ሙስናን የሚጠየፉና በጽናት የሚታገሉ አመራሮች፤ ሰራተኞችና ዜጎች እንዲበራከቱ በትብብር መሥራት፤ በመንግሥት ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሠራር በዘላቂነት እንዲቀንስ፤የአሠራር ሥርዓት ግልጽነትና ተጠያቂነት መከታተልና ማረጋገጥ፤ የሙስናና ብልሹ አሠራር ተግባራትን መረጃና ማሰረጃ በማደራጀት፤ የሕዝብና መንግሥት ሀብት ከብክነት ለማዳን ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መሥራት እና የሚመጡ የሙስና መረጃ ጥቆማዎች የቅበላ ሥርዓትን በማዘመን መረጃዎችን መቀበል፣ መተንተን ለሚመለከተው አካል ምክረ ሀሳብ ጋር ማስተላለፍና ውጤቱን መከታተል፣

**የቀጣይ አሥር ዓመታት ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የተለዩ የማስፈጸሚያ ሥልቶች**

የስነምግባር ግንባታ ፣ ስልጠናና ስርፀት፤ የሥነ-ምግባር አውታሮች ማስተባበር፤ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ጥናት፤የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ፣ የሀብት መረጃ ትክክለኛነት እና የመረጃ ተደራሽነት ማረጋገጥ፤

# ምዕራፍ ሰባት

# 7 የሰላም ግንባታ እና ቀጠናዊ የጋራ ልማት ዕቅድ

## 7.1. የሰላም ግንባታ ዘርፍ ልማት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠላምና ፀጥታ ዘርፍ የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይቷል**

የግጭትና የፀጥታ መረጃ ሥርዓት ግንባታ በማጠናከር ግጭትን አስቀድሞ መከላከል፣ የሰላም፣ የብዝሀነት፣ የአብሮነትና የመከባበር እሴትን መገንባት፤ በክልሉ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን በዘላቂነት መፍታትና የህግ የበላይነትን ማስከበር፤ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓትን ዉጤታማ ማድረግ፤ የሚሊሻ ሀይል ምልመላና አቅም ግንባታ አቅሙ የጎለበተና ውጤታማ የሚሊሻ ሀይል ማደራጀት

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠላምና ፀጥታ ዘርፍ ዓላማዎች እንደሚከተለው ተለይቷል፥**

የክልሉን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ የግብዓት ችግሮችን በማሟላት፣ የፈፃሚ አካላትን የሥራ ተነሳሽነት እንዲጎለብት በማድረግና በክልሉ ዘላቂ ሰላምና መልካም አስተዳደር በማስፈን፤ የተጀመረዉን ሀገራዊ የለውጥ እንቅስቃሴ በማስቀጠል፣ የህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት የተረጋገጠ እንዲሆን ማድረግ

**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠላምና ፀጥታ ዘርፍ ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል፥**

የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ መረጃ በየቀኑ ለሚመለከተው አካል እንዲደርስ በማድረግ ሊከሰቱ የሚችሉ የሃይል ግጭቶችን የተለያዩ የፈጣን ምላሽ መስጫ ስልቶችንና ዘዴዎችን በመጠቀም 90 በመቶ የፀጥታ ችግሮችን አስቀድሞ መከላከል በተጨማሪም ለክልሉ ፀጥታ ስጋት በሆኑ ጉዳዮች መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ጥቅም ለይ በማዋል የፀጥታ ስጋትን ለመቀነስ ይሰራል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ በሰላም እሴት ግንባታ፣ ሀይማኖት ነክ የፀጥታ ችግሮች እንዲቀንሱና የብዝሀነት የአብሮነት እሴት እንዲገነባ በማድረግ ዙሪያ ለ32,145,660 የህብረተሰብ ክፍሎችና ለ2,024,253 ባለድርሻ አካላትና ተባባሪ ወገኖች በመቀናጀት የማህበረሰብ ተኮር ዉይይት በማካሄድ የህብረተሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡ በዚህም በየዓመቱ ለ868 የሰላም ኮሚቴ፣ ለ1148 የሰላም ክበባትና ለ26 የሰላም ፎረም አደረጃጀቶችን ማቋቋምና ዉጤታማ የሚሆኑበት ስልት ተቀይሶ በስልጠና በግብዓት በማጠናከር ወደ ተግባር እንዲገቡ በማድረግ ህብረተሰቡ በሰላም ባህል ግንባታው ተሳትፎው እንዲያድግና የህዝብ

ለህዝብ ትስስሩና አንድነቱ የተጠናከረ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል። በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች የሰላም አቅሞች ላይ 8 መሰረታዊ ጥናት በማካሄድ እንዲጎለብቱ ለማስቻል ክልላዊ የሰላም አቅምን ለማጠናከር ይሰራል።

ሀይማኖት ነክ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ያለመግባባቶችንና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢና ወቅታዊ ምላሽ እንዲያገኙ የማድረግ፣ ህግንና ደንብን ያልተከተሉ የአምልኮ ስርዓት አካሄዶች በህግ አግባብ እንዲመሩ አቅጣጫ የማስያዝ እና በክልሉ እየተስተዋሉ የሚገኙ ሃይማኖት ነክ አለመግባባቶች፣ ግጭቶችና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በሚመለከት 10 ጥናቶች ማካሄድ ከአጎራባች ክልሎች ጋር 30 የጋራ ፎረም በማዘጋጀት ሠላምን ማረጋገጥ እና በአጎራባች ዞኖች መካከል 120 ጊዜ ሰላም ወይይቶች በክልሉ በተለያዩ አከባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶችን ህብረተሰቡንና ባለድርሻ አከላትን በማሳተፍ ማስተዳደርና መፍታት፤
የምዝገባ መረጃ አሰባሰብ እና አጠቃቀም ዉጤታማነትን በማጠናከር የኩነት መረጃ ጥራትን 100% እና ተተንትኖ ለአገልግሎት የዋለ መረጃ 100% የማድረስ ሥራ ይሰራል።
**የቀጣይ አሥር ዓመታት የሠላምና ፀጥታ ዘርፍ ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተቀምጠዋል**

ብዝሀነትንና ክልላዊ እንድነትን የሚያጎለብቱ የሰላም ግንባታ ፕሮጀክት፣ በግጭት የተጎዱ አካባቢዎች በዘላቂነት ማቋቋሚያ ፕሮጀክት፤ የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ፈጣን ምላሽ ስርዓት መረጃ ስርዓት (CEWRR & date bese System) የማዘመንና ግብዓት የማሟላት ፕሮጀክት፣ የቢሮ ዌብ ሳት አፕሎድ ሲስተም ልማት ፕሮጀክት፣ በክልሉ የግጭት መንስኤ ጥናት እና ዘላቂ መፍትሄ ቀረጻ ፕሮጀክት፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የተቋማት ማዘመን ልማት ፕሮጀክት፣ የህግ ማስከበር ልማት ፕሮጀክት፣ የአጎራባች አካባቢዎች እና የአካባቢ አስተዳደር አካላት ትብብርና ማዕቀፍ ፕሮጀክት፣ ዘመናዊ የሰው ሃብት አስተዳደር እና ዶክመንት ማኔጀመንት ሲስተም /ICMIS/፤ አካባቢያዊ የሰላም አቅሞችን የመለየትና የማበልጸግ ፕሮጀክት፤ የሰላም ትምህርቶችን ተደራሽነት ማስፈፀሚያ ፕሮጀክት፤ የወሳኝ ኩነት መረጃ ምዝገባ ተክኖሎጂ ማዘመኛና አቅም ግንባታ ፕሮጀክቶች የመንግስት የዉስጥ አቅም ጋር በማቀናጀት ይሰራል።

# ምዕራፍ ስምንት

# 8 የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዕቅድ

## 8.1. የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዕቅድ

### አካባቢ ጥበቃ የትኩረት አቅጣጫዎች

የቀጣይ አሥር ዓመታት የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ዕውን ለማድረግ የክልላችንን የአካባቢ፣ የደን፣ የዱር እንስሳትና ሌሎች የብዝሃ ሕይወት ሀብትን በማልማት፣ በማንበር፣ በመጠበቅና ዘላቂ አጠቃቀምን በማስፈን እንዲሁም ጤናማ የሥርዓተ ምህዳር መስተጋብርን በማሳደግ ዘላቂ ክልላዊና ሀገራዊ ልማትና ዕድገት እንዲረጋገጥ ማድረግ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

### አካባቢ ጥበቃ ዓላማዎች

የቀጣይ አስር ዓመታት የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ልማት ዓላማዎች የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን መዘርጋት፣ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የመጤ ወራሪ ዝርያዎችን የመለየትና እያደረሱ ያሉትን ጉዳት በጥናትና ምርምር በመታገዝ በቅደም ተከተል መቅረፍ፣ የተለያዩ የብዝሀ ሕይወት ዝርያዎችን በመሰብሰብ የጀኔቲክ ሀብትን ማንበር፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት በክልሉ የልማት ዕቅድ ውስጥ እንዲካተትና እንዲተገበር በማድረግ ከዘርፎች የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት መጠን መቀነስና የደን፣ የብዝሀ ህይወትና የዱር እንስሳት ሀብት ልማትና ጥበቃን ማጠናከር የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

### አካባቢ ጥበቃ ዋና ዋና ግቦች

በተቋሙ ስር ባሉት ዘርፎች 30 የተለያዩ አዳዲስና ነባር ካፒታል ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ከክልል መንግስት 794,544,496 ብር እንዲሁም 10 የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች (NGO) 320,000,000 ሚሊዬን የገንዘብ ሀብት ማሳደግ። የአከባቢ ጥበቃ ህጎች ተግባራዊ ያደረጉ ተቋማት ብዛት በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን መጨረሻ 1,216 ማድረስ።

ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ትግበራ የሚረዱ 40 ሰነዶችን ማዘጋጀትና 8 ምርጥ ተሞክሮ መቀመር፣ ክልላዊ የደን ሽፋን አሁን ከነበረበት ከ41.17% በመነሳት 7.76% በማሳደግ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ወደ 48.93% ማሳደግ፣ ለ1,187,200 በደን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ህጎች በየደረጃው ባለ አመራር፣ ባለሙያና

ህብረተሰብ በቂ ግንዛቤ እንዲያገዝ በማድረግ የህግ ተከባሪነት ስርዓትን ማረጋገጥ፣ በደን ልማትና ጥበቃ በሚከናወኑ ተግባራት ወንድ 68566 ሴት 29386 በድምሩ ለ97,952 ወጣቶች፣ ሴቶችና ገቢያቸው አነስተኛ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፡፡

የእንጨት ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም ፍላጎትና አቅርቦት እንዲሁም የሚኖራቸው የሥራ ዕድል አቅም ጥናት በማካሄድ የደን ልማት ለክልላዊና አገራዊ ኤኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ ማሳደግ፣ 9404.8 ሄ/ር ሰው ሰራሽ ደን፣ 558,490.1 ሄ/ር አሳታፊ የተፈጥሮ ደን በመከለል እንዲሁም 62,286.4 ሄ/ር የተመናመኑ ደኖች መልሰው እንዲያገግሙ ማድረግና ካርታ ማዘጋጀት፤

**የብዝሃ ህይወት ሃብቶች ጥበቃን በተመለከተ**

የተመናመኑ እና በመጥፋት ላይ ያሉ 32 ነባር ሰብል ዝርያዎች ከጅን ባንክ በማምጣት፣ 3 የዱር እንስሳት ዝርያ መልሶ በማበልፀግ ከሀብቱ የሚገኘውን ጥቅም ማጎልበት፤ የሰብል ዝርያዎች ማባዣ የሚሆን 6 ቦታዎችን በመምረጥና በማዘጋጀት፣ በአርሶ አደሮች የተመናመኑ/የጠፉ 15 ዓይነት ዝሪያዎችን በመለየት 360 ኩ/ል የነባር ሰብል ዝርያዎችን የመጠበቅ የማህበረሰብ ዕውቀቶችን በዘቦታና ኢዘቦታ የማንበር ሽፋን ማሳደግ፤ በተራቆቱ 15,248 ሄ/ር የውሃ ዳርቻዎችና በ7,248 ሄ/ር በተከለሉ የእጽዋት ፓርኮች መከለል፣ መትከልና እንክብካቤ በማድረግ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት መቀነስ፣ በ41 ወረዳዎች ውስጥ ያሉ የብዝሀ ሕይወት ሀብቶችና 11 የማህበረሰብ ዕውቀቶችን በመመዝገብ የመረጃና ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ሽግግርን ማሳደግ፣

**አካባቢ ጥበቃ የልማት ዕቅዱን የማስፈፀሚያ ስልቶች**

በአንደኛና በሁለተኛው የዕትዕ ዘመን በተቋሙ በሁሉም ደረጃ በዘርፉ የተያዙ ግቦችን ስኬታማ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀቶችን እስከ ወረዳ የመፍጠር የፋይናንስ አቅርቦትን የማጠናከር ስራዎች ለማከናወን ተችሏል፡፡ ስለዚህ በቀጣዩ የ8 ዓመታት እቅድ የተያዙ ተግባራትን ከዚህ በተሻለ መልኩ ለመስራት አዳዲስ ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፍችን ማዘጋጀት፣ የሰው ኃይል አቅም ማጎልበት፣ የፋይናንስ እና የቴክኖሎጂ አቅርቦትን በተሻለ ሁኔታ ማሳደግ፤ በተጨማሪም የባለድርሻ አካላት እና የልማት አጋሮቻችን አስተዋጽኦ በማሳደግ ዋና ዋና ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ፱የካፒታል ፕሮጀክቶች እና የስታትስቲክስና የመልከአ ምድራዊ መረጃ አስተዳደር

## 9.1. ካፒታል ፕሮጀክቶች አስተዳደር

**በክልሉ የሚተገበሩ የካፒታል ፕሮጀክቶች ከትግበራ በፊት የፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት ማካሄድ**

በክልላችን በአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በየዓመቱ በአዲስ መልክ የሚዘጋጁ የካፒታል ፕሮጀክቶችን ፍትሃዊ ስርጭት በጠበቀ መልኩ የአዋጭነት ጥናት በማካሄድ አዋጭ ተብሎ የተለዩ ፕሮጀክቶችን የማክሮ ኢኮኖሚው ሁኔታ እና ሌሎች ጉዳዮችን ባማከለ መልኩ ፕሮጀክትን በመምረጥና ቅደም-ተከተል በማስያዝ በበጀት ላይ እንዲተከል ምክረ ሀሳብ ይቀርባል፤ የፕሮጀክቶች ምልመላና መረጣ መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

**ፍትሃዊ ስርጭቱን እና አፈፃፀም ግምገማ በማድረግ ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥ**

እንዲሁም ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የካፒታል ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ከባለ ድርሻ አከላት ጋር በመቀናጀት ወቅታዊ የሆነ የመሠረተ ልማት ክትትልና ግምገማ በማካሄድ የአፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት አስፈጻሚ አካለት በሚገኙበት መድረክ በክልል ከፍተኛ አመራሮች እንዲገመገም በማድረግ በጥንካሬ የተለዩ ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑና በድክመት የተለዩትን ማነቆዎችን በመቅረፍ አፈጻጸማቸውን ማሻሻል እንዲችሉና የተጀመሩ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሠሌዳ እንዲጠናቀቁና ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ፈጣን አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ የፕሮጀክት ግቦች እንዲሳኩ ትኩረት በመስጠት ይሠራል፡፡

### 9.2. የስታትስቲክስና የመልከአ ምድራዊ መረጃ አስተዳደር

የክልሉ ስታቲስቲካዊ መረጃ አቅርቦት በጥራት፤ በግዜ እና በመጠን የተሟላ በማድረግ የተገልጋይ ፍላጎትና እርካታ 100% ለማረጋገጥ፤ አስተዳደራዊ መረጃዎችን በሁሉም መዋቅሮች በተሟላ ሁኔታ በተገልጋይ ፍላጎት መሰረት የሚቀርብበት ሁኔታ 100% ተግባራዊ ማድረግ፣ ዓመታዊ አብስትራክቶች በልዩ ልዩ ርዕሶች የተዘጋጁ የትንተና ዶክመንቶች በበቂ ኮፒ ተዘጋጅቶ ለተገልጋይ በየዓመቱ /8 ጊዜ/ እንዲቀርብ እና የተገልጋይ የመረጃ ፍላጎት ቅድመ ዳሳሳ 2 /ሁለት/ ጥናቶች የማድረግ ስራ ይከናወናል

በክልሉ አስተዳደራዊ ስታቲስትካል መረጃ አመንጭ ተቋማት የመረጃ አስተዳደር ሂደትና ሥርዓትን ሙሉ በሙሉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ታግዞ የመረጃ ጥራት ችግር በወሳኝ መልኩ 95 በመቶና በላይ በመፍታት ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ፤በየዓመቱ የሁሉም የክልል ሴክተር መ/ቤቶች መረጃ ክፍሎች የተጠናከረ አቅም እንዲኖራቸው ስርዓት ይዘረጋል፣ እያንዳንዱ ሴክተር ከክልሉ ማዕከላዊ መረጃ ክፍል ጋር እንዲቀናጅ ይደረጋል፣ የስታቲስቲካል መረጃ

ቁጥጥርና የማረጋገጥ አገልግሎት 100% ተግባራዊ ይደረጋል፣አንድ አስተዳደራዊ መረጃ መሰብሰቢያ መጠይቆች ስታንደርድ ተጠብቆ ከምንጩ ተሞልቶ ለማመሳከሪያ እስከ ክልል ማዕከላዊ መረጃ ክፍል የሚደርስበት ሁኔታ ይመቻቻል ለሁሉም ሴክተሮች መረጃ መሰብሰብያ ፎርማቶችን በወጥነት የታተሙ እንዲሆኑ እና የሁሉም ሴክተር ስታቲስቲካል እንዲኬተር (Statistical Indicator) በተሟላ መንገድ እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡

የክልሉ ስታቲስቲካል ሲስተም (Regional statistical system) የሚመራባቸው የሕግ ማዕቀፎች፤ የአሰራር ሥርዓቶችን መዘርጋትና የተዛቡና ትክክለኛነታቸው ያልተረጋገጡ መረጃዎችን በሚያቅርቡ አካላት የተጠያቂነት አሰራርን ማስፈን እንዲሁም የተቋማዊ ብቃት ደረጃዎች በማጠናከር ለሀገራዊው ስታቲስቲካል ሲስተም ሞዴል እንዲሆን ማስቻል፤

የሁሉም ዓይነት መረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ እንዲሆኑ በማድረግ እና ለዚህም የሚሆኑ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን ሙሉ በሙሉ እንድሟሉ በማድረግ የመረጃ አሰባሰብ ዘደውን ማዘመን፤

ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ግብዓት በማሟላትና በመጠቀም የገፀ-ምድርና ከርሰ-ምድር መረጃዎችን በማሰባሰብ፤ በማደራጀት እንዲሁም በዘመናዊ ጂኦ-ዳታ ቤዝ በማከማቸት፤ በመተንተንና በተለያዩ ሰነድ ዓይነቶች (በካርታ፤ በአትላስ፤ በቡክሌትና ወዘተ) ለተጠቃሚዎች በማቅረብ የተጠቃምዎችን እርካታ 100 በመቶ ማድረስ፤ የክልሉ ማዕከላዊ መረጃ ክፍል (Regional data center) የመረጃ መረብ ደህንነት ተጠብቆ የማከማቸትና የማሰራጨት አቅም ሀገር አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ እንዲቋቋም በማድረግ የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን ማሻሻል፤ ክልላዊ ስታቲስቲካል ሲስተም ሪፎርም ፕሮግራም፣ በማጥናት፣ ዕቅድ በማዘጋጀትና የትግበራ ሥርዓቱን በመከታተል ውጤታማነቱን ማረጋገጥ እና የመረጃ ቁጥጥር በማረጋገጥ አገልግሎትን መጨመር፤

# ክፍል አራት

# የልማት ዕቅዱ አፈፃፀም ሂደት እና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

# ምዕራፍ አንድ

## 1. የልማት ዕቅዱ መነሻ አቅሞች

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 የልማት ዕቅዱ መነሻ አቅሞች

ዘላቂ ልማትና ብልጽግናን ማረጋገጥ የሚቻለው ውስን ሀብቶችና አቅሞችን በአግባቡ አስተባብሮና አሰናስኖ በመጠቀም አዳጊ፣ ተለዋዋጭና እየሰፉ የሚሄዱ በርካታ ፍላጎቶችን በቅድመ ተከተል በማሟላት ብቻ ነው። ስለዚህ የልማት ዕቅዱ ሲካሄድ በአጠቃላይ ያሉትን የሀብት አይነቶችና አቅሞች አሟጥጦ መጠቀምና በሂደት የአቅሞቹን አድማስ እያሰፉ መሄድ ጠቃሚ ይሆናል። እነዚህም እንደሚከተለው ተዳሰዋል።

**የተፈጥሮ ሀብት፦** በገጸ ምድርና በከርሰ ምድር የሚገኙ እንደ መሬት፣ ውኃ፣ ማዕድን፣ መልካም የአየር ንብረት፣ የብዝሃ ሕይወት እንዲሁም የንፋስና የፀሃይ ኃይል የመሳሰሉ መሠረታዊ የተፈጥሮ ጸጋዎችን ያካትታል። ክልላችን ባለዉ የሥነ ምድር አወቃቀር፣ የተለያየ ሥነ ምህዳርና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ምክንያት የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ያለዉ ሲሆን እነዚህም እንደሚከተለው ተዳስሰዋል።

**መሬት፦** ክልላችን ሰፊ የመሬት ሀብት ያለዉ ሲሆን ካላዉ አቅም ውስጥ እስካሁን ጥቅም ላይ የዋለው ትንሽ ነው። በተለይም መታረስ ከሚችለው መሬት ውስጥ የተጠቀምነው ዝቅተኛ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ። በዚህም በሚቀጥሉት ዓመታት ለግብርና ምርት እንዲሁም ለሌሎች የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ የልማት ፍላጎቶች መዋል የሚችል ሰፊ የመሬት ሀብት ታሳቢ ተደርጓል።

**ማዕድን፦** የተለያዩ የከበሩ፣ ብረትና ብረት ነክ፣ የኢንዱስትሪ፣ የግብርናና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች እንዲሁም ልዩ ልዩ የጌጣጌጥና የኢነርጂ ማዕድናት እንዳሉ ባለፉት ዓመታት በዘርፉ የተካሄዱ የሥነ ምድር ጥናቶች ያሳያሉ። በቀጣዮቹ አስር ዓመታትም ወርቅ፣ የከሰል ድንጋይ፣ የብረት፣ የፖታሽ፣ የእምነ በረድ እና ሌሎች ማዕድናት የማውጣትና የማልማት ሥራዎች ይከናወናሉ። በተለይም በወርቅ ሀብታችን ህጋዊ ግብይት ስርአት ይዞ እንዲካሄድ ይደረጋል።

**ውኃ፦** በውኃ ረገድ ያሉን ከሀይቆች፣ ከኩሬዎችና ክረምት ከበጋ ከሚፈሱ ወንዞች የምናገኘው የውኃ ሀብት ያለውን አቅም ከፍተኛ ነው። በመሆኑም በቀጣይ አስር ዓመት ይህንን አቅም ጥቅም ላይ ለመዋል ታሳቢ ተደርጓል።

**የተፈጥሮ መስህብ፦** የተፈጥሮ መስህብ ሀብቶች ማለትም ማራኪ የተፈጥሮ ገጽታዎች፣ ፏፏቴዎች፣ የተፈጥሮ ፓርኮች፣ የዱር እንስሳት፣ ደኖችና በውስጣቸው የሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳትና አእዋፋት ለቱሪዝም፣ ለትምህርትና ለምርምር ሥራዎች አቅሞች ናቸው።

**ቁሳዊ ሀብት፦** ቁሳዊ ሀብቶች በሰው ልጆች የተገነቡና ለተለያየ ጠቀሜታ ሊውሉ የሚችሉ ተንቀሳቃሽና ቋሚ ንብረቶችን ያጠቃልላል። የኢኮኖሚ ዕድገትን ተከትሎ የሚመጣው ከተሜነት ከፍተኛ የቁሳዊ

ሀብት ልማት ዝግጅትን የሚጠይቅ ሲሆን እስካሁን በኃይል፣ በመጠጥ ውኃ፣ በትራንስፖርትና መገናኛ፣ በመስኖ፣ በማምረቻ ፋብሪካዎች የተፈጠሩት አቅሞች ለቀጣይ ልማት መነሻ ይሆናሉ። ቀጣይ የልማት ግቦችን ለማሳካት ሰው ሠራሽ የቁሳዊ ሃብቶች አቅምን አሟጥጦ ከመጠቀም በተጨማሪ በተለይም የኃይል አቅርቦት፣ የአይሲቲ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የመስኖ፣ የመጠጥ ውኃ፣ የመንገድ፣ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ መሠረተ ልማቶችን በማጎልበት ረገድ ተጨማሪ አቅሞች የሚፈጠሩ ይሆናል።

**የኢነርጂ ሀብት፦** ክልላችን ከተለያዩ ምንጮች ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ሊውል የሚችል ከፍተኛ የሆነ እምቅ ሀብት ያለዉ ሲሆን፣ እስካሁን በሥራ ላይ የዋለው ግን አነስተኛው ክፍል ነው። የውኃና ታዳሽ ኢነርጂ ሃብትን በፍትሐዊነትና በዘላቂነት በማልማትና በማስተዳደር የዜጎችን የኃይል ፍላጎትና ሁለንተናዊ ሕይወት ማሻሻል፣ የኢነርጂ አቅርቦትና ተደራሽነትን በማረጋገጥ ለፈጣን ልማትና ዕድገት አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ይደረጋል።

**መስኖ፦** በአሁኑ ወቅት በመስኖ ሊለማ የሚችለው መሬት ከ---------- ሄክታር ሲሆን ከዚህ ውስጥ የለማው ---------- በመቶ ብቻ ነው። ከዚህ አንጻር በቀጣዩ አስር ዓመታት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል። በዚህም መሠረት የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮችን ጥናትና ዲዛይን ከ---------- ሄክታር ወደ ---------- ሄክታር ማሳደግ፤ የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮች ግንባታን ከ ---------- ሄክታር ወደ ---------- ሄክታር ለማድረስ ግብ ተጥሏል። ይህም ተግባራዊ የሚሆነው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ለይቶ መገንባትና ከዚህ በፊት የተጠኑና ወደ ሥራ ያልገቡ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን ገምግሞ ወደ ግንባታ ማስገባትና የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም ማሳደግ በቀጣይ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት ይሆናሉ።

**ትራንስፖርትና መገናኛ፦** በሀገር ደረጃ የተዘረጉ መንገዶች፣ የቴሌኮሙኒኬሽን አውታሮች በዕቅዱ ዘመን ለሚጠበቀው አጠቃላይ ዕድገት ብሎም የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ለማፋጠን የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው። የእነዚህ መሠረተ ልማቶች መስፋፋት ሎጂስቲክስን በማቀላጠፍ የሌሎች ዘርፎችን አፈጻጸም ያቀላጥፋል። ለምሳሌ ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ ልማቶች ለግብርና፣ ለኢንዱስትሪና ለሰርቪስ ሴክተር ልማት ለተያዙ ግቦች መሳካት እንደ ትልቅ መሠረተ ልማት ሆኖ ያገለግላል።

**ሰብዓዊ ሀብት፦** በክልል ደረጃ  አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት፣ በተለይም ከፍተኛ የወጣቶች ድርሻ፣ የትምህርት፣ የዕውቀትና የክህሎት ዝግጅት ደረጃ እንዲሁም ጤንነቱ የተጠበቀ ዜጋ ለዘላቂ ልማትና ብልጽግና መሳካት ቁልፍ ምንጮች ናቸው። በዚህ ረገድ የክልሉ ሕዝብ ብዛት በ2012 ከተገመተው 21 ሚሊዮን በ2022 ወደ ------ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል። በክልሉ እየተስተዋለ ያለው የሥነ ሕዝብ ሽግግር (demographic transition) በቀጣዮቹ የልማት ዓመታት እንደሚቀጥል ይገመታል። ይህ ወጣት የሠራተኛ ኃይል የዕድገት ምንጭነት አቅሙ ከፍተኛ ነው።

በአጠቃላይ የሰብዓዊ ሀብት መሻሻል በራሱ ለምርት ግብዓትነት ከመዋሉም በላይ የቴክኖሎጂ አቅሞችን አሟጥጦ ለመጠቀም ይረዳል። ሆኖም ይህ እንዲሳካ የሕዝብ ብዛት የዕድገት ምንጭ እንዲሁም ምርታማ እንዲሆን በትምህርት፣ በሥልጠናና በምርምር ዙርያ ከፍተኛ ሥራዎች መሥራትን ይጠይቃል። በዚህ ረገድ እስካሁን በትምህርት ዘርፍ የተገነቡ አቅሞች ሀገሪቷ ብሎም ክልላችን የተሻለ የሰብዓዊ ሀብቶች አቅም እየገነባች ስለመሆኑ አመላካች ነው። በአሁኑ ወቅት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በትምህርት ላይ የሚገኙ ሲሆን ከዚህም ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩት ከግልና ከመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን ጨርሰው ለሥራ ዝግጁ ይሆናሉ። የተያዘውን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ እንዲሁም በየዓመቱ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች እየተመረቁ ለሥራ ዝግጁ ከሚሆኑ ዜጎች ቁጥር አንጻር ክልሉ ከፍተኛ የሰብዓዊ ሀብት አቅም ያለው መሆኑ የማያከራክር ሲሆን ይህም ለታቀዱት የልማት ግቦች ከፍተኛ አቅም ይፈጥራል። **የፋይናንስ ሀብት፦** አንድ ክልል በጥሪት መልክ ያፈራውን በቀጣይም ኢኮኖሚው ከሚያመነጨውም ሆነ ከሌሎች ምንጮች ሊያሰባስብ የሚችለውን ክልላዊ የፋይናንስ ሀብት መጠን ለልማት ዕቅዶች ማስፈጸሚያ ወሳኝ ናቸው። በዚህ ረገድ ክልላችን ባለፉት ዓመታት ፈጣንና ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን ከዚህም የሚሰበሰበው ገቢ እንዲሁም ቁጠባ ለተለያዩ የልማት ፋይናንስ ፍላጎቶች ማሟያነት ሊውል ቆይቷል። በሚቀጥሉትም ዘመናት የኢኮኖሚ ዕድገቱን በማስቀጠልና ከዚህም ሊሰበሰብ የሚችለውን የገቢ መሠረትንና መጠንን እንዲሁም ቁጠባን በማሳደግና እነዚህንም ሀብቶች በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ዘላቂ ልማትንና ብልጽግናን ማሳካት ይቻላል።

**ማህበራዊ ሀብት፦** ህዝቦች ለዘመናት አብሮ በመኖር ሂደት የገነቧቸው ባህሎች፣ ልማዶችና ሌሎች የጋራ እሴቶች የሀገሪቷን ብሎም የክልሉን የልማትና የብልጽግና ጉዞ ለማሳካትና የዜጎቿን መሻቶች ለማሟላት ከሚያስፈልጉ ውድ ፀጋዎች ውስጥ ይካተታሉ። ከላይ የተገለጹ ሀብቶች አቅም አስፈላጊነት እንዳለ ሆኖ እነዚያን ሀብቶች በሚፈለገው መልኩ አቀናጅቶ ሥራ ላይ ለማዋል መልካም ማህበራዊ መስተጋብርና ዘላቂ ሰላም የሚያመጡ እሴቶች ያስፈልጋሉ። በዚህ ረገድ ለዘመናት የኖረው የመከባበር፣ የመደጋገፍ እንዲሁም አብሮ የመሥራት ባህሎችና እሴቶች እንዲሁም በማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ ውስጥ የተሰናሰሉ አዎንታዊ ሥርዓታት በቀጣይ የታቀዱ የልማት ግቦችን በማሳካት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል።

# ምዕራፍ ሁለት

# የዕቅዱ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.1 የዕቅዱ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች

በልማት ዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ሊደረስባቸው የታቀዱ ግቦችን ለማሳካት ተግባራዊ የሚሆኑ ዝርዝር የማስፈጸሚያ ስልቶች በእያንዳንዱ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የመሠረተ ልማት ዘርፍ ዕቅድ ውስጥ በዝርዝር ተመላክተዋል። በዚህ መሠረት የዕቅዱ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች በጥቅሉ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ ጥራት ያለውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥና ወደ አስተማማኝ የዕድገትና ብልጽግና ጎዳና ለመሸጋገር ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በአንድ ሀገር ወይም በአንድ ክልል ውስጥ የሚመዘገብ አነስተኛ የካፒታል ክምችት ከአነስተኛ ቁጠባና ኢንቨስትመንት የሚመነጭ ነው። ይህን ችግር ለመፍታት ትርጉም ያለው የልማት ፋይናንስ በማመንጨት ከብክነት በፀዳ መልኩና በቅልጥፍና ለታለመለት ዓላማ ላይ በማዋል ጥራት ያለው ዕድገትን ማስመዝገብና የካፒታል ክምችትን ማሳደግ ይቻላል።

በልማት ዕቅዱ የተቀመጡ የትኩረት አቅጣጫዎችንና ዋና ዋና ግቦችን ዕውን ለማድረግ የልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ፍላጎት ማዕቀፍን (financial resource envelope) ግልጽና ዝርዝር በሆነ መልኩ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። የልማት ፋይናንስ ምንጭን ከሀገር ውስጥ ገቢ፣ ቁጠባ እና ከሌሎች ምንጮች በአግባቡ በመለየት፣ የኢኮኖሚውን ገቢ የማመንጨት አቅም ከግምት በማስገባት፣ የልማት ዕቅዱ ባስቀመጣቸው የትኩረት መስኮችና አቅጣጫዎች ቅደም ተከተል መሠረት ቅልጥፍናና ውጤታማነትን ባገናዘበ መልኩ አቅርቦትንና ፍላጎትን በማጣጣም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን የተቀመጠውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማሳካት የሚያስፈልገውን የኢንቨስትመንት መጠንና ዝርዝር የልማት ፋይናንስ ምንጭ የሚያሳይ የልማት ፋይናንስ አቅርቦትና ፍላጎት ማዕቀፍ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል።

በዕቅዱ የትግበራ ዘመን የመንግሥት የኢንቨስትመንት ወጪ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ዋና ዋናዎቹን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግቦች ለማሳካት የሚያስችሉ ከፍተኛ ምርታማነት ያላቸው ዘርፎች ላይ በማተኮር የመንግሥት ኢንቨስትመንት ውጤታማ እንዲሆን ይደረጋል። እንዲሁም ጥራት ያለውን የመንግሥት ኢንቨስትመንት በማከናወን በዕቅዱ የተመለከቱትን ግቦች ከማሳካት አንጻር ያላቸው ፋይዳ በተለይም ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ከማስመዝገብ፣ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከማስፈን፤ ድህንትን ከመቀነስ፤ የግል ዘርፉን ድርሻ ከማሳደግ፤ የክልሉን እምቅ አቅም ጥቅም ላይ ከማዋል፣ ዘርፎች መካከል ትስስርና ተመጋጋቢነት በማጎልበት የሥራ ዕድል ከመፍጠርና ከማሳደግ አንጻር የኢንቨስትመንቱን ቅደም ተከተል የሚመሩ መሠረታዊ መነሻዎች እንዲዘጋጁ ይደረጋል።

በዚህም በመንግሥት ፕሮጀክቶች አስተዳደርና አመራር በተመለከተ በዕቅድ ዘመኑ በመንግሥት የሚከናወኑ ከፍተኛ ኢንቨስትመንቶች በሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በዝርዝር ጥናት ላይ ተመስርተው በጥልቀት እንዲዘጋጁ ይደረጋል። ፕሮጀክቶቹም በገለልተኛ ወገን ተገምግመው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አዋጭነታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናሉ። በተጨማሪም በዕቅድ ዘመን የመንግሥትን ኢንቨስትመንት ውጤታማነትና ቅልጥፍናን ለማሳደግ ከላይ በተጠቀሱ መስፈርቶች መሠረት በየዘርፉ የተለዩትን ቅደም ተከተል በማስያዝ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል። ጥራት ያለው የሰው ኃይል የኢኮኖሚን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በማረጋገጥ በዕቅዱ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የማይተካ ሚና ይኖረዋል። የሰው ኃይል ፍላጎት በዓይነትና በጥራት ማቅረብ ካልተቻለ የዕቅዱን ትላልቅ ግቦች ለማሳካት አስቸጋሪ ይሆናል። በመሆኑም ከኢኮኖሚ ዘርፎች የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር የተጣጣመ አቅርቦትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የኢኮኖሚ ዘርፎች የሰው ኃይል ፍላጎት በዓይነት፣ በጥራትና በመጠን ከኢኮኖሚው ባህሪ ጋር ተለዋዋጭ በመሆኑ ይህንን ቀድሞ በማቀድ መዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል። በዚህም የትምህርት ዘርፉ የሚያቀርበው የሰው ኃይል ከኢኮኖሚ ዘርፎች ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም በማድረግ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚከሰተውን የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣምን (skill mismatch) ከማስወገድ በተጨማሪ በኢኮኖሚው ውስጥ ዘላቂ ምርታማነትን በማሳደግ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ያለው አዎንታዊ አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የልማት ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ፍላጎት በክህሎት አይነት፣ መጠንና የጥራት ደረጃ በየዘርፉ በዝርዝር የሚለይ የልማት ዕቅዱ የሰው ኃይል ፍላጎትና አቅርቦት ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል።

ዘላቂ የሆነ የስርዓታት ግንባታ ማዕቀፍ፡- ፖሊሲዎችና የህግ ማዕቀፎችን ወጥና ተናባቢ ማድረግ፣ ዘላቂ የሆነ የተቋማት አደረጃጀት መፍጠር እና አቅም በመገንባት አዳዲስ ሥልቶች አማካኝነት ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ይሰራል።

# ምዕራፍ ሦስት

# የልማት ዕቅዱ ስጋቶችና ስጋቶችን ለመቀነስ የሚተገበሩ ስትራቴጂዎች

## 3.1 የልማት ዕቅዱ ስጋቶች

ስጋቶች፡- የአስር ዓመቱን የልማት ዕቅድ ውጤታማነት ሊያደናቅፉ የሚችሉና በልማት ዕቅዱ የታቀዱ ግቦች እንዳይሳኩ የሚያደርጉ ክስተቶች ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ስጋቶች ከመከሰታቸው በፊት የመከላከያ ስትራቴጂ ለመንደፍና የሚያስከትሉትን አደጋ ለመቀነስ ከወዲሁ መለየት ይገባል። ከዚህ አንጻር በቀጣይ አስር ዓመታት የልማት ዕቅዱን ስኬታማነት ሊፈታተኑ ይችላሉ ተብለው የተለዩ ስጋቶች ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል።

1) ክልላችን ከፍተኛ የሆነ የመሰረተ ልማት ጥያቄዎች ያሉበት በመሆኑ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል ከፍተኛ የሆነ በጀት ያስፈልጋል። ስለሆነም ፋይናንስና በሚፈለገው መጠንና ጥራት ካልተገኘ በልማት ፋይናንስና በመሰረተ ልማት አቅርቦት ላይ ሊፈጥር የሚችለው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆንና ከቅርብ አመታት ወዲህ የካታል ፕሮጀክቶች ድርሻ እቀነሰ የደሞዝ ድርሻ እየጨመረ መምጣቱ ተፅኖው ከፍተኛ መሆኑ፤

2) በሰው ሠራሽ እንዲሁም በተፈጥሮ ለሚከሰቱ አደጋዎች ማለትም ድርቅ፣ ጎርፍ፣ ክልላዊ፣ ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የጤና ወረርሽኞች ተጋላጭ መሆንና አደጋዎችን ለመቀልበስ የሚወሰዱ የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ለልማት ሊውል የሚችለውን ሀብት የሚሻሙ መሆናቸው፣

3) ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ በሀገራችን እየተስተዋለ የመጣው የፖለቲካ አለመረጋጋትና ይህን ተከትሎ ክልላችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ የማይቀር መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ስጋቶች ናቸው።

## 3.2 የልማት ዕቅዱ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች

ስጋቶች ከመከሰታቸውና ወደ አደጋ ከመሸጋገራቸው በፊት ለመከላከል የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች በሁሉም የክልላችን አካባቢዎች እንዲከናወኑ ይደረጋል። በተለይም ደግሞ የአደጋ ስጋትን በመለየት፣ በመተንበይ፣ በመተንተንና የቅድመ ጥንቃቄ ዕርምጃዎችን በመውሰድ ጉዳት እንዳያደርሱ ወይም የሚያስከትሉትን ጉዳት መቀነስ የሚያስችል አሠራር ይዘረጋል።

**የፋይናንስ እጥረትን በተመለከተ፤**

የተጀመረውን የግብር አሰባሰብ ሥርዓት ዘመናዊ የማድረግ ሥራ አጠናክሮ በማስቀጠል እንዲሁም የታክስ መሠረቱን በማስፋት፣ ውስጥ ቁጠባን በማሳደግ፤ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚኖረውን የትብብር ማዕቀፍ ወደ መሬት ማውረድ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል።

የአደጋ ተጋላጭነትን በተለይም የድርቅና የጎርፍ ተጋላጭነትን ከመከላከል አንጻር በሁሉም የክልላችን አካባቢዎች የህዝቡን ግንዛቤ ይበልጥ በማስፋትና በማዳበር በተለይም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በሁሉም የክልላችን አካባቢዎች በተሟላ ሁኔታ የሚተገበሩ ይሆናል። ከዚህ

በተጨማሪ የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራምን በማስቀጠል የክልሉን የደን ሽፋን ለማሳደግ በትኩረት ይሠራል። በተመሳሳይ በልማት ዕቅዱ ዘመን የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የውኃ ሀብቶችን በማነጽ በዓመት ሁለትና ሦስት ጊዜ ለማምረት ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። በአጠቃላይ ለተፈጥሮ አደጋዎች የማይበገር ማህበረሰብ ለመገንባት በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

በአንድ ሀገር በተለያዩ ጊዜያት የፖለቲካ ችግሮች፣ ግጭቶችና አለመረጋጋቶች ሊፈጠሩ የሚችሉ ጉዳዮች ቢሆንም ችግሮቹ ለልማት፣ ለሰላምና ለመሰረታዊ የዜጎች ደህንነት አስጊ ሆነው እንዳይቀጥሉ ዘላቂ መፍትሄ ሊቀመጥላቸው ይገባል። በልማት ዕቅዱ የተያዙትን ውጥኖች ከግብ ለማድረስ የፖለቲካ ችግሮችን እንዲሁም በክልሉ ለሚከሰቱ ብሔር ተኮር ግጭቶች፣ በቡድኖች መካከል ለግጭት መንስዔ ሊሆኑ የሚችሉ ያደሩና ሌሎች አዳዲስ አስጊ የግጭት ምክንያቶች እልባት እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

ለዚህም ይረዳ ዘንድ በተለያዩ ጊዜያት በሀገር ደረጃ የተቋቋሙ የእርቀሰላም ኮሚሽንና የድንበርና ማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን ጋር በቅንጅትና በመተጋገዝ እንዲሁም የቤተሰብ፣ የማሕበረሰብና የዕምነት መሪዎችን በማስተባበር፣ የዕምነት ተቋሞቻችን ለልማት አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንዲኖራቸው በማድረግ፣ ለውይይትና መግባባት የሚረዱ መድረኮችንና ጉባኤዎችን በማጠናከርና በአግባቡ በመጠቀም ችግሮች እንዳይስፋፉ የማድረግ ሥራ ይሠራል። በተለይም በዞኖችና በወረዳዎች መካከል የሚነሱ የድንበር ይገባኛል ጉዳዮችና የማንነት ይከበርልኝ ጥያቄዎች ሀገራዊና ክልላዊ አንድነትን ባስጠበቀ መልኩ ዘላቂ መፍትሄ የሚሰጣቸው ይሆናል።

በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚከሰቱ አለመስማማቶችና የዴሞክራሲ ጉዳዮች ሕጋዊነት ባለው መልኩ እንዲፈቱ በማድረግ ዜጎች የፈለጉትን የፖለቲካ አመለካከት የማራመድ መብታቸው እንዲጠበቅና ለሀገራቸው ብሎም ለክልሉ ልማት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ ይከናወናል። ይህንንም በአግባቡ ለመምራት የሕግ ማስከበር፣ የሰላም፣ የደህንነት፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ተቋማት በተሻለ ደረጃ ከፖለቲካ ገለልተኛና ነፃ እንዲሆኑ ይደረጋል።

# ምዕራፍ አራት

# 4 የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

## 4.1 የክትትል ሥርዓት

ውጤታማ የሆነ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ውጤቶችና ስኬቶች የሚለኩበት ግልጽና መለካት የሚችሉ ቁልፍ አመልካቾች (key performance indicators) ያስፈልጉታል። ይሄንንም ለማሳካት የክልሉ ፕላን ኮሚሽን ከሁሉም አስፈፃሚ አካላት ጋር ውይይት በማድረግና እያንዳንዱ አስፈፃሚ አካል የራሱን ዘርፍ ቁልፍ አመልካቾች እንዲለይ በማድረግ ክልላዊ ቁልፍ የውጤት አመልካቾች ይዘጋጃል። በመሆኑም የ10 ዓመት የልማት ዕቅዱ ውጤቶችና ስኬቶች የሚለኩት በእነዚህ አመልካቾች መሠረት ይሆናል።

የልማት ዕቅዱ የክትትል ሥርዓት በዋናነት ሁለት የመረጃ ምንጮችን ይጠቀማል። እነዚህም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ (Central Statistical Agency) የሚመነጩ የናሙና ጥናትና የቆጠራ መረጃዎች እንዲሁም በዘርፍ አስፈፃሚ ተቋማት የሚመነጩ የአስተዳደር መረጃዎች ናቸው። በተጨማሪም በክልሉ የመረጃዎችን ወጥነትና ተመጋጋቢነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ቼክ ሊስት በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚዘጋጅ ሲሆን በቀጣይ ይህንን መሠረት በማድረግ መደበኛ የአፈጻጸም ሪፖርቶች የሚዘጋጁ ይሆናል።

በዓመታዊ ዕቅድና በጀት የተደገፈ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፦ የልማት ዕቅዱን በተሟላ ሁኔታ በመከታተል፣ በመገምገምና በመደገፍ ውጤታማነቱን ማረጋገጥ በሁሉም የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በባለቤትነት ተይዞ መፈጸም ያለበት ትልቅ ኃላፊነት ነው። በዚህም መሠረት የልማት ዕቅዱን የክትትልና ግምገማ ማትሪክስ መሠረት ያደረገ፣ ቁልፍ የውጤት መስኮችን፣ ኢላማዎችንና ቁልፍ የአፈጻጸም አመልካቾችን በግልጽ ለይቶ ያስቀመጠና በበጀት የተደገፈ ዓመታዊ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዕቅድ ማዘጋጀት ይህንንም ተፈፃሚ ማድረግ ከእያንዳንዱ የመንግሥት አስፈፃሚ አካል የሚጠበቅ ይሆናል። የክትትልና ግምገማው ሥራ በተለያዩ አካላት በተለያየ ደረጃ የሚከናወን ቢሆንም የማክሮ ኢኮኖሚና የዘርፍ መረጃዎችን በመጠቀም አጠቃላይ ዓመታዊ የልማት ዕቅድ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት እየተዘጋጀ ለመንግሥት የሚቀርብ ይሆናል።

በመስክ ጉብኝትና ምልከታ የታገዘ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማካሄድ፦ የመስክ ጉብኝት ክትትልና ግምገማ ማለት የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃን ለማረጋገጥ በተመረጡ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዙሪያ የሚዘጋጅ ጉብኝት ሆኖ ዓላማው በየጊዜው ከሚዘጋጁ የዕቅድ

አፈጻጸም ሪፖርቶች በተጨማሪ በመስክ ምልከታ የአፈጻጸም ልዩነቶችን በማረጋገጥና የአፈጻጸም ክፍተቶች ካሉም የማስተካከያ እርምጃዎች በወቅቱ እንዲወሰዱ ማስቻል ነው። ይህም በዓመታዊ ዕቅድና የአፈጻጸም መርሐ ግብር በሚገባ በመካተት በሃላፊዎችና በከፍተኛ አመራሮች ደረጃም በተመረጡና ፋይዳቸው ከፍተኛ በሆኑ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ላይ የሚከናወን ይሆናል። የመስክ ጉብኝቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ከማመንጨት በተጨማሪ በአንድ የመረጃ ምንጭ ወይም በሪፖርት ላይ ከመወሰን ይልቅ የመረጃ ምንጮችን ማስፋትና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመስክ ከተገኘው መረጃ ጋር ለማመሳካር (triangulation) ጠቃሚ በመሆኑ ነው።

ዓመታዊ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሪፖርቱን በባለድርሻ አካላት ማስገምገም፦ የምክክር መድረኮችን በክልል& በዞንና በከተማ አስተዳደር ደረጃዎች በማዘጋጀት በዓመታዊ የልማት ዕቅዱ ረቂቅ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ይካሄዳል። ይህም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈንና ለማጠናከር እንዲሁም በህብረተሰቡ ዘንድ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር ከማድረግ አንጻር ጠቀሜታው የጎላ ነው። ከምክክር መድረኮች የተገኙ አስተያየቶችን በማካተት የአፈጻጸም ሪፖርቱ ታትሞ ለባለድርሻ አካላት በተለያዩ ዘዴዎች ተደራሽ ይደረጋል።

### 4.2 የግምገማ ሥርዓት

የዕቅድ ትግበራ ዘመን አጋማሽ ግምገማ (mid-term review)፦ ሌላው የክትትልና ግምገማ ዘዴ በዕቅድ ዘመኑ አጋማሽ ላይ የሚደረግ ግምገማ ነው። ዓላማውም በልማት ዕቅዱ የተቀመጡ መሠረታዊ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ዋና ዋና ግቦችና የማስፈጸም ኢላማዎች ምን ያህል እየተሳኩ እንደሆነ በዝርዝር ለመፈተሽና ለማረጋገጥ፣ አስፈላጊ ማስተካከያዎች ካሉም በአስተማማኝ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድና በቀሪው የዕቅድ ዘመን የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ እንዲረዳ ነው። በመሆኑም የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የመካከለኛ ዘመን ግምገማ የሚከናወን ይሆናል።

የዕቅድ ትግበራ ዘመን ማጠናቀቂያ ግምገማ (final evaluation) ፦ የዕቅድ ዘመን ማጠናቀቂያ ግምገማ በልማት ዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት ላይ የሚከናወን ግምገማ ሲሆን፣ ዓላማውም የልማት ዕቅዱ ግቦችና ኢላማዎች በዕቅዱ በተቀመጡ መሠረታዊ አቅጣጫዎችና የማስፈፀሚያ ስልቶች መሠረት መፈፀማቸውንና የዕቅዱ ዓላማዎች መሳካታቸውን ማረጋገጥ፣ መልካም ተሞክሮዎችንና የአፈጻጸም ጉድለቶች ካሉ ከነምክንያቶቻቸው በመለየት በቂ ትንተናና ግምገማ

ማካሄድና በቀጣይ መወሰድ ያለባቸውን የፖሊሲና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚጠቁም ምክረ ሀሳብ ማቅረብ ነው።

የግምገማ ጥናት (evaluative research) ማካሄድ፦ ሌላው የልማት ዕቅድ አፈጻጸም የክትትልና ግምገማ ዘዴ በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የግምገማ ጥናት ማካሄድ ሲሆን፣ በተመረጡ የማክሮ ኢኮኖሚ ወይም በዘርፎች የልማት ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸምና ስኬቶች እንዲሁም ተግዳሮቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። የግምገማ ጥናቶች ዓላማም በየጊዜው ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ርዕሰ ጉዳዮችን በመለየትና ቅደም ተከተል በማውጣት ጥናቶችን በማካሄድ እየተመዘገበ ያለውን ለውጥ፤ ውጤትና የግብ ስኬት እንዲሁም እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን በጥልቀት በመዳሰስ ለፖሊሲ ውሳኔዎችና ለዕቅድ ዝግጅት የሚረዱ መረጃዎችን ማመንጨት ነው።

## 4.3 የክትትልና ግምገማ የማስፈፀሚያ ስልቶች

የክትትልና ግምገማ አሠራር፣ አደረጃጀትና የሰው ኃይል አቅም ማጠናከር፦ የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ፣ አሠራርና አደረጃጀቶችን አስመልክቶ በተለያዩ የመንግሥት አስተዳደር ዕርከኖችና የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት ሰፊ ክፍተቶች ይታይባቸዋል። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን እነዚህን ክፍተቶች በማስወገድ የልማት ዕቅዱን አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በጠንካራ አሠራርና አደረጃጀት እንዲሁም በአስፈላጊ የሰው ኃይል በመደገፍ የሚጠበቀውን ዓላማ ለማሳካት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

በልማት ሂደት ውስጥ አሠራርና አደረጃጀት ብቻቸውን የማስፈጸም አቅም ሊሆኑ አይችሉም። አሠራርና አደረጃጀት ጠንካራ የማስፈጸም አቅም ሊሆኑ የሚችሉት በተሟላ የሰው ኃይል ሲደገፉ ብቻ ነው። በልማት ሂደት ውስጥ ወሳኙ አቅም የተማረና የሠለጠነ የሰው ኃይል ነው። በመሆኑም ይህን የልማት ዕቅድ ውጤታማ ለማድረግና በሀገራችን ብሎም በክልላችን የተጀመረውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ማህበራዊና የአካባቢ ልማት ለማስቀጠል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ የዜጎችን የልማት እኩል ተሳታፊነትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው አግባብ ለማረጋገጥ የተማረና የሠለጠነ የሰው ኃይል በብዛት ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር በተለያዩ የመንግሥት የአስተዳደር እርከኖች በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ተመድበው የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ተግባራትን የሚያከናውኑ ባለሙያዎች ቀጣይነት ባላቸው የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች እንዲታነፁ በማድረግ የሰው ኃይል አቅም በየደረጃው እንዲጎለብት ይደረጋል።

ለክትትልና ግምገማ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት መገንባት፦ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በሕግ ከተሰጧቸው ኃላፊነቶች ጋር በተገናኘ ለልማት ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ የሚያግዙ መረጃዎችን ያመነጫሉ። የእነዚህ መረጃዎች አያያዝ፣ አደረጃጀትና ሥርጭት ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓትን የተከተለና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ ሊሆን ይገባል። ነገር ግን ከተወሰኑ የመንግሥት አስፈፃሚ ተቋማት በስተቀር የአብዛኞዎቹ አሠራሮች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ አይደሉም። በመሆኑም የአስፈፃሚ አካላት የልማት ዕቅድ አፈጻጸም የክትትልና ግምገማ አቅም በዘመናዊ መልኩ የተደራጀና የተቀናጀ የመረጃ ማኔጅመንት ሥርዓት ሊጠናከር ይገባል።

በተጨማሪም መረጃዎቹን ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ማኔጅመንት ሥርዓት (management information system) በመዘርጋትና ሶፍትዌሮችን በማልማት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል። የዘርፍ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች የልማት ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ የመረጃ ቋቶች ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የመረጃ ቋት ጋር የሚተሳሰሩበትን ሥርዓት በመፍጠር የመረጃ ፍሰትን ማጠናከር ያስፈልጋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ከልማት አጋሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ሪፖርት አቀራረብ (performance tracking and reporting) በቴክኖሎጂና ሶፍትዌር እንዲደገፍ ይደረጋል።

የዕቅድ አፈጻጸም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማጎልበት፦ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዓላማ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላትን የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ማሻሻልና በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ነው። ይህም በዕቅድ አፈጻጸም የሚታዩ ድክመቶች መንስዔያቸው ምን እንደሆነ ከመለየት ጀምሮ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማመላከትንና ተግባራዊ መሆናቸውን መከታተልን ይጠይቃል።

ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአስፈፃሚ አካላት የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ደካማነት ከተቋሞቹ የበላይ ኃላፊዎች የሥነ ምግባር ችግር፣ የባለቤትነትና የቁርጠኝነት ጉድለት፣ የሕዝብ ጥቅምን ያለማስቀደምና የአቅም ማነስ ችግር ጋር የተያያዘ ከሆነ በየደረጃው የተቀመጡ የልማት ግቦችና ኢላማዎችን ለማሳካት የሚደረገውን የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ድጋፍ ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል። በዚህም ምክንያት የሕዝብ ጥቅም አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል። ተገልጋዩ ሕዝብም በመንግሥት ላይ ያለው እምነት እየተሸረሸረ እንዲሄድ ያደርጋል። ይህም በሂደት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ማህበራዊ ቀውሶች ሁሉ በዋናነት የተጠያቂነት ሥርዓቱ ደካማ ከመሆኑ የተነሳ የሚመነጩ ናቸው። በመሆኑም የአስፈፃሚ ተቋማትንና ተቋማቱን የሚመሩ የበላይ ኃላፊዎችን የሥራ አፈጻጸም በተሟላ ሁኔታ በየጊዜው በመገምገምና የአፈጻጸም ደረጃ በመስጠት ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓት የሚዘረጋ ሲሆን፣ ይህንንም ለዜጎች ለማሳወቅና ይፋ ለማድረግ ከሚዲያዎች ጋር የሚሰራ ይሆናል።

**ማጠቃለያ**

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ሕዝቦች ክልል በአገራችን ካሉ ክልሎች በተፈጥሮ ሀብት ፀጋዉ፤ በመልማት አቅሙና በአገሪቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ዉስጥ እያደረገ ካለዉ ድርሻ አንፃር ተስፋ ያለዉና የአረንጓዴ ልማት ተምሳሌት ሊሆን የሚችል ክልል ነዉ። ታዲያ ይህ ፀጋ ዘለቂታ ባለዉ መልኩ በጋራ ትብብርና አብሮነት ለምቶ ከክልሉ አልፎ ለአገሪቱ ትልቅ የአቅርቦት ማዕከል ማድረግ እንዲቻል ቆልፎ የያዙ የመሰረተ ልማት ችግሮችንና የማስፈፀም አቅም ዉስንነቶችን መፍታት ለነገ ይደር የሚባል ጉዳይ አይደልም። በመሆኑም ይህ መሪ እቅድ ክልሉ ያለዉን የመልማት እድልና ፀጋን ፈጣን በሆነ ሁኔታ ተጠቅሞ ዘላቂነት ያለዉን የኢኮኖሚ ማህበራዊና ሰብአዊ ልማቶችን ለማካሄድ አቅጣጫ ጠቋሚ ሆኖ የተለያዩ ዘርፎች ከራሳቸዉ ተልዕኮ አንፃር እየቀዱ ለመጠቀም እንደመነሻ ሰነድ ሆኖ እንዲያገለግል ተዘጋጅቷል።